


pdf by @shuktus_books

ይህ መፅሐፍ 70% ምናባዊ ፈጠራ ሲሆን 30% እውነተኛ ታሪክ ላይ የተንጠላጠለ ነው።

# ሸርብትን

pdf by @shuktus_books

አዘርግ

ሚያዚያ 2008

ማስታወሻ 2

ይህን አዝናኝ አስተማሪ መፅሐፍ መልሶ ለማሳተም ሆነ ወደ ልብ እንጠልጣይ ፊልም ለመለወጥ የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

ኮፒራይት © 2008 አዘርግ

## ቀደምት ስራዎች

1. የሆነ የሆነ ነገር ይሠማኛል 2003 (ገበያ ላይ የለም)
2. ኢያሪኮ 777 2004
3. ኢያሪኮ 888 2004
4. ኢያሪኮ 999 2005
5. አዳምና ሄዋን 2005 (ገበያ ላይ የለም)
6. አቢሲኒያ 24 2005
7. አ ... ዘንደኪ 2006
8. አ ... ያያያ 2006
9. በኢያሪኮ ከተማ 2007
10. ሹከ ቱሰ 2007

መልካም ንባብ ...!!

# ማስታወሻ 3

## የምስጋና ጥግ

ለተደራሲያን

ከአዘርግ

እነሆ 2008 መጣ! በ2008 ለውድ አንባቢያን "ሽርብትን እና ቋ" የተሰኙ ጉለጽ መፅሐፍትን ለማበርከት... ጣጣው ሁሉ አልቋል!!

ውድ ተደራሲያን ይቺን 11ኛ መፅሐፍ በማጣጣም፣ ዘና፣ እንደምትሉባት ተስፋ በማድረግ ከወዲሁ እስከዛሬ ከእኔ ጋር በመሆናችሁ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ!! በተቻለኝ መጠን አስራ ሁለተኛ መፅሐፌ የሆነችው "ቋ" ላይ ለየት ያለ ነገር ለማስነበብ ጥረት አደርጋለሁ ፤ በተረፈ ቀና እና ሰናይ ጊዜ እመኝላቹዋለሁ!!

አዘርግ ነኝ፡፡

ታህሳስ 2008

በዚች መፅሐፍ ላይ አስተያየታችሁን ሹኩቱስ ለማለት መሻት ካላችሁ በ 0911048965 ላይ Text ብቻ ይላኩልኝ፤ በተረፈ በርካቶች ያቀረባችሁልኝን ጥያቄ ለመመለስ በአዘርግ ሆነ በመፅሐፍ ስም የከፈትኩት አንዳችም Face book…የለኝም... ወደፊትም አይኖረኝም ፤ ስለዚህ አስተያየታችሁን እየተቀበልኩ ያለሁት በተለመደችው ስልክ ብቻ ነው፡፡

.......... አመሰግናለሁ!!

# ሀ

## ማኮብኮቢያ ታሪክ

### 1

እዎ ፡፡ እሀ... ለመሆኑ 'እዎ' ተብሎ ድርሰት ይጀምራል? እኔንጃ! እኔ ግን ጀመርኩ... ደራሲ ነኝ... ማለቴ ጀማሪ ደራሲ፡፡ በምድር ላይ ካሉት ባለሙያዎች ሁሉ የእኔ ልብ ትርታ ያለችው ከደራሲዎች ጋር ናት... ከልጅነቴ ጀምሮ እስከ ወጣትነቴ በእያንዳንዷ ቀን ስለ ደራሲነት አውጥቻለሁ፣ አውርጃያለሁ!!... በመጨረሻ አቅሜ የፈቀደውን ለአቅመ ድርሰት መፃፍ ስደርስ አንድ መፅሐፍ ለመፃፍ ወሰንኩ!! 'ሽርብትን' የሚል ርዕስ ሰጠሁት!!... እነሆ የምፅፈው መፅሐፍ በእውነተኛ ገፀባህሪያት ላይ እንዲመሠረት ፈለኩ እናም እውነተኛ ገፀባህሪያትን ፍለጋ ገባሁ፡፡

ወይ ጉድ..!! ገፀባህሪያትን ስፈልግ ራሴ ገፀባህሪ ሆኜ ቀረሁ ... እሀ... በእውን ህይወቴ ይቅርና በህልሜ እንኳ ያላሰብኩት ሆነና ህይወቴ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለወጠች... አሁን የሚሰማኝ እንዳችም ነገር የለም... ሁሉ ነገር በፀጥታ ማዕበል የተሞላ ነው! እረጭ! ዝም ... ያለ ነው፡፡ ይህ ፍፁም የማላውቀው አዲስ ግራ የሚያጋባ ህይወት ነው... የት ነው ያለሁት? ምንድነው የተፈጠረው? ስለምንስ ነው ይህ ሁሉ ጉድ የተፈጠረው?

ሁላችሁም ገፀባህሪያት ናችሁ፣ የእግዚአብሔር ገፀባህሪያት፤ ለዚያውም አንዳንዱ የሚያንቀሳቅሳችሁ ... እኔ ግን የራሞስ ኢልያስ ገፀባህሪ ነበርኩ...

የእኔ ህይወት ታሪክ ሲፃፍ አጭር ነው፤ ይህን ይመስላል:: "እነሆ ጀማሪ ደራሲው ገፀባህሪያትን ፍለጋ ከቤት ወጣ፤ በከተማይቱ መሀከል .እጅግ ኳተነ፤ ሚዛን የሚደፉ ገፀባህሪያትንም አጣ... ያ ጀማሪ ደራሲ ራሱ ገፀባህሪ ሆኖ ተመለሰ... አለቀ:: ደቀቀ:: ዲዮጋን ሆነ!!

ዲዮጋን

'ሰው' ፍለጋ ከቤት ወጥቶ

እጅግ ብዙ ተንከራቶ

ተመለሰ ከቤቱ

'ሰው' ጠፍቶ በአገሪቱ::

ለመሆኑ እኔ ማን ነኝ?... እነሆ ራሞስስ ማን ነው?

ገፀባህሪያት ነን:: ኢትዮጵያዊያን ነን:: ታሪካችን 70% ምናባዊ ፈጠራ ሲሆን 30% እውነተኛ ትዕይንት ላይ የተመሠረተ ነው:: ምንም ይሁን ምን ህይወት ግን ትቀጥላለች!!

pdf by @shuktus_books

## ማኮብኮቢያ ታሪክ

## 2

## ራሞስ ኤልያስ

ሀይወት ምንድን ነች ? የሰው ልጅ በምድር ላይ ለምን ይፈጠራል? ለምንስ ይሞታል? እንዴት ባለ ጥበብስ እግዚአብሔር አለምን ከእነግሳንግሷ ሊፈጥራት ቻለ? ለመሆኑ እስከዛሬ ዓለም በስልጣኔ ተራምዳ፣ ዓለም በእድገት ሹክሹክ ብላ ... እንዴት ዓለምን ስለፈጠረው ፈጣሪ መነሻ ማወቅ አልቻልንም ? እሺ እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ፡፡ ተስማማን፡፡ እሺ እግዚአብሔር የሰው ልጅን ከአፈር እና እስትንፋስ ፈጠረው፡፡ ተስማማን፡፡ ስለ ዓለም ብዙ አወቅን ፤ በጥበብ! በስልጣኔ ተመነጠቅን!! ግን እግዚአብሔርን ማን ፈጠረው? ለመሆኑ ፈጣሪ መነሻ ነጥቡ ምንድን ነው? ይቺን ጥያቄ የሚመልስ እስከዛሬ አልተገኘም... ወይም ይህ በጓደኛዬ ራሞስ ኤልያስ ገለፃ መሠረት ፍልስፍና ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲ እያለን ነበር ከራሞስ ጋር የሀንዳዊውን ባጣዋን እሾን እና የአወዛጋቢው ራምፓን የፍልስፍና መፅሐፍት አንብበን ስንጨርስ እንደ ተለመደው ስለ ፍልስፍና መወያየት ጀመርን፡፡ እኔም ስለፍልስፍና ከራሴ እና ካነበብኩት በመነሳት ለራሞስ አስረዳሁት፡፡

"ሲጀመር ፍልስፍና ያነበብከውን ሽምድደህ ለሌላው ማስተጋባት ማለት አይደለም፡፡

ቆም ብለህ ካየኸው እነ ፕሎቶ እና ኒቼ እንዳሉት እያንዳንዱ የሰው ልጅ ፈላስፋ እና በተለይ የሀሳቡ እስረኛ ነው። የማናችንም ህይወት የሚወሰነው በአስተሳሰባችን ላይ ነው፤ ያ አስተሳሰባችን ልምድ ይሆንና ህይወታችንን እውቀነው ይሁን ሳናውቀው ይመራናል፤ ስለ ህይወት ብዙ ነገር ልትሰማ ትችላለህ፤ ቢሆንም ልኬቱ ላይገባህ ይችል ይሆናል፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ አንዲት እሪፍ የኢንግሊዝኛ ቆየት ያለች አባባል አለች 'No matter who tries to teach you lessons about life, you wan't understand it until you go through it on your own,' ትላለች፤ ለማንኛውም ወደተነሳንበት ርዕስ እንመለስና ለእኔ ፍልስፍና ማለት የማያልቅ ጥያቄ ማንሳት ብቻ ነው"

" አልገባኝም" አልኩት።

"ክርስቶስ ምሳሌ ያበዛ ነበር። እኔም እንዲገባህ በምሳሌ ላስረዳህ። ለምሳሌ የሰው ልጅን መነሻ ብንመረምር የሰው ልጅ ከየት መጣ?"

"በሀይማኖታዊያን አስተሳሰብ ነው አልያስ በሳይንስ እይታ?"

"ያው የእነ ቻርልስ ዳርዊን የሰው ልጅ ከዝንጀሮ መጣ መላምት በዚህ ዘመን ሚዛን ስለማይደፋ ለጨዋታ ያህል በሀይማኖታዊያን እንመልከተው"

"እንደዛ ከሆነ የሰው ልጅን እግዚአብሔር ፈጠረው"

"እንዴት? ምን ማስረጃ አለህ? ለምን ፈጠረው? እያልኩ ብዙ ጥያቄዎች እደረድርልሃለሁ፤ አንተም በቻልከው መጠን የሰው ልጅን እግዚአብሔር ዓለምን እንዲገዛ በማይመረመር ጥበቡ መጀመሪያ አዳምን ከአፈር እና እስትንፋስ... ከዚያ ሔዋንን ከአዳም የግራ አጥንት... ወዘተ እያልክ ምላሽ ለመስጠት መቀባጠርህ አይቀርም። እኔ ደግሞ አሁንም ጥያቄዬን እቀጥላለሁ... ለመሆኑ መጀመሪያ እግዚአብሔርን ማን ፈጠረው እልሃለሁ?... ከዚያ አንተ የሆነ ሀይል ትላለህ! እኔ አሁንም ጥያቄዬን በመቀጠል ያን የሆነ ሀይልንስ ማን ፈጠረው የሚል ጥያቄ አነሳለሁ ... እንዲህ እንዲህ እያለ ጥያቄው ይቀጥላል። በዚህ መሠረት ፍልስፍና ማለት የማያልቅ ጥያቄ ማንሳት ነው፤ የማያልቅ ጥያቄ ለማንሳት ግን ወጣ ያለ አመለካከት ሆነ አስተሳሰብ ሊኖርህ ይገባል። እየሀ ፍልስፍና ነገሮችን በልዩ ዓይን የሚመለከት ራሱን የቻለ ከፍተኛ የእውቀት ፍሰት ያለበት ዘርፍ ነው፤ ለዚያ ነው ሶቅራጥስ አዋቂ ነን ባዮችን በአደባባይ ንግግር ሲያደርጉ ይቅርታ በመጠየቅ እያቋረጣቸው በጥያቄ ሲያጣድፋቸው የነበረው። የሶቅራጥስ ትልቅ ጥረት አንድን ነገር ከስር መሠረቱ በሚገባ እንድናውቅ ይፈልግ ነበር።

ለምሳሌ ሰዎች አንድ ነገር ጥሩ ነው ሲሉ 'ይህ ነገር ጥሩ ነው ያልነው ጥሩ ስለሆነ ነው አልያስ ጥሩ ነው ብለን ስለተስማማን ነው?' የሚል ጥያቄ ያነሳል፡፡ ከዚያ በመቀጠል የሶቅራጥስ ቀጣይ ጥያቄ `ለመሆኑ ጥሩ ነው የምንለው ከምን ተነስተን ነው? ለእኛ ጥሩ የሆነው ለሌላ ሰው ጥሩ ባይሆንስ?... መሰል ጥያቄዎችን መጠየቁን ይቀጥላል፡፡ የሶቅራጥስ ግብ አንድን ነገር በስሜታዊነት ሳይሆን ከስር መሠረቱ አብጠርጥረን እንድናውቅ ይፈልግ ነበር፡፡ አንድን ነገር ደግሞ ከስር መሠረቱ ለማወቅ ብዙ ማሰብ እንዳለብን ይነግረን ነበር፡፡ በዓለም ላይ እጅግ ከባድ የሆነ ነገር ማሰብ ነው ይል ነበር፡፡ የዓለማችን በርካታ ምሁራን እንደሚያስረዱት እያንዳንዱ ሰው የአስተሳሰቡ ውጤት ነው ይላሉ፡፡ አንዲት የኦሮሞ አባባል ትዝ አለችኝ፡፡ 'ከን ያደ ቤኩ ያዳን ከን ያደ ሂንቤከኔም ያደቱ አቲ ጠበታ' የምትል ነች፡፡ በቀላል አማርኛ 'ማሰብ የሚችል በሀሳብ ሲጫወት ማሰብ የማይችል ግን ሀሳብ ይጫወትበታል' የሚል ፍቺ አለው፡፡በዚህ መሰረት መሬት በፀሐይ ዙሪያ ትሽከረከራለች የሚለውን እኔ አልቀበልም፤ ይልቅስ መሬትንም ሆነ ዓለምን የሚያሽከረከራት ሀሳብ ነው"

"ስለ ኦሮሞ ህዝቦች ካነሳን በኦሮምኛ እግዚአብሔርን 'ዋቃ' (waQa) ብለው ሲጠሩት የዋቃ መልክ ደግሞ ጥቁር መልክ አለው ይላሉ፤ ይህ የሁሉም ኦሮሞዎች አመለካከት ግን አይደለም፤ እኔ ይህን ሀሳባቸውን እጋራለሁ፤ ቢያንስ ለጥቁር መብት የቆሙ ናቸው፡፡ እነዚያ ብልጦች ነጮች በተለይ የመጀመሪያውን የእነ ኢየሱስን 'የጌታ ራት' የሳለው ዳቪንቺ በስዕሉ ውስጥ የጥቁር መልክ ጨርሶ ቦታ አልነበረውም፤ ለምን ቢባል በዚያን ዘመን የነበረውን እይታ እንተወውና አሁን እንኳ በዘመነ ስልጣኔ ነጮቹ ጥቁርን ቆሻሻ እና ሴይጣን አድርገው ይቆጥራሉ፤ ለነጮቹ የፈጣሪ መልክ ቀይ ነው፡፡ የሴይጣን መልክ ጥቁር ነው፡፡ የሚገርመው በዓለም ላይ የአምላክ መልክ ጥቁር (ሻንቅላ) ፧ ድሬድ ፀጉር ያለው ነው ብለው በዋነኛነት የሚከራከሩት ራስታዎች ናቸው፤ ለማንኛውም ኦሮሞዎች 'Gurracha garaa garbaa` ይላሉ ፍቺዋን የቤት ስራ ሰጥቼኋለሁ፡፡

⋮
▼

ስለ ሀሳብ፣ ስለፍቅር፣ ስለ ፖለቲካ፣ ስለዓለም... ስለፍልስፍና ... ከራምስ ጋር ያላወራነው ነገር የለም፡፡ የራምስ አባት ደራሲ ናቸው፡፡ በዚያ ላይ እጅግ ግዙፍ መፅሐፍ ቤት አላቸው፡፡ በዚህ የተነሳ ራምስ እጅግ በርካታ መፅሐፍትን ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ነው ምጥጥ

እያደረገ ማንበብ የጀመረው... በዚው በንባብ ዙሪያ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለን ዩኒቨርሲቲው ውስጥ በወጣለት ቅፅል ስሙ ጠራሁት:: ተማሪዎች በራሞስ እውቀት በጣም ይደነቁ፣ በጣም ይገረሙ ስለ ነበር ራሞስ ኤልያስ የሚለው ስሙ ተረስቶ 'ኢንሳይክሎፒዲያ እያሉ ይጠሩት ነበር:: እኔም በቅፅል ስሙ ጠራሁት::

"ኢንሳይክሎፒዲያ"

"አቤት" አለ በፈገግታ አሸብርቆ::

"እስከዛሬ ስንት መፅሐፍ አነበብክ?"

"እንዲህ አይነት ቀሽም ጥያቄ ሁለተኛ እንዳትጠይቅ፤ በእርግጥ አንድ መፅሐፍ ብቻ ካነበበ ሰው ተጠንቀቅ ይላሉ ምሁራን ፤ ዋናው ነገር ግን እጅግ በርካታ መፅሐፍቶችን ማንበቡ ሳይሆን ያነበብኩት መፅሐፍ ማስተላለፍ የፈለገውን ሀሳብ ተረድቼዋለሁ ወይ ? የሚለው ጥያቄ ነው:: ለምሳሌ በእኛ ዘመን ከመጡት ዝነኛ ደራሲያን መሀከል በእውቀቱ ስዩም፣ ይስመሀክ ወርቁ፣አዳም ረታ... ወዘተን መፅሐፍት ሁሉ አንብበህ ይሆናል:: እዚህ ጋር ማንበብህ ዋጋ የሚኖረው የሶስቱን ኢትዮጵያዊን ደራሲዎች ሁሉንም መፅሐፍ ማንበብ ሳይሆን እና እንል አንብቤያለሁ ብሎ ወሬ ከማቡካት ባሻገር የሶስቱን ደራሲያን ስራዎች አነበብኩ ማለት የምትችለው በመፅሐፋቸው ውስጥ ማስተላለፍ የሚፈልጉትን አንኳር ሀሳብ ስታገኝ እና ስትገነዘብ ነው፤ በሌላ ቋንቋ ማንኛውም መፅሐፍ ስታነብ ማንሳት ያለብህ በዚህ መፅሐፍ ደራሲው ማስተላለፍ የፈለገው ሀሳብ ምንድን ነው? ሀሳቡስ እውነታ ነው ግላዊ? ያነሳው ሀሳብ እኔን ይመለከተኛል? ለእኔ ምን ይጠቅመኛል? ለመሆኑ ይህን ሀሳብ ከዚህ በፊት እኔ አላቀውም? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ነው ያለብህ፤ ያለበለዚያ ማንበብ በህይወትህ ላይ እንዳችም ለውጥ የማያመጣ ከሆነ መፅሐፍ ካላነበበው አንተ የምትሻልበት ነገር የለም:: አንድ መፅሐፍ አንብበህ አንድ ሀሳብ ካገኘህ ስኬታማ ነህ፤ ምክንያቱም የሁሉ ነገር መጀመሪያ ሀሳብ ነው:: በመጀመሪያ ሀሳብ ነበር፤ ሀሳብም ከሰው ድንቅ አዕምሮ ውስጥ ነበር፤ ሀሳብም ከጊዜ ብዛት ተግባር ሆነ... ያ ተግባር ነው ዓለምን የለወጣት:: በዓለማችን ላይ ካሉት ትላልቅ ግኝቶች ጀርባ ቀዳሚው ነገር ሀሳብ ነበር፤ ለዚያ ነው ኢንግሊዛዊው ሼክስፒር 'ደሀ ማለት ሳንቲም የሌለው ሳይሆን ምንም ሀሳብ (ህልም) የሌለው ማለት ነው' ያለው:: በዓለም ላይ ያሉት ድንቅ ፈጠራዎች ሁሉ መጀመሪያ ሀሳብ ነበሩ:: ዓለምን የሚያንቀሳቅሳት ሀሳብ ነው:: ሁለቱ አሜሪካዊያን ወንድማማቾች አውሮፕላን

ለመስራት ያበቃቸው እይታ እና ሀሳብ ነው፡፡ በሰማይ ላይ ወፎች ሲበሩ ተመለከቱ፣ ወዲያው ታናሽየው በፈገግታ እሽብርቆ

'እንደማስበው ይህን ነገር ማድረግ የምንችል ይመስለኛል' አለው፡፡

' የቱን ነገር?'

'የሰው ልጅ ልክ እንደ አዕዋፋት በሰማይ ላይ የሚበርበትን መሳሪያ መስራት እንችላለን'

' እንሞክራ' አለው፡፡ ከዚያ ሀሳብ ተወለደ፡፡ ከሀሳብ ልምምድ... ከልምምድ ጥረት፡፡ በዓለም ላይ በአንድ ጊዜ ሙከራ ብቻ የሚሳካ ነገር የለም፡፡ ቶማስ አልፋ ኤዲሰን መብራትን ለመስራት 999 ሙከራ አድርጓል፡፡ አስበው እንዴት አይነት ትዕግስተኛ ሰው እንደሆነ፡፡ በዓለም ላይ ያሉት አስገራሚ ግኝቶች ሆኑ ቴክኖሎጂዎች ሁሉ መጀመሪያ ሀሳብ ነበሩ" ስለ ሀሳብ በርካታ ነገሮችን የነገረኝ ራሞስ ኤልያስ ነው፡፡ ራሞስ ኤልያስ እርጋታ የተሞላበት፣ ደስ የሚል ቁመና ያለው፣ ሲራመድ ቀጥ ብሎ የሚራመድ፣ መነፅር ማድረግ የሚወድ፣ ፀጉሩን አፍሮ የሚቆረጥ፣ ውብ አፍንጫ ያለው፣ ካኪ ሱሪ ብቻ የሚያደርግ ፣ ትላልቅ ጆሮዎች ያሉት... ኢትዮጵያዊ ወጣት ነው፡፡ ከምንም በላይ የሚገርመኝ እጅግ በርካታ ነገሮችን ያውቃል፣ ስለማንኛውም ርዕስ ቢጠየቅ ምላሽ አያጣም...

አንድ ዕለት ከሰፈራችን ጃንሜዳ (በእርግጥ አሁን እነርሱ ቤት ቀይረው የሚኖሩት ፒያሳ ጣይቱ ሆቴል ጀርባ ነው) ተነስተን ወደ ምኒሊክ ት/ቤት ወከ ስናደርግ ሁለት እጅግ ግዙፍ ፈረሶች አየን፡፡ (በእርግጥ ፈረስ ማየት ብርቃችን አይደለም፡፡ ሁሌ የፈረስ ውድድር ጃንሜዳ ሲደረግ እየገባን እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ፈረሶች ግን እጅግ ግርማ ሞገስ ያላቸው፣ ግዙፍ እና በጣም የሚያምሩ ስለሆኑ ነው) በተለይ አንደኛው ፈረስ ግዝፈቱ በጣም ያስደንቅ ነበር፡፡

"ዋው! የሚደንቁ ፈረሶች ናቸው ባክህ" አልኩት፡፡

"ትክክል! የሚገርምህ በዓለም ላይ ከሆላንድ እና አርጀንቲና ቀጥሎ ብዙ ፈረስ ያላት

አገር የእኛዋ ሚስኪን ኢትዮጵያ ነች፡፡ በአገራችን ለፈረስ ትልቅ ክብር የነበረው በቀደሙት የኢትዮጵያ ነገስታት እና መሪዎች ዘመን ነበር፡፡ በዓለም ታሪክ ከእያንዳንዱ የጦርነት ታሪክ ጀርባ ፈረሶች ነበሩ፡፡ በፈረስ ዙሪያ ሚስስ ሲልቪያ ፓንክረስት Ethiopia cultural History በተባለው መፅሐፋቸው ላይ 'እንኳን የኢትዮጵያ ወታደር የኢትዮጵያ ፈረስ እንኳ ሀገሩን ኢትዮጵያን ጨርሶ አይከዳም' በሚል ስለ እስደናቂው ዞብል ፈረስ የፀፉትን እውነተኛ ታሪክ ሰምተሃል?"

"በጭራሽ"

"በአጭሩ ልንገርህ በኢትዮጵያዊያን እና በሱዳናዊያን መሀከል በተደረገ ጦርነት ዞብል የተባለው እጅግ ውብ እና እጅግ ግዙፍ ፈረስ ጦርነቱ ላይ ከአንጌታው ተማርኮ ሱዳን ይወሰዳሉ... ሱዳኖቹ የሚያምረውን ዞብል ፈረስ እና ኢትዮጵያዊ ጦረኛ ከነፈረሱ በመማረካቸው በፌሽታ ተሞሉ! በሣቅ ተፍነከነኩ! ጮቤ ረገጡ! የኢትዮጵያንን ባንዲራ! የኢትዮጵያን አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራ መሬት ላይ ጥለውት ይረግጡት ገቡ... ዞብል ይህን ድርጊት ተመለከተ ... የሱዳን ወታደሮች ዞብልን ለመጋለብ ጥረት ማድረግ ገቡ፣ ዞብል ግን እሻፈረኝ እያለ መሬት ላይ ያፈርጣቸው ጀመረ.... ብዙ ጥረት ቢያደርጉም መሬት ላይ እያነሳ ያፈርጣቸው ገባ፡፡ በፈረሰኛ ቋንቋ ማንም ሱዳናዊ እኔ ጀርባ ላይ የሱዳንን ባንዲራ ይዞ ሊጋልብ አይችልም አለ! በቀስታ ጌታው ጋር ተጠጋ... ጌታውም በፍጥነት ዞብል ላይ ዘሎ ወጣ!! ይህን ጊዜ በሚያስደንቅ ፈልም የመሰለ ትዕይንት ዞብል መሬት ላይ ወድቃ የነበረችውን የኢትዮጵያ ባንዲራ በጥርሱ ነክሶ በመያዝ ሳይታሰብ ጌታውን እንደያዘ በመፈርጠጥ አመለጣቸው!! ገሰገሰ! ፈረጠጠ! ሸመጠጠ! በረረ! ከነፈ! ጋለበ! ተምዘገዘገ!... የሱዳን ወታደሮች በፈረሶቻቸው ላይ ሆነው ሊደርሱበት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም የኢትዮጵያ ፈረስ የሆነው ዞብል በኢትዮጵያዊነት ስሜት! በኢትዮጵያዊነት እልበገርም ባይነት ወኔ! የአገሩን የኢትዮጵያን ባንዲራ በመያዝ እና ጌታውን በመሸከም... እየገሰገሰ ከሶስት ቀናት እጅግ አድካሚ ጉዞ በኋላ አገሩ ኢትዮጵያ መሬት ላይ ከተነሱበት ቦታ ላይ ባንዲራውን እና ጌታውን አድርሶ በከፍተኛ ድካም እና ምግብ ማጣት የተነሳ ወዲያውኑ ሞተ፡፡ እየሀ ፈረስ አንድ ጊዜ የሄደበትን መንገድ በምንም ተዓምር አይረሳም፡፡ ይህ ለፈረሶች ዋቃ የሰጣቸው ትልቁ ፀጋቸው ነው፡፡ ዞብል ፈረስ ግን ከፈረስም በላይ የሆነ ታሪክ የሄፈ ፈረስ ነበር፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊያን ቀሽሞች ነን እንጂ ይህ ታሪክ በፈረንጆቹ የተከናወነ ቢሆን ኖሮ እንዴት የመሰለ

ፈልም፣ እንዴት የመሰለ ሀውልት ይሰሩለትና ይህን አስገራሚ ታሪክ ከትውልድ ትውልድ ያስተላልፉት ነበር፡፡ እኛ ሀገር ሀውልት የሚቀረፀው ነገ ትውልድን ከትውልድ የሚያባላ፣ ስለ ዘረኝነት፣ ስለቂመኝነት፣ ስለ ጥላቻ የሚሰብክ ነው፡፡ ለማንኛውም ወደተነሳሁበት ፈረስ ታሪክ ልመለስና በኢትዮጵያ ታሪክ ምንም እንኳ ሀገ አሁን ተቀባይነት ባይኖረውም በአዋጅ መልክ ነጋሪት በማስጎሰም 'ኢትዮጵያዊያን ሴቶች በምንም ዓይነት ፈረስና በቅሎ ላይ ወጥተው እንዳይጋልቡ፣ ሴት ልጅ እግሯን አንፈራጥጣ ፈረስ ላይ መቀመጥ አይገባትም የሚል አዋጅ ያወጁት የኢትዮጵያ ነገስታት ቀዳማዊ አፄ ኢያሱና አፄ ዘ ድንግል ነበሩ፡፡ ለማንኛውም የአፄ ቴዎድሮስ ፈረስ ስሙ ማን ነበር?" አለኝ፡፡

"አባ ታጠቅ"

"የአፄ ዮሐንስ?"

"አባ በዝብዝ"

"የአፄ ምኒልክ?"

"እህ... ጠፋብኝ"

"የአፄ ምኒልክ አባዳኘው፣ የደጃች ባልቻ ሳፎ አባነፍሶ፣ የንጉስ ተክለሀይማኖት አባጠና፣ የአፄ ኃይለስላሴ አባጠቅል... አሀ የመሰሰ ዜናዊ ፈረስስ?" አለኝ፡፡

"እንዴ? ደግሞ መለስ ዜናዊ ፈረስ ቀርቶ መኪና እንኳን መንዳት አይችልም አይደለም እንዴ?"

"አይ አንተ..." አለኝና የሆነ ነገር ሹክ ቱስ አለኝ፡፡ በጣም ሳኩኝ፡፡ ያለኝን ብነግራችሁ ደስ ይለኝ ነበር ፤ ቢሆንም የሚቀየሙ ሰዎች አሉና ይቅር...፡፡

ራምስ የማያውቀው ታሪክ የለም፡፡ የማያውቀው የመረጃ አይነት የለም፡፡ በተለይ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ የማያውቀው ታሪክ የለም፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የተፃፉ ከአስራ ሁለት በላይ መፅሐፍትን አንብቧል፤ ታዲያ ሁሌ ስለ ኢትየጵያ ታሪክ ሊነግረኝ ሲፈልግ በጥያቄ ነው የሚጀምረው፡፡

"ስማ ኬኖ"

"እሀ" አለዋለሁ::

"የኢትዮጵያን ታሪክ ሁሌጊዜ ሳነብ በጣም የሚገርመኝ የጦርነት እና የመገዳደል ታሪክ ይበዛበታል፤ ለመሆኑ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የትኛው ንጉስ ነበር እጅግ በርካታ ከሆኑ ሴቶች ጋር ወሲብ ካደረገ በኋላ ከእኔ ጋር የተኛች ሴት ከሌላ ወንድ ጋር በጭራሽ መተኛት የለባትም በሚል በድብቅ ሴቶቹን ሁሉ ክብር ሳይሰጣቸው ይገድል የነበረው መሪ ማን ነበር ?"

"እሀ"

"ምርጫ ልስጥህ?"

"ደስ ይለኛል"

"ሀ. ይኩኖ አምላክ ለ. ፋሲል ሐ. ዘርያዕቆብ መ. ኢያሱ"

"በግምት ልመልስ?"

"ቀሽም!! ታሪክ በግምት አይመለስም፤ ታሪክ በግምት አይፃፍም፣ ታሪክ አንድን ወገን ለማስደሰት አይፃፍም ፤ ታሪክ ውስጥ ውሸት አይዶለትም፤ ለዚያ ነው በታሪክ ውስጥ "ቢሆን" የሚል ቃል የለም የሚባለው:: በዚያ ላይ አንተ ደራሲ ልትሆን ነው! ከማንም ይበልጥ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ማወቅ ሆነ ማንበብ አለብህ ፤ ምክንያቱም አንዱ ገፀባህሪይ ስለታሪክ የሚያወራ ይሆናል፤ ስለዚህ አሪፍ ደራሲ ነው የሚባለው ደግሞ ስለሚያውቀው ነገር ብቻ የሚፅፍ ነው ፤ ስለምታውቀው ነገር ደግሞ ለመፃፍ በቂ መረጃ ያስፈልግሃል:: እሺ ተጨማሪ ጥያቄ ልጠይቅህ በኢትዮጵያ ታሪክ የትኛዋ የኢትዮጵያ መሪ ሚስት ነበረች ስልጣን ከቤተሰብ እንዳይወጣ ሲባል በኢትዮጵያ ባህል በማይታሰብ መልኩ ከገዛ ወንድሟ ጋር በመዳራት ልጅ የወለደችው?"

ሀ. ጣይቱ ሐ. መነን

ለ. ምንትዋብ መ. ዘውዲቱ"

መልሱን ስለማላውቀው ዝም አልኩት:: ራሞስ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስለተከናወኑት አስቀያሚ፣ አስገራሚ ፤ ዘግናኝ፣ ለመስማት የሚጎረብጡ ታሪኮችን ሁሉ ነግሮኛል፤ እንዳነብም ጉጉት እየፈጠረ በመተው አነቃቅቶኛል:: አንድ ቀን ያው " መገዳደል እና ደባ የበዛበትን የኢትዮጵያ ታሪክ እንስተን ስናወራ ጥያቄ አነሳሁለት::

ዛሬን ከተመሳሳይ ጥፋት መታቀብ ካልቻልን እና ባለፈ ታሪክ የምንባላበት እና ቂም መመንዘሪያ የምናደርገው ከሆነ የታሪክ ጥቅሙ ምንድነው?"

"እኚህ በምድር ላይ ምንጊዜም አዕምሮ ጤነኛ እና አዕምሮ ህመምተኛ ሰዎች አሉ:: በምድር ላይ Protagonist እና Antagonist እይታ ያላቸው ሰዎች አሉ! በምድር ላይ ዓለምን ለመለወጥ የሚጥሩ እና ቁጭ ብለው ነገር እና ጥላቻን እየሰበኩ የሚቆሰቁሱ ሰዎች አሉ... ስለዚህ አዕምሮ ጠማማ ከሆነ ትላንትን ዛሬ ላይ ታመጣለህ! በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በአስራ አምስተኛው ክፍለዘመን ... በ17ተኛው፣ በ18ተኛው፣ በ19ኛው፣ በ20ኛው ላይ ሆነ አሁን በ21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ አምጥተህ እዚህ ዘመን ላይ መዳኘት በጭራሽ አትችልም:: ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የተሳሳተ እይታ ይህ ነው ፤ እኔ በኢትዮጵያ ታሪክ ደስ የሚለኝ ኢትዮጵያ ከውጪ ጠላቶቿ ጋር ያደረገችውን ብቻ ነው! ከዚያ በተረፈ የእርስ በእርሱ ምን ያስደስታል? አንዱ ኢትዮጵያዊ ሌላውን ኢትዮጵያዊ መግደል ምን ያረካል? ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያውን ደም አፍስሶ መሸለል፣ ራሱን ጀግና ብሎ መጥራት ፣ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት፣ የጀግና ዘር ነኝ ማለት ለእኔ እርካታ የለውም!! ይህም አልበቃ ብሎ ትላንት እንዲህ ተደርገን ነበር፣ ትላንት ተረግጠን ነበር፣ ትላንት ተጨፍልቀን ነበር... ስለዚህ ዛሬ እኛ ባለጊዜዎች ስለሆንን ጊዜያችንን እና ስልጣናችንን ተጠቅመን የትላንቱን ብድር መመለስ አለብን ማለት እንዳልኩህ የቀውስ አዕምሮ ውጤት ነው፤ ምክንያቱም ጥላቻን የሚዘራ፣ ትላንትን በይቅርታ የማያልፍ፣ ቂም እየቆጠረ የሚመነዝር፣ ከፍቅር ይልቅ ፀብን የሚበትን፣ ከሰብዓዊነት ይልቅ ራሱን የተለየ ፍጡር አድርጎ የሚመለከት የቀወሰ አዕምሮ ብቻ ነው፤ የቀወሰ አዕምሮ ብቻ ነው ታሪክን ከመማርያነት ይልቅ ለበቀል እና ለጥላቻ የሚነሳበት:: ይህን ጉዳይ በተመለከተ ዝነኛው ግብፃዊ ፈላስፋ አኒስ መንሱር 'ትንሽ አዕምሮ እንደማይከሮስኮፕ ነው የማይረባን ነገር ያጎላል' ይላል..." ብዙ ነገር ነው ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ራሞስ የነገረኝ ፣ ብቻ በዚህ እውቀቱ መንፈሳዊ ቅናት አለብኝ::

▪
▪
▪
▼

እንዲሁ አንድ ጊዜ የተለመደውን ወክ እያደረግን ፒያሣ ደረስን:: ግርግር የማይጠፋባት ፒያሣ ወርቅ ቤቶች ስንደርስ "ወርቅ ትወዳለህ?" አልኩት:: በርከት ያሉትን

ወርቅ ቤቶች እያመለከትኩት::

"በነገራችን ላይ ፒያሣ የድሮ ስሟ አራዳ ነበር ፤ ጣሊያን ስትወረን በተለይ ግንቦት 5 ቀን 1936 የኢጣሊያ ብረት ለበስ ከፍለጦር አዲስ አበባን ሲቆጣጠር አራዳ የሚለው ኢትዮጵያዊ ስም ተቀየረና "ፒያሣ" ተብላ ተጠራች፤ ሀዋሳ ከተማ ውስጥ ፒያሣ የሚባል ሰፈር አለ... ጎንደርም ፒያሣ የሚባል ሰፈር አለ... የአባጅፋር አገር ጅማ ፒያሣ የሚባል ሰፈር አለ... ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞችም ይህ የጣሊያን ቃል የሆነው "ፒያሣ" ወርናል፤ የአዲስ አበባዋ ፒያሣ ግን ልዩ ቦታ አላት፤ አንደኛ በጣም ታሪካዊ ቦታ ናት ፤ ሁለተኛ የአዲስ አበባ ከተማ እንብርት ነች፤ ለማንኛውም ወደ ተነሳንበት ወርቅ ስንመለስ በዓለማችን ላይ ከነዳጅም በላይ በዓለም ገበያ ትልቅ ቦታ ያለው ወርቅ ነው:: የወርቅ ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣት ላይ ይገኛል:: እንደምታስታውሰው በ chemistry ትምህርታችን ወርቅ 'AU' በመባል Atomic Number 79 ላይ ይገኛል፤ በዓለማችን ላይ በዓመት ውስጥ በአማካኝ ከ355,000 ሺ ኪሎግራም ወርቅ በማውጣት እና በመገልገል ቀዳሚ የሆነችው የወርቅ ግንባር ቀደም ሀብታም ቻይና ነች፤ በመቀጠል 270,000 ሺ ኪሎ ግራም ወርቅ ፍጆታ ላይ የምታውለው የዓለማችን ሀገር አውስትራሊያ ነች፤ ከዚያ አሜሪካ፣ ራሺያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ፔሩ፣ ካናዳ፣ ጋና፣ ኢንዶኔዥያ እና አስረኛ ዑዝቤኪስታን እያለ ይቀጥላል:: ለበርካታ የዓለም ሆነ የአፍሪካ ሀገራት ገንዘባቸውን የምታትምላቸው ተንኮለኛዋ ኢንግሊዝ ናት:: ታዲያ ለምታትመው የወረቀት ገንዘብ ከየ አገራቱ ዋጋ የምትቀበለው በወርቅ ነው:: አየህ ኢንግሊዞች ምን ያክል ቆቅ እንደሆኑ? ወረቀት ሰጥተው ወርቅ ይቀበላሉ፤ ወርቅ ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ገናናነቱ እንደቀጠለ ነው:: የአለማችን ጢባራም ሀብታሞች የወርቅ አሊጋ፣ የወርቅ አልባሳት በተለይ የወርቅ ሰዓት... ይጠቀማሉ:: ወርቅን በማምለክ ዓለምን የሚመሩት ህንዳዊያን ናቸው:: አንዲት ቀሽት ህንዳዊት ቺክ ለመጥበስ የውሸት ወርቅ አንገትህ እና እጅህ ላይ ማድረግ ብቻ ይጠበቅብሃል..."

"በዓለማችን ላይ ከሚመሩት ህዝብ የበለጠ ለወርቅ ከፍተኛ ፍቅር የነበራቸው ንጉሶች ነበሩ:: ለምሳሌ የህንዱ ታጅ ሙሃል አይነቱ ጥንታዊ ቤተመንግስት 75% ውስጡ የተሰራው ከወርቅ ነው:: ስለ ወርቅ ከተነሳ ጥንት አንድ የፐርሺያ ንጉስ ነበር፤ ይህ ንጉስ ለወርቅ ከፍተኛ ፍቅር ከፍቅርም አልፎ በወርቅ ማምለክ ደረጃ ደርሶ ነበር እናም 'ስትፀልይ ጥንቃቄ አድርግ ምናልባት ፀሎትህን ዋቃ ሰምቶ ፈጣን ምላሽ ሊሰጥ ይችላልና' የሚባለውን

አባባል ዘንግቶት እና ችላ ብሎት ጠዋትና ማታ " ፈጣሪ ሆይ እባክህ የነካሁት ሁሉ ወርቅ ይሁንልኝ" እያለ ለ35 ቀናት ፀሎት አደረገ:: በ36ተኛው ቀን ለዚያ ንጉስ ፈጣሪ እንደ ሙሴ፣ አብርሃም መሰሉ የተመረጡ ብፁዓን ሰዎች ለንጉሱ ስሙን በመጥራት "ፀሎትህን ሰምቻለሁ የነካኸው ሁሉ ወርቅ ይሁንልህ" አለው:: ንጉሱ በደስታ ጮቤ ረገጠ:: ወዲያው እንጨት ሲነካ ወርቅ ሆነለት! ድንጋይ ሲነካ ወደ ወርቅ ተቀየረለት! ምግብ ሊበላ እጁን ሲዘረጋ ምግቡ ወርቅ ሆነለት! የሚወዳት ሚስቱ ስትመጣ ሲነካት ወርቅ ሆነችለት ... እነሆ የሚነካው ነገር ሁሉ ወርቅ ይሆንበት ገባ:: የዚያን ጊዜ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ:: በርሃብ የተነሳ ከሶስት ቀናት በኋላ ሞተ ይባላል:: እየህ የስግብግብነት መጨረሻ ራስህን ማሳጣት ደረጃ ያደርስሃል:: ይሆን በተመለከተ ማላዊያን "ለምታፈቅረው ነገር ምን ይሁን ምንም ለከት እና ገደብ አበጅለት ያለበለዚያ የምታፈቅረው ነገር እስረኛ ትሆናለህ" የምትል ግሩም አባባል አለቻቸው::"

ራሞስ ስለመፅሐፍት ፣ ስለህግ፣ ስለጋዜጣ፣ ስለዓለም ታሪክ... ብቻ ስለማንኛውም ርዕስ ቢጠየቅ ያለ አንዳች ችግር የሚለውን አያጣም:: የሀይስኩል ተማሪዎች እያለን የራሞስ ቅፅል ስም "ራሞስ ሸሌ" ነበር:: ራሞስ ሸሌ የሚለውን ስያሜ ያገኘው ከበርካታ ሸሌዎች ጋር ሽርሙጥና ፈፅሞ ሳይሆን ይሆን ስያሜ ያገኘው የአማርኛ አስተማሪያችን የነበረችው ቀጫጫ ነገረኛ ዮዲት መሳኩ ስለ ዐ/ነገር መዋቅር እና ስለ አንቀፅ አፃፃፍ እያስተማረችን "አበበ በሶ በላ" የሚለውን የተለመደ አሰልቺ ዐ/ነገር "እስቲ ልጆች ይሆን የተሰላቸ ከሊቹ" የሆነ አባባል በዘመናዊ ዐ/ነገር ተኩ" አለችን:: ወዲያው ተማሪዎች እጃቸውን አያነሱ

⇒ አበበ ከትፎ በላ::

⇒ አበበ ቺዝ በርገር በላ::

⇒ አበበ ጥብስ በላ::

ወዘተ እያሉ ሲናገሩ ከእኔ ጎን የሚቀመጠው ራሞስ እጁን በማውጣት አንዳችም ሳይፈራ "አበበ ሸሌ በዳ" የሚል ዐ/ነገር ተናገረ... አስተማሪዋ "ባለጌ" በማለት አንበረከከችው... ተማሪዎች ደግሞ "ራሞስ ሸሌ" የሚል ቅፅል ስም አወጡለት ::

ራሞስ ብልህ እና ቀለሜ ተማሪ መሆኑ የታወቀው ገና የአራተኛ ክፍል ተማሪ እያለን ነበር:: ድምፁ እንደ ሴት ቀጭን የሆነው የሂሳብ አስተማሪያችን "ልጆች አንድ ሰውዬ ፲ ኪሎ ድንጋይ ተሸክሟል ! አንዲት ሴትዮ ደግሞ አስር ኪሎ ጥጥ ተሸክማለች፣ ከሁለቱ የበለጠ ከባድ ሸክም የተሸከመው ማን ነው?" ሁላችንም

"እንዴ ሰውየው ነዋ! እርሱ እኮ የተሸከመው ድንጋይ ነው፣ የእርሷ ጥጥ ስለሆነ ቀላል ነው" እንላለን:: ራሞስ እየሳቀ "ቲቸር እእ! እእ" ይላል የሂሳብ አስተማሪያችን እድሉን ለራሞስ ይሰጠዋል:: "ሁለቱም እኩል ናቸው:: ሁለቱም እኮ የተሸከሙት ዕቃ አይነት ቢለያይም የሁለቱም አስር፣ አስር ኪሎ የሚመዝን ነው" በማለት ይመልሳል:: አጨብጭቡለት ይባላል:: ተንኮለኛው እና እንድናስተውል የሚፈልገው የሂሳብ አስተማሪያችን በሌላ ጊዜ አዘናግቶ "ልጆች ከሶስት ድንች ላይ ሶስት ካሮት ስንቀንስ ስንት ይቀራል?" ይለናል:: እኛ በፍጥነት "ዜሮ ነዋ!" እንላለን:: ራሞስ እየሳቀ እጁን ያወጣና "ከድንች ላይ ካሮት እንዴት ይቀነሳል ጥያቄው ተሳስቷል" ይላል... በሂሳብ ትምህርት እኛን ግራ የሚያጋቡ ጥያቄዎች ለራሞስ ቀላል እና ተራ ናቸው:: በጣም ጥቂቶች እንጂ አብዛኛው የኢትዮጵያ እና የአሜሪካ ተማሪዎች በሂሳብ ትምህርት ደካሞች እና ቶሎ አይገባቸውም የሚል ጥናት አንብቤ ይህ ጥናት በጭራሽ ራሞስን እንደማያካትት ተረድቻለሁ፣ ምክንያቱም ራሞስ ገና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ እያለ የአስራ አንደኛ እና የአስራ ሁለተኛ ክፍል የሂሳብ ጥያቄዎችን በቀላሉ ይፈትናቸው ነበር:: ለምሳሌ አንድ ጊዜ በእረፍት ሰዓት ሁለት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በሚከተለው ጥያቄ እየተከራከሩ ነበር:: አንደኛው የእኛ ሰፈር የጃንሜዳ ልጅ ነበርና አጠገባቸው እኔና ራሞስ ቆመን ማዳመጥ ጀመርን:-

ጥያቄው

What is the area of the region between the graphs of $Y=-X^2+2$ and $Y=|x|$ where $-1 \leq x \leq 2$?

A. 11/6 B. 25/6 C. 7/3 D. 11/3

ብታምኑም ባታምኑም ይህን ጥያቄ ሁለቱ የ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች እየተከራከሩ ራሞስ በቃሉ አሰልቶ ጨርሶት ድንገት በክርክራቸው መሀከል "ትክክለኛው መልስ B ነው" ሲላቸው ሁለቱም ደነገጡ:: በግራ የተቀመጠው በግርምት "እንዴት አወክ?" አለው::

"አሰላሁት"

"ቢቃልህ?"

ወዲያው ምንም ሳይናገር እጃቸው ላይ የነበረውን እስኪርቢቶ ተቀበለና ሁለት ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሰርቶ አሳያቸው:: ሁለቱ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች እውን ይህ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ነው? እንዴት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሆኖ የአስራ ሁለተኛ ክፍልን ጥያቄ ሊሠራ ይችላል? እድሜ በቂጡ ይሆን እንዴ? በሚል ግርምት ተመለከቱት::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ሆነን አንድ ቅዳሜ ዕለት አንበሳ ግቢ የዱር እንስሳትን ለማየት ገብተን እጅግ በርካታ ቻይናዊያንን አየን::

"አንተ እነዚህ አይነጠባብ ሰዎች እኮ ኢትዮጵያን እየወረሯት ነው" አልኩት::

"በአሁኑ ጊዜ በቅርቡ በደረሰኝ መረጃ በትንሹ ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ 75,000 ሺ የሚጠጉ ቻይናዊያን አሉ:: በአፍሪካ ውስጥ ብዛት ያላቸው ቻይናዊያን ያሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፤ የሚገርምህ በዓለማችን ላይ ካሉት አገራት ከኢንግሊዝ ቀጥሎ ቆቅ እንደቻይና የለም:: ምንም እንኳ ቁጥራቸው የተወሰነ ምሁራንና ሊቃውንቶች ከመሀከላቸው መኖራቸው የማይካድ ቢሆንም ኢትዮጵያ ውስጥ ከምታያቸው ብዛት ያላቸው ቻይናዊያን አብዛኞቹ ሌቦች እና ወንጀለኞች ናቸው:: ቻይና" ኮንፊሺየስ 622" የሚባል እጅግ ግዙፍ የተሰወረ ቦታ ያሰራችው ሚስጢራዊ እስር ቤት አላት፣ እዚያ እስር ቤት ውስጥ የስርቆት፣ የድብድብ፣ የማጭበርበር፣ የሰው መግደል... ወንጀሎች ሲሰሩ ወደ ዘብጥያው ይገቡና ባላቸው ችሎታ ላይ ተመስርቶ ለሰድስት ወራት የተለየ የሥነምግባር እና የሙያ ትምህርት ታራሚዎች እንዲማሩ ይደረጋል፤ ከዚያ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሚስኪን ታዳጊ የአፍሪካ ሀገራት "ባለሙያ" የሚል ታርጋ ይለጠፍባቸውና ይላካሉ፤ ከዚያ እዚህ ቀብረር እያሉ፣ እራቸውን እያኑብን፣ ፊሳቸውን እየፈሱብን ይኖራሉ:: የሚገርምህ ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን በላይ ህዝብ ያላት ቻይና አሰበው 54ቱ የአፍሪካ ሀገራት አንድ ላይ የህዝብ ብዛታቸው 915 ሚሊዮን ብቻ ነው:: ኮሚኒስት ቻይና ትንሽ እስር ቤቶች ብቻ አላት፤ በተለይ ይህ " በቻይና ምድር በየዓመቱ ለእስረኞች ቀለብ ከማውጣት ይልቅ ሰድስት ወራት ተምረው ወደ ተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ተልከው ቢሰሩ ይሻላል፤ ቢታሠሩ አገራቸን በወጪ ያከስራሉ፤ እኛው ራሳችን ለአፍሪካ ሀገራት

ብር እያበደርን የራሳችንን ሰራተኞች አብረን እየላክን በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ የሚባለውን የብልህ አነጋገር ተግባራዊ እናደርጋለን" የሚል አላማ ይዞ የተነሳ ተቋም ነው፡፡ እየሀ እንዴት ያሉ ብልጦች እንደሆኑ? ታዲያ ኢትዮጵያ ውስጥ ከቻይናዊያን ሰራተኞች ጋር ሚስኪን ሰራተኛ መስለው ተቀላቅለው የገቡ እጅግ በርካታ የሰለላ ባለሙያዎች እንዳሉም እንዳትዘነጋ"

"ለምን?"

"ለመቦጥቦጥ ነዋ! እየሀ ኢትዮጵያ ውስጥ ገና በአገልግሎት ላይ ያልዋለ ወርቅ አለ፡፡ ነዳጅ አለ፡፡ የተለያዩ አስፈላጊ ማዕድናት አሉ... የተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች አሉ... እነዚያ ላይ በድብቅ ጥናት ያደርጉና እዚህ መሬት ላይ አበባ እንትከልበት፤ መኖሪያ ቤት እንሰራበት፤ ፋብሪካ እንክፈትበት... ይሉና የኢትዮጵያ መንግስትን አታቂለው የኢትዮጵያን ንብረት ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል እንደሚባለው ይቦጠብጡናል ማለት ነው፡፡ ሰዎች እንዳይመስሉህ ተንኮለኞች፤ መሰሪ የሆኑ ፍጡሮች ናቸው፡፡ በተለይ ለጥቁር ያላቸው አመለካከት እንደዓይናቸው ጠባብ ነው፡፡ ለማንኛውም ኢትዮጵያን እንዲቦጠብጧት መንግስታችንም በሩን ብርግድ አድርጎ ከፍቶላቸዋል፤ እነሱም አሻሮ ይዘህ ወደ ቆሎ ተጠጋ የሚለውን መርህ እየተገበሩ ናቸው፡፡ የሚያሳዝነው በየከፍላሀገሩ መንገድ የሚሠሩት ቻይናዊያን ለጋ ለጋ የሆኑ ትናንሽ ኢትዮጵያዊያን ህፃናትን ጭምር ድንግል እልባ እያደረጓቸው ነው፤ ደፍረዋል፤ ግን የውጪ ዜጋ ናቸው! ሀገራችንን ለማልማት የመጡ ናቸው! በማለት ወንጀል እየሰሩ እንኳ መንግስት በዝምታ ይመለከታቸዋል፤ በጣም የሚያበሳጨኝ የኢትዮጵያ መንግስት ለራሱ ዜጎች ሳይሆን ቅድሚያ የሚሰጠው ለውጪ ሀገራት ዜጎች መሆኑ ነው፡፡ ይህ በጣም የሚያሳዝን ነው፤ ለማንኛውም ስለ ቻይና ከተነሳ ስለ ቼንጂንግ የተባለ አንድ አስገራሚ ቻይናዊ ወጣት ያነበብኩትን ልንገርህ፡፡ ይህ የቻይና ወጣት የክርስቲያን እምነት አራማጅ ነበር እና በአገሩ ቻይና አብዛኛው ሰው የሚከተለው የቡዲዝም እምነት ነው፡፡ ታዲያ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጨረሻ ላይ የቡዲዝም እምነት በሰፋት በተጠለቀለቀባት የቻይና ምድር ላይ አንድ አጠር፣ ቀጠን ያለ ፣ ረጅም ሉጫ ፀጉር ያለው ቻይናዊ እንደ ሶቅራጥስ ህዝብ በብዛት ያለበት አደባባዮች ላይ እየቆመ ድምፁን ከፍ በማድረግ

"የሀገሬ ህዝቦች ቻይናዊያን ሆይ! እነሆ ንስሐ ግቡ ከሀይማኖት ባርነት ነፃ እንውጣ! ሀይማኖት አያድንም እምነት ግን ያድናል ፤ አሁን እያመለካችሁት ያላችሁት ቡዲዝም ጣኦት ነው! ጣኦት አታምልኩ አዳኝ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ብቻ ነው! እነሆ ለመዳንም ሆነ

ዘላለማዊ ህይወት ለመኖርም ክርስቶስን መቀበል እና ክርስቶስ በህይወታችሁ ሊገባ የግድ ነው! መዳን በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ ብቻ ነው" እያለ መናገር እና መስበክ ቀጠለ፡፡ ድምፁ እጅግ የተለየ እና ለመስማት የሚያጓጓ ስለ ነበር ሰዎች ሳይወዱ በግድ በድምፁ ውበት እየተማረኩ ይሰሙት ገቡ፡፡ አንዳንዶቹም ስለ እግዚአብሔርም ሆነ ስለ ልጁ ክርስቶስ ይበልጥ እንዲነግራቸው ልባቸውን ከፍት ያደርጉለት ጀመር፡፡ ይህ ሰው አንድ ዓመት ሳይሞላ ዝናው እየገነነ መጣ፡፡ ሁኔታው ያልጣማቸው የቡዲዝም እምነት ተከታዮች በምሽት አፍነው በመውሰድ ዳግም እንዳያወራ ምላሱን ቆረጡት! ለአላማው ፅናት የነበረው ወጣቱ ቻይናዊ ሌላ መንገድ መምረጥ እንዳለበት በመወሰን በአፉ ሲናገር የነበረውን ወረቀት ላይ በመፃፍ እና በማሳተም አደባባይ ላይ ወጥቶ ወረቀቱን ይበትን ገባ፤ በዚህ ሁኔታ ይበልጥ የተናደዱት የቡዲዝም መሪዎች ምሽትን ጠብቀው ሁለቱን እጆቹን እንዳይፅፍ ቆረጡት! መናገር አይችልም! መፃፍ አይችልም አበቃለት! አዲዮስ አሉ! ወጣቱ ቻይናዊ ቼን በራሱ ከፍተኛ ጥረት በእግሩ መፃፍ ተለማምዶ አሁንም በእግሩ እየፃፈ በእግሩ አደባባይ ላይ ወረቀት ማደል ጀመረ... በመጨረሻ ግን በትልቅ መኪና ጨፈላለቁትና ሞተ፡፡ እየህ አንተ ወደፊት እንደነገርከኝ ደራሲ መሆን ትፈልጋለህ! ደራሲ ለመሆን ምን ያህል ጥረት እንደምታደርግ አላውቅም ፣ ህልምህን ለማሳካት ምን ያህል ርቀት እንቅፋቶች ከፊት ለፊትህ ቢደቀኑ እንደምትገፋበት አላውቅም! ይህ ቻይናዊ ወጣት ቼን ጂንግ ግን እስከ መጨረሻው ጥረት አድርጓል፡፡ ይህ ቻይናዊ ለእኔ ጥሩ ምሳሌ ነው! ያነቃቃኛል! ህልሜን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንዳለብኝ ይነግረኛል! ውስጤን በወኔ እና በሞራል ይሞላዋል! ትንሽ እንቅፋት ሲገጥምህ ወዲያው ተስፋ ቆርጠህ ህልምህን የምትሰርዘው ከሆነ መጀመሪያውኑ ህልምህ የውሸት ነበር ማለት ነው!! መጀመሪያውኑ ውስጥህን አላሳመንከውም ነበር ማለት ነው፡፡ የሰው ልጅ ደግሞ የአስተሳሰቡ እስረኛ ነው፡፡

ራሞስ ሽሌ ደስ የምትል ሳቅ አለችው፡፡ እጭር ሣቅ፡፡ በእኔ የህይወት ጉዞ እጅግ በርካታ ነገሮችን ያስተማረኝ ራሞስ ነው፡፡ የእኔ የእውቀት ሀሁ ራሞስ ነው... ስለ ሁሉ ነገር ያውቃል... እውቀት ብቻ አይደለም የተግባር እና ሥራ አከባሪ ወጣት ነው፡፡ በእርግጥ ሰው

ፍፁም አይደለምና ከራሞስ የማልወድለት ፀባይም አለው:: አንዳንዴ ድብቅ ነው:: ለምሳሌ ከሚከፈለው ገንዘብ በላይ በርካታ ብሮች ያጠፋል፤ ግን ከየት እንደሚያመጣ መናገር አይፈልግም... አንዳንዴ ከእኔ እየተደበቀ በከፍተኛ ብር ቁማር ይጫወታል!! እነዚህ ድብቅ ማንነቶቹ እንዳሉ ሆኖ... ስለ ወሲብ ብዙ መረጃዎች የነገረኝ ፤ ስለ መውደድ እና ፍቅር ብዙ ነገር የነገረኝ፣ ስለሙዚቃ፣ ስለሀይማኖቶች ልዩነት የነገረኝ... ስለ ኪነጥበብ እና ሥነጥበብ የነገረኝ ... ብቻ በእውቀት ተሞላ ወጣት ነው... ስለድርሰት እና ደራሲያን ብዙ ነገር የነገረኝ ራሞስ ነው፤ በተለይ መቼም የማልረሳው የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያለን ቤቱ ወስዶ ከገነኛ ደራሲ አባቱ ጋር ያስተዋወቀኝን ልዩ ቀን ነው:: ሽበት በሽበት የሆኑ ትልቅ ሰው ነበሩ::

"ሙሉ ስምህ ማን ነው" አሉኝ::

"ኪኛ ዮሐንስ በረዳ"

"ደራሲ መሆን እንደምትፈልግ ልጄ ነግሮኝ ነበር:: ክፍል ውስጥም በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ግጥሞች እና አጫጭር ልቦለዶች እንደምትሞነጫጭር ነግሮኛል"

"ትክክል ነው"

"ጥሩ ነው! የዛሬን አያድርገውና እኔም እንዳንተ ተማሪ እያለሁ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ግጥሞች፣ አጫጭር ልቦለዶች፣ ወጎች፣ መነባነቦች፣ እየፃፍኩ አቀርብ ነበር:: መፃፍ ደስ ይለኝ ነበር፤ ከወረቀት እና ብዕር ጋር ማውራት ደስ ይለኝ ነበር:: ነጭ ወረቀት እና እርሳስ ካገኘሁ ደስታዬን ተወው! ለመጀመሪያ ጊዜ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ለአባቴ "አባቴ ደራሲ ለመሆን እፈልጋለሁ ምን ማድረግ አለብኝ" አልኩት:: አባቴ የሣቀብኝን ሣቅ እስከዛሬ አስታውሰዋለሁ... ብዙ ከሳቀብኝ በኋላ "ወይ አንተ ኢትዮጵያ ውስጥ ደራሲ ከምትሆን መንገድ ላይ ቁጭ ብለህ ብትለምን ይሻልሃል! ደራሲ ሆንክ ማለት እስከመጨረሻው ከድህነት ጋር ተስማምተህ ለመኖር ቃል ኪዳን ፈፀምክ ማለት ነው! እኛ ቤት የሚመጣውን እየለን ታውቀዋለህ ? "አዎ" አልኩት

'ለምንድን ነው የሚመጣው?'

'ራበኝ ምግብ ስጡኝ ይላል! ምግብ ይበላል! አንተ ደግሞ ተጨማሪ ገንዘብ ትሰጠዋለህ'

'እየህ እሱ ሶስት መፅሐፍ የፃፈ ትልቅ ደራሲ ነበር፤ ግን በደራሲነት ያተረፈው ድህነትን ብቻ ነው:: የሺ. ቡና ቤት ጋር የሚቀመጠውን አብድ ታውቀዋለህ?'

'ያ ብቻውን እያወራ፣ ጫት እየቃመ፣ የሚስቀው ሰውዬ ነው?'

'አዎ! እሱም ታዋቂ ደራሲ የነበረ ነው አየህ ልጄ የደራሲነት መጨረሻ ይህ ነው፡፡ አንተ መሆን ያለብህ ደራሲ ሳይሆን ዶክተር አልያም ተመራማሪ ነው፡፡ እኔ ውድ ት/ቤት የማስተማርህ ተምረህ ትልቅ ሰው እንድትሆን ነው እንጂ የማይረባ ደራሲ እንድትሆን አይደለም' አለኝ፡፡ አባቴን ስለምፈራው አልተከራከርኩትም፡፡ ቀጥሎ ለአማርኛ አስተማሪዬ ደራሲ መሆን እንደምፈልግ እና ምን ማድረግ እንዳለብኝ ጠየኩት፡፡ አማርኛ አስተማሪዬ በትኩረት አየኝ

'ኤልያስ' አለኝ

'አቤት መምህር'

'ኢትዮጵያ ውስጥ ደራሲ ሆነህ ገንዘብ አገኛለሁ ብለህ የምታስብ እና በደራሲነት ሙያ ብቻ ለመኖር ካሰብክ በጣም አስቸጋሪ እና የማይቻል ነገር ነው'

'ለምን?'

'የህዝቡ ንቃተ ህሊና ገና ነው! ኢትዮጵያ ብዙ አንባቢ የላትም! በጣም ትንሽ አንባቢ ነው ያሉን! እነሱም መፅሐፍ ከመግዛት ይልቅ ተውሰው የሚያነቡ ናቸው፡፡ በእርግጥ ደራሲ ለመሆን የፈለከው ራስህን ለማዝናናት ከሆነ ማድረግ ያለብህን እነግርሃለሁ'

'አልገባኝም'

'ኢትዮጵያ ውስጥ በደራሲነት መኖር አይቻልም፣ ይህ ሀቅ ነው፣ ስለዚህ ደራሲነትን የትርፍ ጊዜ ስራህ ለማድረግ የምትፈልግ ከሆነ እኔ በቂ መረጃ እሰጥሃለሁ'

'ደስ ይለኛል'

ከአማርኛ አስተማሪዬ ጋር ምርጥ ጓደኛ ሆንኩ፡፡ ብዙ ነገር ነገረኝ፡፡ ከብዙ ፈተና በኋላ የመጀመሪያ መፅሐፌን አሳተምኩ፡፡ በእርግጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ደራሲ ለመሆን በጣም ብዙ ፈተና አለው፡፡ ብዙ እንቅፋቶች አሉት፡፡ በጣም ብዙ በፈተና ማለፍ ያለብህ ነገሮች አሉ... ለማንኛውም አንተም ደራሲ ለመሆን የምትፈልግ ከሆነ ከጎንህ ነኝ፡፡ ሁሉም ሰው ይሮጣል፣ ሁሉም ሰው ሯጭ መሆን ግን አይችልም፡፡ ሁሉም ሰው መፃፍ ይችላል፣ ሁሉም ሰው ግን ደራሲ መሆን አይችልም፡፡ ሯጭ ለመሆን ትልቅ ሳንባ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ደራሲ ለመሆንም ልዩ ተሰጥኦ ያስፈልጋል፣ ውስጥህ ተሰጥኦ ካለህ ያን የምታዳብርበትን ስልት እኔ እነግርሃለሁ፣ ስለዚህ ፈተና ትፈተናለህ፣ ያ ፈተና ውስጥህ የደራሲነት መንፈስ እንዳለብህ እና

እንደሌለብህ የምለይበት ይሆናል፣ ውስጥህ የደራሲነት ተሰጥኦ ካለህ ደራሲ ለመሆን የሚያበቃ ወይም አንድ ደራሲ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ማወቅ ያለበት ዘጠኝ ወሳኝ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚያን ነገሮች በአንድ ዓመት ውስጥ ቀስ በቀስ እስተምርሃለሁ" አሉኝ፡፡ ፈተናውን በሚገባ አለፍኩኝ፡፡ ውስጤ የድርሰት ተሰጥኦ እና የመፃፍ መክሊት እንዳለኝ አወኩኝ... የራሞስ አባት ጋሽ ኤልያስ በቃላቸው መሠረት ለአንድ ዓመት ሳይሰለቹ አንድ ደራሲ መሆን የሚፈልግ ሰው ማወቅ ስላለበት ዘጠኝ ነገሮች በእርጋታ አስተማሩኝ...

1ኛ. በጣም ብዙ ማንበብ እና የማንበብ ዘዴ

2ተኛ. ስለምትፅፈው ነገር ብዙ መረጃ ማሰባሰብ

3ተኛ. እስተዋይነት /ሶስተኛ ዓይን/

4ተኛ. ስለ ምናባዊነት

5ተኛ. ስለ ኢቃቂር ፈላጊነት

6ተኛ. የአፀመዋቅር አሳሳልን ማወቅ

7ተኛ. የድርሰት አለባዊያንን መለየት

8ተኛ. የስርዓተ ነጥቦች እና ዐ/ነገሮችን አጠቃቀም ማወቅ

9ኛ. የህይወት ልምድ...

ስለ እነዚህ ዘጠኝ ነገሮች አሁን በዝርዝር ለማስረዳት ሆነ በዝርዝር ለመፃፍ ብሞክር አንድ 800 ገፅ ያለው መፅሐፍ ያፅፈኛል፡፡ ይህን ሁሉ በገንዘብ የማይተመን እውቀት በነፃ የሰጡኝ የራሞስ አባት ናቸው፡፡ ብቻ ራሞስ ለእኔ ብዙ እውቀት የሰጠኝ ወጣት ነበር... የእኔ ጭንቅላት በእውቀት እንዲበረቅቅ ካደረጉት ሰዎች መሀከል አንደኛው ራሞስ ነበር፡፡ ራሞስ ለእኔ አንድ ራሱን የቻለ ቤተመፅሐፍ ነበር!! "ዓለም መድረክ ስትሆን ሰዎቹ ደግሞ ተዋንያን ናቸው፣ እ/ር ደግሞ ዳሬክተር ነው" የሚለውን የሼክስፒርን አባባል መናገር የሚያዘወትረው ራሞስ ለእኔ በሚገባ አንብቤ ያልጨረስኩት ትልቅ መፅሐፍ ነበር...

በኢትዮጵያ የምርጫ ታሪክ መቼም ሊረሳ የማይችለው ምርጫ 1997 የካርድ አውጡ ቅስቀሳ ሲጀመር፣ ኢትዮጵያ በምርጫ ቀውጢ ስትሆን ራሞስን "ራሞስ ቀበሌ እንሂድና ካርድ እንውሰድ እንጂ" አልኩት፡፡ መጀመሪያ ደስ የምትለውን ሳቁን ለገሰኝና

"አይ አንተ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ገና አልገባህም Anyway የአንተን የመምረጥ መብት ላለመጋፋፍ አብረን ቀበሌ መሄድ እንችላለን። አንተ አውጣ እኔ ካርድ ይለፈኝ"

"ምነው የቅንጅት ደጋፊ ነኝ ስትል አልነበረም እንዴ?"

"ብያለሁ!! አመነኝ ቅንጅት በከፍተኛ ድምፅ ያሸንፋል፤ ቢሆንም ኢህአዴግ በዋዛ የስልጣን ወንበሩን ይለቅለታል ብለህ እንደ ጅል አታስብ! የኢህአዴግ መርህ እንዳያማህ ጥሬው እንዳይበላ ግፋው የሚል ነው፤ በዚያ ላይ 40 ዓመት በስልጣን ላይ እቆያለሁ ብሎ ገና ሚኒካ እያለ ወስኖ የመጣ እምባገነን ፓርቲ ነው። ኢህአዴግ የስልጣን ወንበር ላይ የተቀመጠው በምርጫ ካርድ አኮ አይደለም፤ በጠመንጃ ነው። በጠመንጃ ስልጣን ላይ የተቀመጠ መንግስት በምርጫ ካርድ ይወድቅ ይሆን? አብረን የምናየው ሀቅ ይሆናል!! ይልቅ ከምርጫ ካርድ ጋር በተያያዘ 1976 ዓ.ም ላይ ስለተከሰተው ዘፋርመር ኬሪ ታሪክ ሰምተሃል?"

"አልሰማሁም"

"ባጭሩ 1976 በአሜሪካ በተደረገ የካሊፎርኒያ ግዛትን ፕሬዝዳንት ለመምረጥ በተደረገ ምርጫ ላይ ለመምረጥ 14,200 መራጮች ተመዝግበው በሚገርም ሁኔታ ሁለቱ ተወዳዳሪዎች እኩል 7,198 እና 7,198 አመጡ። እኩል ወጡ!! ወዲያው ከተመዘገቡት 14,200 መራጮች ምንም እንኳ ውጤቱ ቢታወቅም፤ ቆጠራ ቢደረግም ሁለቱ የቀሩ መራጮች በከፍተኛ አሰሳ ተፈልገው እንዲመርጡ እና ከሁለቱ ተወዳዳሪዎች አንደኛውን አሸናፊ ለመለየት ተፈለጉ። አንደኛዋ አሮጊት ከምርጫው በፊት በድንገተኛ አደጋ ሞታለች፤ ሌላኛው ታታሪው ገበሬ ኬሪ ነበር። ኬሪ የምርጫ ካርድ ቢወስድም በስራ ተወጥሮ ስለ ነበር ስለ ምርጫው ቀን ረስቶት ነበር። በመጨረሻ ግን የእርሱ አንዲት የምርጫ ካርድ አጅግ ወሳኝ እንደሆነች እና ከሁለቱ ተወዳዳሪዎች አንደኛውን መምረጥ እንዳለበት ተነገረው። ማንም ጣልቃ ሳይገባበት እና ወከባ ሳይፈጠርበት በራሱ ውሳኔ ድምፁን በነፃነት ለዲሞክራት ተወዳዳሪ ሰጠ! የዲሞክራት ተወዳዳሪ በአንዲት ድምፅ ብቻ 51% >49% በማምጣት አለፈ! ይህ ምርጫ አስገራሚው ምርጫ ተብሎ ተመዘገበ። እየህ አንዲት ድምፅ ምን ያህል ዋጋ እንዳላት? ይህን መሠል ምርጫ አፍሪካ ውስጥ ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ በእኔ እና አንተ ዘመን ይመጣል ብዬ አላስብም! የአፍሪካ ምርጫ ቱልቱላ እና ውሸት የበዛበት! ሽጉጥ እየተደቀነብህ የምትመርጥበት ! እንዲ 100% አሸነፍኩ ብሎ የሚደነፋበት! የህዝብ ገንዘብ በምርጫ ስም በዋዛ የሚበላበት! ብቻ የይስሙላ ጉዳይ ነው" ሲል ነበር የነገረኝ።

ራሞስ ሱሪው ጨዋ ነው፡፡ ሀይስኩል ሆነ ዩኒቨርሲቲ እያለን ከሴቶች ጋር ሆነ ቺኮች ጋር ያለው ግንኙነት ቀዝቃዛ ነበር፡፡ ለሴቶች ብዙ ግድ የለውም፤ ምክንያቱን ባይነግረኝም ከሴቶች ጋር መሆን ብዙ ምቾት አይሰጠውም፡፡ በሴቶች የተፃፉ ማንኛውንም ነገሮች አያነብም... ለሴት መምህራኖች ራሱ ባይናገርም ንቀት ያሳያቸው ነበር... ልክ ለወንዶች የሚሰጠውን ክብር ለሴቶች አይሰጣቸውም ነበር… የዚህን ነገር ምክንያት ሳላውቅ ራሞስ በአንዲት ወጣት በመኪና ተገጭቶ መሞቱ ያሳዝነኛል!! ሴትን ይጠላ ነበር፤ በሴት ህይወቱ ተቀጠፈች... የሚገርም አጋጣሚ እኮ ነው...

ስለ ስኬት ለመጀመሪያ ጊዜ የነገረኝ ራሞስ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ አዲስ አበባ ስታዲዮም ይሆን የምትውን ፤ እያዩት እንቅልፍ የሚያስመጣውን፤ በዘመናዊ ሳይሆን በባህላዊ መንገድ የሚንቀሳቀሰውን አግር ኳሳችንን ለማየት ገብተን ኳሱ እስከሚጀምር ስለስኬት እያወራኝ ነበር፡፡

"በእርግጥ ስኬት አንፃራዊ ነው፡፡ ባጠቃላይ ግን ስኬት ማለት እንደ ዚግዚግላር የተባለው ሰው አባባል "አንድ ሰው ስኬታማ ነው የሚባለው ገንዘብ የሚገዛቸውን ነገሮችና ገንዘብ የማይገዛቸውን ነገሮች ለማግኘት መቻል ነው" ይላል፡፡ በገንዘብ የማትገዛቸው እና በገንዘብ የማትተምናቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ እነ ክብር፣ ፍቅር፣ በሰዎች ልብ ውስጥ ልዩ ቦታ ማግኘት የመሰሉትን ማግኘት መቻል ራሱ ስኬታማነት ነው፡፡ የአንተ አዕምሮ ውስጥ ያለውን ነገር መሬት ላይ መተግበር ራሱ ስኬታማነት ነው፡፡ ለምሳሌ ስለ ስቴፈን አኩዋሪ ልንገርህ፡፡ ስቴፈን አኩዋሪ የታንዛኒያ ተወላጅ ነበር፡፡ በህይወት ዘመኑ አገሩ ታንዛኒያን በሩጫው ዓለም በዓለም መድረክ ለማስጠራት ከፍተኛ ህልም ነበረው፤ እናም ዘመኑ ደርሶ ከከፍተኛ ልምምድ በኋላ አገሩ ታንዛኒያን በታላቁ የሩጫ ንጉስ ማራቶን ላይ በመወከል እ.አ.አ በ1968 ዓ.ም በሜክሲኮ ኦሎምፒክ ላይ ተሳታፊ ሆነ፤ ሩጫው እንደተጀመረ ስቴፈን እንደ አቦ ሸማኔ

እየገሰገሰ 15ኪሎ ሜትር ያህል ከመላው ዓለም የመጡትን ሯጮች ከኋላው እንደጭራ በማስከተል የሀገሩን ታንዛኒያ ባንዲራ በደረቱ ላይ በመለጠፍ መላው ዓለም ታንዛኒያ የሚል ፅሁፍ እንዲያነብ በማድረግ መራ...የኋላ የኋላ ሌሎች አገሮች እየቀደሙት ሄዱ:: በተለይ ኢትዮጵያዊው ማሞ ወልዴ በልዩ ብቃት በሚገርም አሯሯጥ እጅግ በርካታ የነበሩትን ሯጮች ከኋላው በማስከተል በወቅቱ የዓለም ፈጣን በሆነ የማራቶን ሰዓት አንደኛ በመውጣት የአገሩን የኢትዮጵያን አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ባንዲራ ከፍ በማድረግ እውለበለበ!! የኢትዮጵያና የአፍሪካ ኩራት ሆነ!! ታዲያስህ በማራቶን የኦሎምፒክ ታሪክ በጣም ዘግይቶ ባጠቃላይ ከ4ሰዓት ከ20 ደቂቃ በኋላ ታንዛኒያዊው ስቴፈን አኩዋሪ እንደ ኤሊ እየተጓዘ የመጨረሻው ተወዳዳሪ በመሆን ስታዲየውም ውስጥ ገባ:: በሁኔታው እጅግ በጣም የተገረሙ ጋዜጠኞች "በማራቶን ታሪክ እንደ አንተ 4፡20 ደቂቃ ዘግይቶ የገባ እስካሁን የለም!! ውድድሩ ሲጀመር 15 ኪሎ ሜትር ያህል አንደኛ በመሆን እየመራክ ነበርክ! በህመም ምክንያት ነው መጨረሻ የገባኸው?" ብለው ጠየቁት:: ስቴፈን አኩዋሪ በደማቅ ፈገግታ ተሞልቶ ፤ ፊቱ በሀሴት አሸብርቆ መናገር ቀጠለ "እርግጥ ነው ከ41 አገራት የተውጣጡ 74 ተወዳዳሪዎች የተሳተፉበትን የማራቶን ውድድር አሁን እንዳየሁት ኢትዮጵያዊው ማሞ ወልዴ 2፡20፡26 ሴኮንድ በመግባት ባለወርቅ ሆኗል:: እኔም በጣም ዘግይቼ ቢሆንም መጨረሻ ገብቻለሁ:: ማሞ ወልዴ የአገሩን የኢትዮጵያ ስም ወርቅ በመውሰድ እንዳስጠራው ሁሉ እኔም ለአገሬ ታንዛኒያ የገባሁትን ቃል በመጠበቁ ቃሌን በማክበሬ ስኬታማ ሆኛለሁ!! ለሀገሬ ሩጫው ሲጀመር 15 ኪሎ ሜትር በመምራት የካሜራ ትኩረት መያዝ ከዚያ ሩጫው ሲያልቅ መጨረሻ መግባት !! ይህን እቅጄ ነበር ከታንዛኒያ የመጣሁት እናም እቅዴን ስላሳካሁ እኔም እንደ ማሞ ወልዴ ስኬታማ ነኝ" ሲል ተናገረ፤ አየህ ስኬት አንፃራዊ ናት!! ስኬት የምትገመገመው ከእያንዳንዱ ሰው ስለ ስኬት ከሚሰጠው እይታ አንፃር ነው:: በዓለም ላይ ያለው ነገር ሁሉ አንፃራዊ ነው፣ ስለዚህ ስኬትን መገምገም ያለብህ ስለ ስኬት ባስቀመጥካት ሚዛን መሆን አለበት:: ለምሳሌ ወ/ሮ ሜሪ ማክሲዌል በካንሰር ህመም ከመሞቷ በፊት ለልጇ "የዓለም ቁጥር አንድ ሀብታም ሁን፣ ታዲያ ለደሀ የሚያዝን ልብ ይኑርህ" እያለች ያሳደገችው አስተዋይ፤ ቀጫጫ ልጇ ተማሪ ቤት ገባ:: አደገ:: የዓለም ቁጥር አንድ ሀብታም በመሆን በዓለማችን ላይ ካሉት ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች አንደኛው ለመሆን በቃ:: የቢልጌት የብር መጠን 55 ቢሊየን ዶላር ሲደርስ ጋዜጠኞች እያሸቃበጡለት እና እንደ ውሻ ጭራቸውን እየቆሉለት

ጠየቁት "አንተ የዓለማችን ቁጥር አንድ ሀብታም ሰው በመሆንህ ምን ይሰማሃል? መቼም እንደ አንተ በዓለም ላይ ስኬታማ ሰው አለ ለማለት አስቸጋሪ ነው?" አሉት፡፡

የቢልጌትስ መልስ አጭር ነበር "የዓለም ቁጥር አንድ ሀብታም ሆነ ስኬታማ ግለሰብ ለምንዱባን እና አቅም ለሌላቸው የሚያዝን ልብ ያለው ነው፤ በዚያ ላይ በርካታ ገንዘቦች ባንክ ቤት ውስጥ አስቀምጠህ ሀብታም ነኝ ማለት ምፀት ነው፤ ከዚህ በተጨማሪ ሀብታምነት መለካት ያለበት በገንዘብ ሳይሆን በምትሰራው መልካም ነገር ቢሆን ዓለማችን የተሻለች ትሆን ነበር" ሲል "በዓለም ላይ በተለይ ለአፍሪካ በየዓመቱ በአንተ ስም ለተቋቋመው የእርዳታ ድርጅት ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ወጪ ታደርጋለህ፤ በተለይ ለካንሰር ህሙማን ልዩ ትኩረት ትሰጣለህ፤ ለመልካምነትህ የእናትህ እጅ አለበት?" ሲባል

"ትክክል ነው፤ ከዚያ በላይ ግን በዓለማችን ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች እሉ አንተ ጠግበህ ስትቀመጥ ከዓለማችን ከፍል የሆነ ቦታ ፈልጎት ይሁን ሳይፈልገው የሆነ የተራበ ሰው እንዳለ መገንዘብ አለብህ! የራስህን ኑሮ ብቻ የምትኖር ከሆነ ይህ ራስ ወዳድነት ነው፤ ካለህ ነገር ላይ ለሰዎች እንደ ማካፈል ደስ የሚል ነገር እኮ የለም" ሲል ነበር የመለሰላቸው፡፡ እንግዲህ ለአለማችን ቁጥር አንድ ሀብታም ቢልጌት ስኬት ሰዎችን መርዳት ነው፤ ለዚህ ነው የወ/ሮ ሩቂያ ልጅ የሆነው ሼከ ሁሴን አሊ አላሙዲም ሁልጊዜ ለእርዳታ እጁን የሚዘረጋው፤ በእርግጥ ሼኩ የእርዳታ እጁን የሚዘረጋው ለችግረኞች ሳይሆን ለቀሽት ቀሽት ቺኮች፤ ለዘፋኞች እና ላለው መጨመር ነው እንጂ ለምንዱባን የሚራራ ልብ የለውም እያሉ በርካቶች ያሙታል፡፡ ከመብት አንፃር በግድ እርዳታ አድርግ ብለህ ማስገደድ አትችልም! በብሩ የፈለገውን ማድረግ ይችላል፤ anyway ወደቁም ነገሩ ስንመለስ ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞቹ የዓለማችን ሀብታሞች የሰበት ህግን ይከተላሉ "አውጣ ተጨማሪ ታስገባለህ" የሚለውን !!

⋮

▼

አ! ራሞስ ሸሌን ይበልጥ ባስታወስኩት ቁጥር ብዙ ነገር አስታውሳለሁ "አንድ ሰው ለእኛ ምን ያህል ጠቃሚ እንደ ነበር የምንገነዘበው ያን ሰው ስናጣው ነው" የሚባለው እንጋገር ትልቅ እውነት ነው፡፡ ራሞስ ለእኔ የእውቀት አባቴ ነበር... ስለ ፍቅር የተለየ ግንዛቤ ያስጨበጠኝ ራሞስ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ የሶስተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለን ፍሬወይኒ ከምትባል ልጅ ጋር ፍቅር ያዘኝና ለአንድ ወር ገደማ ፍዳዬን ለመብላት ችዬ ነበር፡፡ ልጅቷን

እንዳፈቀርኳት ሳልፈራ ሹከ ቱስ ስላት እሺም እምቢም ሳትል ጢባጯን ነሰነሰች! እንኳን ልታናግረኝ ስታየኝ ሁሉ ብጥስጥስ ማለት ጀመረች... እኔን ስታይ ቂጧን እያማታች ማለፍ ጀመረች፣ እያየችኝ ባላየሙድ ቀርቅራኝ ማለፍ ጀመረች:: ይህን ጉዳይ ለራሞስ ሹከቱስ አልኩት::

"ፍሬወይኒን አፈቅርሻለሁ ስላልኳት አየህ እንዴት እንደምትሆንብኝ" አልኩት::

" መብቷ እኮ ነው" አለኝ::

"እንዴት?"

"አለም ላይ ያለው ፍቅር ሁሉ የውሸት ፤ ጥቅም ላይ የተመሠረተ፣ እውነተኛውን የፍቅር ትርጉም የያዘ አይደለም"

"ይብራራ"

"ለምሳሌ አንተ የወደድካትን ልጅ ማግኘት፣ አብረሃት መኖር፣ መጋባት፣ ባጠቃላይ ትልቁ ምኞትህ ያፈቀርካት ልጅ የአንተ ንብረት እንድትሆን ነው:: ይህ ደግሞ ፍቅር አይባልም ራስ ወዳድነት ነው:: እውነተኛ ፍቅር ልብህ ውስጥ ካለ እና ልጅቷን ከልብህ የምትወዳት ከሆነ ተዋት! እኔ ከአንዲት ልጅ ድብን ያለ ፍቅር ቢይዘኝ ለልጅቷ ያለኝ ፍቅር እንዳይቀዘቅዝ ፍቅሬን አልነግራትም፣ ያፈቀርኳትን ልጅ የእኔ የግል ንብረት ለማድረግ ሆነ ለማግባት ጨርሶ አልፈልግም! እውነተኛ አፍቃሪ ከሆንክ እና እውነተኛው የፍቅር ትርጉም ከገባህ ካፈቀርካት ልጅ ምንም አትፈልግም፣ ምንም መጠበቅ የለብህም! የአንተ ለማድረግ እንዳችም ጥረት ማድረግ የለብህም! በዓለም ላይ ያለው ግን ይህ እውነታ ሳይሆን ራስ ወዳድነት! ነው ሀሳቤ ገብቶሃል?"

"ገብቶኛል፤ ግን ወደ ፍልስፍና የሚያደላ ሀሳብ ይመስለኛል"

"እውነቱን ለመናገር ፍልስፍና አይደለም! ሀቅ ነው፤ ችግሩ በምድር ላይ የፍቅር እና የመውደድ ልዩነት አልገባንም:: ፍቅር ምንም ነገር አይፈልግም ፤ ያለ አንዳች ክፍያ በነፃ ያለ አንዳች ጥቅም የምትሰጠው ነገር ነው:: መውደድ ግን መቀበልና መስጠት ነው:: አሁን አንተ ፍሬወይኒን አላፈቀርካትም፣ ወደሃታል:: ከፍሬወይኒ የሆነ ነገሯ ተመችቶህ ስባሃለች፤ በተቃራኒ ፆታዎች መሀከል ደግሞ መሳሳብ ያለ ነው:: በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በቅርቡ የሆነ ጥናት ሳነብ በተቃራኒ ፆታ ለምን እንሳባለን ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ ሳይንቲስቶች እንደሚያስረዱት

እና በከፍተኛ ምርምር ደረስንበት ያሉት ነገር የእያንዳንዱ የሰው ልጅ ላይ ወንዱ ሆነ ሴቶች አፍንጫ ውስጥ የሚገኝ የጠረን ማሽተቻ ማዕከል "ቬሮሞኖሳል" የሚባል አለ፤ ይህ ለእኛ የሚስማማውን ተቃራኒ ፆታ ሲያገኝ ያሸታል፣ ለእኛ የሚስማማውን ሹክ ቱስ ይለናል፤ ይህ በሳይንሱ መጠሪያ Histocompatibility complex ይባላል:: ይህ የፍቅር ማግኔት ሜጀር ሂስቶኮምፓቲቢሊቲ ካፍንጫችን በሚደርሰው መረጃ መሠረት ለእኛ የሚሆነውን ተቃራኒ ፆታ ይነግረናል፤ ለእዚህ ነው ለምሳሌ አንድ ሺ ሴቶች ቢደረደሩልህ አንዷን ብቻ አብልጠህ ትመርጣታለህ፤ ይህን ምርጫ እንድታከናውን የሚያደርግህ ይህ ሂስቶኮምፓቲቢሊቲ የተባለው የፍቅር ማግኔት ነው:: የአንተ የሆነችውን አልያም ለአንተ ልትሆን የምትችለውን ይመርጥልሃል፤ በዚህ የተነሳ ነው በተቃራኒ ፆታ የምትሳበው:: ታዲያ ይህ መውደድ ነው እንጂ ፍቅር አይባልም:: መውደድ ውስጥ አንድን ነገር የራስ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለ:: መውደድ ውስጥ ከፍተኛ ራስ ወዳድነት አለ:: በዓለም ላይ በጣም ምን እንደሚያስቀኝ ታውቃለህ? በጣም ስለምወዳት ገደልኳት፣ አፍቅሬ እንቢ ስላለችኝ ገደልኳት፣ ለፍቅሬ ምላሽ አልሰጥም ስላለችኝ አረድኳት፣ የምወዳት ሴት ከሌላ ሰው ጋር ስለባለገች ገደልኳት.... ወዘተ የሚባሉ ሀሳቦች ናቸው:: መውደድ እንዳልኩህ ራስ ወዳድነት ስሜት ስላለበት ውስጡ ሞት አለ፤ ፍቅር ውስጥ ግን ሞት የሚባል ነገር የለም! ለማንኛውም ምርጫዋ ካልሆንክ እንቢ የማለት መብቷ የተጠበቀ ነው፤ ቢሆንም እንደነገርከኝ እንቢም እሺም አላለችም"

"እም"

"ታዲያ ቀሽሙ አንተ ነህ!"

"እንዴት?"

"ስለ ወሲብ እና ስለ ፍቅር በነፃነት ማውራት እንደ ሀጢያት የሚቆጠርባት ኢትዮጵያ ውስጥ እኮ ነው ያደግነው! የግልፅነት ባህላችን በጣም የሞተ ነው:: በውስጣችን የሚሰማንን ነገር የመናገር ባህላችን በጣም ደካማ ነው:: ከዓለም ላይ ካሉት ሴቶች ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ ሴቶች ቅልራስ የሉም! ቀሽሞች ናቸው:: ዙሪያ ጥምጥም ይወዳሉ:: ሴላውን ተወውና ፊደል ቆጥረዋል፤ ተምረዋል፤ በእውቀት ዘምነዋል፤ አንብበዋል ፤ የተሻለ ጭንቅላት አላቸው የምትላቸው ኢትዮጵያዊያን ሴቶች እንኳ እንድትለምናቸው እና እንድትወተውታቸው ይፈልጋሉ:: በውስጣቸው የሚሰማቸውን ስሜት በግልፅ መናገር አይፈልጉም!! ይቺ አሁን

አንተ የተሳብከባት ቅል ራስም ይሆን ነገር ፈልጋ ነው እሺም እንቢም ያላለችው፤ በሌላ በኩል እሺም እንቢም ለማለት የምችለው በአንተ ፍጥነት እና አተራረብ ነው እያለችህም ነው፤ ስለዚህ በሩን ከፍታልሃለች፤ እየህ የሴቶች ልብ እንደጡታቸው የተንጠለጠለ እና በስሜት ተመስርተው ውሳኔ የሚያሳልፉ ስለሆነ እንደ ገገማ ወንድ ድርቅ ሳትል ቅረባት! ቀርበሃት ከተመቻቻህ እና ጠረናችሁ ማች የሚያደርግ ከሆነ ትቀጥልበታለህ! በሌላ በኩል ጠረናችሁ ማች የማያደርግ ከሆነ እና አመለካከታችሁ ፍፁም የማይገናኝ ለየቅል ከሆነ ያንተንም የእርሷንም ጊዜ ሳታባክን እንደ ሰለጠነ ዘመናዊ አመለካከት እንዳለው ሰው በሰላም በጊዜ መለያየት ነው"

ራሞስ እንዳለው ፍሬወይኒን ለአንድ ወር በአካል ፣ በስልክ… በጓደኞቿ ንዝንዝ ሳደርጋት… በእኔ ሀሳብ ሰጠመች፡፡ በአንድ ጊዜ ልቧ ተነፈሰች፤ ቢሆንም ከሁለት ወራት በኋላ ተለያየን፤ ያው ራሞስ እንዳለው ጠረናችን ማች አላደረገም!! ከርቀት ወደድኳት ፤ ስቀርባት ግን ባዶ ሆነችብኝ!! ከርቀት እንደ እንቁ አድርጌ ሳያት ነበር፤ ስቀርባት እና ስመዝናት ግን የነሀስ ያህል እንኳ አልሆንልህ አለችኝ፡፡ በቃ ቀላ ተገኘችብኝ! ለነገሩ "ማኔ ቴቄል ፋሬስ" ይባል የለ? በዚህ አጋጣሚ ለእናንተም ምክር ቢጤ ሹክቱስ የምላችሁ በጣም የምትወዱት ሰው ስትቀርቡት / ስትቀርቢው/ ባዶ ቅል እንዳይሆንባችሁ ለፍቅር አምላክ ፀሎት ቢጤ አስቀድማችሁ እንድታደርሱ ነው… ለማንኛውም ስለ ፍቅር እና መውደድ ልዩነት የነገረኝ ምንም ይፈጠር ምን ለእኔ ወድ ጓደኛዬ የነበረው ራሞስ ኤልያስ ነበር… !!

pdf by @shuktus_books

# ሽርብትን

# ለ

# ፈላሻዋ

ደሊላ ዶ/ር ሐይለመስቀል ይጥና፡፡

መጋቢት 14... አዲስ አበባ ፡፡

እንደ ራምሰ በጭራሽ ለሴቶች ጥላቻ የለኝም፤ ሊኖረኝም ከቶ አይችልም፤ ፍቅርን በተመለከተ ግን በፀባያቸው ዝጋታምና ጋግርታም ሴቶች ደስ አይሉኝም፡፡ ከመሬት ተነስተው ኩፍስ የሚሉ ሴቶች ደስ አይሉኝም... የሚያካብዱ ሴቶች አይመቹኝም... በህይወቴ በጣም የምጠላው ሆነ መቼም የማላደርገው ጉዳይ ቢኖር ሴቶችን መለማመጥ ነው፡፡ ለሴቶች የሚሆን እንዳችም ትዕግስት የለኝም፡፡ ቀለል ያሉ እና ፍሪክ ሴቶች፣ ተጫዋች ሴቶች፣ ነገሮችን

ቀለል አድርገው የሚመለከቱ ሴቶች በጣም ደስ ይሉኛል:: እንደዚህ አይነት ሴቶች የእኔ ምርጫ ናቸው:: በተለይ ስራ ለምትወድ እና ፈዘኛ ላልሆነች ሴት ያለኝ ከብር ግዙፍ ነው:: ኮስሞቲክ የማታበዛ ሴት ትመቸኛለች፤ ምንም ሆነች ምን በራሷ የምትተማመን ሴት ትመቸኛለች፤ የሞግ ፀጉር የማትጠቀም ሴት ትመቸኛለች ... ደሊላ እኔ የምወዳቸው ሴቶች አይነት ስለነበረች የተመቸችኝ ገና አንድ ወር ሳይሞላት ነበር:: በዚያ ላይ ጠዋት ጠዋት ሁልጊዜ የሰውነት እንቅስቃሴ ስለምትሰራ ዘመናዊ ሴት እንደሆነች ያስታውቃል...

ጠይም፣ ረጅም ፣ ደስ የሚል ቁመና ያላት፣ ሸንቃጣ ሰውነት ያላት፣ ፈገግታ ከፊቷ የማይጠፋ ... በቃ ለአይን የማትከብድ ወጣት ናት:: እኔ ቤት ተከራይታ ወር ባለፈ የመጀመሪያው እሁድ ቀን ከጠዋቱ 4:00 ላይ በጣም ይበርድ ስለ ነበር ከሳሎን ወጥቼ የጠዋቷን ፀሐይ ለመሞቅ ውጪ ተቀመጥኩ:: ብዙም ሳይቆይ ደሊላ ቀይ ረጅም ሳሳ ያለ ቀሚስ አድርጋ፣ ያን ረጅም ፀጉሯን ለቃው ደስ በሚል የእግር አጣጣል እና ፈገግታ ተሞልታ የተቀመጥኩበት ጋር ወንበር ይዛ በመምጣት

"ሻሎም" ብላኝ በመጨበጥ ተቀመጠች::

"ሻሎም" አልኳት::

"የዛሬው ብርድ በጣም ያንዘፈዝፋል"

በደሊላ ሀሳብ በመስማማት ራሴን ነቀነኩላት::

"እርግጠኛ ነኝ ቤቱንና ሰፈሩን ለምደሽዋል ?"

አልኳት ለጨዋታ ያህል::

"አ! በጣም!! እስካሁን አራት ቤት ተከራይቻለሁ! ስለ እውነት እንደዚህ የሚያምር ውብ ግቢ፣ ንፁህ ግቢ ፣ በአትክልቶች የተዋበ፣ በጣም ሰፊ እና ደስ የሚል ክፍሎች ያሉት ቤት አላጋጠመኝም፤ በጣም ደስ ብሎኛል" አለችና ወዲያው "ይህን የሚያምር ገነት የመሰለ ግቢ ጥለው ቤተሰቦችህ ግን የት እየኖሩ ነው?" አለችኝ::

"እናትና አባቴ እዚች ምድር ላይ እስከሚበቃቸው ድረስ ሸርብትን ብለው ኖረው ከሞቱ ሁለት ዓመት አለፋቸው:: አባቴ በዘጠና ዘጠኝ ፣ እናቴ በዘጠና ሁለት ዓመቷ ነው የሞተት:: ሁለት ወንድ ልጆች አፍርተዋል:: እኔንና አሜሪካ ያለውን ታላቅ ወንድሜን፤ ይህን ውብ ቤት የገዛውና በዚህ መልኩ የዛሬ አምስት ዓመት ያሠራው ታላቅ ወንድሜ ነው:: እናትና አባቴ በጣም ጎበዝ ባንክ ሰራተኞች ነበሩ፤ እኔም የእነሱን ሙያ በመከተል ባንክ ቤት

እየሰራሁ አገኛለሁ፤ ይህን ይመስላል የቤተሰባችን ትንሚቢ ታሪክ"

"ዋው 99 እና 92! በጣም ብዙ ዓመት ነው! አ የባንክ ሠራተኛ ነህ?"

"አዎ"

"ታዲያ ከባንክ ጋር በማያያዝ የምትነግረኝ ቁምነገር ምን አለ?"

"100,000ሺ ብር ባንክ ቤት ከምታስቀምጪ አስር ሺ ብር አስቀምጠሽ በ90,000ሺው ስራ ብትሰሪበት ትርፋማ፣ ነሽ! እውነቱን ለመናገር የብር የመግዛት አቅም እና ዋጋው በየቀኑ እየቀነሰ ስለሚሄድ ባንክ ቤት ከተቀመጠ በርካታ ገንዘብ ይልቅ ስራ ላይ የዋለ አስር ብር የተሻለ አቅም አለው፡፡ በጣም ፈሪ ሰዎች እና የቢዝነስ ጭንቅላት የሌላቸው ሰዎች ናቸው በብዛት ብራቸውን ባንክ ቤት የሚያስቀምጡት፡፡ ይህን ስልሽ ቁጠባ ጥሩ አይደለም እያልኩሽ አይደለም፣ ብርን ባንክ ከማስቀመጥ ማንቀሳቀስ በጣም የተሻለ ነው ለማለት ያክል ነው"

"እረ ስለ ባንክ ቤት ከተነሳ ስለስዊዝ ባንክ የሆነ መረጃ ሰምቼ ነበር፤ ስዊዝ ባንክ የሀገሩን ብር እየዘረፈ የማያስቀምጥ የአፍሪካ መሪ የለም ይባላል እስቲ ይህን ነገር አንተ ንገረኝ"

"እውነት ነው፤ የኛዋን ሚስኪን ኢትዮጵያን ጨምሮ እጅግ በርካታ ስግብግብ የአፍሪካ መሪዎች ከህዝባቸው በርካታ ገንዘብ እየሠረቁ ስዊዝ ባንክ ቤት ውስጥ ያስቀምጣሉ፤ ያን ገንዘብ መጠቀም የሚችሉት በህይወት እስካሉ ድረስ ብቻ ይሆናል፤ ሲሞቱ ያ ገንዘብ የባንክ ቤቱ ይሆናል፤ አንዳንዴ ደግሞ ለእርዳታ ድርጅቶች ይሰጣል፡፡ ስለ ባንክ ከተነሳ በዓለም ላይ ያሉ ባንኮች የራሳቸው የተለየ ህግና ደንብ አላቸው ፤ በዓለማችን ላይ አምስቱ እጅግ ሀብታም ባንኮች የሚከተሉት ናቸው፡፡ አምስተኛ ደረጃ "ባንክ ኦፍ አሜሪካ"፣ በአራተኛ የኢንግሊዙ 'HSBC' ፤ በሶስተኛ የቻይናው "ኢንዱስትሪያል ኤንድ ኮመርሻል ባንክ" ፤ በሁለተኛ የአሜሪካው እጅግ በርካታ ደንበኞች ያሉት JP Morgan Bank ሲሆን የአለማችን ቁጥር አንድ ሀብታም እና ከፍተኛ ካፒታል ያለው ባንክ የአሚሪካው Wells Frago Bank ሲሆን 262 ቢሊዮን ዶላር ካፒታል አለው፡፡ በዓለማችን ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ ገንዘብ ለሠራተኞች የሚከፍለው እና የአዲስ ዓመት ልዩ ስጦታ የሚሰጠው ተወዳጅ ባንክ Love Bank የሚባለው ሲሆን በካፒታል ደረጃ 96 ቢሊዮን ዶላር ሲኖረው ይህ በሁሉ ነገር ለየት ያለው ባንክ በየዓመቱ ለዘመን መለወጫ በዓል ለባንኩ አንድ ደንበኛ በልዩ ዕጣ ባንኩ ውስጥ ያስቀመጠው ብሩ አካውንት ላይ እንደ ሰርፕራይዝ ስጦታ አንድ ሚሊዮን

ዶላር ይጨምርለታል፡፡ ይህን መልካም ስራ የሚሠራ ባንክ እንዳለ ሁሉ በዓለማችን ላይ NBM Bank የሚባል አለ፤ ይህ ባንክ አገልግሎት የሚሠጠው ለነጭ ሰዎች ብቻ ነው፤ እዚህ ባንክ ውስጥ በምንም ተዓምር ጥቁር ሊገባ አይችልም፤ እንግዲህ በዓለማችን ላይ የተለያዩ ባንኮች አሉ፤ ባንክ ሲባል እኛ ሀገር በፍጥነት የሚመጣብን "ገንዘብ የሚቀመጥበት ቦታ ነው" ግን የደም ባንክ አለ፤ ወርቅ ብቻ የሚያስቀምጥ ባንክ አለ፤ ጌጣጌጦች፣ የከበሩ ድንጋዮች ... ብቻ በርካታ ባንኮች ከበርካታ አገልግሎት ጋር አሉ፡፡ በዓለማችን ላይ ከሚገኙት ለየት ያሉ ባንኮች እንደኛው ዴን ማርክ ውስጥ የሚገኘው Talent Bank ነው ይህ የ24 ሠዓት አገልግሎት የሚሠጠው ባንክ ዋነኛ ስራው ሀሳብ መሸጥ፣ ሀሳብ መግዛት እና በታማኝነት ሀሳብ ማስቀመጥ ነው፤ ለዚህ ባንክ አሪፍ ሀሳብ፣ እቅድ፣ ትልም አለኝ ካልሽ እና ተቀባይነት ካለው ወዲያውኑ ይከፈልሻል"

"ኦ በጣም ደስ ይላል፤ እኛ አገርስ በዚህ በማይረባው በዘር ላይ የተመሠረተ ባንክ የለም?"

"በጣም የሚገርምሽ ብዙ ሰዎች ከሚጠይቁኝ ጥያቄዎች አንደኛው ይህ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባንክ በቀድሞ የኢትዮጵያ ስም የሚጠራው አቢሲኒያ ባንክ ነው፤ ከዚያ ተራ በተራ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ባንኮች አሉ፡፡ አዋሽ፣ ዳሽን፣ ዘመን፣ ንግድ ባንክ ፣ አባይ፣ ደቡብ ግሎባል፣ አንበሳ፣ ቡና፣ ብርሃን፣ ወጋገን፣ ኦሮሚያ፣ ኮንስትራክሽን... ይጠቀሳሉ፤ ያው እንዳልሽው በዝርዝር ባልነግርሽም በዘር ላይ መሠረት ያደረጉ ባንኮች አሉ፤ በችሎታ ሳይሆን በዘር እና ቋንቋ ላይ ብቻ መሠረት በማድረግ ሰራተኛ የሚቀጥሩ የማይረቡ ባንኮች ከተጠቀሱት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እኔ የምሰራበት ባንክ ግን ከዚህ የማይረባ ዘረኝነት የተባለ የጠባቦች አዕምሮ የሚመነጭ አስተሳሰብ የፀዳ ይመስለኛል"

ቤት ሳከራይ የተከራዩትን ሰዎች ማንነት የሚያስረዳ ስልክ ቁጥራቸውን እና መታወቂያቸውን ኮፒ በማድረግ ወዲያው ለከፍለ ከተማችን አሳውቃለሁ፤ ታዲያ የደሊላ መታወቂያ ስራ የሚለው ላይ ያነበብኩት "የግል" የሚል ነበር፤ አሁን አጋጣሚውን በሚገባ ስላገኘሁ

"ስላንቺ ቤተሰቦች እና ስራ ንገሪኝ" አልኳት፡፡ ፈገግ አለች፡፡ እጅግ በጣም ስስ ከንፈር አላት፡፡ ቀጫጭን የሚያምሩ ጥርሶች... አሏት፡፡

"ከባህር ዳር ከተማ ወጣ ብላ የምትገኘው ሀሙሲት ከተማ ሁለት ዝነኛ ሰዎችን

አፍርታለች:: የስል የሙዚቃ ንግስት አስቴር አወቀን እና ብዙም ያልተወራለት ዶ/ር ሐይለመስቀል ይጥና:: ያው ታሪኩ ብዙ ቢሆንም ባጭሩ የዘር ሐረጋችን የሚመዘዘው ከእስራኤል በስደት ኢትዮጵያ ውስጥ መጥተው ሲኖሩ ከነበሩት እስራኤላዊያን ወይም በሀበሻ አጠራር ከፈላሻዎች የሚመዘዝ ነው:: እናም እስከ አስራ ስድስት ዓመቴ ኢትዮጵያ ውስጥ ካደኩ በኋላ ወደ እስራኤል ከዶ/ር አባቴ እና እናቴ ጋር አመራሁ:: ታላቅ ወንድሜ ወዲያው ወታደርነት ተቀጠረ:: እኔም ትምቴን ቀጠልኩ... እስራኤል አገር አምስት ዓመት እንደቆየሁ ቤተሰባችን መሀከል የነበረው ሰላም ደበዘዘ... በጣም የማከብረው ፣ በጣም አንባቢው ፣ እርጋታ የሰፈነበት አባቴ ፀባዩ ሙሉ ለሙሉ ተለዋወጠብኝ:: አንድ ምሽት ለብቻዬ ጠርቶኝ

"አሁን አንድ የህይወት ሀላፊነት ልሰጥሽ ነው በጣም ለምትወጂያቸው ጓደኞችሽ እንኳ አንዳችም ነገር ሹክ ቱስ ሳትይ እኔ ሁሉን ነገር አመቻችልሻለሁ!! በፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ ትሄጂያለሽ"

' ምን ተፈጠረ አባቴ'

'ያልሆነ አስቀያሚ አደገኛ መረጃ እጄ ገባ'

'የምን መረጃ አባቴ? ምንድን የምታወራው ? ለምን በግልፅ አትነግረኝም?'

'ያልሆነ መረጃ እጄ ገብቷል ፣ ስለዚህ ቤተሰባችን አደጋ ላይ ነው! ትልቅ አደጋ ላይ ነን! አሁን ጥያቄ ሳትከምሪ እኔን የምትወጂኝ ከሆነ እኔ የምልሽን ብቻ አድርጊ! በፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ ትሄጃለሽ!!?'

"ምክንያቱን ንገረኝ? ለምንድን ነው ወደ ኢትዮጵያ የምመለሰው?"

"እንግዲህ ስሚኝ ህይወትሽን የምትፈልጊ ከሆነ በፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ ሂጂ!! ከዚያ ኢትዮጵያ ስትደርሺ ምክንያቱን እነግርሻለሁ" ሲል በቁጣ ተናገረኝ:: ይህን ካወራን ከሁለት ሰዓት በኋላ ታላቅ ወንድሜ በድንገተኛ አደጋ ሞተ ተባልን፤ በተፈጠረው ሁኔታ እያዘንኩ፤ አባቴ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር የዚያን ምሽት አስተዋወቀኝ፤ በሌላ ሰው ስም፤ በሌላ ሰው ማንነት በድብቅ ከብዙ እና አስቀያሚ ጉዞ በኋላ አባቴ የመደበልኝ ሰዎች አዲስ አበባ ጥለውኝ ሄዱ:: ከአንድ ወር የአዲስ አበባ ቆይታ በኋላ ባልታወቀ ሁኔታ እናቴም አባቴም መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንደሞቱ እዚህ ያደረሱኝ ሰዎች አረዱኝ... በተጨማሪ ከአራት ወር በኋላ የአባቴ ጓደኛ በኢሜል እንደነገረኝ ከሆነ አባቴ እጅ መግባት የሌለበት መረጃ ስለደረሰው ነበር:: የእስራኤል የደህንነት ሰዎች በረቀቀ ሁኔታ እንዲገደል ሴራ የደገሱለት ፣ እየሀ አባቴ ለመጀመሪያ ጊዜ

በከፍተኛ ሚስጢር ሲከናወን የነበረውን ከኢትዮጵያ ወደ አገራቸው እስራኤል የሚያመሩትን ፈላሻዎች ከአወዛጋቢው ዘመቻ ሰለሞን እስከ አሁን ድረስ ከኢትዮጵያ ወደ እስራኤል የሚጓዙትን ኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ የነበሩትን ቤተ እስራኤል ሴቶችን ሁሉ ልጅ መውለድ እንዳይችሉ እና ከዋናዎቹ ከእስራኤላዊያን ጋር ጋብቻ እንዳይፈፅሙ በረቂቅ መንገድ የጤና ምርመራ በሚል ሽፋን የማምከኛ መርፌ እየወጉ መኳን እንደሚያደርጓቸው አባቴ ደረሰበት!! ይህን መረጃ ዶ/ር አባቴ እንደደረሰበት ሲደርሱበት ነው እንግዲህ እኔን ጨምር በሞት ሊጨርሱን የነበረው፤ በዚህ አጋጣሚ እኔም የስልጠና ካምፕ ውስጥ እያለሁ ሳላውቅ በረቀቀ ዘዴ የመካንነት መርፌ ስለተወጋው ልጅ መውለድ አልችልም... እናልህ በዚህ ከፍተኛ ሀዘን ላይ እያለሁ ሁሙሲት አቶ ይገዙ ካሳ የተባሉ ቄስ አባቴ በአደራ የሰጣቸውን መሬት እና ቤት ጭምር ሸጠው ተሰወሩ... ከእስራኤል ያመጣሁት ገንዘብ እየተመናመነ መጣ:: እዚህ ደግሞ አለኝ የምለው የሚረዳኝ ዘመድ ሆነ የቅርብ ጓደኛ የለኝም... እስራኤል ለሚገኙት ጓደኞቼ እርዳታ እንዳልጠይቅ ምናልባት መረጃ አግኝተው ይመጡና ይገሉኛል ብዬ ፈርቼ በዝምታ ተቀመጥኩ:: በመጨረሻ ያለኝ ብቸኛ አማራጭ ከህይወት ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ ስለሆነ ከእስራኤል ስመጣ ያመጣሁት ብር ሳያልቅ እጅግ በርካታ ቢሮዎች ስራ ለማግኘት ጥረት ባደርግም ከቶ ለማግኘት አልቻልኩም "ኢትዮጵያ እና ህንድ ውስጥ ዲግሪ መያዝ ቀላል ነገር ነው፤ ስራ ማግኘት ግን እንቁ የመፈለግ ያክል አስቸጋሪ ነው" የሚባለው አባባል እውነት መሆኑን ተገነዘብኩ... በመጨረሻ እስራኤል አገር እንዳለው መስሎኝ የሶስት ወራት ስልጠና በመውሰድ ስራ ጀመርኩ፤ ከገባሁበት በኋላ አስረኛ ሆኜ ቁጭ አልኩልህ"

"በእውነት በጣም ጠንካራ ሴት ነሽ!! ይህንን ሁሉ ህይወት ያሳለፍሽ አይመስለኝም ነበር:: በተለይ ሁሌ ፈገግታ ከፊትሽ ስለማይጠፋ ከጀርባሽ ይህን የመሰለ አሳዛኝ ታሪክ ይኖራል ብሎ ማሰብ በጣም ይከብዳል!!"

"ልክ ነህ! ዶክተር አባቴ ካስተማረኝ ነገር አንደኛው ከእውነታ ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥን ነው:: የሌለኝን ነገር እያሰብኩ ወይም ይህ ባይሆን ኖሮ እያልኩ እንደሰነፍ ሰዎች ከራሴ ጋር መጣላት ሆነ ራሴን በስንፍና ማጠር አልፈልግም፤ እዚህ ጋር አንድ ጥሩ ምሳሌ ላሜውትህ መፅሐፍትን ማንበብ በጣም ደስ ይለኛል፤ በተለይ በባዮግራፊ መልክ የሚፃፉ ታሪኮች ይማርኩኛል፤ አንድ ጊዜ ስለ አንዲት የሩሲያ ሴት አስገራሚ የህይወት ውጣ ውረድ ሳነብ ባለታሪኳ የ14 ዓመት ልጅ እያለች ተደፍራ ነበር፤ እናም ለወንዶች በዚህ የተነሳ ጥላቻ

አላት፡፡ የሀያ አራት ዓመት ወጣት ሳለች እንደ አጋጣሚ ባቡር ውስጥ ያገኘቻቸው ሽማግሌ አስተሳሰቧን ለወጡላት፡፡ በልጅነቷ እንደ ተደፈረች እና እስካሁን ለወንዶች ጥላቻ እንዳለባት ስትነግራቸው ሽማግሌው

"አይ ልጄ በዓለም ላይ ሁሉም ሰው አንድ የራሱ የሆነ ቀላል ሆነ ከባድ ቁስል አለው፡፡ ጥላቻ ጥላቻን ይወልዳል ፤ ፍቅር ግን ጥላቻን ያጥባል!! ለመሆኑ አንቺ መቼ ነው በወንድ የመደፈር አደጋ የደረሰብሽ?" ሲሏት

'የዛሬ 14 ዓመት'

'አሁን ስንት ዓመትሽ ነው ልጄ?'

'28 ዓመቴ ነው አባቴ?'

'እህ ድርጊቱ የተፈፀመብሽ ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ነበር ማለት ነው?'

'አዎ'

'ታዲያ እኮ ያ ሰው አሁንም ድረስ እንዲደፍርሽ ሆነ እየደፈረሽ እንዲኖር ለምን ፈቀድሽለት?'

'አልገባኝም አባባ'

'እየሽ ልጄ በአንድ ነገር መሸነፍ ያለብሽ አንድ ጊዜ ብቻ መሆን አለበት! አንቺ ግን ስለደፈረሽ ሰው እስከዛሬ አልረሳሽውም! እያስታወሽው ነው፤ ስለዚህ ይህ ሰውዬ አሁንም በሀሳብ እየደፈረሽ ነው ፤ ስለዚህ ይህን ሰውዬ ማሸነፍ አለብሽ፡፡ ያን ያለፈ ታሪክ መጋዘን ውስጥ መከተት አለብሽ! እያንዳንዱ ንጋት አዲስ የምንወለድባት ልደት ነች! ምንም እንኳ በህይወታችን ውስጥ ትልቅ ጨለማ ቢኖርም እኛ ማሰብ ያለብን በህይወታችን ውስጥ ስላለች ትንሽዬ የብርሃን ጭላንጭል ማሳቡ የተሻለ ነው፤ ስለዚህ እንዴ ስለተፈጠረ ጨለማ ሁሌ እያሰቡ ህይወትን ከንቱ ማድረግ ከንቱነት ነው" ነበር ያሏት፡፡ ግሩም ንግግር ነው፤ ያቺ ሴት በሽማግሌው ንግግር ተለወጠች፡፡ ከእውነታ ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጠች፡፡ እኔም ያደረኩት ያንን ነው፡፡ ስለ ቤተሰቦቼ ሞት ዘወትር ማሰቡ፣ ስለ ተወረሰብኝ ቤት እና ንብረት በማሰብ ከውድቀት ባሻገር የሚያመጣልኝ ውጤት የለም፤ ከዚህ ይልቅ የተሻለው ከራስ ጋር መታረቅ እና ህይወትን ለማሸነፍ ጥረት ማድረግ ነው፡፡ በጣም ብዙ ሴቶች በትንሽ ነገር ቅስማቸው እንክትክት ይላል! ለውድቀታቸው ሁሌጊዜ ሰበብ እና ምክንያት ይደረድራሉ!! እኔ ደግሞ እንደዚህ አይነት ሴት መሆን አልፈልግም፡፡ በቃ እውነታውን መቀበል ራሱ ፀጋ ነው! ከራስ

ጋር መታረቅ ነው! እኔም ያደረኩት ያንን ነው፤ ለዚህ ነው እንዳልከው ዘወትር ፈገግታ ከፊቴ ላይ የማይጠፋው! ሀዘን ሀዘንን ከመጥራት ባለፈ የሚያመጣው ነገር የለውም! ይህ የእኔ አቋም እና እምነት ነው"

ፀሐዩዋ ሞቅ እያለች ነው፤ በጣም አስፈሪው ቅዝቃዜ እየቀነሰ ነው:: ይቺ ከአንደበቷ ጣፋጭ ቃላት የሚወጣት ሴት ለምዕፈው መፅሐፍ ገፀባህሪ ልትሆነኝ ትችላለች ስል አሰብኩ... ውስጤ የምትላወሰው የደራሲነት መከሊት ይበልጥ ስለዚች እስራኤላዊት ወጣት እወቅ አለችኝ... እናም እዛው እንደ ተቀመጥን ደስ የምትለዋን የጠዋት ፀሐይ እየተመገብን

"ታዲያ አሁን ምን እየሰራሽ ነው ?" አልኳት::

"Massage theraphist and sex worker"

ስለ ማሳጅ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የነገረኝ ራሞስ ኤልያስ ነበር:: አንድ ጊዜ ቦሌ ኤድና ሞል የ7D ቴክኖሎጂ ለማየት ሄደን ጨርሰን ስንወጣ ሸገር ህንፃ ጋር ዩኒቨርሲቲ አብራን ትማር የነበረች የዩኒቨርሲቲያችን መልከኛ ሴት ማስታወቂያ ላይ ፎቶዋን አየነው:: ከትልቁ ማስታወቂያ ላይ ራቁት ለመሆን ሩብ ጉዳይ የሆነ ፎቶ ነበር የተነሳችው "ሊሊ ማሳጅ" ይላል:: ልክ እንዳየሁት በጣም ገርሞኝ "እንዴ ራሞስ ይቺ ሊሊ አይደለችም እንዴ?" አልኩት::

"Ya" አለኝ ምንም ሳይሞቀው፣ ሳይበርደው::

"እና ማሳጅ ቤት ከፍታ ነው?"

"All most" አለኝ አሁንም ምንም ሳይሞቀው ሳይበርደው በእርጋታ እየተራመደ:

"ይገርማል"

"ምኑ?"

"ስለ ማሳጅ ቤት የሚወራውን መቼም ታውቃለህ?"

"አይ አንተ! Ethiopia has become a magnet for sex tourism ይላል በቅርቡ ያነበብኩት ጥናት፤ ምንም ኢትዮጵያ የወሲብ ቱሪዝምን ህጋዊ እንዳደረጉት ሀገራት ጀርመን፣ ብራዚል፣ ሞሮኮ፣ ዶሚኒከ ሪፐብሊክ፣ ኔዘርላንድስ፣ ታይላንድ፣ ኬፕ ቬርዴ፣ ናይጄሪያ፣ ቺሊ፣ ህጋዊ ባታደርገውም አንደኛዋ የወሲብ ቱሪዝም መዳረሻ አገር ሆናለች:: አንድ በቅርቡ የተደረገ ሌላ ጥናት ሳነብ በጣም ነበር የደነገጥኩት:: አዲስ አበባ ውስጥ በተደረገ ጥናት ከምሽቱ ሁለት ሠዓት ጀምሮ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች በሸሌዎች ይሞላሉ፤

እጅግ በርካታ ቡና ቤቶች፣ ሆቴል ቤቶች፣ ፔንሲዮኖች ውስጥ በርካታ ሸሌዎች አሉ፡፡ በጥናቱ መሠረት የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 97 ሚሊዮን ደርሷል፤ ከእነዚህ ከዘጠና ሰባት ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ ከሶስት ሚሊዮን ህዝብ በላይ ነዋሪዎች ያላት አዲስ አበባ ውስጥ ከትንሽ ቡና ቤት እስከ ባለኮከብ ሆቴሎች ውስጥ 15,000 ሺ ሴተኛ አዳሪዎች ሲኖሩ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ምሽት ለወሲብ ንግድ የሚቆሙ 5,460 ሸሌዎች ሲኖሩ ከዚህ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ውስጥ 358 የተመዘገቡ ማሳጅ ቤቶች ውስጥ በማሳጅ ቤት ስም የወሲብ ንግድ ላይ የተሰማሩ ሸሌዎች 3,200 ይጠጋሉ፡፡ ባጠቃላይ አዲስ አበባ ውስጥ 15,000 +3,200 + 5460 =23,660 የሚጠጉ ሸሌዎች አሉ ማለት ነው፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ በ1982 ደርግ ስልጣን ላይ እያለ የነበሩ የሸሌዎች ቁጥር 6,484 ገደማ ነበሩ፤ በዘመነ ኢህአዴግ ቁጥሩ እጅግ ግዙፍ ነው፤ እንግዲህ ለሴቶች ልዩ ትኩረት እሰጣለሁ፣ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ማሻሻል ማህበረሰብን ማሻሻል ነው፣ የሀገር ለውጥ መሠረት ሴቶች ናቸው፣ በሴቶች ቅድሚያ ሰጥተናል፣ እጅግ በርካታ ሴት ሚሊየነሮችን ለማፍራት ችለናል፣ ሴቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ራሳቸውን እንዲችሉ አድርገናል፣ ለሴቶች ልዩ ትኩረት ሰጥተናል... የሚለው ኢህአዴግ አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ 23,660 ሸሌዎች አሉ ሲባል ምን ይሰማው ይሆን ? በነገራችን ላይ ስለ ሸሌዎች ከተነሳ ሸሌነት እኮ አዲስ ነገር አይደለም፤ ጥንትም የነበረ ነው ፤ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሸሌነት (ጋለሞታ ሴቶች) ብዙ ታሪኮች እኮ አሉ፡፡ ያው ገላን ለንግድ ማቅረብ ብርቅ ባይሆንም አንድ ጊዜ ታይምስ መፅሔት ላይ Jenskofod የተባለ በአንትሮፖሎጂ PHD ያለው ዝነኛ ሪሰርቸር የሆነ ግለሰብ በሸሌዎች ላይ ያደረገውን ጥናት ሳነብ ለምንድን ነው ሴቶች ሸሌ የሚሆኑት? ለሚል ጥያቄ በጥናት የደረሰባቸው ምክንያቶች አሉ፡፡ በቁጥር አንድ የኢኮኖሚ ችግር ጋር የሚቆራኝ ሲሆን ፤ በሁለተኛነት የተቀመጠው በተፈጥሮአቸው ከፍተኛ የወሲብ ጥማት (ሱስ) ያላቸው ሴቶች ወደ ሸሌነት መግባት፣ በሶስተኛነት በሳይንስ መጠሪያ "ሴክስዚንቶቢያ" የሚባል የሴቶች ችግር የተነሳ ነው፤ በዚህ በሽታ የተለከፉ ሴቶች የወሲብ እርካታ የሚያገኙት ከተለያዩ ወንዶች ጋር በመማገጥ ብቻ ነው፤ ከአንድ ወንድ ጋር በጭራሽ አይረኩም፡፡ በአራተኛነት የተቀመጠው ምክንያት ራስን መደበቂያነት፣ የፆታ ጥቃት፣ የጓደኛ ግፊት፣ የመጠጥ ፍቅር፣ ያልተሳካ የፍቅር ግንኙነት... ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው ይላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይ መንገድ ላይ ከሚቆሙት ሸሌዎች ጋር 'Clinic prostitutes' የሚባሉ እደገኛ ሸሌዎች አሉ፤ እነዚህ ሸሌዎች አሁን እሁን የአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይም

እየበዙ ናቸው:: ልክ እንደ ሸሊዎች ምሽት ላይ ተኳኩለው ይወጡና ወንዱን እያሳሳቁ እኔ ጥሩ መኝታ ያለበት ቦታ አወስድሃለሁ ይሉና ያስደፍሩታል፣ ያሰርቁታል፣ ሊያስገድሉትም ይችላሉ"

ስለ ሸሌነትም ሆነ ስለማሳጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ያጫወተኝ ራምስ ነበር:: ወይኔ የራምስን ያህል እውቀት እና መረጃ ቢኖረኝ ኖሮ እኮ ወዲያው ነበር ድርሰቱን የምጀምረው:: ለአንድ እፍታ ከሄድኩበት የትዝታ መነፅር ተመልሼ እጠገቤ ያለችውን እና በጭራሽ ሸሌ ትሆናለች የሚል ግምት ያልነበረኝ ወጣት ደሊላ ላይ ትኩረት አደረኩኝ፤ በባህላችን ግን አዘንኩ፤ ግሎባላይዜሽን ምን ያህል እንደተንሰራፋ ተገነዘብኩ:: በፊት ሸሌ ነኝ ማለት በጣም ያሳፍር፣ ያስነውር፣ ያሰቀጥጥ ነበር፤ አሁን ማንም ግድ የለውም፤ በተለይ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለን እጅግ በርካታ የተማሪ ሸሌዎች እናውቅ ነበር፤ ምንም ሳይመስላቸው "ገንዘብ ቆጭ ካደረክ በሞርኮ ባዝ የታጠበ፣ ደረጃውን የጠበቀ፣ ከበሽታ ንፁህ የሆነ፣ ጥሩ ማዕዛ ያለው እምስ ይሰጠሃል" የሚሉ ሴቶች ነበሩ"

... እጠገቤ የተቀመጠችው ደሊላም አንዳች የፍርሃት ስሜት ሳይሰማት ነበር በነፃነት የተናገረችው፤ ለማንኛውም ይበልጥ ስለ ስራዋ መረጃ ለማግኘት ጥያቄዬን ቀጠልኩ:: እንዴ ደራሲ እኮ ነኝ! ለደራሲ መረጃ መሰብሰብ ከጣፋጭ ምግብም የበለጠ ነው!! ከመፃፍ በፊት ብዙ መረጃ መያዝ፣ ብዙ ማንበብ፣ ብዙ ማውጠንጠን ያስፈልጋል... እናም ጥያቄዬን ቀጠልኩ::

"እ ... እስቲ ስለ ማሳጅ ቤት አጫውቺኝ"

"ተጠቅመህ አታውቅም?"

"በጭራሽ"

"ለምን?"

"አስቤው አላውቅም"

ረዘም ረዘም ባሉት የግራ ጣቶቿ ወደፊት የመጣውን ጥቁር ደማቅ ፀጉሯን ወደኋላ መለሰች፤ ከዚያ መናገር ቀጠለች::

"እውነቱን ለመናገር ቅድም እንዳልኩህ ወደ ስራው ስገባ እኔ የማሳጅ ስራ እስራኤል ውስጥ እንዳለው መስሎኝ ነበር፤ በፍጥነት የሶስት ወር ኮርስ ወስጄ ስራውን የጀመርኩት:: ማሳጅ ጥንትም የነበረ ነው፤ አፍሪካ ውስጥ ጥንታዊያን ግብፆች 2500 ዓ.ዓ ከክርስቶስ ልደት

በፊት ይጠቀሙ ነበር። በተለይ በቻይና ከ2700 ዓ.ዓ ጀምሮ የህክምና ዘዴ እና አንዱ የመዝናኛ ዘዴ ነበር፤ በህንድም ከ3000 ዓ.ዓ ጀምሮ "አይሩቬዳ" በመባል መለኮታዊ ተዓምር ተደርጎ ይጠቀሙበት ነበር፤ ባጠቃላይ ከጥንት እስከ አሁን ድረስ ማሳጅ ህመምን ለማሻል፣ ጉዳትን ለመቀነስ ፣ አዕምሮን ዘና ለማድረግ በጣም ከፍተኛ ጥቅም አለው፤ በተለይ የሞቱ ሴሎችን ለመተካት ያለው ጠቀሜታ በጣም ወሳኝ ነገር ነው። እኔ እስራኤል እያለሁ ከወንድሜ እና እባቴ ጋር በ15 ቀን ልዩነት ማሳጅ ቤት እየገባን እንጠቀም ነበር። ለሰውነታችን መነቃቃት እጅግ ወሳኝ ነገር ነው። እጅግ በርካታ አይነት የማሳጅ አይነቶች ከበርካታ ጥቅሞች ጋር አሉ። በጣም የታወቁት እና በብዛት የሚታወቁት Swedish massage, Hot stone massage, chair massage, Deep Tissue massage, Trigger point massage, Neuromuscular Therapy, shiatsu massage, Thai, massage, sports massage, Dry massage ይጠቀሳሉ ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ በቅርቡ ስምተህ ከሆነ በየጋዜጣው፣ መፅሔቱ፣ መፅሐፉ፣ ስለማሳጅ ቤት እና የወሲብ ቅሌት ሲፃፍ ነበር"

"እንብቢያለሁ"

"አዲስ አበባ ውስጥ ያለው እውነት ትክክለኛውን ስራ የሚሠሩ እውነተኛ የማሳጅ አገልግሎት የሚሰጡ ትንሽ ቤቶች አሉ፤ አብዛኛው ግን ለወሲብ ንግድ ብቻ የተመሠረቱ ናቸው። እኔም ትክክለኛውን እሰራለሁ ብዬ አስቤ ነበር፤ ስገባበት ግን ተፈተንኩ፣ በፈተናው ወደኩ... ከዚያ ከሌሎች ጋር ተመሳሰልኩ... ሀቁን ለመናገር ካሉት ማሳጅ ቤቶች 10% ትክክለኛውን ህጋዊ ስራ ብቻ የሚሠሩ ናቸው። 90% ግን ዋና ትኩረታቸውን የሚያደርጉት በገንዘብ ላይ ነው። እኔ ወደ ስራው ከገባሁ ሁለት ዓመት አለፈኝ። እጅግ በርካታ ቤቶች ለማየት ችያለሁ። አንዳንድ ዘመናዊ ቤቶች ውስጥ ድብቅ ካሜራ ሁሉ የተገጠመላቸው አሉ። አንተ ሳታውቀው ይቀረፅና ለእነ አሜሪካ፣ ኢንግሊዝ የመሳሰሉት ሴክስ ለሚሠሩ ፊልሞች ይሸጣል፤ ያው ስራው ውስጥ ስትገባ ስለ ስራው ብዙ ነገር ታውቃለህ፣ ከበርካታ ሰዎች ጋር ትተዋወቃለህ፣ ብዙ ገጠመኞች ያጋጥሙሃል። እኔ በደረስኩበት ጥናት ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉት ማሳጅ ቤቶች አምስት አይነት ናቸው፤ ልንገርህ?"

"እንዴ ምን ጥያቄ አለው!"

"አንደኛው VIP massage የሚባል ነው፡፡ እነዚህ በብዛት "ፍርድ ቤቶች" የሚል መጠሪያ አላቸው፤ ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ ታዋቂ ሰዎች፣ ለስብሰባ የሚመጡ መሪዎች፣ አንግዶች ፣ ሀብታም ቱሪስቶች፣ የሀገሪቱ ሀብታሞች የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ማሳጅ ቤቶች ለመጠቀም ለአንድ ጊዜ ብቻ ከ3000 ሺ እስከ 15,000 ሺ ብር መያዝ አለብህ፤ ማንኛውንም አይነት አገልግሎት ታገኛለህ፤ ቢሆንም ተራ ሰዎች ግን መግባት አይችሉም!!"

"በሁለተኛነት ጥላ ፎቅ የሚባሉ ናቸው፡፡ ሁሉም አይነት የማሳጅ አገልግሎት ሆነ ወሲብ ታገኛለህ፣ መካከለኛ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው መግባት ይችላል፡፡ ከ400 ብር እስከ 1,200 ብር መያዝ አለብህ"

" ሶስተኛው ከማን እንሼ የሚባሉ ናቸው፡፡ ለወሲብ ንግድ ብቻ በሴተኛ አዳሪዎች ጥቃቅንና አነስተኛ እንደሚባሉት ተደራጅተው የሚከፈቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ዋጋቸው ርካሽ ናቸው፡፡ ከ200 ብር እስከ 700 ብር መያዝ ይጠበቅብሃል፤ አራተኛው ፖስተኛ የሚባሉ ናቸው፡፡ የማሳጅ እና የወሲብ አገልግሎት በስልክ ጥሪ ቤት ለቤት ሲደወልላቸው ሄደው የሚሠሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ቋሚ ዋጋ የላቸውም"

"አምስተኛው ዝግ ልዩ የሚባሉ ማሳጅ ቤቶች አሉ፤ ግብረሰዶሞችና ሌዚቢያን የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡ እየሀ በማሳጅ ቤት ስም ኢትዮጵያ ውስጥ ኢሉሚናቲዎች በጣም እየተስፋፉ ናቸው፡፡ በዓለም ላይ ወሲብ እንዲስፋፋ ፣ ግብረሰዶማዊነት እንዲስፋፋ ከፍተኛ ስራ ከሚሠሩ ድርጅቶች አንደኛው ኢሉሚናቲዎች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን ደግሞ የአፍሪካ የወሲብ ማዕከል ለማድረግ ከፍተኛ ስራ እየሠሩ ናቸው"

"ቆይ መንግስት ብዙ ቤቶችን ዘጋ ሲባል ሰምቼ ነበር እኮ"

"የተሳሳተ መረጃ ነው!! ውሸት ነው!! ሲጀመር ህጋዊ ግብር እስከ ከፈሉ ድረስ ማሳጅ ቤቶችን አይዘጋም፡፡ ራሳቸው የመንግስት ባለስልጣናት ምሽት የት የሚገኙ ይመስልሃል? በየማሳጅ ቤቱ አይደለም እንዴ! እኔ እንኳ ስንት ባለስልጣናት አይቻለሁ መሰለህ፤ ግን የሚጠቀሙት በልዩ ቤቶች ነው፤ ለወጉ መንግስት ዘጋው ይበል እንጂ በዓመት አንድ ጊዜ ድንገት የተወሰኑ ሰዎች ይመጡና ማሳጅ ቤቱ ውስጥ ኮንዶም ካለ ይፈትሻሉ ፤ ከተገኘ "ህገወጥ ስራ ላይ በመሠማራት" በሚል ዛቻ ቤቱ ይዘጋል ይላሉ፤ ባለቤቶቹ 10,000 ብር ሙስና ይቦጭቃሉ በቃ ሠላምታ ተለዋውጠው ይሄዳሉ፤ ካልሆነም አንዳንዴ ሲቪል ፖሊስ እንዲጠቀም ይልኩና ወሲብ ካደረገ በኋላ ኮንዶሙን ለመረጃ በመያዝ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል

ለእሱም የተወሰነ ብር ትቦጭቃለህ.. አለቀ"

"እንደው ወገንተኛ ሳትሆኚ እንቺ የትኛውን ትደግፊያለሽ? መዘጋት አለባቸው ወይስ የለባቸውም?"

"እንዲህ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ እኮ አይደለም ፤ በጣም የተወሰኑ የማሳጅ ማሰልጠኛ ት/ቤቶች አሉ፤ ቢሆንም በርካታ ሴቶች በማሳጅ ሰልጥነው እየተመረቁ ናቸው:: በርካታ ማሳጅ ቤቶች አሉ፤ ይሄንን ንግድ በሰው የስራ ዘርፍ መንግስት አቆመዋለሁ ቢል ለዚያውም እንደ ኢትዮጵያ ባለች ደሀ ሀገር ጨርሶ የማይታሰብ ነው፤ ማሳጅ ቤቶች ቢዘጉ ራሱ በሌላ ዘርፍ ስማቸውን ቀይረው ይመጣሉ፤ ቆይ እንተን አንድ ሀቅ ልጠይቅህ?"

"እሺ"

"በርካታ ማሳጅ ቤቶች እንዳሉ ታውቃለህ! ወጣት ነህ ! ገንዘብ አለህ! ለምን እስከ ዛሬ አልሄድክም?"

"ብዙም ፍላጎት የለኝም"

"እየህ የምርጫ ጉዳይ ነው:: ፍላጎት ከሌለህ ምንም ነገር አታደርግም:: ማሳጅ ቤት ያለ አንተ ፍላጎት ጎትቶህ የሚያስገባህ ሰው የለም:: ራስህ ነህ በፍላጎት የምትሄደው:: ለምሳሌ ማሳጅ ቤት ብትመጣ ራሱ ያለ አንተ ፍላጎት በግድ ወሲብ እናድርግ ሴቶች አይሉህም:: በእርግጥ ማሳጅ ቤት ስለ መጣህ ማንኛዋም ሴት ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት በተለይ ከማን አንጻ ማሳጅ ቤቶች ስትገባ ትቆሰቆሳለህ ባትፈልግም አፍህን አውጥተህ እንድትናገር፣ እንድትሻፍድ ፤ እንዲቆምብህ ፤ ወሲብ እንዲያምርህ ሆን ተብሎ Seduced ትደረጋለህ፤ ቢሆንም አንተ ጋር የፍላጎት ጭላንጭል ከሌለ እና ለሚስትህ አልያም ለፍቅረኛህ ታማኝ ከሆንክ ባጠቃላይ ፊስ ያሰበት ዝላይ አይችልም የሚባለው አይነት ወንድ ካልሆንክ ወይም አንተ ውስጥ መነሳሳት ከሌለ ፈተናውን ማለፍ አያቅትህም!! ለእኔ ሆነ ሌሎቹም ሴቶች ሲነግሩኝ ግን አብዛኛው ወንዶች ማሳጅ ቤት የሚመጡት ለወሲብ ሲሉ ብቻ ነው::"

ፀሐዩዋ እየጋለች መምጣት ጀምራለች:: የደሊላ ወሬ እየጣመኝ ነው:: ቁርስ ስላልበላሁ ደግሞ ሆዴን በመጠኑ እየሞረሞረኝ ነው::

"ይቅርታ ደሊላ! ጨዋታችን በጣም ደስ ብሎኛል እንቀጥላለን ቁርስ አልወሰድኩም፤ ፀሐዩዋም እየከበደች ስለሆነ አንቺም ቁርስ እንዳልበላሽ ተስፋ አደርጋለሁ ፤ ስለዚህ ነይ እሪፍ ቁርስ እለኝ እየበላን እንጫወታለን"

"ባንዳፍ" አለች::

የሀበሻ ወንድ ብሆንም እንደ ሌሎች የሀበሻ ወንዶች በምግብ ስራ አልታማም:: እንጀራ መጋገር፣ ወጥ መስራት፣ ዶሮ መስራት፣ ቡና ማፍላት፣ ወዘተ ከሴቶች በላይ የተካንኩበት ስራዬ ነው:: በተለይ የስምንት ወር የምግብ አሰራር ስልጠና መውሰዴ በጣም ጠቅሞኛል እናም ምርጥ የሆነ ጨጨብሳ ሰርቼ ከጥሩ የማሽን ቡና ጋር አቅርቤ በላን:: በጣም ነበር የተገረመችው ፤ ስንጨርስ

"ዋው የሚገርም ቁርስ ነው ፤ ስለዚች ሙያማ ሌላ ጊዜ በሰፋት እናወራለን:: ኮርቼብሃለሁ! ወደ ጨዋታችን እንመለስ?"

"ደስ ይለኛል"

"ለምሳሌ አንተ ማንም ሳያስገድድህ ማሳጅ ቤት ብትሄድ እንዳልኩህ እውነተኛ ማሳጅ ቤቶች ከሄድክ ትክክለኛ አገልግሎት ይሰጡሃል፣ ወሲብ ራሱ ብትጠይቅ እንቢ ትባላለህ:: ለማሳጅ ሙያ ክብር ስላላቸው ለገንዘብ ሆነ ለህገወጥ ስራ አይታለሉልህም!! እነዚህ መሰል ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ሴቶች በጣም ሃይማኖተኛ ፤ ዝሙትን እጅግ የሚፀየፉ ፤ በምንም ተዓምር በገንዘብ የማትገዛቸው ፤ ለወሲብ ሆነ 'Extra' ከሚያገኙት በርካታ ገንዘብ ይልቅ በንፁህ ልብህ ተደስተህ የምትሰጣቸውን በጣም ትንሽዬ ቲፕን የሚመርጡ እና የሚያከብሩ! ስራቸውን ብቻ በፍቅር የሚሠሩ ታማኝ ሰዎች ናቸው:: በሌላ በኩል እስመሳይ ማሳጅ ቤቶች ዋና ትኩረት አድርገው የተነሱት ሮማንቲክ ማሳጅ እና ወሲብ ወይም ገንዘብ ስለሆን ገና እንደገባህ ይቆሰቁሱሃል:: በተለይ አዲስ ከሆንክ ሙድ ይይዙብሃል"

"አዲስነቴ በምን ይታወቃል?"

"ውይ ይሄማ በጣም ተራ ነገር ነው:: ለምሳሌ አሮማ ማሳጅ ለመጠቀም 200 ብር ብዙ ቤቶች የተተመነለት ዋጋ ነው:: ከዚህ ብር ላይ ማሳጅ ቤት የምትሰራዋ ሴት በፐርሰንት ከድርጅቱ ጋር ትካፈላለች፤ ስለዚህ የእርሷ ጥቅም ትንሽ ስለሆነ አንተን ፍላጎት ካለህ አሰየው ከሌለህም Seduced ተደርገህ Extra አልያም ወሲብ ብትጠቀም የተሻለ ገንዘብ ስለምታገኝ አንተን ለመቆስቆስ ትዘጋጃለች፤ እውነቱን ለመናገር ከልምዴ እንዳየሁት እንደ የኢትዮጵያ ወንዶች ደግሞ በተፈጥሮዋቸው ቶሎ እና በቀላሉ የሚሸፍዱ የሉም! ስለዚህ አምሮት ውስጥ ማስገባት በጣም ተራ እና ቀላል ነገር ነው እና አንተ አዲስ መሆንህን ለማወቅ በጣም ቀላል ነው፤ እንዳልኩህ ለምሳሌ አሮማ ስሪኝ ብለኸኝ "ምን አይነት ልስራህ?" ስልህ ዝም ካልከኝ

ወይም "አልገባኝም?" ብለህ ትጠይቀኛለህ፤ እየህ የምታውቅ ከሆነ ማንኛውም ማሳጅ አራት መሠረታዊ እሽታዎች አሉት:: ኢፍላራጅ፣ ፐትራሳጅ፣ ዲፐቲሹ፣ ፐርኩሽን ይባላሉ፣ ስለዚህ ከእነዚህ ከአራቱ አንደኛውን ከመረጥክ አዲስ እንዳልሆንክ ያስታውቃል፤ ምናልባት ከሌላ ተጠቃሚ መረጃ አሰባስበህ ብትመጣ ራሱ በምታደርገው የሰውነት ሁኔታ ጥያቄ ሳትጠየቅ ራሱ ማወቅ ይቻላል:: እንዴ ብዙ ብር በአንድ ቀን ስለምታገኝ እኮ ሳትፈልግ ሰውዬውን ትቆሰቁሰዋለህ:: ለምሳሌ ቆስቁስህ ቆስቁሰህ አንዳንዱ ስሜት ውስጥ ገብቶ ፈርቶ ለመናገር ዝም ሲል የማሳጅ ቤት ቋንቋ ትጠቀማለህ

'ተመቸህ?' ትባላለህ

'አዎ' ትላለህ

'ቅር ያለ ነገር አለ?'

'የለም'

'ይበልጥ እንዲታሽልህ የምትፈልገው ቦታ አለ?"

"የለም" ትላለህ

ልጅቷ ስሜት ውስጥ መግባትህን በሰውነትህ ሙቀት፣ ትኩሳት፣ የቁላህ መቆም.... ስለምታውቅ አንተ አስቀድመህ ጥያቄ ሳታነሳ ' Extra' ልስራህ ትባላለህ በብዛት 'Extra' አገልግሎት የሚሰጠው ሴጋ ለመምታት ወይም ብልትህን እንዲታሽልህ ነው፤ ለዚህ አብዛኛው ቤት ተጨማሪ ከ150-200 ብር ያስከፍሉሃል... ወሲብ ካልክ ተጨማሪ ብር ትጠየቃለህ:: እህ በተለይ ጥቢልኝ ካልከም ተጨማሪ ብር ትጠየቃለህ... እየህ አንዲት ሴት በአንድ ቀን ውስጥ አነሰ ከተባለ ከ500 –3000 ብር ታገኛለች:: ስለዚህ ማሳጅ ቤት ያልተበላበት ዕቁብ ስለሆነ በርካታ ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁ፣ ከአረብ ሀገራት የሚመጡ፣ ስራ ያጡ ወጣቶች ሁሉ በመጉረፍ ስራው ላይ እየገቡ ይገኛሉ፤ ታዲያ በዚያው ልክ በቂ የማሳጅ እውቀት ሳይኖራቸው፣ ትምህርት ሳይማሩ፣ የውሸት ወረቀት እያሰሩ በስራው ላይ የተሰማሩ በጣም በርካታ ሴቶች በመኖራቸው ወንዶች ላይ በጭራሽ መታሸት የሌለባቸውን የሰውነት ክፍሎች በማሸት ከቀላል እስከ ተወሳሰበ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ ናቸው::"

"ይህ ከፍተኛው ችግር ነው፤ በዚያ ላይ ጊዜው ያለፈበት የወይራ ዘይት የሚጠቀሙም አሉ፤ ይህ ደግሞ በቆዳ ላይ ከፍተኛ ጉዳይ ያመጣል ፤ ይህን ይህን ስታስብ በተለይ ከነርቭ ጋር በሚያያዝ በሽታ በቀላሉ ልትያዝ ትችላለህ፤ ብዙዎቹ በቂ እውቀት

ስለሌላቸው አንድ ሰው ቢበዛ ማሳጅ ማብዛት የለበትም፤ እነርሱ ግን ለገንዘባቸው ሲሉ በየቀኑ ብትጠቀም ራሱ ችግር የለውም ይሉሃል፤ ለጠየከኝ ጥያቄ እውነቱን ለመናገር እኔ ማሳጅ ቤቶች ይዘጉ በሚለው በጭራሽ አልስማማም:: ይልቅ ማሳጅ ራሱን የቻለ የህክምና ጥበብ ስለሆነ ትምህርቱ በዘመናዊ መልኩ በዩኒቨርሲቲዎች ራሱ መሰጠት ያለበት ሙያ ነው:: ዋናው ቁም ነገር እኮ ማሳጅ በሰውነት ላይ ምንም ነገር አያደርግም፤ ሆኖም የሚያደርገው ብቸኛ ነገር ሰውነታችን መደበኛ ተግባራቱን ይበልጥ እንዲያከናውን ያነቃቃል፤ ያበረታታል፤ የሞቱ ሴሎችን ይተካል፤ ስለዚህ ማሳጅ አንተ ለሌላው ሰው የምታደርገው ሳይሆን ሰውነትህ አፀፋዊ ምላሽ እንዲሰጥ አንተ የምታነሳሳው ሂደት ነው:: ማሳጅ መነቃቃትን ሲሰጥ ሰውነት ደግሞ እንቅስቃሴውን ያካሄዳል:: ባጭሩ በማሳጅ የሚገኘው ጥቅም የጡንቻ ውጥረትን ማርገብ፣ ጡንቻዎችን ማጎልበት፣ የደምና የሊምፍ (ቀለም አልባ ፈሳሽ) ዝውውርን ማነቃቃት ነው"

"... ስቦችን ማስወገድ፣ የሰውነት እንቅስቃሴን ማፋጠን የመሰሉትን ጥቅሞች ማከናወን ናቸው፤ ስለዚህ እውነተኛ የሆነውን ማሳጅን ማንኛውም ሰው ሊጠቀመው የሚገባ ዘመናዊ ህይወት ውስጥ ሊኖር የሚገባ ነገር ነው!!"

"ስለዚህ አይዘጋ ትያለሽ?"

"No! ቃል በቃል አይዘጋ ማለቴ ሳይሆን እንደነገርኩህ ማሳጅ በጣም ጥንቃቄ የሚፈልግ እና በማንም ተራ ሰው የሚከናወን ሳይሆን ስለማሳጅ በቂ እውቀት ባለው ሰው የሚከናወን ከፍተኛ ጥቅም ያለው ሳይንስ ነው፤ ግን አገራችን ውስጥ አሁን ያሉት በስራው የተሰማሩ 90% የሚሆኑት ማሳጅ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ሴቶች በእርግጠኝነት በቂ እውቀት የላቸውም:: ማሳጅ ማለት በቃ ቀላል እና ተራ ድርጊት አድርገው ይቆጥሩታል:: እኔ ጋር ተጠቃሚዎች ሲመጡ መጀመሪያ ስለ ጤንነት ሁኔታቸው ነው የምጠይቀው:: ምክንያቱም ለማሳጅ የማይስማሙ ህመም ያለባቸው ሰዎች ይኖራሉ፣ ለምሳሌ ነብሰጡር ሴት በጭራሽ መታሸት የለባትም ፣ ቫሪኮዝ ቬይን ችግር ያለበት ግለሰብ በጭራሽ መታሸት የለበትም፣ ከፍተኛ የደም ግፊት ህመም ያለበት ግለሰብ... መሰሎች መታሸት የለባቸውም:: እኛ ሀገር ያሉት ሴቶች ለገንዘባቸው ብቻ ሲሉ ያለ ምንም ጥያቄ በቀጥታ ወደ ስራቸው ነው የሚገቡት:: በእነዚህ የተነሳ ማሳጅ ቤት ውስጥ ተጠቅመው ከወጡ በኋላ መንገድ ላይ ራሳቸውን ስተው የሞቱ በርካታ ሰዎች አሉ:: አየህ እውነተኛ የማሳጅ ባለሙያ ስትሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ የምታደርገው ለገንዘብ ሳይሆን ለሰዎች ጤና እና ደህንነት ነው:: ከብር ይልቅ

የሰው ጤና ይቀድማል፤ በዚያ ላይ በምንም ተዓምር መታሸት የሌለባቸው ከታሹም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ቦታዎች አሉ:: ለምሳሌ በማንኛውም አጥንቶች፣ አከርካሪ፣ በጉልበት ሎሚዎች ወይም ከጉልበቶች ስር ያበጡ ጡንቻዎች፣ መጋጠሚያዎች ላይ ማሳጅ ማድረግ አደጋ አለው፤ ይህን መሰል ነገር በብዛት ስለማያውቁ ስንቶች ለህመም ይዳረጋሉ መሰለህ፤ ለዚህ ነው ሙያውን በተመለከተ ስለሙያው በጥንቃቄ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርት እየተሰጡ በቂ እውቀት ያላቸው ወንዶች ሆነ ሴቶች ተመርቀው በሙያው ላይ መሠማራት አለባቸው የምልህ"

"የሚገርምህ እኔ ስለሙያው በሚገባ ለማወቅ ስለማሳጅ የሚያወሩ በርካታ መፅሐፍትን እንብቤያለሁ፣ በቪዲዮ የተዘጋጁ ትምህርቶችን ወስጃለሁ! አብረውኝ ለሚሰሩት ራሱ አስለጥናቸዋለሁ፤ ችግሩ እንደ ኢትዮጵያ ሴቶች ጠማማ የለም?"

"እንዴት?"

"በጣም ቅናተኞች ነን! ከምትበልጠን ሴት እውቀት ከመውሰድ ይልቅ ማናናቅ እና ማጥላሸት ይቀናናል! No ይሀ ነገር ልክ አይደለም ስትላቸው እታካብጂ ባክሽ ምንም ችግር አያመጣም! ወገኛ! ብለው ይሰድቡሃል:: በእውቀት የምትበልጣቸውን ሴት ከእጠገባቸው ማባረርን ይመርጣሉ:: የኢትዮጵያ ሴቶች ከሴቶች ከሚማሩ ይልቅ ከወንድ መማርን እንደ ክብር ያዩታል:: በዚህ የተነሳ ከስንት ሴቶች ጋር ነበር መሰለህ መጀመሪያ አካባቢ የምጨቃጨቀው እና የምጣላው"

"... ከዚያ መዳረቁ ሲበዛብኝ በዝምታ የራሴን ስራ ብቻ በጥንቃቄ መስራቱን መርጫለሁ፤ ባጠቃላይ ማሳጅ ቤት የሚሰሩ ሴቶች ራሳቸውን ለማሳደግ ፍላጎት የላቸውም:: በግዴለሽነት የመጣውን ሰው ነካክተው ኪሱን አራቁቶው መላክ ምርጫቸው ነው:: ለምሳሌ አልኮል የጠጣ ሰው በምንም ተዓምር ማሳጅ መደረግ የለበትም! የጀርባ ህመም በተለይ የዲስኮች መንሸራተት ያለበት ሰው መታሸት የለበትም! የካሪዮፕራክተር ዶክተር ወይም የፊዚዮቴራፒስት ባለሙያን አማክሮ ብቻ ነው፤ አለበለዚያ እዛው ጭጭ ሊል ይችላል፤ የቆዳ ኢንፌክሽን ያለበት ሰው አይታሸም... ምግብ ከተበላ ከሁለት ሰዓት በታች ማሳጅ አይደረግም፤ የሚገርምህ ስለ ገላ መታጠብ እንኳ በቂ እውቀት የሌላቸው በርካቶች ናቸው"

"ማለት?"

"በእርግጥ ከማሳጅ በፊት ለብ ያለ ሻወር መውሰድ ችግር የለውም፤ በጣም በሞቀ ውሃ

ታጥቦ ወዲያውኑ ማሳጅ መደረግ ከፍተኛ አደጋ አለው፤ ይቺን ህግ እንኳ ብዙዎች አያውቁም ፤ በተለይ የካንሰር በሽታ ያለበት ግለሰብ ማሳጅ ለዚያውም ቀላል ማሳጅ የሚፈቅድለት ለእጅና ፊት ብቻ ነው፤ ይህን የሚያውቁ እና ጥበቡን አክብረው የሚሰሩ ትንሽ ናቸው፤ እያልኩህ ነው፤ ሌላው ትልቁ ችግር የማሳጅ ተጠቃሚ ወንዶች ሆኑ ሴቶች ማሳጅ ቤት ይመጣሉ እንጂ ስለ ማሳጅ ብዙዎቹ አንዳችም እውቀት የላቸውም:: እውቀት የሌለውን ሰው ደግሞ እንደሱው ሌላ እውቀት የሌለው ሰው ሲያጋጥመው ደግሞ በምሳሌያዊ አነጋገር ምንድን ነው የሚባለው? ግም ለግም አብረህ አዝግም ወይም አይነስውር አይነስውርን እንዴት ሊመራው ይችላል? የሚባለው ነው የሚከሰተው:: ለማንኛውም ሌላ ማወቅ የምትፈልገው ነገር አለህ?"

"ገጠመኞች ንገረኝ"

"በጣም ብዙ ነው:: የተወሰኑትን ብቻ ልንገርህ:: አባትና ልጅ አብረው መጥተው ተጠቅመው ይሄዳሉ:: ልጁ የሲሲ ተማሪ ነው:: ሁልጊዜ አባቱን ጓደኛዬ የምታስተናግደው ሲሆን ልጁ የእኔ ደንበኛ ነው፤ አንድ ጊዜ አስር ሺ ብር ይዞ መጣ:: ሁልጊዜ ሲመጡ ከአባቱ ጋር ነው:: እናልህ ማሳጅ ሠርቼው ስጨርስ

"ዛሬ ለየት ያለ ወሲብ ነው የምፈልገው" አለኝ

"ምን አይነት?" ስለው

በዝምታ ተነሳና ኪሱ ውስጥ የያዘውን ወረቀት አወጣና ሰጠኝ፤ የተጠቀለለውን ነገር ስከፍተው ገና ከባንክ እንደታሸገ የወጣ 10,000 ሺ ብር ነው:: ደነገጥኩ:: እኔ ወሲብ ሲጠይቁኝ ከ600-1000 ብር ነው የማስከፍለው:: የውጪ ሀገር ዜጋ ከሆነ ዋጋው ይጨምራል ፤ በምንም ተዓምር ለአረብ፣ ናይጄሪያ እና ኬኒያ ወንዶች እሺ ብዬ ግን አላውቅም፤ የሶስቱንም አገር ወንዶች በጭራሽ ሰውነቴን አላስነካቸውም እና የሲሲው ተማሪ የሰጠኝ ብር በርካታ ስለነበር 'ምንድን ነው' አልኩት::

"የቂጥ ወሲብ ማድረግ እፈልጋለሁ"

"በጭራሽ" አልኩት::

ብዙ ለመነኝ:: እንቢ አልኩት:: ታዲያ በሳምንቱ ከአባቱ ጋር ተመልሰው መጡ:: እኔን ሳይሆን ሌላ ሴት መርጦ ገባ:: ከዚያ ወዲያው የመረጣት ኤዲ የምትባል ልጅ ስለነበረች ልጁን ከፍል ውስጥ አስቀምጣው መጣችና 'ከደንበኛሽ ጋር ተጣላችሁ እንዴ ?' አለችኝ::

'እም'

'ለምን?'

'በቀደም የቂጥ ወሲብ ጠይቆኝ'

'እና?'

'ምን እና አለው እንቢ አልኩታ'

'ስንት ብር ይዞ ነው?'

'10,000 ሺ'

"ግራሲያ!" ብላኝ ሄደች:: የሊሴው ተማሪ ከኤዲ ጋር ብሩን ከፍሏት የቂጥ ወሲብ አደረጉ:: እንግዲህ አባት ለልጁ የሚያስተምረውን ተመልከት::"

"አንድ እኛ ጋር የሚሠራ ጆን የሚባል የወንድ ማሳጂስት አለ:: እጅግ በርካታ ሴት ደንበኞች አሉት:: ልጁ በጣም የሚያምር ወንዳወንድ ቁመና ስላለው በቀን ውስጥ ከፍተኛ ገንዘብ ያገኛል፤ አንድ ጊዜ ታሞ ቀረና አንዲት ደንበኛው መጣች፤ "ጆን የለም እንዴ?" ስትለን ለቀልድ ብዬ "ውይ ትላንት ኢንግሊዝ ሄደ እኮ" ስላት ምንም ሳትናገር በድንጋጤ መሬት ላይ ፈረጠች:: እንዴት ከው እንዳልኩ ልነግርህ አልችልም:: ልጅቷን ለማረጋጋት 30 ደቂቃ ነበር የፈጀብን:: ልጅቷ የአንድ የኢህአዴግ ባለስልጣን ልጅ ነች:: ከወር በኋላ ባለስልጣን አባቷ ጆንን አስጠርተውት "ወይ አግባት ወይ ሞትህን ምረጥ" ተብሎ ጆንም የሆን ልበሙቅ፤ ፈሪ ፤ በጭባጫ ነገር ስለሆን ወዲያው አገባት... ሰርጉ ላይ የነበረውን ውስኪ ብዛት እና ሰው እንደ ውሃ ሲራጨው ስታይ ወይ ኢትዮጵያ አዘንኩልሽ! ሙሰኞች ብሩን ቦጠቦጡልሽ ትል ነበር::"

"እህ... ስለ ኢህአዴግ ከተነሳ አንድ ቀጫጫ ደንበኛ ነበረኝ:: ብዙ ስለማያወራ ፤ ቀለል ያሉ አልባሳት ብቻ እየመረጠ ስለሚለብስ ደስ ይለኛል:: ወሲብ ላይም በጣም ጎበዝ ከመሆኑ ባሻገር HIV ስለሚፈራ በጣም ጠንቃቃ ነው፤ በጣም ስንግባባ ማውራት ጀመርን:: አንድ ጊዜ

'በነገራችን ላይ ስምሽን አልወደውም' አለኝ

'ለምን?' ስለው

'ደሊላ ማለት የሳምሶምን ፀጉር አስላጭታ ሀይሉ እንዲነጠቅ ያደረገች ሴት ስለሆነች በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ታሪኳን ካነበብኩ በኋላ ደሊላ የሚል ስም ያስጠላኛል፤ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ማርሲላስ እያልኩ ነው የምጠራሽ'

`ዋው! በጣም ደስ የሚል ስም ነው እመሠግናለሁ`

`በነገራችን ላይ የራስሽን ማሳጅ ቤት መከፈት ትፈልጊያለሽ`

` በጭራሽ`

`ለምን?`

` እኔም የግድ ሆኖብኝ ነው የምሰራው እንጂ ዝሙት እኮ በጣም አፀያፊ ድርጊት ነው! በዚያ ላይ በዝሙት የሚመጣ ብር ራሱ በረከት የለውም! ምንም ሳታደርግበት ቶሎ ነው የሚያልቀው`

`እና ሌላ ስራ ምን ትሰሪያለሽ?`

` አልወሰንኩም ግን ይህን ስራ ቶሎ መተው እንዳለብኝ ውስጤ ይነግረኛል፤ ምክንያቱም በህይወት ከመራራ ሀቅ ጋር ሁሌ እየተጣላህ መኖር አትችልም። ለምሳሌ አንተ ፍቅረኛህ ማሳጅ ቤት ብትሰራ ታገባታለህ? ሳትዋሽ ንገረኝ?`

`በጭራሽ`

` ለምን?`

`መቼም መልሱን መገመት እያቅትሽም! ዝሙተኛ ሴትን ማን ይፈልጋታል። ይልቅ ለምን ስራ አላስቀጥርሽም?`

` ደስ ይለኛል! ምን አይነት ነው?`

` እኔ የኢህአዴግ ደህንነት ነኝ ከፈለግሽ አዲስ አበባ ውስጥ እንዳንቺ ለይምሰል ማሳጅ ቤትም የሚሠሩ የደህንነት ሰዎች አሉ፤ ስለዚህ አንቺም ከፈለግሽ ላስቀጥርሽ እችላለሁ`

` እመሠግናለሁ ግን አልፈልግም`

` ለምን? በጣም ቀላል ስራ ግን አሪፍ ገንዘብ እኮ ታገኛለሽ! ቀልጣፋ ከሆንሽ ደግሞ እንዱን ባለስልጣን በፍጥነት ትጠብሻለሽ`

`በእርግጥ ሕይወት ራሷ ፖለቲካ ናት። አፍሪካ ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ፖለቲከኛ መሆን ግን የእዞ እንባ ማንባት ነው። እኔ ደግሞ የእዞ እንባ ማንባት ስለማልፈለግ ከፖለቲካ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ስራዎች አልሰራም! በአነጋገሬ ከተቀየምከ ይቅርታ የሚሰማኝን ነው የተናገርኩት`

`ለማንኛውም አስቢበት` አለኝ:: ብዙ ጊዜ እየመጣ ጨቀጨቀኝ እንቢ ስለው ተፋታኝ:: አንድ ጊዜ ደግሞ አንዲት ሲዚቢያን መጥታ ብር አውጥታ ስትለምነኝ እንቢ ስላት በግድ ልትስመኝ ስትል የተጣላሁትን አልረሳውም:: የእኔን ሳይሆን በጣም የሚገርመኝ የሌላ ሰው ታሪክ ልንገርህ?"

"ደስ ይለኛል"

"መጀመሪያ! በጥንቁልና ታምናለህ?"

"እህ... በሴይጣን አምናለሁ! ዓለም ደግሞ የሴይጣን ነች! ሴይጣን ኢየሱስን ራሱ ሊፈትነው ተራራ ላይ ወስዶት አልነበረም?"

"ቢቃ የሴይጣን ስራ በለው ጥንቁልና መጀመሪያ ስሰራበት የነበረው ማሳጅ ቤት ውስጥ አንዲት 'አውጥቸዋለሁ' የምንላት ልጅ ነበረች:: በጣም ሸንቃጣ ውብ ልጅ ነች:: 'አውጥቸዋለሁ' የሚል ስም የሰጠናት ይህንን ቃል በብዛት ስለምትጠቀም ነው... ኢትዮጵያ ውስጥ ያላወጣችው ዝነኛ ሰው የለም... ስለማንኛውም ሰው ሲነሳ እንዳወጣቻቸው ትናገራለች:-

' ቴዲ ...'

' ውይ ገና ታዋቂ ሳይሆን የምሽት ክተፋ ሲዘፍን አውጥቸዋለሁ'

' በእውቀቱ...'

'ውይ .... አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እያለን'

' አቤል ... '

' ውይ እሱንማ ... '

'ሰይፉ ... '

'ውይ የኔ መላጣ ... እሱንማ... '

'ዮሴፍ ... '

'ውይ የኔ የደሀ አንባ እሱንማ ... '

የማትለው ነገር የለም! ድንገት ለመታዘብ ልታገኛቸው የማትችላቸውን ሰዎች በመፈለግ ስትጠይቃትም ምላሽ አታጣም

'መለስ ... '

'በሀሳቤ አውጥቼዋለሁ ' ትልሃለች! ይቺ ልጅ አንድ ቀን ለብቻዬ ጠርታኝ! በቀስታ

'አንድ ሺ ብር ትከፈያለሽ' አለችኝ::

'ለምን?' አልኳት::

'ደንበኛ ማሠሪያ እሰጥሻለሁ'

'የምን ማሠሪያ?'

'ቅባት ነው'

'የምን ቅባት?'

'የተደገመበት'

'ምን እያወራሽ ነው?'

'የተደገመበት ቅባት አለኝ:: የሚመጡት ወንዶች ላይ ከጀርባቸው ጠብ አድርገሽ ማሸት ብቻ ነው፤ ከዚያ አንቺ ጋር ብቻ ይመላለሳሉ! አንቺ የጠየቅሻቸውን ብር ይከፍሉሻል'

'መቱት ነው? '

'አዎ '

'ድግምት?'

'አዎ'

'አይ ይቅርብኝ'

"ላንቺው ብዬ ነው!!" አለችኝ:: እውነቷን ነበር:: እርሷ ጋር በየሠዓቱ በወረፋ ለመጠቀም የሚመጡትን ወንዶች ብዛት ብታይ ትደነግጣለህ፤ በተለይ ቅዳሜና እሁድ የመኪናው ብዛት ሠርግ ቤት ነው የሚመስለው" አለችና ድንገት በትኩረት እየተመለከተችኝ

"ለቁርሱ እና ለጫዋታችን በጣም አመሠግናለሁ፤ ሌላ ጊዜ በስፋት እንጫወታለን አሁን ልሂድ" አለችኝ:: ወሬዋ ድንገት በመቋረጡ ቅር ቢለኝም

"እኔም አመሠግናለሁ" አልኳት::

ከደሊላ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ያወራነው ይህን ነበር:: ከዚያማ ይበልጥ ተግባባን:: ንፅህና በጣም ትወዳለች:: አንዳንዴ የግቢውን አበቦች ውሃ ታጠጣለች፣ ትኮረኩማለች... በተለይ ነፋሻማው የግቢው መዝነኛ ቦታ በጣም ስለተመቻት ቀንቀን ስራ ሳይኖራት መፅሐፍ ታነብበታለች... ደስ ሲላትም ትተኛበታለች... በብዛት ግን ስራ ቦታ ስለምታሳልፍ ቤት ውስጥ አትገኝም:: ደሊላ ማንም ስለሌላት አዘንኩላት.. ልጅ መውለድ ስለማትችል አዘንኩላት... ለድርሰቴ መነሻ ሀሳብ አልያም ገፀባህሪ ልትሆነኝ ስለምትችል ይበልጥ ልቀርባት ወሰንኩ:: በዚያ ላይ እውነቱን ለመናገር ደሊላ የሆነ ደስ የሚል ነገርም አላት::

# 2

## መምህር መሳይ... ??

### ሚያዚያ 23፡፡

የላብ አደሮች ቀን ስለነበር ሥራ የለም! እናም ቤት ውስጥ ነበርኩኝ፡፡ አዲስ የገዛሁትን መረቅ የተሰኘ የአዳም ረታ መፅሐፍ እያገበገብኩ ነበር ድንገት ራሞስ የመጣው፡፡ ራሞስ እንደተለመደው በእጁ ጋዜጣ እና አንድ መፅሐፍ ይዟል፡፡ አመድማ ሱሪ እና መስመር መስመር ያለው ሸሚዝ አድርጓል! ቀለል ያለች ጫማ ተጫምቷል! ከራሞስ ጋር ተቀምጠን ወሬ እየከካን ድንገት ጩኸት ሰማን፡፡ ሁለታችንም አልደነገጥንም፡፡ ሌላ ሰው ቢሆን ይደነግጥ ነበር፡፡ ይህን መሰል ጩኸት በወር ውስጥ ቢያንስ ለሁለት ቀናት መስማት የተለመደ ነገር ነው! ይህ ጩኸት የሚመጣው የመጀመሪያውን ቤት ከተከራየው ተከራይ ነው፡፡

እኔ ለተከራዮቼ ያስቀመጥኩት ህግ የለም፡፡ በነፃነት እንዲኖሩ እፈልጋለሁ፡፡ ለሊቱን ሙሉ ለምን መብራት አበራችሁ? ለምን ብዙ ውሃ ተጠቀማችሁ? ለምን እንግዶች አበዛችሁ? መሰል ጥያቄዎችን አልጠይቅም፡፡ አከራዮች በተከራዮች ላይ የሚያደርሱትን በደል እና የሚያወጡባቸውን የህግ አይነቶች ለምቻለሁ፡፡ በተለይ ያረገዘች ሴት ቤት የሚያከራያት የለም... ብቻ ቤት አከራዮች በተከራዮች ላይ የሚያደርሱትን በደል ለመዘርዘር ጊዜ ስለሚፈጅ ትቼዋለሁ፡፡ ኢትዮጵያዊያን በኢትዮጵያዊያን ላይ ለምን እንደምንጨክን ግን አይገባኝም፡፡ ቤት

የእግዚአብሔር ነው፡፡ ይቺ ምድር ከጉዱ ናት፤ ነገ ግላናት እንነዳለን... ኢትዮጵያ ውስጥ ግን እያንዳንዱ ሰው ባሰው ነገር ባለስልጣን መሆን ይፈልጋል፤ ልክ እንደ አንባገነን መንግስት ማስፈራራት ይፈልጋል፡፡ ይህ ነገር በጣም ውስጤን ይከነክነኛል፤ እናም እኔ ለተከራዮቼ ነፃነትን ሰጥቻለሁ፤ ያጋጣሚ ሆኖ ተከራዮቼ በብዛት መልካም ናቸው፡፡ አንድ አየሰከረ ማታ ማታ የሚበጠብጥ ተከራይ ነበር፤ ማታ ማታ ከመበጥበጡ በተጨማሪ ለምን እንደሆነ ባላውቅም ልበቢስ ነበር፤ ሁለት ጊዜ የሻወር ቤቱን ውሃ ሳይዘጋ ሞልቶ ግቢውን በውሃ አጥለቅልቆት ነበር፤ ቢሆንም አንድ ቀን በጨዋታ በጨዋታ ስናወራ የግል ችግሩን ስለነገረኝ ምንም ያልኩት ነገር የለም፡፡ በዚያ ላይ ሰው ነውና ሊሳሳት ፣ ሊረሳ ይችላል... ምንም ሳልናገረው በራሱ ጊዜ ከቤቱ ወጣ፡፡ እሱ በወጣበት ቤት ነው ደሊላ የገባችው፡፡

በአሁኑ ወቅት ቤቱ ውስጥ አራት ተከራዮች አሉ፡፡ አራተኛው ቤት ውስጥ ያለው ዘኪዮስ በርናባስ የተባለ ግለሰብ ነው፡፡ ሰባኪ ነው፡፡ ሶስተኛው ቤት ውስጥ ያለው ጋዜጠኛው እንዳልካቸው ሰው አትመን ነው፤ ሁለተኛው ቤት ውስጥ ያለችው ደሊላ ነች፡፡ ቤት አንድ ውስጥ ያለው አስተማሪው መሳይ ቁምላቸው ነው፡፡

መቅደላ አፋፍ ላይ ጩኸት በረከተ

የቤቱን እናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ

ይህ ለመይሣው ካሳ የተገጠመ ቅኔ ነበር፡፡ እኔ ቤት በወር ውስጥ ሁለት ቀናት እረታ እና ጩኸት ይሰማል የጩኸቱ መንስኤ ከአስተማሪው መሳይ ቁምላቸው ቤት ውስጥ ነው፡፡ በተማሪነት ዘመኔ ለአስተማሪዎች ትልቅ ከበሬታ ነበረኝ፡፡ ምርጥ አስተማሪ ምርጥ ትውልድ ያፈራል!! አንድ ቀን ከመሳይ ቁምላቸው ጋር ሳወራ ከው ነበር ያልኩት... ቤቴን በተከራዩ ሳምንቱ ምናልባት የመሳይ ማንነት እና ታሪክ ለምዕፈው ድርሰት የሚሆነኝ ታሪክ ወይም ገፀባህሪ ካገኘው በማለት ሆን ብዬ ጊዜ መርፌዬ ቤቴ ጋበዝኩት፡፡ ኮፒ አድርጎ የሰጠኝ የቀበሌ መታወቂያው ላይ ሥራ የሚለው ቦታ ላይ " አስተማሪ" የሚል ስላነበብኩ

"እሺ መምህርነት እንዴት ነው?" አልኩት፡፡

"በጣም ደስ ይላል፡፡ እንደ አስተማሪነት ቀላል የሆነ ስራ የለም"

"ቀላል? ብዙ ጊዜ ብዙ ሰዎች ግን አስቸጋሪ እንደሆነ ነው የሚያወሩት"

"በእርግጥ ስራው በጣም አሰልቺ ነው፤ ከተማሪዎች ጋር መዳረቅ በጣም ያስጠላል፡፡ እኔ ፋብዮለስ አካዳሚ የሚል ሁለገብ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ነው የማስተምረው፡፡ በጣም

አሪፊ ገንዘብ ይከፍሉኛል፤ ከዚህ በተጨማሪ ቀሽት ቀሽት ስርኪዎች አገኛለሁ"

"ስርኪዎች ምንድን ናቸው?"

"አ ሀንድኛ ነው ሴቶች ማለት ነው"

"ሴቶች ማለት?"

"እየህ እንደምታውቀው የአስተማሪ ክፍያ ኢትዮጵያ ውስጥ ትንሽ ነው፤ ስለዚህ አስተማሪ ስትሆን ትልቁ የምታገኘው ደሞዝ ከሴት ተማሪዎች ጋር ዘና ፈታ ማለት ነው:: አስተማሪ ስትሆን ትልቁ የምታገኘው ደሞዝ ከሴት ተማሪዎች ጋር ዘና ፈታ ማለት ነው:: ብዙዎች የውሸታቸውን ለማስመሰል አስተማሪና ተማሪ የፍቅር ግንኙነት ማድረግ የለባቸውም ይላሉ! እኔ ግን ይህን ሀሳብ በጭራሽ በተለይ የወሲብ ግንኙነት ማድረግ የለባቸውም ይላሉ! እኔ ግን ይህን ሀሳብ በጭራሽ አላምንበትም፤ እስካላስገደድኳት ድረስ ተማሪዬ ፍቃደኛ ከሆነች ለመዝናናት ዝግጁ ነኝ፤ እየተዝናናሁም ነው"

"እና ወሲብ ታደርጋለህ?"

"ከብዙዎች ጋር አድርጌያለሁ! ሁሉም ድንግሎች ነበሩ! ከድንግል ሴት ጋር ወሲብ እንደማድረግ ምን የሚያረካ ነገር አለና?"

"ምን አስተማሪ ነህ?"

"Physics"

"ስንተኛ ክፍል?"

"ዘጠነኛ"

"እና እስከዛሬ ችግር አላጋጠመህም? ከቤተሰቦች? በተለይ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች በመሆናቸው?"

"አላጋጠመኝም በነገራችን ላይ ቀን ቀን አስተምራለሁ! ማታ ማታ ደግሞ I'm a pimp አሪፍ ገንዘብ አገኝበታለሁ! አንተም ተማሪ ማውጣት የምትፈልግ ከሆነ ንገረኝ፤ ያው ቤት ስላከራየኸኝ በአነስተኛ ዋጋ አመጣልሃለሁ!!"

"እየቀለድክ መሆን አለበት?"

"በጣም የምጠላው ነገር ቀልድ ነው:: ለጠየከኝ ጥያቄ እኔ በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው እንጂ ማንኛዋንም ተማሪ ፍቃደኛ ስለሆነች አላወጣትም ወይም በገንዘብ ለሀብታም ወንዶች አላጣብሳትም! መጀመሪያ ምን አይነት ቤተሰብ እንዳላት ከፍተኛ ጥናት አደርጋለሁ፤ የአዲስ አበባ ቤተሰቦች ደግሞ ስለ ልጆቻቸው ግድ የለሽ እና ክትትል ስለማያደርጉ እስካሁን ችግር

አላጋጠመኝም"

"ግልፅነትህን አደንቃለሁ ስለዚህ የሚሰማኝን በግልፅነት መጠየቅ እችላለሁ"

"ኧረ አትጨናነቅ ግጣ የለውም"

"እንደ አስተማሪነትህ ከተማሪ ጋር ወሲብ ማድረግ እንዲሁም ተማሪህን በወሲብ ጉዳይ ማሠማራት ከሞራል አንፃር ተገቢ ነው?"

"እህ... ሞራል ሀብታሞች ደሀን እንደ ፈለጉ ለመቆጣጠር የፈጠሩት ቀመር ነው እንጂ ሞራል የሚባል ነገር እኔ አላምንም! ሀጢያት ነው ብትለኝ ራሱ ሀጢያትም የሚባል የለም!! አንተ በሀጢያት ታምናለህ?"

"አዎና"

"እንግዳውስ ሀጢያት ስትሰራ ትንሹን ሳይሆን ትልቅ ነው የምትለውን ሀጢያት ስራ!"

መሳይ ቁምላቸው ለምንም ነገር ግድ የለውም። ሀይማኖት ፣ ሞራል፣ ሥነምግባር ወዘተ ለመሳይ የልጅ ጨዋታ ናቸው። ሀብታሞች ደሀን ለማሰር የፈጠሩት ነው ይላል። ስለ ምንም ነገር ግድ የለውም... ይሀን ባወራን በሳምንቱ ዕለተ ቅዳሜ ዋው! እጅግ በጣም የምታምር ትንሽዬ ተማሪ ይዞ ከች አለ፤ ሠላምታ በርቀት ሰጠኝ ... ከአንድ አርባ ደቂቃ በኋላ ከመሳይ ቤት ውስጥ የሴት ጩኸት ተሰማ... የዚያች ውብ ትንሽዬ ልጅ ድንግልና እንደ በረረች ወዲያው ገባኝ... ይህ ሲገርመኝ በነጋታው እሁድ ከጠዋቱ 4:20ደቂቃ ገደማ ከቤት ልወጣ ስል አንዲት ጠይም ፈረንጅ የመሰለች ትንሽዬ ልጅ ይዞ ገባ... ነገሩ ገርሞኝ ቁጠሮዬን ሰረዝኩና ቤት ተመልሼ ቁጭ አልኩ። ከግማሽ ሰዓት በኋላ ከመሳይ ቤት ውስጥ ጩኸት ተሰማ... የልጅቷ ድንግል እንደ ጠፋች ለራሴ ሹክ ብዬ አልኩኝ... ይህ እየተደጋገመ ሲመጣ ግን ይሰቀጥጠኝ ጀመረ። መሳይን ከቤቱ በዘዴ ላባረው? አላባረው? እያልኩ ከራሴ ጋር ውዝግብ ገባሁ... ይህ በሆነ በሳምንቱ መሳይ ጤነኛ መሆኑን የተጠራጠርኩበት አጋጣሚ ተፈጠረ፤ እሁድ ጠዋት ውጪውን ከዘበኛዬ ጋር እያፀዳን መሳይ ኩርሲ የምትባለው ወንበር ላይ ውጪ ተቀምጦ ሞባይሉን እየነረነረ ነበር። ድንገት በሣቅ ይንከተከት ገባ... እጅግ ከጣሪያ በላይ የሳቀውን ነገር ለመስማት፣ በዚያ ላይ የደራሲነት እና የጠያቂነት ባህሪ ስላለችብኝ ጠጋ አልኩት። ከዚያ "ምን ተገኘ?" አልኩት።

"ኢንተርኔት ላይ አስገራሚ ዜናዎች እያነበብኩ ነው፤ ላንብብልህ አልያስ ራስህ ታነበዋለህ?"

"ላንብበው" አልኩና ሞባይሉን ተቀበልኩት፡፡ ሞባይሉ በጣም ትልቅ እና ውድ ዋጋ የሚያወጣ ነው፤ ይሄኔ እንደ ሚስኪን ድንግልናዋን የበጠሳት ሀብታም ተማሪው በስጦታ መልክ ሰጥታው ይሆናል... ዜናውን ሳነበው በቆምኩበት ደርቄ ልቀር ትንሽ ነበር የቀረኝ፡፡ ዜናው ወይም አስገራሚ ታሪክ ተብሎ ኢንተርኔት ላይ የተለቀቀው በኮሎምቢያ የሚገኝ አንድ የናጠጠ ሀብታም ለመንደሩ ሰዎች የእራት ግብዣ አዘጋጅቶ በመሀከል መድረክ ላይ በመውጣት "አሁን 100,000 ሺ ዶላር ሽልማት የምሰጥበት ሰዓት ነው! ከእናንተ መሀከል ሽልማቱን የምሰጠው ለአንድ አባት እና ልጅ ይሆናል፤ ስለዚህ ከእናንተ መሀከል ማን ነው ከራሱ ልጅ ጋር እዚህ መድረክ ላይ ወሲብ የሚያደርገው?" ሲል ወዲያው አንድ አባት እና ልጁ መድረክ ላይ ወጡ፡፡ ሀብታሙ መድረክ ላይ የቀረቡት የ48 ዓመት ሰውና 19 ዓመት ሴት ልጅ እውነተኛ መሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ ወሲብ አስደርጎ 100,000 ዶላሩን በደስታ ሰጣቸው... የሚል ከማንኛውም ባህል ፣ እምነት፣ ሀይማኖት ውጪ የሆነ ዜና ነው፤ እናም ከት ብሎ ያሳቀው ይህ ዜና መሆኑን ስገነዘብ ስለ እውነት ከልቤ ነው የደነገጥኩት... ወዲያው ነው አብድ ይሆን እንዴ ስል የተጠራጠርኩት፡፡

"ይህ አስተማሪ እኮ ልጆቹን ጨረሳቸው" አለኝ ራሞስ ከገባሁበት ሀሳብ እየመለሰኝ፡፡ እስከ ዛሬ አስቢ የማላቀውን ወዲያው አሰብኩኝ፡፡ በትኩረት ራሞስን እያየሁት

"ድንገት እኮ ይዞ ከሚመጣቸው ትንሽዬ ሴት ተማሪዎቹ አንዷ ብትሞት እኛም ተጠያቂ ነን! ስለዚህ መሳይን መምከር ወይስ ሌላ ቤት እንዲከራይ መንገር የተሻለ ነው?"

"እኔ ደብልዋ የተሻለ ሀሳብ አለኝ"

"ምን?"

"ለመፅሐፍህ ገፀባህሪያት አትፈልገውም? አንተ እኮ ደራሲ ለመሆን እየሞከርክ ነው! ይሆን ሰው በትኩረት መከታተል አለብህ! የደራሲ ስሜት ስስ ነው፤ ደራሲ ለስሜት ቅርብ ነው! ደራሲ ለነገሮች ሁሉ ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ነው! ነገሮችን በትኩረት ከማራና ቀኝ የሚመለከት ነው!! ለምንድን ነው ግድ የለሽ የሆነው? ለምንድንነው አስተማሪ ሆኖ ሞራል ያጣው? ብለህ ይሆን ሰው ማጥናት አለብህ ፤ ምክንያቱም ከእያንዳንዱ ሰው መልካምነት ሆነ መረን ለቀቅነት

በሰተጀርባ በእርግጠኝነት መነሻ ምክንያት አለው፤ የዓለማችን ጨካኝ ሂትለር በእርግጠኝነት ጨካኝ ሆኖ አልተወለደም፤ ጭካኔን በእርግጠኝነት የተማረው ከመሬት ላይ ነው፤ በህይወቱ ያጋጠሙት ሰዎች ናቸው ወደ ጭካኔ እንዲገባ ያደረጉት! ስለዚህ ከዚህ አስተማሪ ምራል አለመኖር እንደነገርከኝ በአባትና ልጅ ወሲብ የሚደሰት አዕምሮ ያለው ከሆነ የሆነ የሳላ ብሎን አለው ማለት ነው፤ ስለዚህ ይህን ወጣት ከዚህ ቤት ሳታባረው ልጅ ይዞ እንዳይመጣ በዘዴ ገዘው፤ ግን ደራሲ መሆን የምትፈልግ ከሆነ ከማንም ይበልጥ ለነገሮች ትኩረት ሰጥተህ መከታተል አለብህ፤ እስቲ ስለዚህ አስተማሪ የት እንደሚያስተምር በዘዴ ጠይቀህ ትብቱ ሄደህ ምን አይነት ሰው እንደሆነ ለማጣራት ጣር! ደራሲ ለመሆን የምትፈልግ ከሆነ መረጃ ለማግኘት ሰላይም መሆን ይኖርብሃል ! ደራሲ ተጠራጣሪ መሆን አለበት! ዝም ብለህ ማመን የለብህም! ውሸቱን ቢሆንስ አስተማሪ ነኝ የሚለው? እስቲ እዚህ ቤት ውስጥ ያከራዩኋቸውን ተከራዮች ሰልላቸው … ምናልባት እኮ በስለላህ ሂደት ለድርሰትህ መነሻ ሀሳብ ታገኝ ይሆናል!!"

ይህን ሀሳብ ከራሞስ ጋር ባወራን ምሽት ለብቻዬ ተቀምጬ ቤት ያከራየኋቸውን አራት ተከራዮች ለመሰለል የሚሆን የአንድ ወር እቅድ አወጣሁ፤ በዚያውም እጅግ በርካታ ያበበኳቸው የእንጋፋው ተርጓሚ የማም ወድነህ የስለላ መፅሐፍት እንደሚሰሩ ለማረጋገጥ እድል አገኘሁ… በዓለም ላይ እንደ ስለላ ምን የሚያረካ ነገር አለና?

pdf by @shuktus_books

# 3

# ዘኪዮስ በርናባስ

ዕለተ ቅዳሜ፡፡ ግንቦት አንድ፡፡

እንደ ባንክ ቤት ስራ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ ስራ የለም፤እናም በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው የምሰራው፡፡ በርካታ የባንክ ቤቱ ሰራተኞች ገንዘብ ሳያስቡት እየጠፋባቸው ለእስር ተዳርገዋል፡፡ በእኔ ላይ እስከዛሬ የደረሰ ነገር የለም፡፡ ተመስገን ነው፡፡ እውነቱን ለመናገር በሥራዬ ላይ ጠንቃቃ ነገርም ነኝ፡፡

... ብቻ ህይወት አሪፍ ነች... ከደሊላ ጋር ይበልጥ ቅርበታችን እየጨመረ ነው፤ እኔም ከደሊላ ጋር ባለኝ ግንኙነት በተለይ በምናወራው ነገር ይበልጥ እየተደሰትኩ ነው፡፡ የዶክተር ልጅ የሆነችው ደሊላ ዛሬ ከፉ አጋጣሚ ህይወቷን አበላሸው እንጂ ብሩህ አዕምሮ ያላት ልጅ ነች... በጣም ደስ ያለኝ ፀባዩዋ ያጋጠማትን ችግር ለመፍታት ጥረት ታደርጋለች እንጂ ስታማርር አላጋጠመኝም... ዶ/ር አባቷ ጠንካራ አስተሳሰብ እና ከችግር ጋር እየተጋፈጠች እንድትኖር በሚገባ እየኮተኮቱ እንዳሳደጓት ያስታውቃል፤ በተለይ በሥነ ስርዓት እንዳደገች የምታደርጋቸው ነገሮች ያሳብቃሉ...

ግንቦት አንድ ቅዳሜ ነበር፡፡ እስከ ስድስት ሰዓት ባንክ ቤት ከሰራሁ በኋላ ወደ ቤት አመራሁ፡፡ ቤት መምጣቴን ያወቀችው ደሊላ ድንገት መጣች፡፡

እቅፉ ሳመችኝ:: እቤት የጠረኗ ማማር...!!

"እንዴ በዕለተ ቅዳሜ ስራ እንዴት አልገባሽም? አልኳት:: ማሳጅ ቤት በብዛት ከፍተኛ ስራ አለ ያለችኝ አርብ፣ ቅዳሜ እና እሁድ ስለነበር ተገርሜ::

"ሀይለኛ ቁርጠት ሲያመኝ ቀርቼ ነው"

"እና እንበውሃ በማር እና ሎሚ ለቁርጠት ፍቱን መድኃኒት ነው ይላሉ፣ ካልሆነ ሆስፒታል ነይ እንሂድ"

"ትንሽ ልየውና ካልሆነ እንሄዳለን... ከሰዓት ፕሮግራም አለህ?"

አንድ ቀጠሮ አለችኝ በፍጥነት እመለሳለሁ፣ በጣም ካመመሽ ደውይልኝ ፕሮግራሙን ትቼው እመጣለሁ"

"ኧረ ግድ የለም አትቸገር፣ በቃ ስትመለስ ከባሰብኝ ሆስፒታል ትወስደኛለህ መልካም ጊዜ" ብላኝ ከቤቴ ወጣች:: የነበረኝን ቀጠሮ ልሰርዘው አሰብኩና ከራሴ ጋር ትንሽ ተመካክሬ ቶሎ ሄጄ በመምጣቱ ወሰንኩ፣ መስሪያ ቤት ለብሼ የምሄድበትን አልባሳት ቀይሬ ከቤት ወጣሁ:: ታክሲ በመያዝ በቀጥታ ወደ ስላሴ አንድ አመራሁ:: ወደ ተከራይ ተሰላይ ዘኪዮስ በርናባስ::

ዘኪዮስ በርናባስ በጣም እርጋታ የተላበሰ ወጣት ነው:: ብዙ ጊዜ ማታ ማታ እኔ ቤት እየመጣ ተጫውተናል:: ቤተሰቦቹ ሀብታም ቢሆኑም ከቤተሰቦቹ ጋር በሀይማኖት ግጭት የተነሳ እንደወጣ ነግሮኛል:: ይህ ነገር ገርሞኝ

"እንዴት?" ስለው::

"አባቴ እና እናቴ በጣም አክራሪ ኦርቶዶክሶች ናቸው:: በከፍተኛ ሃይማኖታዊ ስርዓት ነው ያደኩት:: ቤት ውስጥ ፊልም ማየት፣ ልቦለድ ማንበብ፣ መፅሐፍ ማንበብ ፣ ጋዜጣ ማንበብ... ወዘተ. አይፈቀድልንም :: የሚፈቀድልን መዝሙር እንድንሰማ፣ መፅሐፍ ቅዱስ እንድናነብ፣ ቤተክርስቲያን እንድንሄድ... ብቻ ነው:: እናም ከልጅነቴ ጀምሮ መፅሐፍ ቅዱስ በማንበቤ የተነሳ በተለይ በኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ ተመሰጥኩ፤እናም ይበልጥ ስለ ኢየሱስ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ጀመርኩ:: በመሀከል ት/ቤት ከጴንጤዎች ጋር ተዋወኩኝ::

እየተደበኩ ከእነርሱ ጋር ችርች መሄድ ጀመርኩኝ፤ በዚያው ጴንጤ ሆንኩኝ፤ ታዲያ አንድ ቀን ረስቼው "ኢሉቫዳይ" የሚል መጽሔት ቤት ይገፍ በመግባት እያነበብኩ አባቴ መጣ:: ገና እንዳየኝ አፈጠጠብኝ:: ከዚያ እጄ ላይ የነበረውን መፅሔት ተቀበለኝ

"አንተ ይሄ መፅሔት የእነዚያ የጴንጤዎች አይደለም እንዴ?"

"አዎ"

"እና ለምን አመጣኸው?"

"ላነበው"

"የሚወራውን አላምንም ብዩ ነበር፤ለካ! ወሬው እውነት ነው ማለት ነዋ? መናፍቃን ቤተክርስቲያን ስትገባ እንደታየህ ተነግሮኝ ነበር"

ዝም አልኩት::

"ተናገር እንጂ"

"ሄጃለሁ"

"ምናባክ ልታደርግ?"

ዝም አልኩት:: በቃ በዚህ የተነሳ ዘወትር ከአባቴ ጋር ንትርክ፤ ጭቅጭቅ፤ ስድብ፤ ተጀመረ... ይባስ ብሎ ከቤት እንድወጣ ነገረኝ:: አባቴ ከዘመኑ ጋር አልዘመነም፤ የአባቴ አስተሳሰብ ባህላዊ ነው፤ በዚህ በአባቴ አመለካከት አዝናለሁ እንጂ አልጠላውም:: ጥላቻ ውስጥህ ካለ እግዚአብሔርን አምናለሁ ማለት ምፀት ይሆናል:: እግዚአብሔርን ስታምን በፍቅር ማመን ጀመርክ ማለት ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነው:: በፍቅር ማመን ከጀመርክ ደግሞ የመጀመሪያ ህግ ጠላትህን መውደድ ነው:: አንድ ሰው ካንተ የተለየ ሀይማኖት ስላለው እና አንተ የምታምነውን ካላመነ የምታርቀው አልያም የምትጠላው ከሆነ የአንተ እግዚአብሔርን አምናለሁ ስላቅ ይሆናል፤ምክንያቱም በእግዚአብሔር የምታምን ከሆነ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን የሰው ልጆች ሁሉ በፍቅር መቅረብ አለብህ:: ለምሳሌ አንተ የምታምነው ሀይማኖት ልክ ነው ብለህ የምታስብ ከሆነ ይህን እምነትህ ለሌላው ይጠቅማል ካልክ በጥላቻ ሳይሆን በፍቅር ቀርበህ መስበክ አለብህ ፡፤ የሀይማኖት እና የእምነት ሰው ስትሆን ምላስህ የተቆጠበ እና ከአንደበትህ መልካም ነገር ብቻ የሚፈልቅ መሆን አለበት፤ አለበለዚያ አንተ ያመንከውን የማያምኑትን ሰዎች የምታጥላላ እና ጥላቻ ውስጥህ ካለ የአንተ እምነት ውሸት ነው:: እዚህ ጋር ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ብዙ ነገር የሰራውን የኢትዮጵያ ንጉስ

የነበረውን ንጉስ ዘርአያእቆብ ንግግርን ማስታወስ ጥሩ ነው"

"ዘርአያእቆብ ከሀይማኖት መለያየት ጋር በተያያዘ ቃል በቃል ያለው

"እስላሞች፣ አይሁዶችና ክርስትያኖች ሁሉ በየፊናቸው የእኔ ሃይማኖት ጥሩ ነው የእናንተ ልክ አይደለም ይላሉ፡፡ ማነው ትክክለኛው ፈራጅ? ሰዎች የየራሳቸውን ስለሚያምኑ ፈራጅ ሲሆኑ አይችሉም፡፡ እኔ የራሴ እምነት ልክ ሆኖ እንደሚሰማኝ ሁሉ ሌላውም የራሱ ሃይማኖት የበለጠ ልክ ይመስለዋል! እና ማነው ፈራጅ?"

ይላል፡፡ ብቻ ከአባቴ ጋር በሀሳብ መግባባት ሲያቅተኝ ከቤት ወጥቼ ቤት ተከራየሁ፡፡ የመጀመሪያ ዓመት የወንደላጤነት ኑሮ ተራራ ነበር የሆነብኝ፤ ግን የጌታ ፍቃድ ሆኖ የማያልፍ የለም አለፈ፡፡ አንዳንዴ ህይወታችንን ጌታ እንዲመራት ከፈቀድን ተራራው ሜዳ ይሆንልናል፤ የሚገርምህ ከቤት ከወጣሁ ሁለት ዓመት በኋላ አባቴ ቤት ተመለስ፤ የፈለከውን ማመን ትችላለህ ብሎኝ ነበር፤ ግን የወንደላጤነት ሕይወትን ስለለመድኩት በወንደላጤነት ህይወት ቀጠልኩ፡፡ አሁን ከቤተሰቦቼ ጋር ሰላም ነን፡፡ እኔ የመጀመሪያ ዲግሪዬን የወሰድኩት በቲዎሎጂ ትምህርት ነው፡፡ አሁን ስታየኝ የተረጋጋሁ ሰው ሆንኩ እንጂ በፊት መፅሐፍ ቅዱስም አያነበብኩ፤ ስለ እግዚአብሔር ህግጋት እያወኩ ራሱ በጣም የወጣልኝ ዱሪዬ ነበርኩኝ፡፡ መጠጥ እየተደበኩ እጠጣ ነበር፣ በተለይ ለሶስት ዓመት ሲጋራ እጨስ ነበር፣ ጫት ቤት፣ ሺሻ ቤት ፣ ሴተኛ አዳሪ ቤት.. እሄድ ነበር፤ በብዙ ሀጢያት ተከብቤ ነበር፤ ግን ህይወቴን ከጨለማ ወደ ብርሃን ያመጣኝ ጌታ ስለሆነ አሁን ሙሉ ጊዜዬን ለጌታ ሰጥቼ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ በመሆን እየሰራሁ እገኛለሁ"

በለርጋታ መናገር የሚወደው ዘኪዮስ እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ባለታሪኩ ዘኪዮስ አጭር አይደለም፤ ረጅም ነው፡፡ ከምንም በላይ በጣም የሚያምር ድምፅ አለው፡፡ ያለ ጨርቅ ስራ 'ኧዝ' ምናምን ሲያደርግ እስከዛሬ አላየሁትም... አንድም ቀን እንኳ ቤት ይዞ ሲመጣ አላየሁትም... በብዛት የማየው መዝሙር ሲሰማ፣ ሲፀልይ፣ መፅሐፍ ቅዱስ ሲያነብ ነው... ሁሌ

ፈገግታ ከፊቱ አይጠፋም፣ ደስተኛ ነው፡፡ እኔንም ሆነ ሌሎች ተከራዮችን ከሰላምታ እና ጨዋታ ባሻገር "እነሆ ዘመን ከፍቷል ኢየሱስ እየመጣ ነው ኢየሱስን የግል አዳኛችሁ.." ምናምን እያለ ሰብኮን አያውቅም... ብቻ የዘኪዮስ እርጋታ በጣም ይመቸኛል... ስለ እውነት ሴት ብሆን ፍቅር ከዘኪዮስ ይይዘኝ ነበር፡፡

ዘኪዮስ ስለ መፅሐፍ ቅዱስ ፣ ስለፍልስፍና ... በተለይ ከእግዚአብሔር ማንነት ጋር በተያያዘ እግዚአብሔር ከየት መጣ? ሀይማኖት ከየት መጣ? ለሚሉት እጅግ ወሳኝ ጥያቄዎች ስለሚያብራሩት ከ1866-1943 ለኖሩት ኢንግሊዛዊ የሰው ዘር ጥናት ባለሙያ ዲ አር ማሬት እኒሚዝም ንድፈ ሀሳብ... ከ 1854-1941 የኖረው ስኮትላንዳዊው የዘልማድና አፈታሪክ አጥኚ ጀምስ ፍሬዘር The Golden Bough የተባለው አወዛጋቢ መፅሐፍ፣ ስለገበኛው ከ1856 -1939 የኖረው አስትሪያዊው የስነልቦና ሊቅ ሲግመን ፍሮይድ Totem and Taboo መፅሐፍ እንዲሁም አሁን በመላው አለም እንዴት የሰው ልጅ በማይታይ ፈጣሪ ሊያምን እንደቻለ ስለሚያስረዱት ሶስት ወሳኝ አንኳር ንድፈ ሀሳቦች Subjective theory (ግለኛ ንድፈ ሀሳብ ቅመራ)፣ Evolution theory (የዝግመተ ለውጥ ሀሳብ ቅመራ) እንዲሁም Original monotheism theory (የአሁዱ አምላክ ንድፈ ሀሳብ) በሚገባ ደስ በሚል የማስረዳት ችሎታው አስረዳኝ... ስለ እግዚአብሔርን ማን ፈጠረው ጥያቄ እንዲህ ነበር ያለኝ "ብዙዎች ስለምድር አፈጣጠር ስትነግራቸውና እግዚአብሔር ራሱ ፈጣሪ ስለሆነ ፈጣሪ እያስፈልገውም ስትላቸው የሚያቀርቡት ጥያቄ If the universe needs a cause, then why doesn't God need a cause? And if God doesn't need a cause , why should the universe need a cause?" ይላሉ እንተም ይህ ጥያቄ ካለህ ይቺ በ Jonathan sarfati የተፃፈች 75 ገፅ ያላት "If God created the universe, then who created God?" የምትል መፅሐፍ ትመልስልሀች፣ በጥንቃቄ አንብባት በማለት እነስ ያለችውን መፅሐፍ በስጦታ መልክ አበረከተልኝ..

ብቻ ብዙ መረጃ ሰጥቶኛል፣ በተለይ ስለ ኢየሱስ ስጠይቀው ቃል በቃል የመለሰልኝ ይህን ነበር፡-

"ታዲያ ኢየሱስ በአዳምና ሄዋን የመጣውን የሰው ልጆችን ሀጢያት ለመስረይ እና

ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ከዮሴፍ ፍትረኛ ድንግል ማርያም በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ከተወለደ ለምንድንነው በወቅቱ የነበሩት እስራኤላዊያን በተለይ አይሁዶች ኢየሱስን ያልተቀበሉት? በተለይ አስተድሞ ስለ ኢየሱስ መምጣት ጳውሎስ

"እኔ በውሃ አጠመቅኋችሁ እርሱ ግን
በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል"

"እያለ ይሰብካቸው ነበር" ስለው

"ትክክል ነህ! ነገሩን ቀለል ለማድረግ ኢየሱስ በድንግል ማርያም አማካኝነት በመንፈስ ይወለድ እንጂ ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸውም በፊት ከአባቱ ጋር አብረው የነበሩ ናቸው፡፡ ኢየሱስ ድንገት የመጣ ክስተት አይደለም፡፡ ይህን ነገር ይበልጥ ለመረዳት የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ

"በመጀመሪያ ቃል ነበር፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፤
ቃልም እግዚአብሔር ነበር"

ከዚያ ቁጥር 14 ላይ "ቃል ሥጋ ሆነ" የሚለው ኢየሱስ ድንገት ክስተት አለመሆኑን ይበልጥ ያብራራል! ለማገናኘውም ወደ ነጥቡ ልመለስልህና እየሀ ወደ ኋላ ተመልሰን የእስራኤላዊያንን ታሪክ ስንመረምር በተለይ የአይሁዶችን የታሪክ ድርሳናት በሚገባ እንደሚያብራሩት በ63 ዓ.ዓ አካባቢ የሮማው ገዥ ኢየሩሳሌምን በቁጥጥሩ ስር ያስገባ ሲሆን በዚህ የተነሳ እስራኤላዊያንም ለተከታታይ አመታት በከባድ ጦርነት፣ በግጭትና በስደት ለመኖር ተገደው ነበር እናም ጊዜው ለአይሁዶች ወሳኝ እና እጅግ ፈታኝ ወቅት ነበር፤ በተለይ እስራኤላዊያን በግሪኮች የጥበብ ተፅዕኖና በሮማዎች ባርነት መሀከል የሚራወጡ ህዝቦች ነበሩ እናም ከሮማ ግዛት በተደቀነባቸው ከቅም በላይ በሆነባቸው ፈተናና የኑሮ ስቃይ የተነሳ የሆነ "መሲህ" ይጠብቁ ነበር "አንድ መሲህ ይመጣል! ይህ መሲህ አረማመዱ የሚማርክ፣ በእርጋታ የሚናገር፣ ተዓምራትን የሚሰራ፤ እኛንም የጠፉ መሬቶችን አድርገውን ከባርነት ነፃ የሚያወጣን ቆራጥ ጦረኛ ይሆናል" የሚል ፅኑ እምነት ነበራቸው፡፡ ያው እንደተባለው ኢየሱስ በአስገራሚ ሁኔታ በከብት በረት ተወለደ፤ በጥበብ አደገ... ከዚያ ለዘመን ስብከት ሲደርስ በጣፋጭ አንደበቱ

መስበክ ጀመረ!!

"እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ:: እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ (ዮሐ.18፡34-35)

ማለት ጀመረ፤ አስገራሚ ተዓምራትን መስራት ጀመረ፣ በሽተኛ ማዳን፣ ማየት የማይችልን ዓይኑን መግለጥ፣ የሞተን ማስነሳት!

... በዚህን ወቅት አይሁዶች ወደ ኢየሱስ በመምጣት "ጠላቶቻችንን ትወጋልን ዘንድ ና አንተ ልዩ ብቃት ያለህ ነህና የጦራችን መሪ እናድርግህ" አሉት:: ትክክለኛው መሲህ እርሱ እንደሆነ በማመን:: ኢየሱስ ግን

" ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ! የሚረግሙአችሁንም መርቁ! ስለሚበድሉአችሁም ፀልዩ:: ጉንጭህን ለሚመታህ ደግሞ ሁለተኛውን ስጠው:: መጎናፀፊያህንም ለሚወስድ እጀ ጠባብህን ደግሞ አትከልክለው:: ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ! ገንዘብህንም የሚወስድ እንዲመልስ አትጠይቃው! ሰዎችም ሊያደርጉላችሁ እንደምትወዱ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው (ሉቃ. 6፡27-31)

አላቸው:: እየሀ ኢየሱስ የሚላቸው ሀጢያት ስርቃችኋል እኔ ግን ከአብ ጋር ላስታርቃችሁ ራሱ አብ ላከኝ ሲል አይሁዶች ደግሞ የኢየሱስን ብቃት በማየት የጦር መሪያቸው ሆኖ ልክ ሰምሶን በአህያ ውርንጭላ ጭንቅላት አጅግ በርካታ ጠላቶቹን እንደፈጀ ሁሉ ኢየሱስም

የአይሁዶች ጠላት የሆኑትን ሮማውያንን እንዲ ጨርስላቸው ተመኙ፤ ኢየሱስ ደግሞ በተቃራኒው ጠላቶቻችሁን ውደዱ ይላቸዋል... የቄሳርን ለቄሳር ይላቸዋል... እኔ ህይወት እና መንገድ ነኝ ይላቸዋል... ስለ መንግስተ ሰማያት ያወራላቸዋል... ባጠቃላይ ኢየሱስ የመጣበት ተልዕኮ እና የአይሁዶች ተልዕኮ የተለያዩ ስለሆነ ሁኔታቸው አሬባናዊ በመሆኑ አይሁዶች ኢየሱስን ጠሉት፤ ከዚያም በጠላትነት ያሳድዱት ገቡ..."

ዘኪዮስ ከሀይማኖት ጋር በተያያዘ እጅግ በርካታ ነገሮችን ነው ያሳወቀኝ፡፡ እጅግ ብዙ እንዳነበበ ያሳብቅበት ነበር፤ ለነገሩ የመጀመሪያውን ዲግሪ የያዘው በቲዎሎጂ አይደለም እንዴ??... ስለ ሂንዱይዝም፣ ቡዲሂዝም፣ ኮንፊሺያኒዝም፣ ሺንቶይዝም፣ ይሁዲ፣ ክርስትና፣ ኢስላም በተለይ ከእስልምና ጋር በተያያዘ ስለ ነብዩ ሙሀመድ፣ የነብዩ ሙሀመድ ህልፈት እና የሱኒና ሺዓ ክፍፍል ፤ የቁርዓን ከአምላክ (አላህ) መውረድ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ (ኢሳ) ቦታ በኢስላም፤ የመርየም (ድንግል ማርያም ሚና በኢስላም በሚገባ አስረድቶኛል ፤ በተለይ ስለ ነብዩ ሙሀመድ የሚከተለውን ነበር ያስረዳኝ፡-

"ነብዩ ሙሀመድ የተወለዱት መካ ሱኡድ አረቢያ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ570 ዓ.ም ከእናታቸው አሚና እና ከአባታቸው አብዱላህ ነው፡፡ እንግዲህ ነብዩ ከተወለዱበት ዘመን ቀደም ያሉ የመካ ህዝቦች አራት ማዕዘን ቅርፅ ባለውና አሁን ሙስሊሞች ትልቅ ክብር በሚሰጡት "ካዕባ" በሚባለው ቤተመቅደስ 360 ጣኦታት በማስቀመጥና ለእያንዳንዱ ጣኦት አንድ ቀን በመስየም ሚልኪ ያደርጉባቸው ነበር፡፡ ታሪክ እንደሚያስረዳው ይህ ባለ አራት ማዕዘኑ ቤት ወይም "ካዕባ" የነብያት አባት በሆኑት ነብዩ ኢብራሂም (አብርሃም እና በልጁ እስማኤል) እንደተገነባ በእስላሞች ይታመናል... እንግዲህ ነብዩ ሙሀመድ እያደጉ ሲመጡ በዚያን ወቅት ይዘወተሩ በነበሩ ሀይማኖታዊ ስርዓቶችና ምልኪዎች ፋይዳ ከፍተኛ ጥያቄ ጫሪባቸው፡፡ ከሁሉም ይበልጥ የነብዩ ሙሀመድ ጎሳ አባላት በነበሩ ቁረይሾችና በተቀረው የዓረቡ ዓለም ይዘወተሩ የነበሩ ኢሞራላዊ ዘማናዊ ድርጊቶች ለምሳሌ ቤት ልጆቻቸውን ከእነ ነፍሳቸው መቅበር፤ ባሎች በሚስቶቻቸው እየተወራረዱ ቁማር መጫወት፤ እጅግ መጠን ያለፈ ስካር፤ በቃላት ሊገለፅ የማይችል የባርነት አያያዝ... በመሳሰሉት አሲቃቂ የሥነ ምግባር ችግሮችን ሲመለከቱ ነብዩ ሙሀመድ እጅግ ይረብሻቸው ጀመር እናም በዚህ ምክንያት ከአካባቢያቸው ራቅ ብሎ በሚገኘው አል- ኑር ኮረብታ "ጋሩ- ሂራ" በሚባል ዋሻ እየሄዱ መሠረታዊ የሚባሉ የህይወት ጥያቄዎችን እያነሱ በጥልቅ ተመስጦ (Meditation) ውስጥ ይዘፈቁ

ነበር፤ ከዚያ ልክ 40 ዓመት ሲሞላቸው በአምላክ ዘንድ ለነብይነት በመልዓኩ ጂብሪል (ገብርኤል) አመካይነት ጥሪ ቀረበላቸው..."

ብዙ ነገር ነው ዘኪዮስ ያጫወተኝ በተለይ በክርስትና እጅግ ወሳኝ ስለሚባለው የንጉሷ ቆስጠንጢኖስና የኒቂያ ጉባኤ በርካታ ነገሮች ነገረኝ... ለዘኪዮስ በመጨረሻ ጥያቄ የሰነዘርኩለት የሚከተለውን ነበር።

"ታዲያ ፕሮቴስታንት ወይም ጴንጤ እንዴት ነው ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የተገነጠለችው?"

"ጥያቄህ ጥሩ ነው፤ ግን ፕሮቴስታንት ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሳይሆን የተገነጠለችው ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ነው። ሲጀመር ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት በመላው አለም ላይ ካለው ህዝብ መሀከል ወደ 2.2 ቢሊዮን ህዝብ የክርስትና እምነት ተከታይ ነው፤ ክርስትና ሲባል ካቶሊክ ፣ ፕሮቴስታንት፣ ኦርቶዶክስ፣ ኢንግሊካንና ሌሎችም ይጠቃለሉ። ሁሉም በክርስትና የተጠቃለሉት በእግዚአብሔር እና በልጁ ክርስቶስ ያምናሉ ግን እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ልዩነት እና የትኩረት አቅጣጫ አላቸው። ይህን ማወቅ ፍላጎትህ ከሆነ ሌላ ጊዜ በሰፊት እንወያያለን። አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድንነው? ልዩነታቸው ምንድንነው? የትኛው ነው በተሻለ መልኩ ወደ ሀቅነት የሚቀርበው? እንዴትስ ልዩነታቸውን አጥብበው አንድ ሊሆኑ እስከ ዛሬ አልቻሉም? የሚሉትን ወሳኝ ጥያቄዎች ሌላ ጊዜ በሰፋት እንወያያለን ለጠየከኝ ጥያቄ ያው እንዳልኩህ ፕሮቴስታንት የተገነጠለችው ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው፤ ለዚህ ደግሞ ትልቁን ሚና የተጫወተው ከ1483-1546 ዓ.ም የኖረው የአውግስቲያኑ መነኩሴ ማርቲን ሉተር ነበር።"

"ማርቲን ሉተር በሥነ መለኮት የዶክትሬት ዲግሪ የነበረው እና በዊንበርግ ዩኒቨርሲቲ የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያስተምር የነበረ መልካም ንግግር ማድረግ የሚችል የሰውጥ ሰው ነበር፤ እንግዲህ ዋነኛ ጥያቄው የሉተር ጥያቄ እና መነሻ ሀሳብ ምን ነበር? የሚል ሲሆን ዝርዝር ታሪኩን ይበልጥ ለማወቅ ከፈለክ በእንግሊዝኛ የተፃፈ The story of the Reformation የሚል አሪፍ መፅሐፍ አለ አውርደህና አንብበህ መመለስ ትችላለህ እናም ባጭሩ ለማስረዳት የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በተለይ በ15ተኛው ክፍለ ዘመን እጅግ ሀብታም ሆና ነበር። ዋነኛ ትኩረቷን የምታደርገው ለምዕመናን ስለ እግዚአብሔር መስበክ ሳይሆን ንብረት እና ገንዘብ ማከማቸት ላይ አድርጋ ነበር... ከምዕመናን ቁሶች እንጻልይላችሁ በማለት ገንዘብ

ይቀበሉ ገቡ፤ በተለይ ቤተክርስቲያን በከፍተኛ የገንዘብ ምዝበራ እና የሙስና ቅሌት ተዘፈቀች፤ ከምዕመናን በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ቁጥር 16 ላይ

' የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት'

ኢየሱስ ያለውን ረስተው እነሆ ይበልጥ ገንዘብ ለማግኘት ቄሶች

'የገነት መግቢያ ትኬት ይሸጣል ግዙ! ከሀጢያት መንፃት የሚቻለው ቄሶች በሚሰጡት መመሪያና ምዕመናን ለቄሶች በሚያደርጉት ኑዛዜ ነው'

በሚል ከፍተኛ ገንዘብ መሰብሰብ ጀመረች፡፡ በዚህ ሰዓት ነው እንግዲህ የቤተክርስቲያኗ መነኩሴ የነበረው ሉተር

'በጭራሽ አትመኑ! ከሀጢያት መንፃት የሚቻለው ቄሶች በሚሰጡት መመሪያና ምዕመናን በሚያደርጉት ኑዛዜ ሳይሆን በፅኑ የውስጥ እምነት ብቻ ነው'

የሚል ሀሳብ በመያዝ የራሱን ሀሳብ በማደራጀት ጥቅምት 31፣1517 ዓ.ም ጠዋት ላይ 95 ንድፈ ሀሳቦች በመያዝ ሳክሶኒ በሚገኘው የጀርመን ቤተክርስቲያን በር ላይ በመለጠፍ ተቃውሞውን ይፋ ያደረገው፤ ያው 'Protestant' ማለት ፍቺው ራሱ መቃወም ፤ በሌላ እይታ መመስከት ማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ከፍተኛ የሀሳብ ፍጭት ሲደረግ ቆይቶ ሊስማሙ ባለመቻላቸው በንግስት ኤልሳቤት አንደኛ (1558-1603) ከሉተር ሞት በኋላ ማለት ነው ሙሉ ለሙሉ ከካቶሊኮች ፕሮቴስታንቶች በመገንጠል ራሳቸውን ችለው ለመውጣት ችለዋል፤

ዋነኛው ጥያቄ ፕሮቴስታንት ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን የለዩት ጥና ጥና ምክንያቶች ምን ነበሩ ለሚል ጥያቄ ሶስት መሠረታዊ የአመለካከት ልዩነቶች ነበሩ፤ እነዚህ ነገሮች ሉተር ሲዘረዝራቸው

፩ኛ. ሉተር ከዘለቢያት የሚነፃው በሰው የውስጥ እምነት እንጂ ቄሶች በሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም በምዕመናን ንዛዜ አይደለም ይላል

2ኛ. ንስሀ (መዳን) የሚገኘው በእግዚአብሔር ፍቃድና ከብር እንጂ በቄሶች ወይም ጳጳሳት ስልጣን አይደለም ይላል።

3ኛ. ሁሉም የሀይማኖት መመሪያዎችና ቀኖናዎች መፅሐፍ ቅዱስን ብቻ የተንተራሱ እንጂ በጳጳሳት ጉባኤ ወይም በቤተክርስቲያን ምክር ቤት የሚረቀቁና የሚፀድቁ መሆን የለባቸውም ይላል፤ ባጠቃላይ መፅሐፍ ቅዱስን ብቻ መጠቀም ፣ በእምነት ብቻ መዳን እና ሁሉም አማኞች ደቀመዝሙራን ናቸው የሚል ሀሳብ ነበረው። ባጭሩ ይህን ይመስላል" ሲል አጫውቶኛል፤ በሌላ ጊዜም ስንጫወት በፕሮቴስታንት፣ ኦርቶዶክስ እና ካቶሊኮች መሀከል ስላለው የአመለካከት ልዩነት ነግሮኛል፤ አብዛኛው የልዩነታቸው መንስኤ ሶስቱ ነጥቦች ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው፤ በተለይ አዕምሮዬ ላይ ሲያንቃጭል የነበረውን ጥያቄ የመለሰልኝ ዘኪዮስ ነበር።

"በሀይማኖት የተነሳ ሰዎች ሲደባደቡ ብታይ ምን ይሰማሀል? ስለው

"ያጋጥማል። እኔም ብዙ ጊዜ የተገረምኩባቸው ገጠመኞች አሉ። በሀይማኖት የተነሳ እብድ ያለ ክርክር፣ ድብድብ ፣ ስድድብ፣ ጥላቻ፣ አይቻለሁ። በእርግጥ እውነቱን ለመናገር እኛ ኢትዮጵያዊያን የሀይማኖት አክራሪነት አለብን ለማለት በጭራሽ አያስደፍርም፤ እንዴ እኮ ሐረር፣ ድሬደዋ፣ ወሎ... ለስብከት ሄጄ የሚገርም ፍቅር አይቻለሁ ። እስላሙ ፣ ጴንጤው ፣ ኦርቶዶክሱ በፍቅር አብረው ይኖራሉ። በፍቅር አብረው ይመገባሉ። በሀይማኖት ልዩነት አንዳችም ፀብ አታይም። ሲጀመር ሰው መሆንህ ይበቃል እንጂ ማን ነህ? ሀይማኖትህ ምንድን ነው? ተብለህ አትጠየቅም፤ እየሀ ይህ ከፍተኛ የመብሰል ችሎታ እና የፍቅርን ፍሬ በሚገባ ማወቅ ነው። በሀይማኖት ውስጥ በዓለም ላይ ያለው ትልቅ ችግር ወይም ትልቁ ፈተና ግማሽ እውቀት የሚያመጣው ችግር ነው፤ እየሀ ስለ አንድ ነገር ግማሽ እውቀት ካለህ ከሁለት ሰዎች ጋር ሁልጊዜ ትጣላለህ። የመጀመሪያው ከራስህ ጋር ነው፤ ሁለተኛው ከሌላ ሰው ጋር ነው።

የዓለም ትልቁ ችግር መንስኤው በጥግሽ እውቀት የተሞሉ ሰዎች በየቦታው በመብዛታቸው የተነሳ ነው ! ከጥግሽ እውቀት ምንም አለማወቅ በጣም የተሻለ እውቀት ነው:: ሞኝ ዝም ቢል ጠቢብ ይሆናል ይባል የለም እንዴ? አንድ ጥሩ አባባል አስታወሰከኝ 'ዕውቀት ያለ ሀይማኖት ሰንካላ ነው፤ ሃይማኖትም ያለ ዕውቀት እውር ነው' ይባላል:: እውነት ነው::"

"አንድ የገጠመኝን እውነተኛ ነገር ልንገርህ አንድ ጊዜ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር መንገድ ላይ እየሄድን ባጠገባችን በርከት ያሉ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ቀኑ 21 የማርያም ቀን ስለ ነበር እየዘመሩ ያልፋሉ፤ ይህ ጓደኛዬ "ተመልከት እነዚህን የመሬ ሆግ የሚያከብሩ ከንቱዎች" ሲል ከወጣቶቹ አንደኛው በፍጥነት መጣ:: ምንም ሳይናገር በቦክስ መሬት ላይ አነጠፈው:: ይበልጥ ሊመታው ሲል "ወንድም በጣም ይቅርታ" በማለት ለምኜው ተው እንጂ ተጨማሪ የባሰ ነገር ሊመጣ ይችል ነበር:: እየህ አሁን እውነቱን ለመናገር የእኔ ጓደኛም ሆነ ጓደኛዬን የመታውም ልጅ ስህተት ናቸው::  ሁለቱም ግማሽ እውቀት ነው ያላቸው:: ሀይማኖተኛ ነኝ አያልክ ከአንደበትህ ፀያፍ ቃላት የሚወጣ ከሆነ፤ የምትሳደብ ከሆነ፤ የምታናንቅ ከሆነ፤ ለፀብ የምትጋበዝ ከሆነ የአንተ ሀይማኖተኝነት ግማሽ እውቀት ነው!! አንድ የምወደው አሪፍ አባባል አለ "አማኞች እንጂ እምነቶች ለአኩይ ተግባር ያቀነቀኑበት የታሪክ አጋጣሚ አልተፈጠረም" የምትል ናት! እውነት ነው:: ለምን የእኔን እምነት አልተከተለም ብለህ በሰው ምርጫ ላይ መጣብትም ሆነ መፍረድ አትችልም! መብትም አልተሰጠህም ፤ ግን ግማሽ እውቀት ካለህ የምታደርገው እነዚህን ነገሮች ነው:: ስለ እምነት እና ሀይማኖታቸው እንደ እኔ አመለካከት ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ፕሮቴስታንቶች፣ እስላሞች፣ ኦርቶዶክሶች ፤ ካቶሊኮች... ሙሉ እውቀት ያላቸው በጣም ትንሽ አማኞች ናቸው:: አብዛኛው ግማሽ እውቀት ያለው ይበዛል:: እውነቱን ለመናገር እኔ ከበርካታ የሙዝሊም ሆነ ኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮች ጋር አቀራረባለሁ:: በርከት ያሉ ጓደኞች አሉኝ:: አሪፍ አሪፍ አመለካከት አላቸው:: አንዳንዴ ስለ ሀይማኖት ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር በተለይ ስለ "እምነት" እንከራከራለን:: በሀሳብ መለያየት ያለ ነገር ነው:: ፍቅር የተሞላበት ክርክር እኮ ደስ ይላል:: መረጃ ትለዋወጣለህ፤ ግማሽ እውቀት ሲኖርህ ግን የምታወራውም ሆነ የምትከራከረው ስለ እምነት ሳይሆን ስለ "ሀይማኖት" ነው:: በእኔ እይታ ሀይማኖት ስለማያድን ስለ ሀይማኖት ብታወራልኝ ጆሮ ለመስማት አይሞላም በማለት አዳምጣለሁ እንጂ ሀሳብ አልሰጥህም::በጣም በርካታ ሰዎች ሀይማኖትህ ምንድንነው እያሉ ይጠይቁኛል "እኔ እምነት እንጂ ሀይማኖት

የለኝም ስላቸው ግር ይላቸዋል። መቼም ቢሆን እኔ አማኝ እንጂ ሀይማኖተኛ መሆንም ሆነ ማባለም አልሻም። አማኝ ስትሆን ደግሞ ዋና ነጥብህ ሆነ ትኩረትህ እውነትን እና እግዚአብሔርን መፈለግ ነው እንጂ ስለ ሀይማኖት አትጨነቅም እናም እንዳልከው የሚደባደቡትም ሆነ ለጥላቻ የሚጋበዙት ግማሽ እውቀት ያላቸው እና ከእምነት ይልቅ ለሀይማኖት ትኩረት የሚሰጡት ናቸው። ለዚያ ነው ከእምነት ጋር በተያያዘ " ሙቅ አልያም ቀዝቃዛ ሁን እንጂ ለብ ያለ አትሁን" የሚባለው።"

"እናህ ይሄን ምድር እያተራመሱት ያሉት በሀይማኖቱም ለብለብ ያለ እውቀት ያላቸው፣ በፖለቲካውም ለብለብ ያለ እውቀት ያላቸው፣ በፍልስፍናውም ፣ በሥነፅሁፍ ፣ በመዝሙሩ፣ በምርምሩ፣ በታሪክ እውቀት፣ በኢትዮጵያዊነት... ወዘተ ለብለብ ያለ እውቀት ያላቸው ናቸው ግዙፍ ችግር እየፈጠሩ ያሉት፤ ባጠቃላይ እምነት ውስጥ ፍቅር፣ ትህትና፣ አክብሮትን ፣ ጠላትን መውደድን ፣ ካንተ የተለየ ሀይማኖት የሚከተልን እንኳ ብታገኝ መሳደብ፣ ማንቋሸሽ፣ መጣላት ሳይሆን በእርጋታ ተጨባጭ መረጃ ይዘህ፣ ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ ለማሳመን መጣር አለብህ። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ከእምነት እና ሀይማኖት ጋር በተያያዘ ያለው ግዙፍ ችግር አለማንበብ ነው። በእርግጠኝነት የምነግርህ በእያንዳንዱ የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክ ፣ ፕሮቴስታንት... ቤት ውስጥ መፅሐፍ ቅዱስ አለ፤ የሚያነቡት እና የሚያጣጥሙት እጅግ ቁጥራቸው ትንሽ ነች። ከመፅሐፍ ቅዱስ አንድ ታሪክ ያነቡና መፅሐፍ ቅዱስን ሙሉ ለሙሉ እንዳነበበ ሰው አኩት ለማድረግ ይፈልጋሉ። መፅሐፍ ቅዱስን ማንበብ ያለብህ እንብቢያለሁ ለማለት ሳይሆን ከልብህ መሆን አለበት። ለእውነት ፍለጋ መሆን አለበት። ለምሳሌ የአለማችን ውድ መኪና ሐመር ነው፤ እናም ሐመር መኪናን ተደግፈህ ውብ ፎቶ ስለተነሳህ ብቻ ሐመር መኪና የአንተ ሆነች ማለት አይደለም፤ መግዛት አለብህ። ልክ እንደዛው ሀይማኖተኛ ሆነህ እምነት ላይ ትኩረት ካላደረክ እና እንደ የዋሆች በከንቱ እግዚአብሔር ቤት ብትመላለስ እና ስለ እግዚአብሔር ብታወራ ትርጉም የለውም፤ ስለ እግዚአብሔር ከማወቅ አንፃር ሲይጣንም ብዙ ያውቃል፤ በዚህ ዘመን ደግሞ የሰው ልጅ ብዙ ፈተናዎች አሉበት፤ በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥም የሲይጣን አምላኪዎች ኢሉሚናቲዎች በጣም እየተስፋፉ ናቸው፤ ስለዚህ በዚህ ዘመን በእምነታችን በመፅናት ጊዜያችንን መዋጀት አለብን!!"

"የሀይማኖት መቻቻል ግዴታ ነው። ፍቅር ማለት ከሁሉም ጋር አብሮ የመኖር ጥበብን መላበስ ማለት ነው። እግዚአብሔርም ደግሞ የሚፈልገው ያንን ነው። እኛ በፍቅር ፣

በመተሳሰብ፣ በመቻቻል አብረን ስንኖር ያን ጊዜ እግዚአብሔር ሊትዮጵያን ይባርካታል ፤ ያው እግዚአብሔር ማስተዋል እንዲሞላብንና ልባችንን ክፍት እንዲያደርገው መፀለይ ብቻኛ መፍትሔው ነው፡፡ ለምሳሌ አንተ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነህ! ቤትህ መጥቼ ስከራይ ምንም ያልከኝ ነገር የለም!! የሚገርምህ በጣም ብዙ ቤት ሄጄ ቤት አላከራይህም ያሉኝ አሉ፡፡ በተለይ አንድ ሲታከሲ የሚመች ቤት አግኝቼ በሂሳብ ተስማምተን ስንጨርስ ባለቤቷ ድንገት

"ለመሆኑ ሀይማኖትህ ምንድንነው?" አሉኝ

"ጴንጤ ነኝ" አልኳቸው ለመግባባት ያህል ነው እንጂ ቅድም እንዳልኩህ እኔ በሀይማኖት አላምንም ፤ እናልህ ሴትዮዋ ወዲያው ሀሳባቸውን ቀየሩ፡፡

"ነው እንዴ? እንግዳውስ ቤቴን መከራየት አትችልም" አሉኝ፡፡

"ለምን እማማ?" አልኳቸው፡፡

"ማታ ማታ ሆነ ቀን ቀን ለፀሎት እያልክ ብዙ ሰዎች እያሰባሰብክ ትመጣለህ! በጩኸት ቤቴን ትረብሻለህ! እኔ የመናፍቅን መዝሙር መስማት አልፈልግም ፤ ከሁሉም በላይ ልጆቼን ይሆን የማይረባ ሀይማኖትህን ልትሰብክብኝ ትችላለህ! በተጨማሪ አንተ እና መሰሎችህ የእምዬ ማርያም ጠላት ናችሁ፡፡ ማርያም አታማልድም ትላላችሁ አሉ!! ስለዚህ ቤቴን መከራየት አትችልም" አሉኝ፡፡

"ችግር የለውም እማማ! እግዚአብሔር ይባርኮት ብያቸው በሰላም ተለየሁኝ፡፡ አልተከራከርኩም!! የዚህ ሁሉ መነሻ እንዳልኩህ ያለ ማወቅ ስለሆነ ቢያንስ ያንን ለመለወጥ መጣር ብቻ ነው፡፡ በጣም የሚገርምህ ኢጋጣሚ አንድ ቀን ቸርች አምሽቼ ወደ ቤት ለመሄድ ከቸርች ስወጣ ታክሲ የምንይዝበት ቦታ እኚያ ሴትዮ እንድ ስልክ እንጨት ስር ተኝተው አገኘዋቸው፡፡ በጣም አሟቸው ነበር፡፡ ከፍተኛ የስኳር ህመም አለባቸው፡፡ መናገር ሁሉ አይችሉም ነበር፤ ወዲያው ታክሲ ኮንትራት በመያዝ ሆስፒታል ወሰድኳቸው፡፡ ትንሽ ሻል ሲላቸው ቤታቸውን ያኔ አይቼው ስለ ነበር ወሰድኳቸው ፤ ከዚያ ከልጆቻቸው ጋር አገናኘቼ ልወጣ ስል "ይቅርታ አድርግልኝ ልጄ ስላደረክልኝ ነገር ፈጣሪ ወሮታውን ይመልስልህ" አሉኝ፡፡ እየህ ህይወት በአጋጣሚዎች የተሞላች ስለሆነች በተቻለ መጠን ለምታገኘው ሰው ሁሉ በተቻለህ መጠን መልካም ለመሆን መሞከር ጥሩ ነገር ነው፡፡ ይቺ ምድር እኮ ከንቱ ነች!! ሁሉን ነገር ጥለነው እንሄዳለን! ሁላችንም እዚች መሬት ላይ ለእንግድነት የመጣን የእግዚአብሔር ሀሳቦች ነን!"

እውነቱን ለመናገር ከዘኪዮስ በርናባስ በጣም ብዙ ነገር ነው የተማርኩት፡፡ ከምንም በላይ እርጋታው በጣም ይማርካል፡፡ ለገፀባህሪነት ከምመርጣቸው ሰዎች መሀከል አንደኛው እርሱ ነው... በጨዋታ በጨዋታ ዘኪዮስ የነገረኝ የቤተሰቦቹ ሰፈር እና ቅዳሜ ቅዳሜ ዘወትር እገኝበታለሁ ወዳለኝ "መካነ ኢየሱስ" ቤተክርስቲያን ለመሄድ ኮንትራት ታክሲ ያዝኩኝ፡፡

አ! ተሰላይ አንድ ዘኪዮስ በርናባስ እንዳችም የዋሸው ነገር የለም.. ያለው ነገር ሁሉ እውነት ነው፡፡ ሰፈሩ የሚገኝበት ሰቅ ድንገት ት/ቤት አብረን የተማርነውን ከድርን አግኝቼው ስለ ዘኪዮስ ስጠይቀው ዘከዝኮ ነገረኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዘኪዮስ ቅዳሜ ቅዳሜ እገኝበታለሁ ወዳለኝ ቤተክርስቲያን ሳመራ እርግጥም እንዳለኝ ለወጣቶች "የዮሴፍ ታሪክን" እያስተማረ በርቀት አየሁት፤ ትንሽ ሰማሁት...

እነሆ ዘኪዮስ በርናባስ ሀቀኛ መሆኑን ተረዳው ... በቀጥታ ወደ ቤት ተመለስኩኝ... በቁጥር ሁለት የሚሰለለው ደግሞ ጋዜጠኛው እንዳልካቸው ሰው አትመን ነው፡፡

ጃንሜዳ የሚገኘው ዘመናዊ ቤቱ እንደደረስኩ በቀጥታ ያመራሁት ወደ ደሊላ ነበር፡፡ በቤት አያያዝ እኔንጃ ደሊላን የሚያክል አለ ለማለት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ 10 ከ10 ነጥብ!!... ሴት ልጅ ደግሞ ንፅህና የምትወድ ከሆነ ለራሷ ያላትን ከፍተኛ ክብር ያሳያል፤ ሲጀመርስ ዝርክርክ የሆነችን ሴት ማን ይፈልጋታል? ያው እንደርሷው ዝርክርክ ከሆነ ይፈልጋት ይሆናል! ግም ለግም አብረህ አዝግም ይባል የለም እንዴ? ለማናቸውም ደሊላ ብዙ ኮተት የላትም... አረፍ አረፍ ትንሽዬ ዕቃዎች ብቻ አሏት፡፡ ቤቱ ውስጥ በዝቅተኛ ድምፅ ቆየት ያለ "ቀበጥባጣ ወጣት" የሚል ወዝወዝ የሚያደርግ ሙዚቃ ተከፍቷል፡፡

ሠላምታ በመጠኑ ተለዋወጥን፡፡ ከዚያ በቀጥታ "አሁን እንዴት ነሽ?" አልኳት፡፡

"ተመስገን ነው እስካሁን ሽንት ቤት አልሄድኩም"

"ለማንኛውም ተነሽ ሆስፒታል እንሂድ"

"አሁን ምንም ስሜት አይሰማኝም ዛሬን ልየውና ነገ እሄዳለሁ፡፡ ምን የእኛ ሀገር ሆስፒታል እኮ አፍንጫዬን ነስረኝ ብትላቸው እስቲ ጉዳዩን ለማጣራት ፤ ሽንት፣ ሰገራ እና ደም ምርመራ አድርግ ብለው ብርህን ለመብላት ያሰፈስፋሉ፡፡ ከሰብዓዊነት ይልቅ ለሚያገኙት ገንዘብ ትልቅ ትኩረት ያደርጋሉ፤ እኛ እስራኤል አያስን ህክምና የሚሰጠን በነፃ ነው!! ለማንኛውም የአንተ ቀጠሮ ተሳካልህ?"

"ቀጠሮ አልነበረም! ስሰላ ላይ ነበርኩኝ፡፡ ዛሬ የሰለልኩት ዘኪዮስ በርናባስን ነበር፤ በቅርቡ አንቺንም እሰልላለሁ" ልላት ነበር፤ ግን አልወጣኝም፤ በአንፃሩ

"አሀ ጥሩ ነበር፤ እጠር ያለች ጉዳይ ነበረች ጨርሼ መጣሁ፡፡ እሺ ቢያንስ እራፍ ምግብ ሳዘጋጅልሽ እንቢ እንዳትይኝ አባክሽ ልንከባከብሽ"

"እሺ ... እና... በጣም አመሠግናለሁ!!"

* * *

እራፍ ምግብ ሰርቼ አበላዋት፡፡ ስለ እውነት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳለችው ማንም ስለሌላት በጣም ልቤን ነክታዋለች፡፡ እንደ ብቸኝነት ደግሞ ምን አሰቃያሚ ነገር አለና? እናም እስከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሳጫውታት እና በተቻለኝ መጠን እንክብካቤ ሳደርግላት ቆይቼ እንዲሁም ምናልባት ካመማት እንድትቀሰቅሰኝ ነግሬያት ተሰያየን፤ ባጠቃላይ ደስ የሚል ጊዜ ነበር ያሳለፍኩት፤ ይቺ ብቸኛ ወጣት ስሜቴን እየገዛችው ይሆን? ለምንድንነው በቃላት መግለፅ የማልችለው የደስታ ስሜት እየተሰማኝ ያለው??

pdf by @shuktus_books

# 4

## ተስፋ የቆረጠው

# ጋዜጠኛ

ዕለተ ቅዳሜ

ግንቦት 8...

አንደ ቅዳሜ የምወዳት ቀን የለችም፤ ምናልባት የተወለድኩትም ቅዳሜ ቀን ስለሆነች ይሆናል፤ በህይወቴ በጣም አሪፍ አሪፍ የምላቸው ነገሮች ሁሉ የተፈጠሩት በቅዳሜ ቀናት ነው፤ እናም ቅዳሜ የኔ ምርጥ ቀን ነች፡፡ ከስራ እንደወጣሁ በቀጥታ ያመራሁት አራት ኪሎ ነው፡፡ ማስታወቂያ የሚነበብበት ቦታ በመሄድ በህይወቴ ገዝቼ አንብቤው የማላቀውን ትልቁን አዲስ ዘመን የተባለውን የመንግስት ፕሮፓጋንዳ ማስፈሪያ ጋዜጣ ፈልጌ ገዛሁ፡፡ ብዙም ሳልቸገር ጋዜጣውን ገለጥ ገለጥ ሳደርግ አምደኞች የሚለው ቦታ ላይ "እንዳልካቸው ሰው አትመን" የሚል ስም ተመለከትኩ፡፡

የእንዳልካቸውን ፅሁፍ ለማንበብ ብቻ ጋዜጣውን አጣጥፌ ኪሴ ውስጥ በመከተት ከአራት ኪሎ አምባሳደር ለመሄድ ከቱሪስት ሆቴል ዝቅ ብሎ ካለው ቦታ በመሄድ ታክሲ ተሳፈርኩ፡፡ ደረስኩ፡፡ አምባሳደር የአስር ሰዓት ፊልም ለማየት አነስ ያሉ ወጣቶች ወረፋ ይዘው ቆመዋል... በአይኔ የሚታየውን ፊልም ባላየውም ሸፍ አድርጌው በቀጥታ ወደ

ኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በአግሬ አመራው፡፡ የመስሪያ ቤት መታወቂያዬን ለተበቃው አሳይቼ ገባሁ፡፡ አንዲት ጡልጡል አያለች የምትሄድ ቀጭን ምግብ በሌታ የማታውቅ የምትመስል ሴት ይትርታ በመጠየቅ አስቁሚ

"አባከሽ የአንዳልካቸው ሰው አትመን ቢሮ የት ነው?" አልኳት፡፡

"ውይ አሁን የሰም ለዘገባ ወጥቷል፤ ሞባይሉ ላይ ብትደውልለት ይሻላል"

"እሺ አመሠግናለሁ" በማለት በፍጥነት ከድርጅቱ ወጣሁ፡፡ በእርግጥ አንዳልካቸው የነገረኝ ሁለት መረጃ እውነት መሆኑን በመጠኑ አረጋገጥኩ፡፡ የሚኖርበትን ሰፈር፣ ያደገበትን ሰፈር፣ እትብቱን የቀበረበትን ሰፈር ለማጣራት ግን አልቻልኩም ፤ ምክንያቱም አንዳልካቸው አዲስ አበባ አልተወለደም፡፡ እኔ ሳልጠይቀው ራሱ ነበር አንድ እሁድ ስለ ህይወቱ ያጫወተኝ፤ በእርግጥ ወሬው የተነሳው የሻወር ቤቱ መታጠቢያ ተበላሽቶበት ላስተካክልለት ያከራየሁት ቤቱ ገብቼ ልወጣ ስል ግርግዳው ላይ የቡና ተክል ውስጥ የሚያምር ትልቅ የቁም ፎቶ የተነሱ አዛውንት አይቼ በጣም ያምር ስለ ነበር፡-

"የእውነት በጣም የሚያምር ፎቶ ነው" አልኩት፡፡

"አባቴ ነው፤ በቡና አይነቶች ላይ ከፍተኛ ምርምር ያደርግ ነበር፤ ይህን ፎቶ የተነሳው ጅማ እርሻ ቦታ ውስጥ ነበር"

"እ! የጅማ ሰው ነህ?"

"አዎ ! ጅማ ፈረንጅ አራዳ የሚባል ሰፈር ነው ያደኩት" ብሎ በመጀመር ስለጅማ በመጠኑ ነገረኝ፤ በእርግጥ ጅማን በመጠኑ አውቃታለሁ፡፡ አራት ቀናት ለስብሰባ ተቀምጬባታለሁ፡፡ መርካቶ እየተባለ የሚጠራውን ሰፈር፣ ፒያሳን ፤ ፈረንጅ አራዳን፤ የአባጅፋር ሙዚየምን... ሌሎችንም ቦታዎች አይቻለሁ፡፡ ጅማ ሴንትራል ሆቴል ነበር በወቅቱ ያረፍኩት ... በእርግጥ ጅማ እኔ የምወዳት አይነት ከተማ አይደለችም ... ለማንኛውም የአባጅፋር አገርን ጅማ በመጠኑ አውቃታለሁ፡፡ አንዳልካቸውም ስለ ጅማ ነግሮኝ እንደጨረሰ ስለ አባቱ ጠየኩት

"ስለ አባትህ ንገረኝ የቡና አይነት ማለት?"

"ቡና ትጠጣለህ?"

"ሳይበዛ"

"ምን ዓይነት ጣዕም?"

"ምን ዓይነት ጣዕም? አልገባኝም?"

"እየሀ ስለ ቡና ይብልጥ ለማወቅ የቡና መነሻ በሆነችው ጅማ የተወሰነ ጊዜ መቆመጥ ይኖርብሃል:: ከቡና የሚሰራ በጣም ጣፋጭ የሆነ ቆሪ የሚባል ምግብ እንዳለ ራሱ የምታውቅ አይመስለኝም! ለማንኛውም ጅማ ተወልዶ ጅማ ያደገው አባቴ ቡና ላይ ባደረገው የበርካታ ጊዜ ምርምር በኢትዮጵያ ውስጥ አምስት የቡና አይነቶች አሉ፤ አምስቱም የራሳቸው የሆነ የተለየ ጣዕም አላቸው:: ስለዚህ ነገር የምታውቀው አለ?"

"በጭራሽ"

"ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው ሰው ቡና ይጠጣል እንጂ ስለ ቡና ጣዕም አያውቅም:: እየሀ ኢትዮጵያ ውስጥ አምስት የቡና አይነቶች አሉ:: እያንዳንዳቸው የራሳቸው የተለየ ጣዕም እና ጥቅም አላቸው:: በአባቴ ምርምር መሠረት እና አሁን በሳይንቲስቶች ተጠንቶ በተደረሰበት አሳማኝ ግኝት አምስት ናቸው:-

⇒ ሊሙ ቡና: ይህ ቡና የሚገኘው ጅማና ኢሊባቡር ውስጥ ሲሆን የወይን ጠጅ (Winy) ጣዕም አለው::

⇒ ወለጋ ቡና : ይህ የአራቱ ወለጋዎች ቦታ ይበቅላል፤ በጣዕም ደረጃ የፍራፍሬ ጣዕም (Fruity) አለው::

⇒ ሐረር ቡና: ይህ በሁለቱ ሐረሮች የሚበቅል ሲሆን የቾኮላት (Mocha) ጣዕም አለው::

⇒ ጎጂ ቡና : ይህ በጉጂ የሚበቅል ሲሆን በጣዕም ደረጃ የቅመማቅመም ( Spicy) ጣዕም አለው:: የመጨረሻው የአበባ (Floral) ጣዕም ያለው የቡና አይነት ሲሆን ቦረና ቡና በመባል ይጠራል፤ ከዚህ በኋላ አንተም እየመረጥክ መጠጣት ነው"

"እና አንተ በአባትህ ሙያ እንዴት እግራቸውን ተከትለህ አልተሰማራህም?"

"የአባቴን ፈለግ ነው የተከተልኩት! አባቴ መጀመሪያ ጋዜጠኛ ነበር:: ጡረታ ሲወጣ ነው ወደ ቡና ምርምር የገባው፤ እኔም እንደ አባቴ ትንታግ የሆንኩ ጋዜጠኛ እንድሆንለት ይፈልግ ስለ ነበር ዩኒቨርሲቲ ስገባ በጋዜጠኝነት እንድመረቅ ይፈልግ ነበር፤ አስራ ሁለተኛ ክፍልን ስጨርስ ቤልጂየም ተወዳድሬ በመሄድ በልማታዊ ጋዜጠኝነት ተመርቄ በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ ተመለስኩ:: የተወሰነ ጊዜ ተቀጥሬ በመስራት ከዚያ የራሴን ጋዜጣ

ለመከራት የሚል አቅድ በመያዝ ነበር ኢትዮጵያ ተመልሼ የመጣሁት:: ከዚያ እንዴት እንዳሰሩኝ እና ምን ማኖ ኢህአዴግ እንዳስነኩኝ ባላውቅም የነበረኝን ትልቅ ህልም ሁሉ ትቼ እየተልከሰከስኩ እገኛለሁ፤ ለነገሩ በቅርቡ ጥሩ ዜና ይኖረኛል"

"የምን ጥሩ ዜና?"

"ወይ ለpress TV አልያም CNN ካልሆነም ለ ESAT ለመስራት ውስጥ ለውስጥ ጥረት እያደረኩ ነው፤ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ጋዜጠኛ ለመሆን ከሁለት ነገሮች አንዱን መምረጥ አለብህ ወይ አልም ያልክ ግዙፍ ውሸታም አልያም ለሀቅ ኖረህ ፤ ሀቅን ወግነህ፤ ከሀቅ ጋር በመቆም ለሀቅ ለመሞት መዘጋጀት!!"

"በእርግጥ የሚወራውን እሰማለሁ! ሥራው ግን ደስ አይልም?"

"ሥራውማ በጣም ደስ የሚል ነው:: ጋዜጠኝነትን የመሰለ በጣም ኢንተረስቲንግ የሆነ ሥራ እኮ የለም! በየዕለቱ ታነባለህ፤ የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት ታገላብጣለህ፤ ከተለያዩ እና የተለያየ እውቀት ፤ የህይወት ልምድ እና ግንዛቤ ካላቸው ሰዎች ጋር ትገናኛለህ፤ ስለ ሰዎች፤ ስለ ህይወት ፤ ስለፖለቲካ ፤ ስለ ማህበራዊ ህይወት፤ ስለህይማኖት... ብዙ ነገር ታውቃለህ!! በእያንዳንዱ ሴኮንድ ከመረጃ ጋር ቅርርብ አለህ!! ችግሩ ይህ የኢህአዴግ ስርዓት ጋዜጠኝነትህን እንድትጠላው ያደርግሃል፤ በተለይ እንደ ልማታዊ ጋዜጠኝነት አስደሳች የለም፤ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛው የልማታዊ ጋዜጠኝነት ሙያ እንዲያድግ መንግስት በጭራሽ አይፈልግም!! ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ አለው"

"ካላስቸገርኩህ ይቺን ነገር በደንብ ንገረኝ ልማታዊ ጋዜጠኛ ሲባል ሰምቻለሁ ግን ልዩነቱ አይገባኝም ከሌላው ጋዜጠኝነት ይለያል?"

"ኮተቱን ልተውልህና ባጭሩ ከ1963 ዓ.ም ጀምሮ በዓለም ላይ አራት የፐሬስ ንድፈ ሀሳቦች መጥተዋል፤ እነዚህ The Four theories of the press የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው:-

⇒ የፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት የፐሬስ ንድፈ ሀሳብ

⇒ የፐሬስ ነፃነት አራማጆች ንድፈ ሀሳብ

⇒ የሶቪየት ኮሚዩኒስት ፐሬስ ንድፈ ሀሳብ

⇒ ማህበራዊ ኃላፊነት የሚሰማው ፐሬስ ንድፈ ሀሳብ ናቸው:: ከዚያ በዋንኛነት

በተለይ ለሶስተኛው ዓለም ሀገሮች ጠቃሚ ስለሆን መተግበር አለበት ተብሎ የተነደፈው አዲሱ የፕሬስ ንድፈ ሀሳብ የልማት ጋዜጠኝነት (Development Journalism) የሚባለው ነው:: አሁን ስለ ልማታዊ ጋዜጠኝነት ከመንገሬ በፊት ጋዜጠኛ ለምን ያስፈልጋል? የሚለውን በመጠኑ ልንገርህ"

"በአማርኛ አንተ እንዳሻህ ተርጉመው ስለ ጋዜጠኝነት what is journalism? ለሚል ጥያቄ የሚሰጠው አጠር እና ቀለል ያለች መግለጫ Journalism is the activity of gathering, assessing, creating, and presenting news and information. It is also the product of these activities. የምትል ናት! አንዲት ሀገር በዲሞክራሲ ትተዳደራለች ከተባለ በዲሞክራሲ ሥርዓት መርህ ሕዝብ የማወቅ መብት አለው! ጋዜጠኞች ደግሞ ሕዝቡን ወክለው መረጃ የመሰብሰብና የማሰራጨት ኃላፊነት አለባቸው:: አርቲክል 19 የተባለው የፕሬስ ተሟጋች ድርጅት ቃል በቃል እንደሚለው

> ' መልካም የዲሞክራሲ ሥርዓት ያላቸው መንግስታት በእጃቸው የሚገኘውን መረጃ ለህዝባቸው የማድረስ ግዴታ አለባቸው፤ መጥፎ አስተዳደር ያላቸው መንግስታት ግን መረጃን ከህዝብ የመደበቅና ሚስጢር የማድረግ ፍላጎት አላቸው፤ ከህዝብ መረጃ ሲደበቅ ደግሞ ለአስተዳደር ብልሹነት፣ ሙስናና ንቅዘት በጣም ይጋለጣሉ:: ለዜጎቹ መረጃ የማግኘት መብት የሚከለክል መንግስት አምባገነን መንግስት ብቻ ነው

ይላል:: ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር ይህ ነው::"

"በዲሞክራሲ አመራሩ ካልዘ ዜጎች ማንኛውንም ሀሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ መብታቸው ያለ አንዳች ገደብ የተረጋገጠ ነው:: ይህ ማለት የመንግስትን ፖሊሲን ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓቱን እና በስልጣን ላይ ያሉትን አስፈፃሚዎችን ጭምር የመተቸትና የመቃወም መብትን ያካትታል! እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የመሰለህን

የመደገፍ ሆነ የመቃወም መብት አለህ፤ ይህንንም አንተ ባመችህ መልኩ በቃል፣ በፅሁፍ ሆነ በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የመግለፅ መብት አለህ! በዚህ ምክንያት ለምን የተሰማህን ሀሳብህን ገለፅክ ተብለህ የሚደርስብህ አንዳችም ቅጣት ሆነ ማስፈራሪያ መኖር የለበትም!! ሀሳብህን የመናገር መብት በህገ መንግስቱ በተለይ በአንቀፅ 29 ላይ በግልፅ ተቀምጧል፤ ይህ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ሀገ መሬት ላይ ወርዶ አለ ወይ? ስትል ነው ጉድ የሚፈላው፤ የመንግስትን ልማት ብታጣጥል፣ ስለሚሰራው ግድብ ጥያቄ ብትጠይቅ፣ አደጋ ደርሶበት የነበረው ግልገል ጊቤ የትደረሰ ብትል ፣ ስለሚሰራው ባቡር ትችት ብታቀርብ፣ በስልጣን ላይ ስላሉት አመራሮች ደካማ ነገራቸውን ብታጋልጥ፣ ሀገሪቱ ውስጥ ስላለው ደካማ እና በፍጥነት መወገድ ስላለባቸው ጉዳዮች መረጃ ብታቀናብር ... ወዲያው ልማት አደናቃፊ፣ አሸባሪ፣ የተቃዋሚዎች አንደበት፣ ነፍጠኛ፣... ወዘተ በሚል ስያሜ እስር ቤት ትወርዳታለህ!!"

"እንዴ! አንተ አሁን እኮ ኢትዮጵያ በፍርሃት ተወጥራለች! ማንም ደፍሮ እኮ ማውራት እያቆመ ነው:: ሰው ሁሉ በፍርሃት ተሸብቧል! የመናገር መብቱ ተነጥቋል! ዋነኛው የእድገት መለኪያ ቴክኖሎጂ እና ቁሳዊ ነገሮች ብቻ ሳይሆን የሰዎችን አዕምሮአዊ፣ አካላዊ ፣ አከባቢያዊ፣ መንፈሳዊ ነፃነትና በነፃነት የመናገር መብትን ያካትታል:: አንዲት ሀገር ውስጥ እውነተኛ እድገት አለ የሚባለው ሰዎች የፈለጉትን የመናገር እና የመፃፍ፣ የማንበብ መብት ሲኖራቸው ነው፤ እየህ የመናገር ነፃነትን እግዚአብሔር የሰጠን መሠረታዊ ነገር ነው:: እነ ኢህአዴግ የነጠቁን ደግሞ ይህን እግዜር በተፈጥሮ የለገሰንን መብታችንን ነው!! ለማንኛውም ወደ ልማታዊ ጋዜጠኝነት ልመለስልህና እንግዲህ ልማታዊ ጋዜጠኝነት ማለት እንደ ነገርኩህ በ1960ዎቹ ገደማ ሲመሠረት ዕድገትና የሰዎች ኑሮ መሻሻልን ቀዳሚ አላማ በማድረግ የተመሠረተ ነው፤ በዚህ መሠረት የልማት ጋዜጠኝነት አንድን ሀገር ከአረንቋ ድህነትና ኋላቀርነት በማላቀቅ ቀጣይነትና ዘላቂነት ወዳለው የኢኮኖሚ ዕድገት በማሸጋገር ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ለማስገኘትና የህዝብን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ጥረት የሚያደርግ ሳይንስ ሲሆን ሕዝቦች ማንኛውንም አስተያየታቸውን ፣ ምኞታቸውን፣ ፍላጎታቸውን ያለ አንዳች ፍርሃት እንዲገልፁ የሚያደርግ ነው፤ በተለይ የህዝቡን ፍላጎት መዘገብና ማህበራዊ ችግሮችን ማጋለጥ እንዲሁም የልማት ጥረቱን የሚያደናቅፉ አሠራሮችን ሙስናን የመሰሉ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ የሚያስከትሉ ነቀርሳ የሆኑ ችግሮችን በተጨባጭ መረጃ ማጋለጥ የእውነተኛ የልማት ጋዜጠኝነት አብይ ተግባር ነው"

"አይውግንም እያልከኝ ነው?"

"ትክክል! እንዳልኩህ አብይ ትኩረቱ አገራዊ ዕድገት ለማምጣት አገልግሎቱን ለህዝብ ያደረገ ፤ ራሱን ፍፁም ነፃ በማድረግ ለመንግስት ሆነ ለተቋዋሚዎች ጥብቅና የማይቆም ለእውነት ብቻ ዘብ የሚቆም ባጠቃላይ የአንድን ድርጊት ክስተት፣ ከነውንና የሚያስከትለውን ውጤት ጭምር ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ያቀርባል እንጂ ለአንድ ወገን አይድሎአዊ ሽፋን በመስጠት ዕውነታን የማያደበዝዝ ነው፤ እዚህ ጋር የጥላሁን ገሰሰን ሙዚቃ ማንሳት ትችላለህ፡፡

ውሸት ለመናገር አትሻም ምላሴ
ለዕውነት እሞታለሁ አልሳሳም ለነፍሴ፡፡
ያልሆነውን ሆነ ብዬ ከማውራት
ዕውነት ተናግሬ ይሻለኛል ሞት፡፡
ውሸትን የማይወድ ዕውነተኛ ሰው ነው
ተብዬ መጠራት ታላቅ ኩራቴ ነው፡፡

አሁን ወሳኙ ጥያቄ እውነት እኛ አገር ልማታዊ ጋዜጠኝነት አለ ወይ? የሚል ነው? መልሱ በጭራሽ ነው!! ኢትዮጵያ ውስጥ ልማታዊ ጋዜጠኝነት ትርጉሙን ስቷል! በዚች ሚስኪን ታሪካዊት ኢትዮጵያ አገራችን ውስጥ ልማታዊ ጋዜጠኛ ማለት የመንግስትን ጠንካራ ጎን እየፈለጉ ያዩትን እያጋነኑ ማውራት! ማጫፈር! ጭራ መቁላት! ማሸቃበጥ! ፃፉ የተባሉትን ብቻ መፃፍ! ስለ መንግስት ጠንካራ ጎን ብቻ ማውራት ነው ብለው የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር የሌላቸው ወፍዘራሽ ጋዜጠኞች ያሉባት አገር በመሆኗ ልማታዊ ጋዜጠኝነት ትርጉሙን ስቷል፡፡ በጣም የሚገርምህና የሚያሳዝንህ እኛ ሀገር ማንኛውም መፃፍ የቻለ፤ መቅረፀ ድምፅ ይዞ ሌላውን ቃለመጠይቅ ያደረገ ሁሉ ጋዜጠኛ ነው፤ ቢያንስ እንኳ የጋዜጠኝነት ዋና ዋና የሥነ ምግባር መርሆች ስለሚባሉት

⇒ እውነትን መፈለግና መዘገብ!!

⇒ ትክክለኛነት !!

⇒ ሚዛናዊነት !!

⇒ ገለልተኝነት!!

_ የሚባሉትን መርሆች እንኳ ጠንቅቀው በቅጡ የማያውቁ በርካታ ጋዜጠኞች የበዙባት አገር ነች:: እየሀ ጋዜጠኛ ማለት ሁልጊዜ የሚያገለግለው አንድ ወይም ሌላውን ወገን ሳይሆን ሕዝብን ነው:: ለዚህ ነው ጋዜጠኛ የህዝብ ዐይንና ጆሮ ነው የሚባለው ፣ ጋዜጠኛ ገለልተኛ መሆን ይጠበቅበታል:: በዘገባው አንዱን ወገን ለመጥቀምና ሌላውን ለመጉዳት መሥራት እንደሌለበት በፅኑ ይነገራል:: ከምንም በላይ ጋዜጠኛ የፖለቲካ ፓርቲ አባል እንዳይሆን ይፈለጋል:: ምክንያቱም የአንዱ ፓርቲ አባል ወይም ደጋፊ ከሆነ የሙያውን ሥነ ምግባር በትክክል መተግበር አስቸጋሪ ይሆንበታል ተብሎ ይታመናል:: ኢትዮጵያ ውስጥ እንግዲህ ለከርሳቸው አደር በርካታ ጋዜጠኞች አሏት፤ አይ! ለህሊናቸን እንጂ ለሆዳችን አናድርም ያሉት ደግሞ በየእስር ቤቱ ከአቃቂ እስከ ቂሊንጦ፣ ከሸዋሮቢት እስከ ዝዋይ ...ታስረው ይገኛሉ... እኔ አሁን በጣም ምርር ስላለኝ ነው ጠዋትና ማታ ከኢትዮጵያ ለመውጣት ነገሮችን እያመቻቸው ያለሁት:: "ሁልጊዜ እንደ ጅብ ፈሪ ሆኖ ከመኖር ለአንድ ቀን እንኳ እንደ አንበሳ ደፋር ሆኖ መኖር ይሻላል" ይላሉ ጣሊያኖች እናም አዕምሮዬ በማየው ኢሞራላዊ ስራ ከማበዱ በፊት ከኢትዮጵያ መውጣትን መርጬ ተቀምጫለሁ፤ በዚያ ላይ ከመስሪያ ቤት ሁለት የማስጠንቀቂያ ደብዳቤም ተሰጥቶኛል"

"ምን አድርገህ?"

"የመጀመሪያው አሁን የተዘጉትን አዲስ ጉዳይ እና ፋክት መፅሔት ሳነብ ተገኝቼ"

"ምን ችግር አለው ታዲያ መረጃ የማግኘት መብት እለህ አይደለም እንዴ?"

"አይ አንተ አሱቴ ሆድ ይፍጀው አንተ ስለ ኢህአዴግ ምንም የምታውቀው ነገር የለም! አልደረሰብህም፤ ለነገሩ አንተ የግል ባንክ ውስጥ ነው የምትሰራው:: አምስት ለአንድ አትሰላል! የሥራ ነፃነትህ አይገፈፍ! ካንተ በትምህርት የሚያንስህ ከንተ እለቃ አይመራህ! ይልቅ በቅርቡ ስለ ኢህአዴግ የተገጠሙትን ሁለት ቅኔዎች ልንገርህ:-

ከጫካ ሰው ጋር ቁማር ተጫውቼ
ወና ቀርቻለሁ ሀገር ተበልቼ::
እሰቡ ሳልጨርስ ምርት እህሌን ላፍሰው
ከጫካ የመጣ ዝንጀሮ ጨረሰው ::

በተለይ የአንተ አሊቃ ካንተ የተሻለ እውቀት እና ድፍረት ከሌለው ይሆህ ገደል ይገባል:: ናፖሊዮን ቦናፓርት አንዲት ምርጥ ንግግር አለችው:: If you build an army of 100 lions and their leader is a dog, in any Fight, the lions will die like a dog. But if you build an army of 100 dogs and their leader is a lion, all dogs will fight like a lion. ትሳለች አሪፍ አይደለችምን?"

"በጣም! ሁለተኛውስ?"

"እውነቴን ነው የምልህ ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ልቤን ከፋኝ የሚሰብረው ጉዳይ መንግስት አማራ፣ ትግሬ ፣ኦሮሞ፣ ወላይታ... ቅብርጥሶ እያለ ለመከፋፈል የሚያደርገው ጥረት ነው:: እንደ ዘረኝነት እጅግ የሚያንገሸግሽ ነገር የለም:: ሰው መሆን ብቻ ይበቃል! በዚህ ጉዳይ ዙሪያ እና ኢትዮጵያ ውስጥ በፍጥነት መቅረት ስላለባቸው ጉዳዮች አንድ ፅሁፍ አቅርቤ ነበር፣ ለህትመት አልበቃም! እንኳን ለህትመት ሊበቃ ለእኔ የማስጠንቀቂያ ወረቀት አሰጠኝ:: እኔ ኢህአዴግን በምን እንደምመስለው ታውቃለህ?"

"አላውቅም?"

" በእንቁራሪት"

"ምን ማለት ነው?"

"እንቁራሪትን ከወርቅ በተሰራ ዙፋን ላይ ብታስቀምጣት ዘላ ኩሬ ውስጥ እንዘጭ ማለቷ አይቀሬ ነው፣ በዚያ ላይ እንቁራሪት ከንፁህ ውሃ የደፈረሰ ውሃ ይማርካታል"

የዚያች ቀን ከአንዳልካቸው ጋር ብዙ ነገር ነበር ያወራነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት እንደሌለ፣ በጋዜጠኞች ላይ ስለሚደረገው አፈና፣ አብረውት እውነትን እያወቁ ለውሸት ዘብ የቆሙ ሆድ አምላኪ ጋዜጠኞች የተንሳ እንዴት ስራው እንዳስጠላው ... እንዳንገሸገሸው... ምርር እያለ ነበር የነገረኝ... ከአንዳልካቸው ጋር በብዛት እያመሸ ስለሚገባ አንገናኝም፣ አንድ ሁለት እሁዶች ግን አንዲት ትልቅ ቂጥ ካላት ሴት ጋር ሲገባ አይቼዋለሁ::

ከአንዳልካቸው ጥቁር ፊት ላይ ደስታም፣ ሀዘንም አንብቤ አላውቅም፣ በዚያ ላይ ካላናገሩት አያናግርም፣ በስራው እንደተሰላቸ ገፅታው ያሳብቅበታል፣ ለነገሩ እንደመዋሸት እና ለመውጣት ሸፍቷል:: እውነት ስትጨፈለቅ እንደማየት ምን የሚያስጠላ ነገር አለና? በዚያ ላይ ልቡ ከኢትዮጵያ

ቤት እንደተመለስኩ የገዛሁትን የመንግስት ልሣን የሆነውን አዲስ ዘመን አገላበጥኩና የእንዳላካቸውን ፅሁፍ አነበብኩ፡፡ ስለ ልማታዊ ገበሬዎች ምናምን የሚያወራ ፅሁፍ ነው…

እንዳልካቸውን ሳየው ሁልጊዜ ትዝ የሚለኝ አንድ ዕለት በጨዋታ መሀከል የነገረኝ አባባል ነች፤ "አንድ ዓለም የሚባል የለም፤ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ዓለም አለው!"

pdf by @shuktus_books

# 5

# ደሊላ

በነጋታው ደሊላ ጠዋት ለስራ ስትወጣ ሳታየኝ በኮንትራት ታክሲ ተከተልኳት፡፡ ባለታክሲው ዘና ያለ ልጅ ነው፡፡ ከታክሲዋ ውስጥ የማዲንጎ አፈወርቅ "ስወድላት" የተሰኘ ሙዚቃ ተከፍቷል፤ ከሙዚቃው ጋር አብሮ እየዘፈነ ነው፡፡

... ስወድላት ለኔ ያላትን ፍቅር

ስወድላት ለኔ ያላትን ፍቅር...

"ይቅርታ ጥያቄ ልጠይቅህ?

"ይቻላል"

"የምትወዳት ልጅ አለች?" አልኩት፡፡ከት ብሎ ሣቀ፡፡

"ምነው?" አልኩት፡፡

"ለሴት ልጅ ልብህን አታስገዛ፡፡ ልጇ ሆይ ከሴት ምላስ ተጠንቀቅ! ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ እንቁ እጅግ ይበልጣል!' ይባላል! አሁን የኔ የአምስቱ ዓመት እቅዴ ከሴቶች መሸሽ ነው፡፡ በእርግጥ አንዲት ፍቅረኛ ነበረችኝ ያኔ ጅል እያለሁ ቡጥቡጥ አድርጋ መናጢ ደሀ አድርጋኝ ሄደች፡፡ ሁለት መቶ ሺ ብር ነው ያጫረሰችኝ፡፡ እንዴት እወዳት ነበር መሰለህ! ያለችኝን ሁሉ ነበር የማምናት፡፡ እሷን ሳላያት ማደር አልችልም ነበር፤ በእርሷ የተነሳ ከሰው ጋር ተጣልቼ ሰስት ወራት እስር ጠጥቼያለሁ ፤ ግን ምን ዋጋ አለው? ልጅቷ የሆነች ማቴሪያሊስት ነበረች ከኔ የሚበልጥ ወንድ ጠበሰችና ቀይ ካርድ ሰጥታኝ አባረረችኝ፡፡

ከዚያ ሴት የምትባል ለጊዜያዊ ወሲባዊ ስሜት እንጂ ለፍቅር አስቤ አላውቅም፤ አሁን ለሴት የሚሆን ጊዜ የለኝም፡፡ ከጠዋት እስከ ማታ ሰራ ሰራ አድርጌ የዚች ታክሲ ዕዳ አለችብኝ እከፍላለሁ፤ በዚያ ላይ የኮንዶሚኒየም ክፍያም አለብኝ፤ ስለዚህ ሴትን በሩቅ ብያለሁ፡፡ ይህን መዝሬታ የምዘፍነው የማዲንን እድናቂ ስለሆንኩ ብቻ ነው"

"ጥሩ ነው! በርታ"

"የምትከተላት ልጅ ቺከህ ነች?"

"እህ..."

"አስቸገረችህ?"

"በጣም"

"ስለ ሴት ልጅ ከህይወት ልምድ የቀሰምኩትን ልንገርህ?"

"ደስ ይለኛል"

"ሴት ልጅ አባብ ናት! ስለዚህ አንተ እስስት ሆነህ ጠብቃት! ሴት ስልህ እናትን አይወከልም"

"ለሴቶች ጥላቻ ያለህ ይመስለኛል"

"ነገርኩህ እኮ ሴቶችን እጠላለሁ!! እናቶችን አከብራለሁ፤ ይህ ሀሳብ ላይዋጥልህ ይችላል! ሴቶች እኮ ናቸው እናቶች የሚሆኑት ልትለኝ ትችላለህ ግን አንተም ሲደርስብህ ከኔ የባሰ ትሆናለህ! ለኔ ሁሉም ሴቶች አንድ ናቸው፤ በቁመት፣ በመልክ፣ በአለባበስ ይለያዩ ይሆናል እንጂ የሁሉም ሴቶች መንፈስ አንድ ነው!! ሁሉም የሴይጣን ቁራጭ ናቸው፤ ስለዚህ ይቺን ልጅ የምትወዳት ከሆነ ተዋት! ንቀህ ስትተዋት ያንተን ንቀት መቋቋም ስለማትችል ጭራዋን እየቆላች ትመጣለች፡፡ የእኔዋም ንቄ ስተዋት ተመልሳ መጥታ እንታረቅ ብላኝ ነበር፡፡ እኔ ባጣ ቆየኝ አይደለሁም እልኳትና አንድ ጥርሷን አውልቄ አባረርኳት"

"እሺ አስብበታለሁ"

ከልጁ ጋር እያወራን ደሊላን በታክሲዋ ተከተልናት፡፡ ደሊላ ከተሳፈረችበት ታክሲ ወርዳ በእግሯ መጓዝ ጀመረች፡፡ የመስቀል ፍላወርን መንገድ ያዘች... በጣም የሚያምር ግቢ ውስጥ ገባች፡፡ በሩ ላይ የማሳጅ ምስልና ዝርዝር ነገሮች የተለጠፈበት ማስታወቂያ በደማቁ ይታያል፡፡ ድንገት ሀሳቡ ስለመጣልኝ

"ውስጥ እንደምትሰራ እንዴት ማወቅ ይቻላል?" አልኩት፡፡ ባለታክሲው ፈጣን

ጭንቅላት ያለው ምላጭ የሆነ ልጅ ነው፤ ወዲያው

"ምን ጣጣ አለው? ብር ከች አድርግ ቢያንስ አሮማ ተሰርቼ እመጣለሁ 40 ደቂቃ አይፈጅም"

"ማሳጅ ተጠቅመህ ታውቃለህ?"

"ምን ነካህ?" የላዳ ሹፌር እኮ ነኝ! ብዙ ሰዎችን ማሳጅ ቤት ወስጃለሁ! እኔም ለማስረዳት አስቀድሜ ማወቅ ስላለብኝ ተጠቅሜ አውቃለሁ፤ አንተ አታውቅም?"

"አላውቅም ፤ ስለዚህ ስንት ብር ይበቃሃል?"

"200 ብር ለአሮማ..50 ብር ቲፕ ስጣት ካልከኝ 250 ብር ከች አድርግ"

ምንም ሳልናገር ሰጠሁት፡፡

"መኪናዋ ውስጥ ትቆያለህ ወይስ ሻይ ቡና ትላለህ?"

"እዚህ እቆያለሁ"

"መጣሁ ቢቃ! ታዲያ ስመለስ የቆምኩበትን የ40 ደቂቃ ትጨምራለህ! ስቀልድ ነው፤ ሙዚቃ እየሰማህ ዘና በል" አለኝና በኩራት እየተራመደ መጓዝ ጀመረ፡፡

ላዳዋን መቃኘት ገባሁ፡፡ በእርግጥ ላዳዋን በውብት ነው የያዛት፡፡ ሁሉ ነገር ንፁህ ነው፡፡ አዋራ የሚባል ነገር የለም፡፡ የወንበር ጨርቆቹ በአርባ ምንጭ ባህላዊ አልባሳት የደመቁ ናቸው፡፡ ከኋላ የሚያምር አሸንጉሊት አለ...

ፈገግ አልኩኝ፡፡ ፈገግ ያልኩት ድንገት መኪናዋ ላይ የተሰካውን ቁልፍ አይቼ ነው፡፡ ቁልፉን ሳይነቅል ነው ከመኪናዋ የወረደው፡፡ ስላመነኝ ደስ አለኝ፡፡ ሚስኪን በመሆኑ ደግሞ አዘንኩለት፡፡ ከዛሬ ውጪ አይቼው ሆነ አይቶኝ አያውቅም፡፡ መኪናዋን አስነስቼ ብጠፋበት ምን ያመጣል? የት አባቱ ይይዘኛል? ከልጅቷ ጋር መኪናዋን ለመስረቅ ድራማ እየሰራንበት እንዳልሆነ በምን አወቀስ...? በሚስኪንነቱ አዘንኩለት፡፡

የመኪናዋን ዕቃ ማስቀመጫ ስከፍተው የዕጣፈሏ እና ህልምሽን ንገሪኝ የተሰኙ የሲድኒ ሸልደን መፅሐፍ አየሁ... ሁለቱንም አንብቤያቸዋለሁ በጣም አሪፍ ናቸው... ከነበሩበት ቦታ አስቀመጥኳቸው... ስጎረጉር ድንገት ከመፅሐፍቱ ስር በጋዜጣ የተጠቀለለ ነገር አየሁ፡፡

ሳብኩት:: ገለጥኩት:: ቀልቤ ነው የተገፈፈው! ሽጉጥ ነው!! እውነተኛ ሽጉጥ!! እየፈራሁ በእጄ ያዝኩት! ከዚያ በፍጥነት በህይወቴ ሽጉጥ ስለማልወድ ከቦታው አስቀመጥኩት... ምናልባት ማታ ማታ ሌባ እና አስቸጋሪ ነገሮች ቢያጋጥሙት ሊከላከልበት ይሆናል! ግን ከየት ገዝቶት ይሆን? እኔ ሽጉጥ የሚይዙ ሰዎች አይመቹኝም:: ፈሪ እና ከሰው መጣላት አባዜ ያለባቸው ሰዎች ይመስሉኛል...

ለማንኛውም አርባዋ ደቂቃ እስኪታልፍ ራሴን በሙዚቃ ዘና ለማድረግ ወሰንኩና መንፈሴን ለሙዚቃው ሸጥኩት::

በአበራ ሞላ ያምራል አገሬ ወዝወዝ አልኩኝ... በአወዛጋቢው እና የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ መዲና ላይ ሐውልት በተሰራለት ሀሺሻሙ አፄ ኃይለስላሴ አምላኬ ናቸው ብሎ በሚያመልካቸው ሚች ቦብ ማርሊይ ዋን ላቭ ሙዚቃ ሽርብትን አልኩኝ... ትርጉሙ ባይገባኝም ድምፁ በጣም ደስ ስለሚለኝ በንጉሱ ታምራት ያኒ የተሰኘ አሮምኛ ሙዚቃ አብሬው ዘፈንኩኝ... በዘመናዊው የኢትዮጵያ ወጣት የሙዚቃ ንጉስ ቴዲ አፍሮ ጃ-ያስተሰርያል...

… በእስራ ሰባት መርፌ በጠቀመው ቁምጣ
ለዘውድ ያጎፈረው ዙፋን ላይ ቢወጣ
እንዳምናው ባለ ቀይ የአምናውን ከቀጣ
አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ...

ሙዚቃ በትዝታ ወደ ኋላ ተመለስኩ! መቼም የማትረሳኝ ሚያዝያ 1997 ላይ... በኔ ሀ1997ዓ.ም ላይ ህሳቤ ድቅን አለች... ለአንድ አፍታ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ትዝ አለኝ! ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ የሆነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ትዝ አለኝ...

እንዴት ደቂቃው እንዳለቀ ሳላውቅ አርባዋ ደቂቃ ቀለጠች:: እንዳለው ሰሙን እንኳ ያልነገረኝ ሹፌር ዘና ባለ አረማመድ ሲመጣ አየሁት:: መኪናዋ ጋር ተጠጋ:: ከፍቶ ገባ:: ተቀመጠ::

ግእውነቱን ለመናገር እርጋታዋ ደስ ይላል!! በስራዋ ላይም በጣም ጎበዝ ነች!

ግን የሚሰማህን ንገረኝ ካልከኝ ማሳጅ ቤት የምትሰራ ሴት የምታዋጣህ አይመስለኝም! የሁሉም ናት! ገንዘብ ያለው ሁሉ ይገዛታል! ለማንኛውም ሌላ የምረዳህ ነገር አለ?"

" ይበቃኛል በጣም አመሠግናለሁ:: ፒያሣ ነው የምታደርሰኝ" አልኩትና ስለ ደሊላ የተነሳውን ወሬ ለመቀየር "በነገራችን ላይ ስላመንከኝ በጣም አመሠግናለሁ አልኩት::

"ምን ማለት ነው?"

"የመኪናህ ቁልፍ እኮ መኪናዋ ላይ ነው!! መኪናዋን በማስነሳት ብጠፋብህስ?"

"ቂ... ቂ... ቂ... ቂ" ከመኪናዋ ጣሪያ በላይ ነው የሳቀው:: ከዚያ እንደ ሚስኪን ህፃን እየተመለከተኝ

"ወይ አንተ የአዲስ አበባ ህዝብ በሙሉ ሌባ እና አጭበርባሪ ነው፤ ደግሞ ይህን ሸካካ የአዲስ አበባን ህዝብ ልመን? እዚህ መኪናዋ ላይ የሰካሁት ለሞራልህ ደስ እንዲልህ የውሸት ቁልፍ ነው፤ በዚያ ላይ እዚያ ጋር የተቀመጠው ሲስትሮ እንዲያይህ በኮድ ነግሬዋለሁ"

በውስጤ በሚስኪንነቴ አፍሬ ይሆን? እንጃ... ብቻ ዝም አልኩት:: እየሄድን ስለ ሽጉጡ ላነሳበት አልኩና አስፈላጊ መስሎ ስላልታየኝ በድጋሚ ዝም አልኩት:: ስለሴቶች መጥፎነት እየለፈለፈ እና ላዳዋን እያከነፈ ፒያሣ ካልኩበት ቦታ አደረሰኝ::

"ሌላ ጊዜ ከፈለከኝ" አለና ካርድ ሰጠኝ:: አመስግኜ ተለየሁት::

አሁን መሰለል የቀረኝ ህፃናትን የሚያተራምሰውን አስተማሪውን መሳይ ቁምላቸውን ነው:: እሱን ደግሞ ነገ ከሰዓት ከስራ አስፈቅጄ ወጥቼ እሰልለዋለሁ::

ፒያሳ እንደደረስኩ ለጓደኛዬ ራሞስ ደወልኩለት:: ሰፈሩ ፒያሳ ስለነበር በፍጥነት መጣ:: ዘና አልን፤ ራሞስ በጣም መመገብ የሚወደውን በርገር በላን:: አራዳ ህንፃ ላይ ወጥተን አንድ ላይ ዋሊያ ቢራ ቂ... አደረግን... ብቻ ስንሳሳቅ ቆይተን ወደ ምሽት ላይ ተለያየን... ለእኔ አሪፍ ቀን ነበረች::

pdf by @shuktus_books

# 6

## መሳይ...! አስመሳይ...!

አዎ ነኝ፡፡ አዎ የባንክ ቤት ሰራተኛ ነኝ፡፡ ደራሲ መሆን እፈልጋለሁ... በኢትዮጵያ ሥነፅሁፍ ውስጥ ቢያንስ አንድ ምርጥ ታሪክ ለመፃፍ እሻለሁ... ደራሲ ደግሞ ስለሚያውቀው ነገር ቢፅፍ በቁጥር አንድ ይመከራል ... እናም የመጀመሪያ መፅሐፌን ለመፃፍ እውነተኛ ገፀባህሪያትን እያሰባሰብኩ ነው፡፡ ልቦለድ መፃፍ አልፈልግም! በዚያ ላይ አሁን የልቦለድ ዘመን እያከተመ እየመጣ ነው፡፡ ከዘመናት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ የትርጉም መፅሐፍት ለጉድ ይነበቡ ነበር... ከዚያ ቀጥሎ የፍልስፍና መፅሐፍት... የፍልስፍና ዘመን ሲያበቃ እውነት ቀመስ ታሪኮች ... ከዚያ ፖለቲካ ቀመስ ታሪኮች... የሥነ ልቦና ... እያለ ቀጠለ... ብቻ ልቦለድ የማንበብ ዘመን እያሽቆለቆለ የመጣ ይመስላል... ስለዚህ እኔም ለመፃፍ የተነሳሁት እውነት ቀመስ የሆነ ታሪክ ነው... እንደ ዴርቶጋዳ፣ እንደ ፒያሣ መሀሙድ ጋር ጠብቂኝ.. እንደ በኢያሪኮ ከተማ... እንደ መከሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ ፤ እንደ ከሰማይ የወረደ ፍርፍር.. እንደ የጋዜጠኛው ማስታወሻ... እንደ የተቆለፈበት ቁልፍ... እንደ ያልተኖረ ልጅነት... የመሰሉ መፅሐፍት ሳይሆን የራሴን ለየት ያለች ታሪክ የያዘች መፅሐፍ፤ እናም ገፀባህሪያት እየፈለኩ ነው...

በነጋታው ከምሰራበት ባንክ ቤት ምሳዬን ከበላሁ በኋላ በቀጥታ አራት ኪሎ ጀርባ የሚገኘው ፋብዩለስ አካዳሚ አመራሁ፡፡ ከዘበኛው ጋር ሠላምታ ተለዋውጬ ምንም ሳንነጋገር መምህራን ስታፍ ገባሁ ፤ እንደ አፍንጫው ጠማማ የሆነ ሽበት ጣልጣል የደረገበት መምህር አስቆምኩና

"እባክህ መምህር መሳይን ፈልጌ ነበር" አልኩት፡፡

"መምህር መሳይ?"

"አዎ"

"ምን አስተማሪ ነው?"

"ዘጠነኛ ክፍል ፊዚክስ"

"እርግጠኛ ነህ እዚህ ት/ቤት ነው የሚያስተምረው? ምክንያቱም እዚህ ት/ቤት ሀያ ወንድ አስተማሪዎች ናቸው ያሉት፡፡ መሳይ የሚባል የለም፤ በዚያ ላይ ይህ ት/ቤት የሚያስተምረው እስከ ስምንተኛ ክፍል ነው! ስልኩ ካለህ ብትደውልለት ይሻላል"

"ስልኩ ስለማይሠራ ነው፤ እሺ ይህ ት/ቤት ሌላ ቦታ ቅርንጫፍ አለው እንዴ? ሀይስኩል የሚያስተምርበት?"

"ይሄ ብቻ ነው እስከ ስምንተኛ ክፍል ብቻ ነው የሚያስተምረው፡፡ የሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ፊዚክስ አስተማሪዎች ደግሞ ሁለቱም ሴቶች ናቸው፡፡ ት/ቤቱን ተሳስተህ እንዳይሆን?"

"አመሠግናለሁ" በማለት ከት/ቤቱ ወጣሁ፡፡ በእርግጠኝነት የነገረኝ ት/ቤት ስም ፋቢዩለስ አካዳሚ ነው፡፡ በቀጥታ ቤት በማምራት የመሳይ መታወቂያን በመያዝ መታወቂያ የወሰደበት ጉለሌ ክፍለ ከተማ አመራሁ፤ ቀበሌ ገብቼ መታወቂያው ህጋዊ ይሁን አይሁን ከመጠየቅ እና ሌላ ጣጣ ውስጥ ከምገባ ሀሳቤን በመቀየር እያጠያየኩ መታወቂያው ላይ የተጠቀሰውን የቤት አድራሻ እያጠያየኩ ደረስኩበት… አንድ ልጅ ሳገኝ ይቅርታ በመጠየቅ

"እዚህ ሰፈር ነህ ወንድሜ"

"ነኝ"

"የአነ መሳይ ቁምላቸው ቤት የቱ ነው? የቤት ቁጥር 144?"

"ስንት?"

"144"

"ማን ነው ያልከው?"

"መሳይ ቁምላቸው"

"144?? የእነ ጋሽ ታሪኩ መኪታ ቤት ነው፤ እንደዚህ የሚባል ሰው የለም፤ ምናልባት አድራሻ ተሳስተህ እንዳይሆን"

"እሺ እመሠግናለሁ" በማለት ተለየሁት፡፡ የቀበሌ መታወቂያው ላይ የተመዘገበውን የሌሮጋ ጊዜ ተጠሪ ስልክ ላይ ደወልኩ፡፡ አገልግሎት የማይሰጥ ስልክ እንደሆነ ይገልፃል... የሆነ ነገር እንዳለ ሸተተኝ፤ እናም ይበልጥ ይህን ሰው ለመሰለል አቀድኩኝ፤ የመታወቂያ ወረቀቱ የውሸት እንደሆነ ገባኝ፤ በዚች ሰንት ወንጀል በሚሰራባት አዲስ አበባ እንዲት የመታወቂያ ወረቀት አስመስሎ መስራት ብርቅ ይሆናል እንዴ?

ይህ ከሆነ በአራተኛው ቀን ሐሙስ ጠዋት ስራ እርፍጂ ለመግባት ወሰንኩና መሳይ ጠዋት ሲወጣ ሳላስጠጣ ተከተልኩት፡፡ ታክሲ የሚያዝበት ጋር ሲደርስ ላዳ ውስጥ ገባ፡፡ እኔም በፍጥነት ላዳ በመያዝ ተከተልኩት... ግሎባል ሆቴል ጋር ወረደ፡፡ በእግር ከግሎባል ሆቴል ጀርባ ገባ፡፡ ባለ ላዳው ቆሞ እንዲጠብቀኝ ነግሬው ከመኪናዋ ወርጄ ምናልባት ወደ ኋላ ሲገላመጥ እንዳያየኝ ራሴን በጨርቅ ሸፍኜ እና ይበልጥ ያደረኩትን ኮፍያ ዝቅ በማድረግ ተከተልኩት፡፡ ብዙም ሳይጓዝ የሆነ የሚያምር ትልቅ ቪላ ቤት ውስጥ ገባ፡፡ ራሴን ነቅንቄ እና ቤቱን ከርቀት ሳላስጠጣ በሞባይሌ ፎቶ አንስቼው ከቦታው ጠፋሁ፡፡ መኪናዋ ውስጥ በመግባት መስሪያ ቤቴ አካባቢ ወረድኩ፡፡

መስሪያ ቤት ስለመሳይ ቁምላቸው ሳውጠነጥን ዋልኩ... መሳይ እንዳለው አስተማሪ ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል? ትንንሽ ህፃናቱንስ ለወሲብ ከየት ነው የሚያመጣቸውስ? አሸባሪ? ቅጥር ነፍሰገዳይ? ደህንነት? ሌባ?... ሰላይ?... ወይስ ምን?

ከመስሪያ ቤት ስወጣ ይህን ዜና እና ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ከጓደኛዬ ራሞስ ጋር ለመወያየት በጣም የሚወደውን አፕል ገዝቼለት በዚያው ሳልደውልለት ሰርፕራይዝ ላደርገው ፒያሳ ጣይቱ ሆቴል ጀርባ የሚገኘው ቤቱ አመራሁ፡፡ ምክንያቱ ባይገባኝም ውስጤ ግን ፍርሃት ፍርሃት አለኝ ... የሆነ አስጠሊታ ስሜት ተሰማኝ... ከውስጤ ጋር እየታገልኩ ወደ ራሞስ ቤት ቀረብኩኝ...

# 7

# አ... ሞት!

የፈጣሪ ያለህ...!!

እነሆ የሰማውትን እና በዓይኔ በብረቱ ያየሁትን ነገር ማመን ነው ያቃተኝ... ያ ከልጅነታችን ጀምሮ ስንት ነገር አብረን ያሳለፍነው ጓደኛዬ... ያ የእውቀት ካዝና የሆነ ጓደኛዬ... ያ ለሰው አዛኝ የሆነ ጓደኛዬ ... ያ በእውቀት ሲሞላኝ የነበረ ውድ ጓደኛዬ... ያ ሲመክረኝ የነበረው ጓደኛዬ... ዛሬ ጠዋት ከቤት ከወጣ አንድ ሰዓት በኋላ በሲኖትራክ መኪና ተጨፈላልቆ እንደሞተ ሲነግሩኝ... ድንኳን ተጥሎ ... ሰዎች አሪ እያሉ ሲያለቅሱ በዓይኔ ስመለከት ... ልቤ በሀዘን ተሞላ... ልቤ በሀዘን ደማ... ልቤ ላለማመን አመነ... ከጎኔ የሆነ ነገር እንደተነጠቁ ተረዳሁ... ህይወት የማትጨበጥ ከንቱ እንደሆነች ተገነዘብኩ.. ዋቃን ልወቅሰው ትንሽ ነበር የቀረኝ...

በዚች ቅፅበት እንኳ አዕምሮዬ ላይ ያንቃጨለብኝ የዚያ ውድ ጓደኛዬ ራሞስ አባባል ነው "በተቻለን መጠን በእያንዳንዷ ደቂቃ የሆነች መልካም ነገር ለማድረግ መጣር ነው፤ ምክንያቱም በህይወታችን ውስጥ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ማንም የሚያውቅ የለም!!"

በጓደኛዬ ሞት የተነሳ በልቤ ውስጥ ያለውን ስብራት እንዴት አድርጌ ልግለፀው? እይ እኔን ብሎ ደራሲ? ልቤ ውስጥ ያለውን ሀዘን እንኳ በቅጡ ለመግለፅ ያልቻልኩ እንዴት ስለ ሌሎች ሰዎች የሚሰማቸውን መፃፍ እችላለሁ? ስቅስቅ ብዬ እያለቀስኩ ነው... እውነትም ሞት ሰላቢ ነው::

ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሞት ሰላቢነት ያወራሁት ከራሞስ ጋር የሶስተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለን ነበር፡፡ አንድ ዝነኛ ሰው ለመቅበር አራት ኪሎ የሚገኘው ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ሄደን በዚያው ግቢው ውስጥ የተቀበሩትን ሰዎች እና የተፃፉትን ጥቅሶች እያየን ነበር ወሬ የጀመርነው

"እንደ ሀበሻ እኮ ከንቱ ፍጡር ያለ አይመስለኝም" አለኝ፡፡

"እንዴት?" አልኩት፡፡

"ተመልከት! እስቲ ገምት ለእነዚህ አብነበረዶች ስንት የሚወጣ ይመስልሃል?"

"3,000 ሺ ብር"

"አንተ በጣም ሚስኪን ነህ! ኢትዮጵያ ውስጥ ለአንድ ሀብታም ቀብር የሚወጣውን ወጪ ለማወቅ ፈልጌ አንድ ጊዜ ፒያሣ ቸርችል ጎዳና የሚገኙት ሬሣ መሸጫ ቤት ጎራ ብዬ ከአንድ ወጣት ጋር ሳወራ ምን እንዳለኝ ታውቃለህ? 'ትንሹ የደሀ መቀበሪያ ሬሣ ዋጋ 500 ብር ነው፡፡ የሀገር ውስጥ ሻል ያሉ ከ2000 ሺ እስከ 10,000 ሺ ብር እሉ የሚያወጡ ይህ የኢንግሊዝ ሬሣ ሣጥን ባለመስታወቱ እና መለስ ዜናዊ እና ጥላሁን ገሰሰ የተቀበሩበት ሲሆን እኛ 40,000 ሺ ብር ነው የምንሸጠው፡፡ በተጨማሪ ለአበባ፣ ለቀብር ሥርዓት አስፈፃሚዎች እስከ 10,000 ሺ ብር እንቀበላለን ባጠቃላይ ለአንድ ሀብታም 55,000 ሺ ብር ድረስ እንቀበላለን' ነበር ያለኝ የሀብታሞቹን ተወውና ደሀ እንኳ ሲሞት በእኛ በሀበሻ ምድር በህይወት ሳለህ ከሚደረግልህ ይልቅ ስትሞት ይሽረገድልሃል፡፡"

"ይህ አበሻ ምቀኛ ነው ለሚለው ማረጋገጫ አንዱ ይህ ነው፡፡ በቁምህ ህይወቴን ልለውጥበት 1,000 ብር ብቻ ስጡኝ ብለህ ብትለምን የሚሰጥህ የለም!! ባንፃሩ ስትሞት ለመቃብርህ 10,000 ሺ ብር ይሰጥሃል፤ እየህ ምቀኛ በህይወት ካለህ ይጨክንብሃል፤ ስትሞት ግን የትም ስለማትደርስ ይረዳሃል! አየርላንድ እና ሰለሞን አይስላንድ ስትሞት ጥሩ ባህል አላቸው፡፡ ቀለል ያለች የቀብር ሥነስርዓት ይዘጋጅልሃል! በመቃብርህ ላይ ከመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፣ አባባሎች፣ ፎቶህ ምናምን አይደረግም... በሕይወት ዘመንህ ለአገሪቱ መልካም የሰራህበት ዘመን ይጣራና ያ ዘመን ብቻ ይፃፍልሃል፡፡ ለምሳሌ "ከ2000-2006" የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ እየህ በሁለቱ ሀገራት የኖርክበት ሳይሆን የሰራህበት ዘመን ነው የሚፃፍልህ... በህይወት መስመር ላይ የሰዎች እኩልነት የሚለካበት እና አድሎ የሌለበት በሞት ነው፡፡ ሞትን የመሰለ ሰላቢ ነገር በምድር ላይ የለም፡፡ ምንም ሆንክ ምንም ትሞታለህ! ሞት እውነተኛ ዳኛ

ነው፤ ከሞት ጋር ተያይዞ እኮ ለበርካታ ዘመናት ሳይንቲስቶች ግብግብ አድርገዋል፤ ግን የሰውን ልጅ ከሞት ለመታደግ ያደረጉት ጥረት ሁሉ ከንቱ ነው፤ ሞት ከሳይንስ በላይ ነው፤ ለምሳሌ በዓለም ታሪክ ጥንታዊ ግብፃዊያን ናቸው ሬሳ ማድረቂያ መሚ ለመጀመሪያ ጊዜ የፈጠሩት፡፡ በዚያን ዘመን አንድ ሰው ሲሞት የሚቀበረው ደግሞ ነገ ህይወት አለ፤ ሰው ከሞተ ከ70 ዓመት በኋላ በድጋሚ ይነሳል ብለው ስለሚያስቡ አብረው ከእነ ዕቃው ይቀብሩት ነበር፤ በተለይ ባለስልጣን ከሆነ ከሚወዳቸው ሚስቶቹ መሀከል በጣም የሚወዳት ባትሞትም እንኳ ከእነ ህይወቷ አብራው ትቀበር ነበር፤ ዘግናኝ ነው አይደለም?"

"ምን ጥያቄ አለው?"

"በሀንዳዊያን እምነት ሰው የተፈጠረው ከአፈር እና እስትንፋስ ነው፡፡ ስለዚህ ሰው ሲሞት አይቀበርም፡፡ ይቃጠላል፤ ይህ ባህላቸው ዛሬም ድረስ ይሰራል፤ ታዲያ የተቃጠለው ሰው አመድ ጋንጂስ የተባለው ቅዱስ ወንዝ ውስጥ ይጨመራል፤ ምክንያቱም እንዲባረክ ነው፡፡ በሀንዳዊያን እምነት ሁለት መላምቶች አሉ፡፡ ሰው ሲሞት መጨረሻው ምንድን ነው? ከሞት በኋላ ምን አለ? ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ ምላሻቸው ሰው ሲሞት መጨረሻው ለምሳሌ እናቶች ሲሞቱ በቀጥታ ወደ ከዋክብትነት ይለወጡና ማታ ማታ ብርሃን ይሰጡናል፤ በዚህ የተነሳ ማታ ማታ የምናያቸው ኮከቦች የሞቱ እናቶች ናቸው ሲሉ ወጣት ሴቶች እና ወንዶች ሲሞቱ ከሰባት ትውልድ በኋላ ወደ ተለያዩ እንስሳት ተለውጠው በድጋሚ መሬት ላይ ህይወት ዘርተው ይመለሳሉ የሚል አስተሳሰብ አላቸው፡፡ በጣም ጥሩ ሰው ከነበርክ ቢራቢሮ፣ እርግብ፣ ትሆናለህ ሲሉህ ከፉ ሰው ከነበርክ ደግሞ ጅብ፣ ጥንብአንሳ፣ ቅማል፣ አይጥ፣ እባብ… ወዘተ ሆነህ በድጋሚ ወደ መሬት ትመጣለህ ይላሉ፤ በዚህ መሠረት ሥጋ ይሞታል፤ ነፍስህ ግን ዘላለማዊ ናት ይላሉ፡፡ ከዚው ሞት ጋር ተያይዞ የሰው ልጅ ሆነ እንስሳት ሲሞቱ እኩል ናቸው የሚሉ ወገኖች አሉ፤ ለዚህ ዋነኛ መከራከሪያቸው መፅሐፍ ቅዱስ ላይ እሪት ዘፍጥረት 3፡19 እና መክ. 3፡19-20 ያለውን ያነሳሉ አስታወስከው?"

"አላስታወስኩትም"

"ማስታወስ አለብህ! ለመሆኑ መፅሐፍ ቅዱስ አንብበህ ጨረስክ?"

"አልጨረስኩም"

"ታዲያ ምኑን ደራሲ እሆናለሁ ብለህ ትመኛለህ!? መፅሐፍ ቅዱስንማ በጣም ማንበብ ያለብህ መፅሐፍ ነው፤ ሌላው ቢቀር እኮ ስለ ሥነ ፅሑፍ በተለይ ስለቃላት አጣጣል

ነገር ትማርበታለህ! በዚያ ላይ በምንፅፈው መፅሐፍ ውስጥ አንዱ ገፀባህሪይ ስለ እግዚአብሔር የሚያወራ ሊሆን ይችላል! ያን ደግሞ ለመፃፍ የግድ ማወቅ አለብህ!! ለማንኛውም አሪት ዘፍጥረት 3፡19 ላይ

> 'ወደ መጣህበት መሬት እስከትመለስ በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ፤ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህ' ሲል በመክብብ ላይም 'የሰው ልጆችና የእንስሳ ዕድል ፈንታ አንድ ነው፤ ድርሻቸውም ትክክል ነው፤ አንዱ እንደሚሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል ፤ የሁሉም እስትንፋስ አንድ ነው! ሁሉም ከንቱ ነውና ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም! ሁሉ ወደ አንድ ቦታ ይሄዳል፤ ሁሉ ከአፈር ነው፤ ሁሉም ወደ አፈር ይመለሳል'

ይላል:: ይህን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ነው እንግዲህ ሥጋ ምድር ላይ ይቀራል! ነፍስ ግን አትሞትም ይላሉ:: ይህን ሀሳብ ይዘን ደግሞ እውነት ከሞት በኋላ ገነት እና ሲኦል አለ? የሚል ሀሳብ ማንሳት እንችላለን፤ ለማንኛውም ከዚው ከሞት ጋር በተያያዘ ሶቅራጥስ ዘላለማዊነት ለእኔ በሞት ውስጥ የማገኛት እንዲት ሌሊት ነች' ሲል ሌላኛው ፈላስፋ ኒቼ ደግሞ 'ሞት ባይፈጠር እንኳ የሰው ልጅ ሞትን መፍጠሩ አይቀርም' ሲል ዝነኛው ሾፐርሕውር ደግሞ 'የሰው ልጅ አኮ የሚሞተው ገና ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ ነው' ይላል:: ኮንፊሽየስ ደግሞ 'ስለ ምድራዊ ህይወት በወጉ ያላወቅን ከሞት በኋላ ስላለው እንዴት ማወቅ ይቻላል?' የሚል አሪፍ ጥያቄ ያነሳል:: እንደ አኩይንስ ያሉ መጤ ፈላስፎች 'ስለሞት ከማሰብ ስለ ህይወት ማሰብ ሀይል ይሰጣል' ይላሉ:: ይህ ሁሉ እንዳለ ሞትን ይበልጥ ጣፋጭ የሚያደርጋት ሞት ሰላቢ መሆኑ እና መቼ እንደምንሞት አለማወቃችን ነው:: እንደ እኛ ያሉ ወደ እምነቱ ያዘነበሉ ሊቃውንቶች ደግሞ 'በሞት የምታምን ከሆነ እና እንደምትሞት ካወክ በእያንዳንዱ ቀን ጥሩ እና መልካም ነገር ብቻ ለማድረግ ጣር! ራስህን ለማስደሰት ጣር! የዚያን ጊዜ ሞትን ማሸነፍ ትጀምራለህ' ይላሉ:: እውነታቸውን ነው እጅግ ብዙ ብር እያላቸው የሚስገበገቡ ሰዎች አሉ፤

ለህክምና እንኳ ብር ማውጣት ሰስተው ያን በርካታ ብራቸውን ጥለው የሚሞቱ ከንቱዎች አሉ። እዚህ ጋር አንድ ወሳኝ ጥያቄ ይነሳል። የምንሞትበት ቀን የተፃፈ ነው? ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ በበርካታ ሰዎች ላይ በተደረጉ ጥናቶች 45% 'አዎ የምንሞትበት ቀን በእግዚአብሔር ዘንድ የተፃፈ ነው፤ አንድ ህፃን ልጅ ገና ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ የሚሞትበት ቀኑም አብሮት ይፃፍለታል' ሲሉ የሚሞትበት ሁኔታ ላይ ውበት ለመፍጠር አጋጣሚዎች ግን ይቀናበሩለታል የሚል እይታ አላቸው"

"ለምሳሌ፤ በመኪና ግጭት፣ በጦርነት፣ በድብድብ፣ በእርጅና፣ በመታመም፣ በምግብ መመረዝ፣ በመድኃኒት ፣ በHIV ፣ በእንቅፋት፣ በትንታ... መሰል ይሞታል! ሲሉ እነዚህ የተፃፈልን ቀን ስላለ በተፃፈልን ቀን እንሞታለን የሚሉ ሰዎች የፈለግነውን ነገር ብናደርግ ከዚያች የተፃፈችልን ቀን አንዲት ሴኮንድ እንኳ ዝንፍ አንልም ብለው ሲያምኑ በተቃራኒው 55% የሚሆኑት 'እርግጥ የሰው ልጅ ዕጣ ፋንታ ሲፃፍ ሞት አብሮት የተፃፈለት እንደሆነ ቢረዱም የእነርሱ ሀሳብ እንሞታለን ግን በአራት ነጥብ የተፃፈልን ቀን የለም፤ የምንሞትበትን እልያም እድሜያችንን እስፖርት በመስራት፣ መድኃኒት በመጠቀም፣ ራስን ከሱሶች በመጠበቅ፣ መልካም ነገር በመስራት፣ ህክምና በመከታተል እድሜን ማስረዘም ይቻላል' ይላሉ። ሞት ሰላቢ አይደለም ይላሉ። ስለሞት ከተነሳ አሁንም ጥንታዊ ህንዶች የሚሉት ነገር አላቸው። ሁለት የሞት መድኃኒቶች አሉ። 'አንደኛው ሞትን የምናሸንፈው ለሀገር እና ለሰው ልጆች ሁሉ የሚጠቅም አስተዋይ ተደርጎ የሚያሳድጉትን ልጅ መውለድ ነው፤ ሁለተኛው ሳለመሞት የሚቻልበት እና እስከ መጨረሻው ለመኖር የሚቻልበት መንገድ ራስን ለአምላክ አሳልፎ መስጠት ነው' ይላሉ። በተጨማሪ ህንዳዊያን 'ስለሞት አብዝቶ መጨነቅ እና ሞትን አብዝቶ መፍራት ሞትን መጥራት ነው' ይላሉ። ወደ ኢትዮጵያ እንመለስ... ከሞት ጋር በተያያዘ ስንት የሀገራችንን ምሳሌያዊ አነጋገሮች ታውቃለህ?"

"አራት ያህል አውቃለሁ"

"የመጀመሪያ?"

"ሞቴን ሞት ወሰደው"

"ሌላ?"

"ሞትህ እንደ ህይወትህ ፣ ህይወትህ እንደሞትህ"

"ሌላ?"

"ሞት ሳይቀርለት ምክንያቱ በይሁዳ ሆነበት"

"የመጨረሻው?"

"ሞትም ሞት ነው ያለሀያ ጉበት ነው"

"ጥሩ ነው፡፡ እኔ የተወሰኑ ልጨምርልህ፡-

⇒ የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ የሞተ ሰው አይመለስ

⇒ ሞት ርስት ነው መፈራቱ ለምንድን ነው ?

⇒ ሞት ሲደርስ ቁስ ጦር ሲደርስ ፈረስ

⇒ ሞት በእንቅልፍ ይለመዳል

⇒ ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል

⇒ ሞት አይለመድ ጎሽ አይጠመድ

⇒ ሞትና ዕድሜ ቢፈሩት አይቀርም

⇒ ሞትን ማሰብ ከሁሉ መሰብሰብ

⇒ ሞትን የሰጠ ቀባሪ አይነሳም

ይጠቀሳሉ፡፡ በእኛ ኢትዮጵያዊያን ባህል ሰው ሲሞት ቀብር ፣ ሰልስት፣ አርባ፣ ሰማንያ የመሰሉ ነገሮች አሉ፡፡ ከሞት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ወጣ ወጣ ያሉ ባህሎች አሉ፡፡ ከሀገራችን ለመጀመር በተለይ በደቡብ ከሰል ሰው ሲሞት ማልቀስ የለብንም ብለው በሙዚቃ እየጨፈሩ የሚቀብሩ እንዳሉ መቼም ታውቃለህ? የፔሩ ናቡኪ ጎሳዎች አሁን ድረስ አንድ ህፃን ልጅ ሲወለድ ለመላው ነዋሪ ይነገርና ህፃን ልጁን የወለዱ ሰዎች ጋር ለቅሶ ይደርሳሉ! በተቃራኒው ደግሞ ከማንኛውም ነዋሪ ቤት ሰው ሲሞት ከማልቀስ እና ከማዘን ይልቅ እንኳን ደስ አላችሁ ተብለው ስጦታ ይሰጣሉ፡፡ ቡሩንዲ ውስጥ አንድ ጎሣ አለ ከአንድ ሰው ቤት አንድ ሰው ሲሞት መላዕከ ሞት ሌላ ተጨማሪ ሰው ከዚያ ቤት እና ሰፈር እንዳወስድ ቀይ ዶሮ ይታረድና ከሟች ጋር ይቀበራል! ጊኒ ውስጥ አሁን ድረስ ፐኩቺ የተባሉ ጎሳዎች ሰው ሲሞት ያ የሞተው ሰው ሙት መንፈስ ሌላ ሰው እንዳይጠራ ቤታቸውን በከፍተኛ ጭስ ለሶስት ቀናት ያጥናሉ፤ ሟች ሲተኛበት የነበረው አልጋ ወዲያው ይቃጠላል! እስቲ የማስታወስ ጥያቄ ልጠይቅህ?"

"ቀጥል"

"ግጥም ነው"

"ልሞክር"

"ዝም ያለው ዘመዴ እኔ ሳጣጥር! ሞት ቢሉት መጣ አልቅሶ ሲቀብር… በሚል የሚጀምረው የማን ግጥም ነው?"

"እንዴ! የመንግስቱ ለማ "ዘመዴ" ግጥም ነዋ! ስድስተኛ ክፍል የተማርነው…"

"ልጨምርልህ?"

"ቀጥል"

"ለሁሉም ጊዜ አለው ብሏል ሰለሞን… እጠይቀው ነበር በተገናኘን ሞት … የሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን?"

"አላስታወስኩትም"

"ቀሽም! የቤት ስራ ነው፤ በነገራችን ላይ እኔ ብዙ ሳልኖር ነው በቅርቡ የምሞተው"

"ምን ማለት ነው?"

"ሌላ ጊዜ እሜውትሃለሁ"

… ብቻ ስለሞት፣ ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት፣ ስለነፍስ… በተለይ ነፍስ የት እንደምትቀመጥ… ሞትን በተመለከተ ከሀይማኖት፣ ከፍልስፍና ፣ ከሳይንስ አንፃር ያሳወቀኝ ራሞስ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ራሞስ በሰሳቢው ሞት ከእጠገቤ ተነጥቋል! ሠላሣ ዓመት እንኳ መሬት ላይ ሳይኖር፣ ፍቅረኛ ሳይዝ፣ ልጅ ሳይወልድ፣ እውቀትን እንዳሳደደ፣ በጣም ሲመኘው የነበረውን ህልሙን እንኳ ሳያሳካ! ከውጥን ሳያደርስ! በመኪና ተጨፍልቆ ሞተ!!

■
■
■
■
▼

ምን ይደረጋል እንግዲህ…?? በቃ እውነታውን እየመረረኝ! እያንገሸገሸኝ! ተቀበልኩት፡፡ ያ መንፈሳዊ ቅናት እንዲሰማኝ የሚያደርገኝ ጓደኛዬ … ያ ብቸኛ ጓደኛዬ! ያ ሲመክረኝ የነበረ ጓደኛዬ! ያ ሲያበረታታኝ የነበረ ጓደኛዬ… ተለየኝ፡፡ ተቀበረ፡፡ ሰሳቢው ሞት ሰለበው!!

# 8

# ፍሊጋ

ከባድ ነው። አዎ በጣም ከባድ ነው። ያስፈራል። አዎ በጣም ያስፈራል... ግን ቀናት በቀናት ላይ ሲደረቡ፣ ሰልስቱ ሲያልቅ... አንድ ሳምንት ሲያልፍ እውነታውን ተቀበልኩት... በተለይ ያቺ ሚስኪን ብቸኛ ወጣት ደሊላ በማፅናናቱ በጣም አሪፍ ነበረች! አንድም ቀን ከለቅሶ ቤት ቀርታ አታውቅም ነበር! በሳምንቱ ወደ ቤቴ ስመለስ ራሱ በጣም ታፅናናኝ ነበር... እናም የጓደኛዬን ሞት እየመረረኝም! እያንገሸገሸኝም ተቀበልኩት። በቃ ህይወት ማለት እንደዚህ ነች...!!

የጓደኛዬ ራሞስ ሞት ምናልባት ከእኔ እየተደበቀ ከሚጫወተው ቁማር ጋር ተያይዞ በአጋጣሚ ባይሆንስ የሚል ሀሳብ ድንገት ስለመጣብኝ የራሞስን ጉዳይ የያዘው መርማሪ ጋር ሄድኩኝ... ወጣት እና ረጋ ያለ መርማሪ ነው። እንዴት እንዳወቀኝ ግራ ቢገባኝም ገና እንዳየኝ ራሱ መጥቶ ሰላምታ ሰጠኝ ...

"ኢንስፔክተር አወቀ አንድ ነገር ለማወቅ ፈልጌ ነበር"

"ይቻላል" አለኝ በፍፁም ትህትና።

"ስለ ገዳዩዋ ማንነት ለማወቅ እችላለሁ?"

"ለምን?"

"ወንጀሉ የተፈፀመው በአጋጣሚ ባይሆንስ?"

"ይህ የእኔ ግዴታ ነው፤ አደጋው ከተፈፀመበት ደቂቃ ጀምሮ ስለ ገጪዋ ማንነት ለማጣራት ሙከራ እና ስለላ ለአንድ ሳምንት ያህል አድርጌ ነበር፡፡ ጓደኛህን የገጨችው የሀያ ሁለት ዓመት የኮሌጅ ተማሪ ነች፡፡ መንጃ ፍቃድ የላትም፡፡ በድፍረት የአባቷን መኪና ከቤት ይዛ ወጥታ ነው ድንገት ሲኖትራክ ከኋላዋ በፍጥነት ሲከተላት ከዚያ ከሲኖትራኩ ለማምለጥ ስትል ጓደኛህን ገጭታ የገደለችው ... እኔ ባደረኩት ምርመራ ሌላ የተደበቀ ነገር የለም ፤ ልጅቷም እንደሰማኸው ፍርድ ቤት ቀርባ ጥፋቷን አምና ወደ ዝዋይ እስር ቤት በቀጥታ ተልካለች! የሚገርምህ ከዚህ በፊት ራሱ የ18 ዓመት ወጣት ሆና ሰው በምሽት ገጭታ እንደነበር እና በወቅቱ ጉዳዩን ለያዘው ሆዳም መርማሪ ገንዘብ ጉቦ በመስጠት እንደወጣች ሁሉ ተደርሶባታል! ከዚህ ውጪ ነፍሱን ይማረውና በሟች ጓደኛህ ዙሪያ ባደረኩት ስለላ ከማንም ጋር ንኪኪ የሌለው! ሥራውን በትኩረት የሚሠራ! አብዛኛውን ሰዓቱን በንባብ የሚያሳልፍ ወጣት እንደሆነ ተረድቻለሁ!! ከዚህ ውጪ ሌላ እውነታ የለም፡፡ ፋይሉም በእራት ነጥብ ተዘግቷል"

... በቃ! እውነታውን ከመቀበል ውጪ ምንም የማደርገው ነገር የለም፡፡ በእርግጥ ስለ ኢንስፔክተር አወቀ መልካምነት! ለፍትህ ታማኝነት ! ታታሪ ሰራተኝነት ! በምንም መልኩ ለውሸት እና ከሙሰኞች ጋር እንደማይደራደር... ሙያውን በእውነት እና በክብር እንደሚሰራ ብርካቶች ለቅሶ ቤት ውስጥ ሲያወሩ ሰምቻለሁ... ለስራው ብቻ ከፍተኛ ፍቅር እንዳለው ሠምቻለሁ እናም አመንኩት፡፡

"አመሠግናለሁ ኢንስፔክተር"

"ምንም አይደለም! የኔ ትልቁ እርካታ ህግ ስትከበር ማየት ነው"

ከተቀመጥኩበት ወንበር ላይ ተነስቼ ልወጣ አልኩና ድንገት ትዝ ብሎኝ መልሼ ተቀመጥኩኝ፡፡

"ኢንስፔክተር እኔ ቤት የተከራየ አንድ አስተማሪ አለ፡፡ የሰጠኝ መታወቂያ ላይ አስተማሪ ይላል! ግን አስተማሪ አይመስለኝም የሆነ የሚያጠራጥር ነገር ስላለ ይህን ሰው ብትከታተለው"

"እሪፍ መረጃ..."

የተወሰነ ነገር አወራን፡፡ ልወጣ ስል በጣም በትኩረት እየተመለከተኝ

"ስለዚህ ጉዳይ ለማንም ሰው እንዳትናገር ምናልባት ሰውየው ሀይለኛ ከሆነ ባንተ ላይ አደጋ ሊያደርስ ይችላል፤ ለማንኛውም አንተም በጥንቃቄ ተከታተለው ሁኔታውን በ72 ሰዓታት ውስጥ አስታውቅሃለሁ! እመሠግናለሁ" አለኝ፡፡

ከስንት ጊዜ በኋላ መጠጥ ቤት ሄድኩ፡፡ የኢትዮጵያ እድገት የቢራ እድገት ይመስላል፡፡ የቢራ አይነቶች ሰትድ በየዓመቱ እየፈሉ ናቸው፡፡ ገና ቂጡ ወንበር ላይ እንዳረፈ ... የሆነች ቀልቃላ አስተናጋጅ መጥታ ከወገቧ ሸብረክ ብላ

"ምን ልታዘዝ?" አለችኝ፡፡

"ቢራ ምን አለሽ?"

"ዋልያ፣ ዳሽን፣ በደሌ፣ ሜታ፣ ራያ፣ ሀበሻ ፣ ጊዮርጊስ፣ ዘመን፣ ሀምበር ፣ ሐረረ... የትኛውን ላምጣልህ?"

" እንደውም ቢራውን ተይውና አስቶቴንያ አምጭልኝ" አልኳት፡፡

ወይኔ! ቢራ እንኳ የሚያጣጣኝ ጓደኛ ስለሌለኝ ይብልጥ ብቸኝነት ተሰማኝ፡፡ ባዶነት ተሰማኝ፡፡ የሆነ ነገር እንደጎደለኝ ተሰማኝ... እናም ከስንት ጊዜ በኋላ ሰከሬ ወደ ቤት ገባሁ፡፡

ጠዋት እንደምንም ከመኝታዬ ተነስቼ፤ ቁርስም ሳልበላ ወደ ባንክ ቤት ስራዬ ላመራ ስጣደፍ ጋዜጠኛው እንዳልካቸው ሰው አትመን መጣ፡፡ ድንገት ሳላስበው ጥምጥም ብሎብኝ እቅፍ አድርጎ ግንባሬን ሳመኝ፡፡ ከዚያ

"አሁን ሰዓት ስለሌለህ ምሳ ሰዓት ላይ መስሪያ ቤትህ መጥቼ እናወራለን ፍቃደኛ ነህ?"

"ምንድን ነው? ለመልካም ዜና ነው?"

"በጣም!!"

"ችግር የለውም ደውልልኝ"

"እመሠግናለሁ! 6:20 ደቂቃ ላይ መስሪያ ቤትህ አካባቢ ስደርስ እደውላለሁ! መልካም ቀን" አለኝና በፍጥነት ሄደ፡፡ የሆነ ነገር እንዳገኘ የፊቱ ብርሃን ያስታውቅ ነበር፡፡ እንደዚህ ደስተኛ ሆኖ አያውቅም፤ እኔም እስከዛሬ እንዲህ ፊቱ በደስታ በርቶ አይቼው

አላውቅም… መስሪያ ቤት ገብቼ… ያው የተለመደውን ስራዬን እየሰራሁ… ሳይታሰብ የምሳ ሰዓት ደረሰ::

ጋዜጠኛው እንዳልኳቸው እንዳለው 6:20 ደቂቃ ላይ ደወለ:: የመስሪያ ቤታችን ህንፃ ከሚገኝበት አንደኛ ፎቅ ላይ ካልዲስ መግዘናኛ ስለሚገኝ እዛው ተገናኘን:: ቀለል ያለ ምሳ በላን::

"ያው ሀዘን ላይ ሆነህ ያለፉትን ቀናት ስለ እኔ ደስታ ለመናገር ስለ ከበደኝ ነው:: በፊት እንዳልኩህ የኢትዮጵያ አምላክ ይተመሥገን ይሁንና ህልሜ እውን ሆኗል:: ነገ ማታ በቀጥታ ወደ ኢንግሊዝ እመራለሁ:: ለBBC ያቀረብኩት ማመልከቻ ተሳክቶልኛል!! ከተወዳደርነው 42 የአፍሪካ ጋዜጠኞች በሁለተኛነት ከፍተኛ ውጤት አምጥቼ አልፌያለሁ!! እናም ነገ ማታ ወደ ኢንግሊዝ እበራለሁ!!"

"አ! እንኳን ደስ አለህ!!" በማለት ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ጨበጥኩት:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ አንድ እውነተኛ ልማታዊ ጋዜጠኛ ልታጣ በመሆኗ ውስጤ ቅሬታ ተሰምቶታል::

"እና ያው ቤቱን ስታከራየኝ ውላችን ላይ እኔ መውጣት ከፈለኩ ከወር በፊት እንዳሳውቅህ፤ አንተም እኔን ማስወጣት ከፈለክ እኔን ከወር በፊት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እንደምትሰጠኝ የሚል ነበር፤ ስለዚህ በውላችን መሠረት የአንድ ወር ሂሳብ አንተ ተከራይ እስከምታገኝ እከፍላለሁ"

"በጭራሽ! ስለ እሱ አትጨነቅ በእርግጠኝነት ብዙ ወጪ አለብህ፤ በዚያ ላይ የማታውቀው ሀገር ስለምትሄድ ቢያንስ ገንዘብ መያዝ አለብህ!! ስለዚህ በጭራሽ ገንዘቡን አልቀበልህም! አባቴ ይሙት ብያለሁ አልቀበልህም"

"እግዚአብሔር ይስጥልኝ በእውነት መልካም ሰው ነህ! ውለታ መላሽ ያድርገኝ :: እንደነገርኩህ ቤተሰቦቼ ጅማ ናቸው:: ግዜ ስላጣሁ ወደ ጅማ መሄድ አልቻልኩም፤ ስለዚህ አንድ ውለታ እንድትውልልኝ ልለምንህ ነበር"

"ችግር የለውም የምችለው ጉዳይ ከሆነ እተባበርሃለሁ"

"መጀመሪያ በጣም ይቅርታ ሌላ የማስቸግረው ሰው ስለሌለኝ ነው:: ለእህቴ ነግሬያታለሁ ከአራት ቀናት በኋላ ትመጣለች ቤት ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች ትሰጠልኛለህ ፤ በተረፈ ቅድም ስወጣ ወደ ህምሳ መፅሐፍት ለዘበኛው ሰጥቼልሃለሁ፤ ያጋጣሚ ሆኖ እህቴ

ማንበብ ስለማትወድ ለአንተ ስጦታ አበርክቼልኃለሁ፡፡ ዛሬ ማታ እና ጠዋት በፍጥነት መስሪያ ቤት የምጨርሰው ጉዳይ ስላለኝ እዛው አዳሪ ነኝ፤ ከዚያ በቀጥታ ወደ አየር መንገድ ስለማመራ ሳንገናኝ ስለምንችል የቤቱ ቁልፍ ይኸው!! በተረፈ እንዳንተ ያለ በጣም ቀና የቤት አከራይ አይቼ አላውቅም!! በእውነት ከልብ ነው የማመሠግነው" በማለት በድጋሚ ከወንበሩ በመነሳት እቅፎ ሳመኝ፡፡ ወዲያው ተሰናብቶኝ ተለየኝ፡፡

ለምን እንደሆነ በግልፅ ባይገባኝም ቅር አለኝ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አሳዘነኝ፡፡ በአገሩ ኢትዮጵያ መኖር እየፈለገ የሥራ ነፃነት ስላጣ! የሥራ ነፃነትን ፍለጋ ከኢትዮጵያ እጅግ ርቆ ከፈረንጅ ሀገር መሄዱን ሳስብ ኢህአዴግን ጠላሁት! ለነገሩ ኢህአዴግን በጣም የጠላሁት በስንት ጉጉት ቅዳሜ ቅዳሜ እየጠበኩ የማነባቸውን አዲስ ጉዳይ መፅሔት እና ፋክት መፅሔትን ሲዘጋ ነው... አቤት! በሁለቱ መፅሔቶች ላይ እኮ ስንት ሀሳብ በየሳምንቱ ይፈልቅ ነበር...?? ስንት እውቀት... ስንት መረጃ... ስንት እውቀት አዘል ትንታኔ ይቀርብ ነበር... እናም ይህ ወጣት ጋዜጠኛ ከኢትዮጵያ በመውጣቱ ስለ እውነት ከልቤ ነው ያዘንኩት... መንገድ ያደርሳል መንገድ ይመልሳልና የፕሬስ ነፃነት በታሪካዊት ቅድስት አገር ኢትዮጵያ ሲመጣ መመለሱ አይቀርም!! "በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን...? (ትንቢተ ኤርሚያስ 13:23)

pdf by @shuktus_books

# 9

## የፍቅር ሀሁ...

ከመስሪያ ቤት ልወጣ ስል ደሊላ ደወለች ፡፡ በሁለተኛው ጥሪ አነሳሁት፡፡

"ሻሎም"

"ሻሎም"

"ከስራ ስትወጣ ፕሮግራም ከሌለህ ራት ልጋብዝህ?

"ደስ ይለኛል"

"ሆላንድ ሬስቶራንትን ታውቀዋለህ?"

"በሚገባ"

"ከስራ እንደወጣህ እዛ ና"

"እመጣለሁ"

ወሬያችን በዚው አለቀ፡፡ ስለ እውነት ደሊላ እያሳዘነችኝ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጥንካሬዋ በጣም እየተገረምኩ ነው፡፡ ቤተሰቦቿ ሞተውባት ደስተኛ ነች፤ ልጅ መውለድ እንደማትችል እያወቀች ደስተኛ ነች፤ የቤተሰቦቿ ንብረት ተወርሶ ባዶዋን ቀርታ ደስተኛ ነች... ምን አይነት ጥንካሬ ነው ያላት?? ደሊላን ይበልጥ ያከበርኳት የሚመጣውን ዓመት እቅዷን ስትነግረኝ ነው "በሚቀጥለው ዓመት በእርግጠኝነት ትምህርት እጀምራለሁ! በቂ የሚባል ገንዘብ እያጠራቀምኩ ነው፡፡ የማሳጅ ስራ ደስ የሚል እና በቀላሉ ገንዘብ የምታገኝበት ነው፤ ቢሆንም በየቀኑ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ዝሙት መፈፀም ደግሞ በጣም ሰላም የሚነሳ ነገር ነው፤ በዚያ ላይ ደግሞ እኔ ህልም አለኝ፤ ያን ህልም ደግሞ ለማሳካት ትምህርት መማር አለብኝ፡፡

ታላቁን መፅሐፍ ሳነብ "ትምህርት የማይወድ ሰው ድህነትና ውርደት ይገጥመዋል" ይላል:: አሪፍ ምክር አይደለም?"

ይቺ ብቸኛ የሆነች፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ማንም ረዳት የሌላትን ጠንካራ ወጣት እንዴት መርዳት እንዳለብኝ እያውጠነጠንኩ ነው:: ለመለወጥ እና የተሻለ ህይወትን የሚፈልግ ሰውን መርዳት በጣም ተገቢ የሆነ ነገር ነው:: ከመስሪያ ቤት ሰወጣ ስለ ደሊላ እያውጠነጠንኩ በጣም እርጋታ እና እጅግ ውበት ያለው ሆላንድ ሬስቶራንት ለመሄድ ታክሲ ውስጥ ገባሁ:: አጠገቤ የተቀመጠው ሰው የፈጣሪ ያለህ!! ይገማል! የመጠጥ ሽታ እና የሲጋራ ሽታ!! ሊያስመልሰኝ ሲል ከተቀመጥኩበት በፍጥነት ተነስቼ ወንበር ቀየርኩ... ነፍሱን ይማረውና ስለ ሲጋራ ለመጀመሪያ ጊዜ ያወጋኝ ጓደኛዬ ራሞስ ነበር... ወሬው የተነሳው አንድ ሰውዬ ጃንሜዳ ከሚገኘው ታዋቂው አረቡ ሱቅ ላይ ቆሞ በአንድ ጊዜ ሁለት ሲጋራ እያጨሰ ተመልክተን ነበር::

"ተመልከት ይህን ሰው ሚስቱን፣ ልጁን ፣ አየር ንብረቱንም እየጎዳ ነው:: እንደ ሲጋራ አስጠሊታ ነገር እኮ የለም:: ሲጋራ ከሚያጨሱ ወላጆች ጋር የሚኖሩ ልጆች በኒሞኒያ (በብሮንካይት) በሽታ የመያዝ ዕድላቸው እጅግ በጣም ሰፊ ነው:: በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ትምባሆን ማጨስ የጀመሩት የአሜሪካ የመጀመሪያ ተወላጅ ናቸው የሚባሉት ሬድ ኢንዲያንስ ናቸው:: በሌላ በኩል በዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ በወረቀት የተጠቀለለ ሲጋራ በ1831ዓ.ም ያስተዋወቀችው የኛዋ የአባይ ወንዝ ተጋሪ ግብፅ ናት፤ አሁን ሳይንቲስቶች በደረሱበት አሳማኝ ጥናት በሲጋራ ውስጥ ኒኮቲን የተባለ አነቃቂና ሱስ የሚያሲዝ ኬሚካል በዋነኛነት ሲገኝበት በተጨማሪ በአንዲት ሲጋራ ውስጥ ታር፣ አስቶን፣ ካድሚየም፣ አርሴኒክ፣ ፎርማሊ፣ ሼላክ፣ ቤንዚን፣ ሳዮናይድ፣ ካርቦንሞኖክሳይድ የተባሉ ለሰውነት በጣም ጎጂ ውህዶች ይገኙበታል:: በዚህ የተነሳ ሲጋራ የሚያጨስ ሰው ሙጥሮ የአፍጠረን አሰው፣ ጥርሱ ይበልዛል፣ የጥፍር ቀለሙ ይለወጣል፣ በወንዶች ላይ ለወሲብ ስንፈት አስተዋፅኦ ያደርጋል ፣ ሳልና የትንፋሽ እጥረት ያስከትላል... ከዚህ በተጨማሪ የሳንባ ካንሰር፣ የልብ በሽታ፣ ኤምፊዚማ የተባለውን በሽታ ያመጣል፤ በተለይ ነፍሰጡር ሴቶች ሲጋራ ካጨሱ ፅንሱ ሊሞት ካልሆነም ያለቀኑ ሊወለድ ይበልጥ ደግሞ ጤነኛ ያልሆነ እና ከብደቱ በጣም አነስተኛ የሆነ ልጅ ሊወለድ ይችላል፤ ለዚህ ምክንያቱ ተመራማሪዎች የሚያስቀምጡት ከእናት ወደ ልጅ ምግብ የሚተላለፍበት መስመር የደም መጠን መቀነስ ስለሚያስከትል ነው"

"ብዙዎች ሲጋራን በቀላሉ ለሙድ ብለው ቢጀምሩም በቀላሱ ለማቆም አይችሉም፡፡ በዚህ ላይ ተመራማሪዎች የሚሉት በሲጋራ ውስጥ ያለው ኒኮቲን ከፍተኛ የሆነ ሱስ የማስያዝ ተፅዕኖ ስላለው ነው፡፡ ለዚያ ነው ሰዎች ሲጋራ ሲያጨሱ ደስ ደስ የሚል ስሜት ይሰማናል! የመረበሽ ስሜትን ያስወግድልናል! የጭንቀት ሙድን ያጠፋልናል... ባጠቃላይ ዘና የማድረግ ስሜት ይፈጥርልናል የሚሉት፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሲጋራ ከሚያጨስ ሰው አጠገብ ብትቀመጥ ራሱ ሲጋራውን ከሚያጨሰው በላይ ተጎጂው አንተ ነህ!! ለምሳሌ ኢንግሊዝ አገር ሰው በተሰበሰበበት ማጨስ ከፍተኛ ወንጀል ነው፤ እኛ ሀገር እኮ ሲጋራ ማጨስ የምሁርነት መገለጫ ስለሆነ በኩራት አንተ ላይ ጭሱን ያቦንብሃል! አባት ልጁን ከሱቅ ሲጋራ ገዝተህ ና እያለው አንተ ግን እንዳታጨስ ይለዋል፡፡ ዶክተሩ ሲጋራ ገዳይ ነው እያለ ራሱ ያጨሳል... ብቻ ከዚው ሲጋራ ጋር በተያያዘ ተመራማሪዎች ታዲያ ሲጋራን እንዴት ማቆም እንችላለን? ለሚለው እንገብጋቢ ጥያቄ የሚከተሉትን ይመክራሉ፡፡ እነዚህን በደንብ አስታውስ ደራሲ ስለምትሆን አንዱ ገፀባህሪይ ሲጋራ የሚያጨስ ሲሆን ስለሚችል ስለ ሲጋራ ማቆሚያ ዘዴዎች ማወቅ አለብህ አይደለም?"

"ትክክል"

"ለአንድ ወር ያህል ሳያቋርጡ እና ሳይዘናጉ ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ለብ ባለ ውሃ ገላን መታጠብ፣ ከቁርስ፣ ከምሳ እና እራት ጋር ውሃ መጠጣት፣ ቢያንስ በቀን ውስጥ ሁለት ሊትር ንፁህ ውሃ መጠጣት፣ ታዲያ አንድ ወሩ እስከሚያልቅ ድረስ በምንም ተዓምር አልኮል መጠጦች ፣ ሻይ፣ ቡና እና የኮካ መጠጦችን አለመጠጣት፣ ባንፃሩ ከተቻለ ወተት መጠጣት ፣ ከተመገቡ ከ15-20 ደቂቃ ሳይቀመጡ የተወሰነ የእግር ጉዞ ማድረግ፣ ከምግቦች ሁሉ ያስቀመጥነው አንድ ወሩ እስከሚያልቅ አትክልቶችና ፍራፍሬዎችን በብዛት ማብዛት፣ በተለይ ጥብስ፣ መረቅ እና ጣፋጭ ምግቦች በጭራሽ አለመመገብ፣ ከተቻለ በኪስ ውስጥ ቆሎ በመያዝ መቆርጠም፣ ሲጋራ የሚያጨስ ጓደኛ ካለን ለማቆም እንደወሰንን መንገር ወይም መራቅ... የመሰሉት ሲሆን በተጨማሪ ለማቆም ሞክረን ሲይጣን ከተፈታተነን መንፈሳዊ እርዳታ ለማግኘት ወደ ፈጣሪ መፀለይ ሲጠቀሱ ሌላው ዘዴ ብለው ባለሙያዎቹ የሚያስቀምጡት ለሚወዱት ሰው ሲሉ ሲጋራን ለማቆም መወሰን ነው፡፡ ለምሳሌ ከፍሌ ሜኔን አወከው?"

"በዮርዳኖስ ፍቅር ያበደው?"

"እኔ እንደሱ አይነት አፍቃሪ እስከዛሬ አይቼ አላውቅም፤ የእውነተኛ ፍቅር ስሜት

ምን ያክል ጊዜ ይቆያል የሚለውን ለማወቅ በርከት ያሉ ስለ ፍቅር የሚያወሩ የሳይኮሎጂ መፅሐፍትን ሳገላብጥ አንድን ሰው ከልብህ ልታፈቅረው የምትችለው ለሁለት ዓመት ወይም ለ730 ቀናት ብቻ ነው፣ ከዚያ ፍቅርህ ደረጃውን ይቀንስና እየከሰመ ይሄዳል! ከፍሌ ግን ፍቅሩ ለአምስት ዓመት ሳይቀዘቅዝ፣ ጠዋትና ማታ ዮርዳኖስን ለ1825 ቀናት እኮ ነው ደጅ የጠናው!! ታዲያ ዮርዳኖስም የምትመሰገን ነች ከልብህ 'የምትወደኝ ከሆነ መጠጥ አቁም! ሲጋራህን አቁም' ነበር ያለችው፡፡ ለአራት ዓመት በቀን ውስጥ አራት ሲጋራ ሲያጨስ የነበረው ከፍሌ ወዲያው እኮ ነው ቀጥ አድርጎ ያቆመው!! እንግዲህ የሚያጨሱ ሰዎች ቢያንስ ለሚወዱት ሰው እንኳ ሲሉ ጨክነው ቢያቆሙ መልካም ነው፡፡ እውነቱን ለመናገር እኔ የምወዳት ፍቅረኛ ብትኖረኝ ሲጋራ ባጨስኩበት ግም ከንፈሬ ከንፈሯን ልስማት አልሻም!!" ነበር ያለኝ፡፡

ስለዚች ሰላቢ ስለሆነችው ሞት... ሮጦ ገና ሳይጠግብ ስለተቀጨው ጓደኛዬ ራሞስ እያሰብኩ... ሳይታወቀኝ ዘመናዊው ሆላንድ ሬስቶራንት ደረስኩ፡፡ ገና ስታየኝ በፍፁም ከልብ በመነጨ ፈገግታ ተቀበለችኝ! በሚያምር ቁመናዋ ፈዘዝ ያለ ሰማያዊ ጅንስ ሱሪ እና ከላይ ቀለል ያለች ነጭ ሸሚዝ ነገር አድርጋለች... ሁልጊዜ ትናንሽ ጆሮ ጌጦችን ነው ማድረግ የምትወደው፡፡ አንድ ቀን እንኳ ሊፒስቲክ ሆነ ቻፒስቲክ ተቀብታ አይቻት አላውቅም፡፡ ስለ ሴቶች ቻፒስቲክ አንድ ጊዜ ራሞስ "ሴቶች ደማቅ ቻፒስቲክ በተለይ ቀላ ያሉ ቻፒስቲኮችን ከንፈራቸው ላይ የሚቀቡት ለውበት ሳይሆን ከንፈራቸውን እንዳትስምባቸው ማራቂያ ጥበብ ናት" ብሎ ነግሮኝ ነበር፡፡ ለማንኛውም ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳምን ... የማይከብድ የሽቶ መዓዛ ከሰውነቷ ላይ ሸተተኝ... ወንበር ስበን ተቀመጥን... ወዲያው ቀና ብላ በትኩረት እያየችኝ

" የማስታወስ ችሎታዬን ለማሳደግ ከድሮ ጀምሮ ማጥም በቃል መያዝ ደስ ይለኛል፡፡ ይህን እየሄድኩ አልሄድም የተሰኘ የፍቃደ አዘዘ የማጥም መድብል ዛሬ ጠዋት ወደ ስራ ሳመራ ነው የገዛሁት "እንዳፍታ" የምትለዋን ማጥም ላንብብልህ?"

"ደስ ይለኛል"

"እንዳፍታ

ያጨማለቀን ጭቃ የሰለቸን ስናቦካ

የገረፈን ዝናብ ዶፉ እንጫንጮን ጠፈጠፉ

የሐሩር ፀሐይ ቢያከረን ጭቃ ዶፉን ተመኘን

ለካስ!

ሁሉም ነገር ሲያጡት ነው

ልብ የሚነድል እሚያደባየው።

ለካስ!

በእጅ ሳለ ይረከስና

ስናጣው ያወጣል ዋጋ።

"ትልቅ እውነት አይደለም? በዚህ ሀሳብ አትስማማም?"

"በጣም ትክክል ነው። በህይወታችን ቁምነገር የማንሰጣቸው ነገሮችን ቁም ነገር የምንሰጣቸው ስናጣቸው ነው። የግጥም መፅሐፍትም እየገዛሽ ታነቢያለሽ ማለት ነው?"

"እውነቱን ለመናገር ገዝቼ እንብቤ አላውቅም፤ በፊት እንዳልኩህ እኔ በጣም ማንበብ የምወደው በባዮግራፊ መልክ የሚዘጋጁ መፅሐፍትን ነው። ከዚያ በተረፈ የታሪክ መፅሐፍት በጣም ያዝናኑኛል። ይህን ጠዋት የገዛሁልህ አንተ ግጥም ስለምትወድ ስጦታ ለመስጠት ነው" አለችና እጄ ላይ አስቀመጠችልኝ።

"አ! በጣም አመሠግናለሁ! ዛሬ ለኔ የመፅሐፍ ስጦታ ቀኔ ነው ማለት ነው? የሚገርምሽ ምሳ ሰዓት ላይ ጋዜጠኛው እንዳልካቸውም 40 መፅሐፍት በስጦታ መልክ አበረከተልኝ። ስለ ስጦታሽ ከልብ አመሠግናለሁ ፤ ታዲያ አስቲ በቃልሽ ከሸመደድሽው ግጥም አንድ ሁለቱን ካላስቸገርኩሽ ንገሪኝ"

"ምን ችግር አለው? ስንት ትከፍላለህ ግን?"

"ደስ ያለሽን" አልኩና ተሳሳቅን። በመሀከል አስተናጋጁ መጣና የሚበላና የሚጠጣ ነገር አዘዝን።

"በጣም የምወደው የኑረዲን ኢሣ ግጥምን ነው።

እኔ ምን አገባኝ

እኔ ምን አገባኝ የምትለው ሀረግ

እሱነው ሀገሬን ያረዳት እንደበግ

የሚል ግጥም ልበና

ብድግ አልኩኝና

ምን አገባኝ ብዬ ቁጭ

አልኩ እንደገና፡፡

ከዚህ ምን አገባኝ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ሁልጊዜ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞችን በተለይ መሪዎቻችንን ሳስብ ትዝ የምትለኝ ግጥም አለች፡፡ ይቺን ግጥም የጋዜጠኛው ማስታወሻ መፅሐፍ ላይ ያነበብኳት ነች፤ መቼም የተስፋዬ ገብረአብ መፅሐፍትን አንብበሃል?"

"ግማሹ ኤርትራዊ ነው፤ ግማሹ የኦሮሞ እና አማራ ህዝቦችን ለማጋጨት የተነሳ መሰሪ ሰው ነው ... ይላሉ፡፡ እኔ በጣም ከማደንቃቸው ደራሲዎች ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ በተለይ የቢሾፍቱ ቆሪጦች፣ ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ፣ የደራሲው ማስታወሻ እና አሁን ያልሽውን የጋዜጠኛ ማስታወሻ መፅሐፍቱን አንብቤለታለሁ... ሌላውን ጉዳይ ትተነው የአፃፃፍ ውበቱ በጣም የሚማርክ ነው" አልኳት፡፡

"በጣም ልክ ነህ! ኢትዮጵያ ሆነ ኤርትራዊ እኔ የሚያገባኝ ነገር የለም" አለችና ግጥሟን ነገረችኝ፡፡

ምን አገባህ?

መቶ ሺህ ብር ይውጣ

ሰው ጠግቦ እንዲወጣ

ውስኪም ብዙ ግዙ

ቢራም ብዙ ግዙ

ምግብም ብዙ ግዙ

ሁሉም በገፍ ይምጣ

ሰው ጠግቦ እንዲወጣ

እየበላህ ብላ እየጠጣህ ጠጣ

ከህዝብ ነው እንጂ ካንተ ኪስ አይወጣ

... በማስታወስ ችሎታዋ አጨበጨብኩላት፤ በዚያ ላይ ድምጿ የሆነ ደስ የሚል ቃና አለው፡፡

"በነገራችን ላይ ስለ ፖለቲካ ከተነሳ በቀደም አንድ ደንበኛዬ በጣም ደስ የሚል እርጋታ ያላቸው ሰው ናቸው፡፡ ከማሳጅ ውጪ ወሲብ ምናምን አንድም ቀን ተጠቅመው አያውቁም፡፡ የጀርባ ህመም ስላለባቸው እኔ ጋር እውነተኛውን ማሳጅ ለመጠቀም በእስራ

ልዩነት ይመጣሉ እና የዚያን ቀን "የህዳሴ አብዮት" የሚል የፖለቲካ ነክ መፅሐፍ ይዘው ነበር:: እኔም ለጨዋታ "ፖለቲካ ይወዳሉ እንዴ ጋሼ?" አልኳቸው"

"ያለ ፖለቲካ መኖር እኮ አይቻልም ልጄ! ህይወት ራሷ ፖለቲካ ነች:: አለምና ምድርን የፈጠረው እግዚአብሔር ራሱ ሀይለኛ ፖለቲከኛ ነው! ስለዚህ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያለ ፖለቲካ መኖር አይቻልም"

"እግዚአብሔር እንዴት ፖለቲከኛ ሆነ?"

"እህ... አስቢው አለም ከተፈጠረችበት እስካሁን በስልጣን ላይ ይገኛል! የስልጣን ክፍፍል እንኳ የለውም! እሱ እና ልጁ ሆነው እኮ ነው አለምን የሚያሽከረክሩት" ሲሉኝ ፈገግ አልኩኝ:: ከዚያ ጥያቄዬን መጠየቅ ቀጠልኩኝ:: ከመሬት ላይ የኢህአዴግ ኖት ወይስ ተቃዋሚ ኖት እስቲ ያስ ተመልካች ገለልተኛ?"

"በነገራችን ላይ ተቃዋሚ የሚባል ነገር የለም:: ትክክለኛ ቃሉ ተቀናቃኝ ነው:: እኛ ሀገር ነው ተቃዋሚ /ጠላት /ባላንጣ/ ስልጣን ፈላጊ ወዘተ የሚል ቃል ያለው:: ጥያቄሽን ለመመለስ 1997 ላይ ያ ባንዳው ሰሙን ቄስ ይጥራውና! ሸኮከ፣ ተለጣፊ፣ ሰላይ፣ ካድሬ የሆነ ሰው በሁለት ካራ እያረደ ጉድ ሰራቸው እንጂ የቅንጅት ቀንደኛ ደጋፊ ነበርኩኝ:: አሁን ለማንም አልደግፍም:: ኢህአዴግም ሌባ ነው:: ተቀናቃኝ ፓርቲዎችም ሌቦች ናቸው:: ሁሉም ለራሳቸው ሆድ ይወሸከታሉ እንጂ ለኢትዮጵያ አይደሉም!! ኢህአዴግ ለጨዋታው ድምቀት ራሱ በገን የደረደራቸው አሻንጉሊት ፓርቲዎችን ጨምሮ የሚገርምሽ እኮ ኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገቡ 74 የፓርቲ አይነቶች አሉ:: በትንሹ መድረክ ፣ ሰማያዊ፣ ቅንጅት፣ ግረና፣ ኢዴፓ... አስቢው እንግዲህ እውነተኛ የሀገር ፍቅር ቢኖራቸው ከኢህአዴግ ጋር ከመወዳደራቸው በፊት እውነት ሁሉም ለሀገር የሚሰሩ ቢሆን መጀመሪያ ከመቧታተን አንድ ይሆኑ ነበር!! አንድ ሲሆኑ ሀይል ያገኛሉ፣ ጠንካራ አቋም ይኖራቸዋል! ከኢህአዴግ ጋር ለመፎካከርም ጥንካሬ ያገኛሉ ፤ በሰለጠኑት ሀገራት እኮ ሁለት የፖለቲካ ድርጅት ብቻ ነው የሚገኘው ለምሳሌ በአሜሪካ ሪፐብሊካን እና ዲሞክራት ናቸው:: በቃ ከሁለቱ አንዱን መርጠሽ መቀሳቀስ ነው:: እዚህ ሁሉም መነሻ ያደረገው ኢትዮጵያን ሳይሆን ሆዱን እና ዘሩን ነው፤ ይህ ደግሞ ከንቱ ነው:: ከዚው ከዘር ጋር በተገናኘ ነፍሳቸውን ይማርና መሰረው ኃይለስላሴ ምን ብለዋል መሰለሽ "የአንዱን ዘር ከፍተኛ አድርጎ ሌላኛውን ደግሞ ዝቅተኛ የሚያደርገው ፍልስፍና ከዓለም ላይ ሙሉ በሙሉ እስካልተወገደ ድረስ ጦርነት ይቀጥላል"

ነበር ያሉት፡፡ ሁቅ ነው፡፡  የኔ ልጅ እኔ አሁን 65 ዓመቴ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ሶስት መንግስት አየሁ፡፡ ከትላንት ዛሬ እየተሻለ መሄድ ነበረበት ግን እየባሰ፣ እየዘቀጠ እየሄደ ነው፡፡ ብዙ አገራት ለስራ ሄጀያለሁ መንግስቶቻቸው የግለሰቦችን መብት ያከብራሉ! እንዳሻሽ የመናገር፣ የመፃፍ፣ ሂስ የመስጠት፣ መንግስት የሚሰራውን ነገር የማጣጣል መብት አለሽ፡፡ እዚህ አገር ግን ተቃራኒ ነው፡፡ መናገር አይደለም መተንፈስ እንኳ አይፈቀድልሽም፡፡ እውነተኛ ስልጣኔ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ ልጄ?"

"እህ?"

"ሰው ክቡር እንደሆነ ማወቅ! ሁሉንም በእኩልነት ማየት! ያለ ምንም አድሎ ኢትዮጵያዊ ስለሆነ ብቻ ክብር መስጠት! እንደነገርኩሽ 65 ዓመቴ ነው፡፡ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ከ1983 ጀምሮ የቀበሌ መታወቂያ የለኝም፡፡ ለምን አትይኝም?"

"ለምን?"

"የቀበሌ መታወቂያ ላወጣ ስሄድ ብሔርህ ምንድን ነው አሉኝ፡፡ እኔ ብሔር የለኝም "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ስላቸው አይ ብሔር ካልተናገርክ መታወቂያ አታገኝም ብለው ከቾች አሉ፡፡ ኢህአዴግ ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ለብሔር ነው ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው፡፡ በሀሳብ ደረጃ እኮ ማንኛውም ግለሰብ በራሱ ቋንቋ ቢናገር፣ በራሱ ማንነት ቢታወቅ ምንም ክፋት የለውም! ኢህአዴግ ግን የሚፈልገው ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ በብሔር እና ቋንቋ ስም ክልል አበጅተን በዘረኝነት አጥር እንድንታጠር ነው"! "አይጥ እና ድመት እንድንሆን ነው!"

"እና የቀበሌ መታወቂያ ላይ ምን መፃፍ ነበረበት?"

"የኔ ልጅ በጣም አሪፍ ጥያቄ ነው፡፡ መሆን የነበረበት እና የተሻለው አማራጭ ብሔር ብሎ መታወቂያ ላይ አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ወላይታ... ወዘተ እያለ ከመፃፍ የትውልድ ቦታ እና ከተማ ብቻ ቢፃፍ የተሻለ ነው፡፡ ለምሳሌ አዲስ አበባ የተወለደ አዲስ አበባ ቢባል ሀዋሳ የተወለደ ሀዋሳ፣ መቀሌ የተወለደ መቀሌ፣ ባህርዳር የተወለደ ባህርዳር... ወዘተ በሚል የኢትዮጵያ ከተሞች ቢፃፍ አንዳችም ችግር የለውም!! ይህ ቦታን እንጂ ብሔርን በዮዮራሽ አይወክልም!! ትልቁ ማወቅ ያለብን ነገር እኮ ማንም አንሁን ማንም! ከማንም እንወለድ_ ሁላችንም ተሰባሪ ሸክላዎች ነን!! እንሞታለን!! ስለዚህ በብሔር፣ በቋንቋ ፣ በዘር ከምናምን እና ከምንኮታረክ የመግባቢያ ምልክታችን ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው ባይ ነኝ" ሲሉ ነበር

የነገሩኝ፡፡ ለማንኛውም ወደሪላችን ወሬ እንመለስ ስራ እንዴት ነበር? ከባንካችሁ ስንት ብር አምብረበርከ" አለችና ፈገግ አለች፡፡ መቀለድ ትወዳለች፡፡ ከደሊላ ጋር አሪፍ አሪፍ ወሬዎች ስንጨዋወት፣ አሪፍ ምግብ ስንመገብ ሰዓቱ መሸ፡፡ ተያይዘን ወደ ቤት አመራን፡፡ እቅፍ አድርጋ ስማኝ ተለየችኝ፡፡ አዎ፣ እውነቱን ለመናገር በጣም ደስተኛ ነበርኩኝ፡፡ ደሊላ ቀለል ያለች ልጅ ስለሆነች ለጨዋታ አትከብድም፡፡ ከስንት ጊዜ በኋላ ከሴት ጋር በውብ ምግብ ቤት ራት በልቼ ስወጣ... ለመጨረሻ ጊዜ አሪፍ ራት የበላሁት የዛሬ ዓመት ከሁለተኛ ፍቅረኛዬ ጋር ከነበረችው ሮዛ አዳም ጋር ነበር፡፡ የቫላንታይን ቀን...

የመጀመሪያ ፍቅረኛዬ ዊንታ ኪዳኔ ነበረች፡፡ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የማይረሳ፣ ህልም የመሰለ ወርቃማ የፍቅር ጊዜያት አሳልፈናል፡፡ ከዚያ ዝነኛ የመሆን ታላቅ ጉጉት ስለነበራት ውብት እንጂ ችሎታ ብዙም ቦታ በሌለው የአገራችን ፊልም ላይ ውበቷን ተጠቅማ ተመረጠች፡፡ ከእነ ግሩም፣ ማንዴላ፣ ማህደር፣ አለማድ፣ ሚሊዮን... መሰሎች ጋር ፊልም ላይ ብቅብቅ አለች፣ ከዚያ ለእኔ ቢሜ አንዳንን ሳታሳየኝ በሾፕታ ቀይ ካርድ አባረረችኝ... ያው በወቅቱ የትንሽነት ስሜት ተሰምቶኝ ነበር፣ የመናቅ እና የመከዳት ስሜት ወርኝ ነበር፣ ቢሆንም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለችው ሴት እርሷ ብቻ እንዳልሆነች ሲገባኝ፣ ሌላ ሴት መጥበስ እንደምችል ውስጤ ሲነግረኝ... አንቺ መንገዱን ጨርቅ ያድርግልሽ አልኳት፣ ለማንኛውም አሁን ከአንድ ዝነኛ ዳሬይክተር አርግዛለች፣ ይመቻት... ሌላ ምን ይባላል!! እንደ ምቀኛ ሰው ትዳርሽ በሳሙን ይጣ! መንገድ ላይ ስትሄጂ ሲኖትራክ መኪና ይደፍጥጥሽ... አልላት...

ሁለተኛዋ ሮዛ አዳም እንደማትሆነኝ ገና ሥርግ ላይ ስንተዋወቅ ልድስተኛ ስሜቴ ሹክ ብሎኝ ነበር ...ቢሆንም ስሜት አሸንፈን ተዋወቅን፡፡

ዋው!! እውነቱን ለመናገር ሮዛ የሆነች ጣጣ የሌላት ውብ ናት፡፡ ዘናጭ ናት፡፡

ሀይወትን ቀላል አድርጋ ነው የምትኖረው:: የሠርጉ ዕለት ከሙሽራዋ ራሷ በልጣ ዝንጥ ብላ ነበር... እንዴት እንደሆነ ባላውቅም ራሷ ነበር መጥታ የተዋወቀችኝ::

"ታዲያስ?" አለችኝ:: ታዲያስ ሲሉኝ ራሞስ ባስተማረኝ በሀንድኛ ቋንቋ ነመስቴ ብሎ መመለስ ደስ ይለኛል:: እናም "ነመስቴ" አልኳት:: የቃሉን ፍቺ አሷም ሳታውቀው አይቀርም ወዲያው መልሳ "ነመስቴ" አለችና ጥያቄ አስከተለች::

"የሆነ ቦታ አውቅሃለሁ?"

"ምናልባት"

"በእናትህ የት ነው የምትሰራው?"

"ባንክ ቤት"

"አ! ያ! በነገራችን ላይ ከቁመና ጋር ሱፍ አጅግ ያምርብሃል! አንዳንዴ ወንዶች ሱፍ ሲለብሱ ግርማ ሞገስ ባይኖራቸውም ግርማ ሞገስ የሚያገኙ አሉ ፤ አንዳንዴ ደግሞ ሱፍ ሲለብሱ ከባህር የወጣ ዓሣ የሚያስመስላቸው አሉ፤ አንተ ላይ ግን to be honest ውበት ደፍቶብሃል!!"

"አመሠግናለሁ! አንቺም በጣም አምሮብሻል"

"To be honest ሠርግ አልወድም"

"አትዋሺ"

"I swear to God ሠርግ አልወድም! I know ብዙ ሴቶች ሠርግ ነፍሳቸው ነው:: ማንኛዋም ሴት ከ17 ዓመቷ ጀምሮ ስለ ሠርግ ማሰብ ትጀምራለች፤ እኔ ግን I hate it, oh its boring!"

"ለምን?"

"To be honest በሠርግ የሚጋቡ ሰዎች የሆኑ ፈሪዎች እና እርስ በእርሳቸው የማይተማመኑ ይመስለኛል:: ቀለበት ሲያስሩ እና የጋብቻ ወረቀት ከመንግስት ማዘጋጃ ቤት ሲቀበሉ እኮ የሆነ ሰዓት እንለያያለን ብለው ስለሚያስቡ ንብረት ለመካፈል ለማስረጃ እና ለህጋዊነት ነው"

"እና አንቺ በሠርግ አታገቢም?"

"To be honest! በጭራሽ!!"

ምንም ጥያቄ የለውም ውብ ናት:: የተስተካከለ ቁመና አላት:: የሚያምር ጥቁር ረጅም ፀጉር አላት:: በንግግሯ መሀከል To be honest ማለት ልማድ ሳይሆንባት አይቀርም... ዋው!! የከንፈሯ ውበት ነፍስ ያጠፋል! ለለዚች ውብ ወጣት ይበልጥ ለማወቅ ፈለኩ... ቢያንስ ወደ ፊት ለምፅፈው መፅሐፍ አንዷ ገፀባህሪይ ልትሆነኝ ትችላለች እናም በፍጥነት

"ኬኛ ዮሐንስ" አልኳት::

"ሮዛ አዳም! ኬኛ የምን ቃል ነው?"

"ኦሮምኛ! የእኛ እንደ ማለት ነው"

"ኦ ኦሮምኛ ትችላለህ?"

"በጭራሽ አልችልም"

"ታዲያ የኦሮምኛ ስም ለምን ወጣልህ?"

"አባቴን ከመንገድ አንስቶ ያሳደገው ኬኛ የተባለ ሰው ነበር፤ ያን ለማስታወስ ነው"

"Ok…" አለችና ወዲያው የሚያምሩት አይኖቿን በልጥጣቸው

"Oh my God!!" ስትል ጮኸች:: ምን ተፈጠረ ብዬ ግራ ገብቶኝ

"ምነው" አልኳት::

ምንም ሳትመልስልኝ በከፍተኛ ስሜት ተውጣ የሚያምረውን የታችኛዋን ከንፈሯን በሚያምረው ጥርሷ ነከሰች:: አይኗ የተተከለበት ቦታ ተከትዬ ሳማትር... ሁለት በጣም ዝንጦ ያሉ፤ ጋርድ የሚመስሉ፤ የዳበረ ቁመት ያላቸው፤ ከንዶቻቸው ላይ ንቅሳት ያላቸው ወንዶች ላይ ነበሩ... ከማድነቅም በላይ የከንፈሯ አነካከስ ለወሲብ ጭምር እንደተመኘቻቸው ያሳብቅባት ነበር... እናም ይቺን ሴት ብጠብሳትም ዋጋ እንደሌለኝ ወዲያው ስድስተኛ ስሜቴ ሹክ ብሎ አለኝ:: ስድስተኛው ስሜቴ ይቺ ሴት ቅንዝራም ነገር ነችና እነሆ አትሆንህም አለኝ.. ቢሆንም ግልፅነቷ ግን ደስ አለኝ! ድብቅ አይደለችም::

"ቅር አይልህም አይደለም?"

"ምኑ?"

"በውስጤ የተሰማኝን ብናገር?"

"በጭራሽ!!"

"To be Honest የኢትዮጵያ ወንዶች ከእነርሱ አጠገብ ሆነህ ሌላ ወንድ ማድነቅ ቀርቶ እንድትመለከት እንኳ አይፈልጉም!! የኢትዮጵያ ወንዶች ሴትን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው እና ማክበር እንዳለባቸው አያውቁም any way እዚያ ጋር የቆሙት ሁለት ወንዶች በጣም ነው የሚያምሩት ፤ እኔ ጡንቻማ እና ደንደን ያለ ወንድ ላይ ነፍሴ ትጠፋለች! ለአልጋ ጨዋታ ብቻ እንጂ ለፍቅር ግን አልፈልጋቸውም!"

"እህ አንቺም ቆንጆ ስለሆንሽ የፈለግሽውን ወንድ መጥበስ ትችያለሽ"

"Thank you! ግን እኔ መጥበስ ሳይሆን መጠበስ ነው ትልቅ እርካታ የሚሰጠኝ ለእኛ ሴቶች በወንዶች መፈለግ እና መፈለግ እኩል ክብር የላቸውም ለዚያ ነው Make other people come to you የሚባለው የሆነሆኖ አንተ ፍቅረኛ አለችህ?"

"ነበረችኝ"

"ተለያያችሁ?"

"አዎ"

"Dump አደረገችህ ወይስ አንተ ነህ Dump ያደረካት?"

"እሷ ነች"

"Oh! ያላዝናል Reinhold Niebuhr ታውቀዋለህ?"

"አላውቀውም"

"Forgiveness is the final form of love! ይላል፤ ስለዚህ የምትወዳት ከሆነ ለምን ለመመለስ ጥረት አታደርግም?"

በዝምታ ራሴን ነቀነኩላት፡፡ ከዚያ ማን ተብዬቶ ማን ይቀራል እልኩና በትኩረት እያየሁት

"አንቺስ" አልኳት

"ሰምንት ነጭ ጋንት"

"ጋንት?"

"እህ"

"ጥያቄዬ አልገባሽም?"

"ገብቶኛል! ቤቴ ውስጥ እስካሁን ሰምንት ነጭ ጋንት አለኝ፡፡

ስምንቱንም የተቀበልኩት ከወንዶች ነው፡፡ ስንት ፍቅረኛ እንደነበረኝ እና ከስንቱ ጋር ወሲብ እንደፈጸምኩ የማውቅበት መንገድ ነው! ወንዶች ነጭ ፓንት ገዝተው ካልሰጡኝ አልጋ ላይ በጭራሽ አልወጣም፤ አሁን ግን እኔም እንዳንተው ነፃ ነኝ!!"

በዚህ መልኩ ነበር የተዋወቅነው፤ እናም የዚያን ዕለት ስልክ ቁጥር ተለዋወጥን፡፡ መደዋወሉ... ሻይ ቡና... ገባ ወጣ... ማለት ጀመርን፡፡ ሮዛ አዳም የሀብታም ልጅ ነች፡፡ ፍሬንድ ሺፕ ህንፃ ላይ አብድ ያለ ግዙፍ ሽቶ መሸጫ ሱቅ አላት... በውስጥ የዶላር ምንዛሪም ትሰራለች... አብዝቶ በመዝናናት እና ሕይወት ማለት ሸርብትን ነች የሚል ፍልስፍና አላት... ለብቻዋ ተከራይታ የምትኖርበት ውብ ቤት አላት... ሁለት ወር ሳይሞላን አንድ ምሽት ከጓደኛዬ ራሞስ ጋር ተለያይቼ ወደ ቤት ልገባ ስል ደወለች፡፡ አነሳሁት፡፡

"to be honest ልሞትልህ ነው"

"ምን ሆንሽ?"

"ዛሬ እናቴ ላይ ሊወጣ ነው"

"ምን?"

"Sex አምሮኛል! ስለዚህ በፍጥነት ቤት ና ! ታዲያ መካከለኛ ሳይዝ ነጭ ፓንት ገዝተህ መምጣትህን እንዳትረሳ! እወድሃለሁ!!" ብላ በፍጥነት ዘጋችው፡፡

ይቺ ሲይጣን... ወዲያው ነው የቆመብኝ እናም በፍጥነት ሻወር ወሰጄ፤ ከቤት በመውጣት የሴቶች ቡቲክ በስንት ፍለጋ ነጭ ፓንት በመግዛት ጥቁር አንበሳ ጀርባ የሚገኘው ቤቷ እንደ አሞራ እየበረርኩ ሄድኩ...

እ... ይቺ ሲይጣን!! እንደ ዶሮ ነው አስራ ሁለት ቦታ የገነጣጠለችኝ፡፡ ከሆነ ዩኒቨርሲቲ በወሲብ የተመረቀች ነው የሚመስለው እንጂ እንዲሁ በቀላሉ ከልምድ ያዳበረችው ነው ለማለት ያስቸግራል... በቃ በወሲብ ችሎታዋ ከልቤ ተገርሜ አጨብጭብላታለሁ... ምርጥ ነች!!

ከዚያ ግንኙነታችን ሁለት ወርም ሳያልቅ የፍቅረኞች ቀን ደረሰ፡፡ ጥሩ ምሽት ለማሳለፍ አቀደች፡፡ የፍቅረኞች ቀን ሊከበር ሁለት ቀን ሲቀር... ደወለች፡፡

"ሃይ ማር"

"አቤት"

"የፍቅረኞችን ቀን አስመልክቶ አንድ ሀሳብ መጣልኝ"

"ምን?"

"ለምን ደብረዘይት አዲሳላ ሪዞልት ሄደን ጥሩ ጊዜ አናሳልፍም? What's your opinion?"

"በጣም ምርጥ ነው"

"በሰማችን ላይ ላለይዝ?"

"ይቻላል"

"To be honest አሪፍ ጊዜ እናሳልፋለን I love you"

"እኔም እወድሻለሁ"

በመላው ዓለም በዓመት አንድ ጊዜ የሚከበረው እና ኢትዮጵያ ውስጥም አሁን አሁን እንደ ሙድ እየተዘወተረ ህጋዊ የመሰጃ ቀን እየሆነ የመጣው የፍቅረኞች ቀን ጠዋት ላይ ደወለች:: ገና ከጠዋቱ 12:10 ደቂቃ ላይ ስለ ነበር ምን ሆነች? ብዬ በፍጥነት ሞባይሉን አነሳሁት::

"የኔ ማር"

"አቤት"

"do you know how much I love you?"

"ፍቅር በተግባር እንጂ በቃላት አይገለፅም"

" I know action speaks louder than words! ግን የኔ ማር እንዳትቀየመኝ"

"ስለ ምን መቀየም ነው የምታወራው"

" ዛሬ ደብረዘይት አብረን አንሄድም"

"ችግር የለውም እዚው እናሳልፋለን"

"No"

"ሮዚ"

"አቤት"

"የምትነግረኝ ነገር አለ?"

"ብቻ ሌላ ሰው ጠብቦሻለሁ ከእርሱ ጋር ለማሳለፍ ተስማምተናል sorry ok"

በዚህ መልኩ ነበር የተለያየነው:: ሮዛን ሳስታውስ የሆነች በራሷ ዓለም፣ በስሜት ብቻ እየተነዳች የምትኖር፣ የሆነች ፍቅርን የምትፈራ፣ ትመስለኛለች...ከዚያ በኋላ ደውላ አታውቅም፣ እኔም ደውዬላት አላውቅም... የሆነ ጊዜ ግን አራት ኪሎ ባጋጣሚ አይቼያት ነበር፣ ከሆነ ግድንግድ ጡንቻማ ጥቁር ሰው ጋር... በቃ ከዚያ በኋላ ሌላ ሴት አልጠበስኩም .. ሴቶችም እኔን አልጠበሱኝም!!

ከዘበኛው ጋር የተወሰነ ነገር ካወራን በኋላ ወደ ሳሎን ቁልፉን ከፍቼ ልገባ ስል በሩ ስር በካርቶን የታሸገ ዕቃ አየሁ... ወዲያው የጋዜጠኛው እንዳልካቸው ስጦታ እንደሆነ ገባኝ:: በደስታ ወደ ሳሎን ቤት አስገባሁት:: ወደ መኝታ ቤት በማምራት ልብሴን ቀይሬ፣ እግሬን በሳሙና በሚገባ አጥቤ... ወደ ሳሎን በጉጉት ተመለስኩ ... ወዲያው በፍጥነት ካርቶኑን ቀዳደኩት፣ ከዚያ መፅሐፍቱን መሬት ላይ ዘረጋሁት... ዋው በጣም ምርጥ መጽሐፍት ናቸው:: በእርግጥ በብዛት እንግሊዝኛ ናቸው::

... Psychology of sex (A man is what his sex is)... Aristotle... war and peace... የብርሃን ፍቅር... ከሰማይ የወረደ ፍርፍር ... እፎይታ .. Body mind balancing... እ በጣም ስፈልገው የነበረውን ጥንታዊ ከአለቃ ዘነበ የተፃፈ መፅሐፈ ጨዋታ ሥጋዊ መንፈሳዊ መፅሐፍ አገኘሁ... የኢትዮጵያ ታሪክ... የዓለም ታሪክ... ስለ ጋዜጠኝነት ሙያ በእንግሊዝኛ የተፃፉ ሁለት ትላልቅ መፅሐፍት... የጭን ቁስል.. የካይሮው ጆሮ ጠቢ... የሁለት ከተሞች ወግ የሚባሉ ምርጥ መፅሐፍት ናቸው:: ሁሉንም ለማንበብ በወረፋ ከመፅሐፍት መደርደሪያው ላይ በክብር አስቀመጥኳቸው:: ዋቃ ውለታውን ይክፈለው፣ መፅሐፍን የሚያክል ውድ ስጦታ ማን ይሰጣል? ከስጦታዎች ሁሉ የላቀው ትልቁ ስጦታ መፅሐፍ ነው ይባል የለ?... እውነት ነው::

# 10

## ኢንስፔክተር...

ቀናት አለፉ፡፡ በእርግጥ በቀናት ብዛት የማይለመድ ነገር የለም፤ በዓለም ላይ በአንድ ነገር ልንገረም፣ ልንደነቅ፣ ልንተከዝ የምንችለው ለሶስት ቀናት ወይም 72 ሰዓታት ብቻ ነው ፤ ከዚያ ስሜታችን እየቀዘቀዘ ይመጣል ይባላል፤ በዚህ ሀሳብ እስማማለሁ፤ ቅሉግን የጓደኛዬን ሞት ለመርሳት ለእኔ ይበልጥ አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም ሌላ የልብ የምለው ጓደኛ የለኝማ!... እናም ለመርሳት ተቸግሬያለሁ፡፡ እውነቱን ግን ተቀብያለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ አንድ ጓደኛ ብቻ ያላችሁ ወጣቶች የሚቻል ከሆነ ቢያንስ ከአራት በታች ጓደኛ ባይኖራችሁ ከህይወት ልምዴ እነግራቹኋለሁ...፡፡

ባንክ ቤታችን ስራ ሲቀዘቅዝ እና በዝምታ ስቀመጥ ስለ ጓደኛዬ እቆዝማለሁ... አንዳንዴ ደግሞ ስለ ድርሰት እውጠነጥናለሁ... ደራሲ መሆን እፈልጋለሁ!! በቃ ቢያንስ አንድ መፅሐፍ መፃፍ እፈልጋለሁ... ሌላው ቢቀር ስለጓደኛዬ ራሞስ የሚያወራ መፅሐፍ መፃፍ እፈልጋለሁ... ዛሬም ስለምፅፈው መፅሐፍ እያውጠነጠንኩ ሳለ የግል ስልኬ ጠራ

"ሀሎ"

"ኪኛ ዮሐንስ"

"ነኝ"

"የእንዳልካቸው እህት ነኝ"

ጣጣ ሳላበዛ ከስራ የምወጣበትን ጊዜ እና ቤት የምደርስበትን ግምታዊ ሰዓት ነገርኳት፡፡ በዚሁ ስልኩ ተዘጋ፡፡

ከስራ በቀጥታ ቤት ነበር ያመራሁት፡፡ ልክ በተቀጣጠርንበት ሰዓት የእንዳልካቸው እህት ስለመጣች የተዘጋጁትን የወንድሟን ዕቃዎች በመኪና በመጫን ወሰደችው፡፡ የልማታዊ ጋዜጠኛውን ወንድሟን እንዳልካቸው በሰላም ኢንግሊዝ መግባትን አበሰረችኝ... ከዚያ ደሊላ ስራዋ የምሽት ስለ ነበር ለለውጥ ያህል ራሴን ዘና ለማድረግ ሀገር ፍቅር ትያትር ቤት ለመግባት ወስኜ ስሄድ "ቅድስት ከካናዳ" የሚል የዝነኛው ሀይሉ ፀጋዬ ተውኔት ነበር፡፡ ይህን ተውኔት ደግሞ ነፍሱን ይማረውና ከጓደኛዬ ራሞስ ጋር አይተነው ስለ ነበር በቀጥታ የራሞስ ቤተሰቦች ጋር በመሄድ ከቤተሰቦቹ ጋር በማምሸት ወደ ቤት ተመለስኩ፡፡ እርግጥ ራሞስ የለም፤ በቤተሰቦቹ ቤት ግን ዳግም ህይወት ቀጥላለች፤ ምንም ይፈጠር ምን ሁልጊዜ ህይወት እንደቀጠለች ናት፡፡

ቅዳሜ ምሽት እስከ ሌሊቱ ሰባት ሰዓት እያነበብኩ እና "2012" የተሰኘውን ፊልም በድጋሚ እያየሁ ስለ ነበር እሁድ ከጠዋቱ 3፡31 ደቂቃ ሲል ተነሳሁ፡፡ ወዲያው የከፈትኩት በጣም የምወዳትን የሸገር 102.1 የወ/ሮ መዓዛ ብሩን ፕሮግራም ነው፡፡ ዋው! የምትጋብዛቸው እንግዶች አሪፍ አሪፍ ከመሆናቸው በተጨማሪ የወ/ሮ መዓዛ ጥያቄዎችም ምርጥ ምርጥ ስለሆኑ ፕሮግራሙ በጣም ይመቸኛል፡፡ ለማንኛውም የወ/ሮ መዓዛን ተወዳጅ ፕሮግራም እየኮመኮምኩ ሳለሁ ነበር ሞባይሌ ድንገት የጮኸው፡፡ በሁለተኛው ጥሪ አነሳሁት፡፡ የመስመር ስልክ ነበር፡፡

"እንደምን አደርክ ኬኛ?"

"ዋቃ ይመስገን"

"ኢንስፔክተር አወቀ ነኝ"

"እ! ጤይና ይስጥልኝ ኢንስፔክተር!"

"በሰባ ሁለት ሰዓት ውስጥ ጉዳዩን ጨርሼ እደውልልሃለሁ ብዬ ሌላ አስቸኳይ ጉዳይ

ጎጥሞኝ ስለ ነበር ነው የዘገየሁት፡፡ አሁን አንድ አፍታ እኔ ጋር መምጣት ትችላለህ?"

"ችግር የለውም እመጣለሁ"

"አመሠግናለሁ"

የወ/ሮ መዓዛ ብሩ የእሁድ ማለዳ የሸገር ካፌ ፕሮግራም እንዳለቀ በፍጥነት ወደ ኢንስፔክተር አወቀ ቢሮ አመራው፡፡ እሁድ ስለሆነ ይሆን ጭር ያለ ነው፡፡ የእግዜር ሰላምታ ተለዋውጠን ተቀመጥኩኝ፡፡

"በ72 ሰዓታት አሳውቅሃለሁ ብዬ ነበር?"

"አዎ"

"ምን ባክህ አንዳንዴ እኮ የምትሰማው የወንጀል አይነት ያሳቅቅሃል፡፡ እዚው ክፍለ ከተማችን ውስጥ አንድ ግለሰብ የገዛ ሚስቱን እና ልጁን በእሳት እያቃጠለ ሲሞቅ ተያዘ ብልህ ታምነኛለህ?"

"የዋቃ ያለህ? እዕምሮ ጤነኛ ነው?"

"ገና ምርመራ ላይ ነን... ለማንኛውም አንተ የሰጠኸኝ መረጃ ትክክል ነው፡፡ በእውነት ከልብ አመሠግናለሁ! አየህ አንዳንተ ከፖሊስ ጋር የሚተባበሩ ሰዎች ወንጀልን የሚጠሉ ናቸው፡፡ እኛ ሀገር ያለው ትልቁ ችግር ወንጀለኛን እያዩ ዝም ማለት ነው! በእኔ ካልደረሰ ምን አገባኝ የሚል እጉል የተሳሳተ ፈሊጥ አለ፡፡ አንተ ያደረከው ነገር በጣም የሚደነቅ ነው፡፡ ባልከኝ መሠረት ተጠርጣሪውን ስንከታተለው ነበር፤ ባጣራነው መሠረት የተጠርጣሪው እውነተኛ ስም "ማንደፍሮ ታረቃቸው" ነው፡፡ ተወልዶ ያደገው ደብረማርቆስ መንቆረር የተባለ ቦታ ነው፡፡ ይህ ወጣት እና ግብረ አበሮቹ ሀሰተኛ የመቶ ብር ኖት በመስራት እና ህፃናትን ለሁብረቲሞች በመሸጥ ኩላሊት ያሠርቃሉ... የሚያሳዝነው ከእነዚህ ወንጀለኞች ጀርባ አንድ እጅግ ከፍተኛ ባለስልጣን እጁ አለበት! ስለዚህ ወንጀሉ ወስብሰብ ያለ ነው፤ አየህ አሁን ብናስረው ራሱ በዚያ ከፍተኛ ስልጣን ባለው ሰው ሀይል ይፈታል፤ ስለዚህ ወንጀለኛውን እጅ ከፍንጅ ለመያዝ ከፍተኛ ክትትል ላይ ነን፤ በተለይ ሀሰተኛ የሆነውን ብር የሚያትሙበትን ቦታ ፍንጭ ስላገኘን በፍጥነት እንይዘዋለን፤ ግን ያው እንዳልኩህ ከጀርባው ትልቅ ሀይል ስላለው ያን ሀይሉን እንዳይጠቀም በብልሃት መንቀሳቀስ ስላለብን ነው"

"ምን መናገር እንዳለብኝ አላውቅም"

"ምን ታደርገዋለህ? በዚህ ወንጀልን እንከላከል እንላለን በዚህ ከፍተኛ ባለስልጣናት በወንጀል ውስጥ ራሳቸውን ዘፍቀው ታገኛቸዋለህ! ለማንኛውም ይህን ጉዳይ ለማንም እንዳትተነፍስ፤ አንተ ምንም እንደ ማያውቅ ሆነህ በዝምታ ልጁን ተከታተለው… በእርግጠኝነት የምነግርህ እሱን ሆነ ከእርሱ ጋር አብረው የሚሠሩትን በርካታ ሰዎች በፍጥነት በቁጥጥራችን ስር እናውላቸዋለን!! ከፍተኛ ስልጣን ያለው ግለሰብም ቢሆን በወንጀል ከመጠየቅ አያመልጣትም!! በተረፈ ቤትህ ውስጥ ስላሉት ሌሎቹም ሰዎች ማንነት አጣርተን ነበር"

"ማለት?"

"ምናልባት በተቀነባበረ መልኩ ያንተን ቤት የተከራዩ መስሎን ነበር፤ ግን ሰባኪውም፣ ማሳጂስቷም ፣ ወደ ኢንግሊዝ የሄደው ጋዜጠኛም ንፁህ ናቸው:: በነገራችን ላይ ቤትህ በጣም የሚያምር እና በንጽህና የተያዘ ነው፤ በተለይ ተክሎቹ በጣም ያምራሉ፤ በዚያ ላይ በጣም በማይታመን ርካሽ የሆነ ዋጋ ነው የምታከራየው:: በእውነት እንደ አንተ ለወገኑ መንግስት እንኳን አይራራም! በጣም ልትደነቅ ይገባሃል… በቃ በቅርቡ የደረስኩበትን እነግርሃለሁ:: በድጋሚ ስለ መረጃህ አመሠግናለሁ"

ከኢንስፔክተር አወቀ ጋር ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋውጠን ተለያየን:: መንገድ ላይ ብቻዬን እያወራሁ ነበር:: እህ ሀሰተኛ የብር ኖት እና ኩላሊት መሸጥ…? ከወንጀሉ ጀርባ ከፍተኛ ስልጣን ያለው ግለሰብ እጅ አለበት ማለት ምን ማለት ነው? አይ አንቺ ሚስኪን አገሬ ኢትዮጵያ! አልኩኝ ለራሴ…

በሌላ በኩል ደግሞ በአስተማሪው መሳይ ቁምላቸው የማስመሰል ጥበብ በጣም አደነኩት:: ስንት ጊዜ ውጪ መናፈሻው ውስጥ ተቀምጦ የተማሪ የፈተና ወረቀት ሲያርም አኮ አይቸዋለሁ!! ብዙ ጊዜ የተማሪዎችን የመማሪያ መፅሐፍ ሲያነብ ተመልክቸዋለሁ… ስለ እውነት ለገፀባህሪይ ፍለጋ የተነሳ ባልሰልለው ኖሮ በጭራሽ አልጠራጠረውም ነበር… እውነትም ይህ ገፀባህሪ መሆን የሚችል ወጣት ነው፤ የሚገርመው እኮ ስለመምህሩን ብዙ ነገር ነው የነገረኝ… ወይ ጉድ! አድናቂው ነኝ… ቢሆንም ወንጀለኛ ነው፤ ለዚያውም የውሸት ገንዘብ የሚያሰራጭ… ለዚያውም በሚስኪን ህፃናት ኩላሊት ንግድ ላይ የተሰማራ… እናም በፍጥነት እንዲያዝ እፈልጋለሁ … ግን ቢያንስ አንድ ገጸባህሪይ እንዳገኘሁ ተሰምቶኛል… ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ነውና::

# 11

# የፍቅር ጥያቄ ...

ህይወት ቀጥላለች፡፡ ከምንም በላይ ከደሊላ ጋር ያለን መስተጋብር እየጠነከረ እየመጣ ነው... አሁን የኔ ጓደኛ ደሊላ እየሆነች ነው፡፡ ምናልባት እንዴት 97 ሚሊዮን ህዝብ ካላት ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ጓደኛ ብቻ ይኖርሃል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ እርግጥ ፈሪ አይደለሁም፡፡ ከሰዎች ጋር መግባባት የማልችል ደካማም አይደለሁም፤ ቢሆንም ከራሞስ ሌላ ሌሎች ብዙ ጓደኞች ነበሩኝ፤ ቢያንስ የቅርብ የምላቸው ስምንት ጓደኞች ነበሩኝ፤ ግን አድስአበስ ነኝ፤ አበል እና ከድር ህንድ ናቸው፡፡ ቢርሳቢህ እና ያሬድ ሩሲያ ናቸው፡፡ ታዲዮስ እና ጢሞቲዎስ ደቡብ አፍሪካ ናቸው፡፡ ማከዳ እና ፍፁም ፈረንሳይ ናቸው፡፡ ራሞስ ደግሞ ይቺን አለም በአሰቃቂ የመኪና አደጋ ተሰናብቷታል... እናም ብቸኛ ነኝ... እናም አድስአበስ ጭምር ሳልሆን አልቀረም... ግን በቅርቡ ከብቸኛዋ ደሊላ ጋር በመግባባቴ ተደስቻለሁ... እውነቱን ለመናገር ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ማታ መታ ስለምፅፈው ድርሰት ሆነ ስለገፀባህሪያት ማሰቤን ትቼ ስለ ደሊላ በብዛት እያሰብኩ ነው ... ቢቃ የሆነ ደስ የሚል ስሜት እየተሰማኝ ነው፡፡

ወይ ጉድ!... ፍቅር ቢጤ ነገር ሳይዘኝ አልቀረም ... የሆነ መልካምነት ደሊላ ውስጥ አንብቤያለሁ... የሆነ ጥንካሬ አንብቤባታለሁ... ልጅ መውለድ እንደማትችል ሁሉ ባውቅም... ቢቃ ውስጤ ያለውን ለመናገር ጥሩ ስሜት እየተሰማኝ ነው...

ቢቃ ካለችበት የዘመነት ህይወት ላወጣት አሻለሁ... ከእኔ ጋር ሆና የልጅነት ህልሟን እንድታሳካ አሻለሁ... የፍቅር እና የክብር ህይወት እንድትኖር እሻለሁ... ስለ ልጅ ከሆነ የአንድ ችግረኛ ቤተሰብ ተቀብለን በማደጎ ማሳደግ እንችላለን... እናም ስለምፅፈው ድርሰት ነቼ፡

ውስጤ ስላለችው የደራሲነት መክሊት ማውጠንጠን ትቼ... ስለደራሲነት መሆን መጨነቅ ትቼ ... ስለ ደሊላ በመኖሪያ ቤቴ ሆነ ባንክ ቤት ስቀመጥ እያውጠነጠንኩ ነው... የፍቅር ስሜት በመላው አካላቴ እየሸተተኝ ነው... እውነተኛ ፍቅርን ተርቢያለሁ... ፍቅርን ሰጥቼ ፍቅርን መቀበልን እሻለሁ!!... እናም ደሊላን የፍቅር ጥያቄ ለመጠየቅ እያውጠነጠንኩ ነው!!

እርግጠኛ ለመሆን በገዘምታ ተቀምጬ ብዙ እውጠነጠንኩ:: ውስጤ የሚለኝ ለደሊላ የፍቅር ጥያቄ አቅርብ ነው:: ደሊላ የእኔን የፍቅር ጥያቄ እንቢ ብትለኝስ?... እ... በዚህን ሰዓት እዕምሮዬ ላይ የመጣው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለን አብሮኝ ይማር የነበረው እንደ ስሙ ቅዱስ የሆነ፣ ቅዱስ ባይከዳኝ ነው:: ፍፁም እርጋታ የተላበሰ፣ ቀና የሆነ፣ ለሰው መልካም ነገር ብቻ የሚመኝ እና የሚያደርግ የደሴ ልጅ ነበር::

አንድ ማክሰኞ ማለዳ እጅግ በጣም ተደስቶ! ከደስታው ብዛት እየዘለለ ሰማዩን ለመንካት ጥረት እያደረገ ተመለከትኩት... እንደ ህፃን ልጅ የሚያደርገውን አጥቶ የሚቦርቀውን ቅዱስን ስታዘብ ቆየሁና በመጨረሻ ተጠጋሁት.

"እጅግ በጣም የተደሰትክ ትመስላለህ! እንደዚህ የደስታ ዝናብ ከፊትህ ላይ አይቼ አላውቅም"

"ትክክል ነህ"

"ምን ተገኘ?"

"ለዚያች በፍቅር እብድ ላልኩላት ፅጌሬዳ ለሶስተኛ ጊዜ የፍቅር ጥያቄ አቀረብኩላት! በጭራሽ እንደማልሆናት ነገረችኝ... ቢቃ ከዚህ በኋላ አልጠይቃትም! በዚህ ነው በደስታ ባህር ውስጥ የገባሁት"

"እየቀለድክ ነው?"

"እባቴ ይሙት"

"እንቢ አለችህ?"

"አዎ"

"ለእርሷ ያለኝን ፍቅር በቃላት ልገልፀው ከቶ አልችልም! የደስታዬ

ምንጭም ውስጤ ያለው የፍቅር ብዛት የወለደው ነው።

"እንዴት ታዲያ እንቢ ተብለህ በደስታ ልትሞላ ቻልክ?"

"በቃ አወራን! ለእኔ ልትሆን እንደማትችል በሚገባ አስረዳችኝ፤ እኔም በፀጋ ተቀበልኩት!! የደስታዬን ምንጭ ልንገርህ? በመጀመሪያ የፍቅር ጥያቄ ስታቀርብ እሺም እንቢም ልትባል እንደምትችል ማወቅ ብልጠት ነው:: ይህን እውነት በሚገባ አውቃለሁ:: ለምኑን ለራሴ የጠየኩት ግዙፍ ጥያቄ በጣም ለማፈቅራት ሴት የመጨረሻ ልሰጣት የምችለው ትልቅ ስጦታ ምንድን ነው? ስል ራሴን በጣም ጠየኩት:: ሁለት መልስ አገኘሁ:: ልንገርህ?"

"እንዴታ?"

"በጣም ለማፈቅራት ልጅ ልሰጣት የምችለው የመጨረሻ ከእንቁም የበለጠ ስጦታ ሁለት ነው:: የመጀመሪያው ያቺን የማፈቅራትን ልጅ አግብቼ መላ ህይወቷን በፍቅር እየተንከባከብኳት አብሬያት መኖር!! ይህ ካልሆነ ሁለተኛው ስጦታ ያቺ የማፈቅራት ልጅ ከእኔ ጋር መኖር ደስታ የማይሰጣት ከሆን! እኔን እንደማትወደኝ ከነገረችኝ! እኔ የእርሷ ምርጫ እንዳልሆንኩ ከነገረችኝ ... በቃ ይህን እውነታ በፀጋ በመቀበል ከምትወደው ሰው ጋር በደስታ እንድትኖር እውነታውን አምኖ መቀበል እንጂ ከችች አለማለት!! እናም እኔም ያደረኩት ይህን ነው!! ይህን ለማድረግ ደግሞ የእውነተኛ ፍቅርን ትርጉም በሚገባ ማወቅ አለብህ" ነበር ያለኝ:: እናም እኔም ለደሊላ የፍቅር ጥያቄ አቅርቤላት እንቢ ከተባልኩ የቅዱስን ምክር እተገብር ይሆናል... በእርግጥ ያስቸግራል! እውነተኛ ፍቅር ግን የማይችለው ሸክም አለ ይሆን...?? እናንተስ በቅዱስ ሀሳብ የእውነት ትስማማላችሁ? በሁለቱም ምርጫዎች... ??

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________ ::

________________________________

# 12

# ሚስኪን ነፍስ...

በእያንዳንዷ ደቂቃ ከገንዘብ ጋር ንኪኪ ስለሚደረግ የባንክ ቤት ስራ ጥንቃቄ በጣም ይፈልጋል፤ በመሆኑም ለሴኮንድ እንኳ ሳልዘናጋ እንከን እንዳይገኝብኝ በጥንቃቄ እየሰራሁ ነው። በስራዬ ደስተኛ ነኝ፣ በተለይ ያሰብኩትን የፍቅር ጥያቄ እስካሁን ባልጠይቃትም ደሊላ ስራ ሳይኖራት ከደሊላ ጋር በማሳልፈው ውብ ጊዜ እጅግ በጣም ሀሴት እያደረኩ ነው። ቤት በማትውልበት እና ብቻዬን ስሆን ደግሞ ስለ ደሊላ እውጠነጥናለሁ። ስለ ደሊላ በማውጠንጠኔ ደግሞ ደስተኛ ነኝ። የፍቅር ጥያቄዬን በሚቀጥለው ሰኞ ላቀርብላት ወስኛለሁ።

እህ ያልነገርኳችሁ ነገር በጋዜጠኛው እንዳልካቸው ቤት ሌላ ተከራይ ገብቷል። የገባው እርጋታ በተሞላበት ሰባኪው ዘኪዮስ በርናባስ አማካኝነት ነው። የእርሱን ቢጤ አይነት ሰው ነው ያመጣው።

እህ ሌላ እስካሁን ያልነገርኳችሁ ነገር ቢኖር ስለ ዘበኛችን ነው። በጣም አሪፍ ሰው ናቸው። ጥሩ ብር እከፍላቸዋለሁ። ለቤተሰቦቹ የበዓል ቀን እየጠበኩ በግ እና የቤት ጣጣ እሸፍንላቸዋለሁ... እሳቸውም መልካም እና ታማኝ ናቸው። ለእኔ የሚሆነውን የባልትና ዕቃዎች ሁሉ የሚገዙልኝ እሳቸው ናቸው። እኔ እንደ ዘበኛ አልቆጥራቸውም። እንደ ቤታቸው ዘና ብለው ይኖራሉ ... እኔ ከመወለዴ በፊት ራሱ እዚህ ቤት ነበሩ፤ በቃ እንደ አባቴ ነው የማያቸው፤ በጣም ደስ የሚሉኝ አሉባልታ አይወዱም። በዚያ ላይ ስለ ማንም ማውራት

አይወዱም፡፡ የሥራ ሰው ብቻ ናቸው ፡፡ አበባ መንከባከብ፣ ግቢውን ማስዋብ፣ በትርፍ ጊዜያቸው ስለኃይለስላሴ ታሪክ ማንበብ... አንዳንዴ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪኮችን ሲያነቡ አያቸዋለሁ ... ብቻ ከእኔ ጋር ተመቻችተናል፣ አንድ ቀንም እኔ ሆንኩ እሳቸው ከፉ ቃል ተነጋግረን አናውቅም፤ ባጭሩ የሚደነቁ ጠንካራ ሽማግሌ ናቸው፡፡ ለምን ለገፀባህሪነት እንዳልመረጥኳቸው አላውቅም፡፡ የሰው ልጅ ሲባል በቅርቡ የተቀመጠውን ሳይሆን በሩቁ ያለን ማየት ይማርከዋል የሚባለው ተከስቶብኝ ይሆን...? እንጃ፡፡

ዕለተ እሁድ፡፡

ደሊላ ቅዳሜ እና እሁድ በጣም ስራ ይበዛባታል፡፡ አብዛኛው የማሳጅ ተጠቃሚ በሁለቱ ቀናት እንደሆነ ሹክቱስ ብላኛለች፡፡ ነገ ዕለተ ሰኞ የዕረፍት ቀኗ፣ ነው እናም ነገ ከስራ ስወጣ ደሊላን ሸራተን አዲስ ሆቴል ልወስዳት ወሰንኩ፡፡ ከዚያ የሚያምረው የውሃ ፏፏቴ ጋር እስቀምጬያት ውስጡ ስለሚሰማኝ ነገር ልነግራት ወሰንኩ፡፡ እርግጠኛ ባልሆንም ደሊላ ጋርም የሆነ ነገር፣ የሆኑ ምልክቶች አያየሁባት ነው፤ በተለይ ስታየኝ የምትሆነው፤ አብረን ስንሆን የምትሆነው... ብቻ እኔ ውስጥ ሹክቱስ ማለት የጀመረው የፍቅር ስሜት ደሊላ ልብ ውስጥም ሹክቱስ ማለት እንደጀመረ ይሸተኛል! ስድስተኛው ስሜቴ ይነግረኛል፣ ስለዚህ ይበልጥ እፍቅሬያት በራሴ ላይ ጣጣ ከማብዛቴ በፊት ውስጡ ያለውን የፍቅር ስሜት ለመንገር እቀድኩ፡፡ ወዲያው ይህን እቅዴን እንደ ጨረስኩ ደወልኩኝ፡፡ ስራ ላይ እልነበረችም መሰለኝ በአንደኛው ጥሪ አነሳች፡፡

"ሻሎም"

"ሻሎም! የሚገርምህ ልደውልልህ እያሰብኩ ቀደምከኝ"

"ምነው?"

"ነገ ሰኞ አይደለም?"

"አዎ"

"ሰኔ ሁለት! ሰኔ ሁለት ደግሞ የተወለድኩበት ቀኔ ነች እና በልደቴ ቀን አንድ ውለታ ከቻልክ ትውልልኛለህ?"

"ምን?"

"ግን ይቅርታ"

"ለምን?"

"ከስራ ነገ መቅረት ትችላለህ?"

"ችግር የለም ማስፈቀድ እችላለሁ፤ በዚያ ላይ ያልተጠቀምኩበት የዓመት እረፍትም አለኝ"

"ስለዚህ ትችላለህ ማለት ነው?"

"በሚገባ"

"ዋው! አመሠግናለሁ"

"ምንም አይደለም"

"ስለዚህ ዛሬ እስከ 2:00 ሰዓት እሰራለሁ፤ ነገጠዋት ተነስተን ሰደሬ ጥሩ ጊዜ እናሳልፋለን፤ ለማንኛውም ማታ ከስራ ስወጣ በዝርዝር እናወራለን ቤት ትጠብቀኛለህ ወይስ?"

"ለዚያውም! ግሩም አራት ሰርቼ እጠብቅሻለሁ"

"ባንዳፍ! አመሠግናለሁ እስከዛው መልካም ጊዜ"

"ላንቺም መልካም ጊዜ"

ተባብለን ተለያየን:: ከዚያ ከራሴ ጋር ማውራት ገባሁ:: ነገ የልደቷ ቀን ከሆን ምርጥ ገጠመኝ ነው:: አዚች ምድር ላይ በመጣችበት የደስታዋ ቀን እንደ ወደድኳት እነግራታለሁ:: ከዚያ እሺ ካለችኝ ይቺን ግራ የምታጋባ፤ የማትጨበጥ ህይወትን በፍቅር፣ በደስታ፣ በመተሳሰብ... ሸርብትን እንላታለን... ቤቃ ህይወት ሸርብትን ነች:: በፍቅር ሸርብትን እንደማለት ደግሞ የሚያረካ ነገር በምድር ላይ ምን አለና ?"

ለማታ የሚሆነውን ግሩም አራት ሰርቼ እንደጨረስኩ አዕምሮዬን ይበልጥ ዘና ለማድረግ አስር ሰዓት ሲሆን ከቤት ወጣሁና የተለመደችው አርጋታ የበዛባት ካፍቴሪያ በመግባት በጣም የምወደውን ካፑችኖ በማዘዝ ጠጣሁ:: ከዚያ ድንገት የራሞስ ቤተሰቦች ጋር ከሄድኩ ብዙ ጊዜ ስለሆነኝ እነሱን ለመጠየቅ ፍራፍሬ ቤት በመግባት አፕል፣ ብርቱካን እና

ሙዝ በመግዛት ወደ ፒያሣ አመራሁ:: ከራሞስ እናት፣ ታናሽ እህቱ እና ታላቅ ወንድሙ ጋር ስንጨዋወት ቆይተን የአራት ሰዓት ከመድረሱ በፊት ልክ 12:55 ደቂቃ ሲል ተሰናብቼያቸው ወጣሁኝ::

ከእነ ራሞስ ቤት ብዙም አልራኩም:: መንገድ ላይ እየተራመድኩ ሳለ ሞባይሌ ድንገት ጥሪ አሰማኝ:: እንደተለመደው የማላውቀው ቁጥር ስለሆነ በሶስተኛው ጥሪ አነሳሁት:: ሁሌ የማላውቀው ቁጥር ከሆነ በሶስተኛው ጥሪ ነው የማነሳው

"ሀሎ"

"ኪኛ እኔን አታውቀኝም ስልክህን ያገኘሁት ከደሊላ ስልክ ላይ ነው!! አሁኑኑ በፍጥነት ደሊላ የምትሰራበት ማሳጅ ቤት ና!! የሚገኘው መስቀል ፍላወር ... " ብላ ወዲያው ስልኩን ጆሮዬ ላይ ጠረቀመችው:: ግራ ስለገባኝ የደሊላ ስልክ ላይ ወዲያው ደወልኩኝ:: አይነሳም:: ልጅቷ ጋርም መልሼ ስደውል አታነሳም... ምን ተፈጠረ በማለት ኮንትራት ታክሲ በመያዝ ደሊላ የምትሰራበት ማሳጅ ቤት አመራሁ:: ደረስኩ:: በፍጥነት ወረድኩ:: ማሳጅ ቤቱ ጋር ስደርስ ከአስር በላይ ፖሊሶች በተጠንቀቅ ቆመው ተመለከትኩ::

ልቤ እየፈራ ወደ ማሳጅ ቤቱ በር ስጠጋ አንደኛው ፖሊስ

"ቁም!!" አለኝ:: ከዚያ በፍጥነት ቀረበኝና

"የት ነው?"

"ማሳጅ ቤት"

"መግባት ከልከል ነው"

"ስልክ ተደውሎ ና ተብዬ ነው"

"መቼ?"

"አሁን"

"ማን ነው ስምህ?"

"ኪኛ ዮሐንስ"

"እዚው ጠብቀኝ" ብሎኝ ከእኔ ራቅ አለና በእጁ በያዘው የመነጋገሪያ ስልክ የሆነ ነገር በትግርኛ ቋንቋ አወራ:: ትግርኛ ቋንቋ ስለማልችል የሚያወራውን ለመረዳት አልቻልኩም... ወዲያው በፍጥነት ሌላ ፖሊስ እኔ ጋር መጣና

"አቶ ኪኛ" አለኝ::

"ነኝ"

"ደሊላን ታውቃታለህ?"

"አዎ"

"በዝምታ ተከተለኝ" አለና በፍጥነት እየተራመደ ከማሳጅ ቤቱ ብዙም ርቀት ላይ የማትገኘው የፖሊስ መኪና ውስጥ አስገባኝ:: ከእርሱ በተጨማሪ ሌላ ፖሊስ መኪናው ውስጥ ተቀምጧል::

"አቶ ኬኛ ደሊላን የት ነው የምታውቃት?"

"እኔ ቤት ነው ተከራይታ የምትኖረው"

"ዛሬ ቀን ከአንተ ጋር በስልክ አውርታችሁ ነበር?"

"ትክክል"

"ስለምን?"

ያወራነውን ነገር ሳልዋሽ ነገርኳቸው:: ከዚያም በጣም ግራ ስለገባኝ

"ምን የተፈጠረ ነገር አለ ጌታዬ?"

"አዎ" አለና በዝምታ በሚመረምር ዓይን በትኩረት እየተመለከተኝ ቆየና

"ጥሩ ዜና ልነግርህ አይደለም" ገና ከማለቱ የልብ ትርታዬ ጨመረ:: ውስጤ እጅግ በጣም ተረበሸ:: ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ:: ራደ:: የሆነ ነገር ነዘረኝ!

"ደሊላ ከቀኑ 11:30 ደቂቃ አካባቢ ማንነቱ ባልታወቀ ሰው በረቀቀ ሁኔታ ተገላለች:: ሬሳዋ ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ሄዷል..."

መናገር ስላልቻልኩ! ከንግግር ይልቅ እንባ ነው የቀደመኝ:: ከሁለቱም አይኖቼ የእንባ ዘለላ ጠብ ጠብ አሉ.. ለምን ይሆን የምወዳቸውን ሰዎች የምነጠቀው? ለረጅም ደቂቃዎች አለቀስኩኝ! ይበልጥ ባዶነት ተሰማኝ! ይበልጥ ብቸኝነት ወረረኝ... ይበልጥ ከንቱነት ተሰማኝ... ሁለቱ ፖሊሶች ሁኔታዬን በዝምታ ሲከታተሉኝ ቆይተው በመጨረሻ

"ምናልባት ወንጀለኛው ላይ ለመድረስ ፍንጭ ሊሆነን ይችላልና፣ ስለ ደሊላ የምታውቀውን እንዳችም ሳትደብቀን ንገረን! በእርግጥ ሁኔታዋ ያሳዝናል ግን ቢሆንስ ወንጀለኛውን መያዝ አለብን"

በተሰበረ መንፈስ፣ ተስፋ በቆረጠ መንፈስ፣ ከደሊላ ጋር ያወራነውን በተለይ ስለ አባቷ ፣ ስለፈላጊነቷ፣ ስለ ኢትዮጵያ የመጣችበት ሁኔታ፣ ከመቼ ጀምሮ እኔ ቤት ተከራይታ

መኖር እንደጀመረች ሁሉንም ዘከዝኪ ነገርኳቸው::

ከምሽቱ 2:45 ደቂቃ ላይ ከሁለቱ ፖሊሶች ጋር በመኪና እኔ ቤት መጣን:: ደሊላ የምትኖርበትን ቤት ከደሊላ ቦርሳ ውስጥ ባገኙት ቁልፍ ከፍተው በመግባት እያንዳንዱን ነገር በጥንቃቄ ፈተሹ:: መረመሩ:: ቁምሳጥኑን ከፍተው በረበሩ:: የቀን ውሎ መፃፍያ አጀንዳ አገኙ... በመጨረሻ እኔን ቤቴ ጥለውኝ ወጡ:: ያጋጣሚ ሆኖ ቤት ውስጥ ሰባኪው ዘኪዮስ፣ አዲሱ ተከራይ እና አጭበርባሪው መሳይ ባለመኖራቸው ማንም አልሰማም ! ለዘበኛዬም ብዙ ሳላወራ በዝምታ ሳሎን ገብቼ መሬት ላይ ተቀምጬ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: እስከሚወጣልኝ ስቅስቅ ብዬ እንደ አልቃሻዎቹ ሴቶች ነፈረኩኝ:: አነባሁ:: እያለቀስኩ... እዛው መሬት ላይ እያውጠነጠንኩ እንቅልፍ በዓይኔ ውል እንኳ ሳይልብኝ አደርኩኝ...

በጠዋት ተነስቼ ምንም ነገር ሳልቀምስ በቀጥታ መስሪያ ቤት በመሄድ ያለውን ነገር ለአለቃዬ ነግሬ ወደ ፖሊሶቹ አመራሁ:: ተገናኘን:: ትላንት አብረውኝ ከነበሩት ሁለት መርማሪዎች አንደኛው ገና እንዳየኝ ወንበር ላይ እንድቀመጥ በምልክት ነገረኝ:: ተቀመጥኩ፡ ከዚህ

"በተደረገላት ምርመራ አደገኛ መርዝ በተነከረ ጨርቅ ታፍና ነው የሞተችው:: ከዚህ በተጨማሪ ከሞተች በኋላ በቂጧ በኩል እንደተደፈረችም የምርመራ ውጤቱ ያሳያል:: እኛ ማሳጅ ቤት ባደረግነው ምርመራ ወጣት ደሊላ ከጠዋት እስከ ሞተችበት ሰዓት ድረስ ስምንት ሰዎችን አስተናግዳለች:: በመጨረሻው ፊቱን ተሸፍኖና ፣ ጥቁር ኮፍያ ያደረገ ወጣት ያስተናገደች ሲሆን ከዚህ በፊት ማሳጅ ቤቱ ውስጥ እንዳልመጣ ለጊዜው በተጠርጣሪነት ይዘን ያሥርናቸው ማሳጅ ቤት ውስጥ የሚሠሩት ሴቶች ተናግረዋል:: ከሴቶቹ ንግግር በመነሳት የሰውየውን ቁመት እና የሰውነት ሁኔታ በሰዓሊያችን አማካኝነት የተሳለ ሲሆን ይህን ሰው ፍለጋ እንጀምራለን:: በእርግጥ አንተ እንደነገርከን ሆነ እኛ ለማግኘት በሞከርነው ሁኔታ ከዚህ ወንጀል ጀርባ የእስራኤል መንግስት እጅ አለበት ለማለት በጣም ያስቸግራል፤ ቢሆንም መረጃውን እናጣራዋለን"

"ከዲያሪዋ ላይ መረጃ የለም? ምናልባት ቂመኛ ሰው ካለት" አልኩት፡፡

"ዲያሪዋ ላይ ምንም የለም! ዲያሪዋ ላይ በሙሉ የፃፈችው በየቀኑ ስለሚሰማት የራሷ ስሜት፣ ስለምታነባቸው መፅሐፍት እና በተደጋጋሚ የፃፈችው በማታውቀው እና ባላሰበችው መንገድ ፍቅር እንደያዛት! ይህን ፍቅሯን ለመግለፅ እንደፈራች፣ ልጁን ስታየው ስለሚሰማት ስሜት... ወዘተ ነው፡፡ ' K ' እያለች ነው የምትፅፈው ፤ ከፃፈችው ሀሳብ በመነሳት ' K ' የአንተ ስም መሰለኝ" አለና ዲያሪዋን በእርጋታ አቀበለኝ፡፡ ከዚያ በትኩረት እየተመለከተኝ "አሁን በፍጥነት የምትቀበርበት ሁኔታ ላይ ብንወያይ የተሻለ ነው፡፡ በእርግጥ ኢትዮጵያ ውስጥ የምታውቀው ዘመድ ስለሌላት ማዘጋጃ ሊቀብራት ይችላል ፤ ከፈለክ አንተም ልታስቀብራት ትችላለህ..."

በዚህ ዙሪያ ተወያየን፡፡ ሬሳዋን እንድመለከት ፖሊስ ሆስፒታል ሄድን፡፡ ሬሳ ክፍል ገብቼ ያቺን ሚስኪን ፈላሻ! ያቺን ሚስኪን ብቸኛ ሴት! ያቺን ሚስኪን ደሊላ... ስመለከታት... ስለ እውነት የተሰማኝን ነገር በቃላት ለማስቀመጥ ይቸግረኛል!! ከልቤ አዘንኩ... አለቀስኩ... አይ ህይወት ከንቱ አልኩኝ... የነበራት ህልም በተለይ የዛሬ ዓመት ያቀደችው እቅዷ ትዝ አለኝና ባርባር  አለኝ... ምግብም ከትላንት ማታ ጀምሮ ስላልቀመስኩ ነው መሰለኝ አዞረኝ! መሬቱ ላይ ወደኩኝ... በዚህን ሰዓት ለሁለት ይዘውኝ ወጡና የሚቀመስ እና የሚጠጣ ነገር ሰጡኝ፤ የግድ ቀመስኩኝ... እየመረረኝ ጎረስኩኝ... አይ ይቺ ከንቱ ህይወት...!!

pdf by @shuktus_books

# 13

# ቀብር

ያስቸግራል። አዎ ያስቸግራል። ልብ ይነካል። አዎ ልብ ይነካል። ግራ ያጋባል። አዎ ግራ ያጋባል። ለማመን ይከብዳል። አዎ ለማመን ይከብዳል... ግን እውነት መራር ብትሆንም መቀበል ግድ ይላልና እጅግ በጣም ትንሽ ሰዎች በተገኙበት ሁኔታ፣ ዘኪዮስ፣ አዲሱ ተከራይ፣ አጭበርባሪው መሳይ፣ ሁለት ፖሊሶች ፣ ደሊላ ጋር ይሠሩ የነበሩ ጓደኞቿ በጊዜያዊ ተጠርጣሪነት ተይዘው እስር ቤት ስለሚገኙ እንዳቸው እንኳ ባልተገኙበት ብቻ... እጅግ አነስተኛ ቀባሪዎች ብቻ በተገኙበት ሁኔታ ያቺ ሚስኪን ወጣት! ያቺ ህልም የነበራት ወጣት! ያቺ ማንም ያልነበራት ወጣት... ለምን እንደ ሞተች? ለምን እንደተገደለች? ማን እንደገደላት እንኳ ሳይታወቅ... ተቀበረች። አፈር ለበሰች። አፈር ነችና ወደ አፈር ተመለሰች።

ደሊላ ዕድር የላት! ሰልስት የላት! ልጄን ማን ገደላት ብሎ የሚጠይቅላት ወገን የላት! እይ ብቸኝነት!! በሰስተኛው ቀን የተቀበረችበት "ዮሴፍ" ቤተክርስቲያን በመሄድ ትኩስ መቃብሯ ላይ አበባ አስቀመጥኩላት። ላለቅስላት ብጥርም የእንባ ቀረጢቱ አልቆታል መሰለኝ እንቢ አለኝ፤ ፈጣሪ ነፍስሽን ምህረት ያድርግልሽ ብዬ ተመለስኩኝ።

መስሪያ ቤት ገብቼ እንደነገሩ ስሰራ ዋልኩና ከስራ ቦታ ስወጣ የደሊላ ጉዳይን የያዘው መርማሪ ጋር አመራሁ። አወራን። ምንም አዲስ ነገር እንደሌለ እና ወንጀለኛውን ለመያዝ ጥረት እንደሚያደርጉ ብቻ ነገረኝ።

የደሊላን ጉዳይ ለማጫወት ወደ ኢንስፔክተር አወቀ ቢሮ አመራው:: እንዴ???... ምንድን ነው እየሆነ ያለው? ሊያሳብዱኝ ነው እንዴ? እየተከናወነ ያለው ነገር ምንድን ነው?... ወደ ኢንስፔክተር አወቀ ቢሮ ልገባ ስል አንድ ፖሊስ አስቆመኝ

"ምን ልርዳህ?"

"ኢንስፔክተር አወቀን ፈልጌ ነበር"

"አልሰማህም?"

"ምኑን?"

"ኢንስፔክተር እኮ በመኪና አደጋ ከሞተ ሰስት ቀን አለፈው"

"የዋቃ ያለህ? በመኪና አደጋ" አልኩኝ የምሰማውን ማመን አቅቶኝ::

"እዎ"

"የት አካባቢ ነው?"

"ዝርዝር ጉዳዩ ምንም አያደርግልህም፤ አሁን እኔ የምረዳህ ነገር አለ?"

"አመሠግናለሁ ሌላጊዜ እመለሳለሁ" አልኩና ከፖሊስ ጣቢያው በመውጣት የሆነ ካፍቴሪያ ገብቼ በመቀመጥ ማውጠንጠን ገባሁ:: ምናልባት ኢንስፔክተር አወቀ እንደነገረኝ ከእነ መሳይ ቁምላቸው ጀርባ አንድ ጡንቻው ጠንካራ የሆነ ከፍተኛ ባለስልጣን እጁ ካለበት እኔ የነገርኩትን ጉዳይ ሲያጣራ ነቅተውበት በረቀቀ ሁኔታ ገድለውት ይሆናል! እናም ከኢንስፔክተር አወቀ ሞት ጀርባ እጇ እንዳለበት ሸተተኝ ወይስ አጋጣሚ ነው??

ወይ ጉድ! እኔን ብሎ ደራሲ! እኔን ብሎ ሰላይ! እኔን ብሎ ገፀባህሪ ፈላጊ!... በቃ አኔም አለቀልኝ! እሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል ማለት ይሄ ነው:: ምን ማድረግ እንዳለብኝ፣ ይህን ጉዳይ ለማን መናገር እንዳለብኝ... እያውጠነጠንኩ በደመነፍስ ቤቴ ተመለስኩ::

ሳሎን ቤት በመቀመጥ ለረጅም ሰዓት ቆዘምኩ:: ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ገባኝ... ይህን ጉዳይ ለመንገር ወደ ታላቅ ወንድሜ ልደውል አሰብኩና ለራሱ በጣም የሚወዳት ፍቅረኛው ታማበት ጭንቀት ላይ ስለሆነ ይበልጥ ጭንቀት እንዳላበዛበት ሀሳቤን ቀየርኩት:: በዝምታ ተውጬ ተቀመጥኩ:: በዚህን ሰዓት ነው ብቸኝነት ምን ያህል አስቀያሚ ነገ

እንደሆነ የተረዳሁት... አዎ ብቸኝነት ከዘረኝነት ራሱ የበለጠ አስቀያሚ ነገር ነው!!

ይህን እያውጠነጠንኩ በዝምታ ተቀምጬ እያለሁ ከምሽቱ 2:45 ደቂቃ ሲል የሳሎን ቤቴ በር ተንኳኳ:: በድጋሚ በሀይል ተንኳኳ:: እንደምንም ከተቀመጥኩበት ወለል ላይ በመነሳት በሩን ሄጄ ከፈትኩት:: አጭበርባሪው መሳይ ቆሞላቸው ነበር:: የሆነ ነገር ውስጤን ወረረኝ!! እንቀው እንቀው የሚል ስሜት መጣብኝ!!

"መግባት እችላለሁ?" አለኝ::

"ግባ" አልኩት በቀዘቀዘ ድምፅ::

ትልቁ ሶፋ ወንበር ላይ ተቀመጠ:: እኔም በዝምታ ፊት ለፊት የሚገኘው ሶፋ ወንበር ላይ ተቀመጥኩኝ::

"አንድ ነገር ልነግርህ ነበር ግን ጥሩ ሙድ ውስጥ ያለህ አይመስለኝም?"

"ችግር የለውም ንገረኝ"

"እርግጠኛ ነህ?"

"ችግር የለም ንገረኝ" አልኩት በድጋሚ::

"እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ሞት በጣም እጠላለሁ:: ሰው ሲሞት ሰላም የለኝም፤ እንቅልፍ አልተኛም፤ ሰዓቱን ራሱ በብዛት ውጪ እየወጣሁ ነው የማድረው:: አየህ እኔ የሞት መንፈስ ቅርብ ያለውን ሰው ይጠራል የሚል እምነት ስላለብኝ እንደምታውቀው ከኔ ጎን የነበረችው ደሊላ ነፍሷን ይማረውና አርፋለች፤ ስለዚህ ነገ ቤቱን እለቃለሁ! ያው በስምምነታችን መሠረት ከወር በፊት አስቀድሜ መንገር ነበረብኝ ያን ባለማድረጌ የኔ ጥፋት ስለሆነ የቤቱን የአንድ ወር ሂሳብ እከፍላለሁ! ይህን ልነግርህ ፈልጌ ነው"

እሆ... ሊበዷት ያሰባትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል አሉ:: ከዚህ መሳይ እስመሳይ የሆነ ሰው ጀርባ ብሁ ጣጣ እንዳለ ተሰማኝ:: ይቺን የሞኝ ምክንያት ያቀረበልኝ ሌላ ስራ ደግሶ እንደሆነ ስድስተኛ ስሜቴ በፍጥነት ሹክ ቴስ አለኝ:: ከኢንስፔክተር እውቀ ሞት በስተጀርባ እጁ እንዳለበት ተሰማኝ:: በግድ ቆይ ማለት አልችልም:: ከፈለገ እኮ ያለ ምክንያትም ከቤቴ መውጣት መብቱ ነው:: ማን ይከለክለዋል...?? እናም ውስጡ እያረረ፣በጎሪጥ እየተመለከትኩት

"ለመሆኑ ቤት አግኝተሃል?" አልኩት::

"ተከራይቼ ጨርሻለሁ"

"የት?"

"ቦሌ ሚካኤል"

"ቦሌ ሚካኤል? እንዴ! አይርቅህም?"

"ለምን?"

"እስተምራለሁ ያልከኝ እኮ አራት ኪሎ አካባቢ አይደለም?" ስለው ደንገጥ ነገር አለና

"እህ... ለጊዜው ነው አቀይራለሁ! በዚያ ላይ ወሩ ሰኔ ስለሆነ በቅርቡ ትምህርት ያልቃል" አለኝ፡፡ ያው ቦሌ ሚካኤል ያለኝም ውሸቱን እንደሆነ ገብቶኛል...

"ቢቃ እመሠግናለሁ ቁልፍና ገንዘቡን ጠዋት አስጥሃለሁ ደህና እደር! ሁለት ሰዓት ላይ እለቃለሁ" ብሎኝ ጠንከር አድርጎ በመጨበጥ ተለየኝ፡፡ ወጣ፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማውጠንጠን ገባሁ፡፡ ይህ ወንጀለኛ በእርግጠኝነት ኢንስፔክተሩን እንዳስገደለው ውሴጤ ሹክ ብሎኛል... ከጀርባው የከፍተኛ ባለስልጣን እጅ ካለበት ብዙ እጆች አሉት ማለት ነው፡፡ ቆይ ግን ኢንስፔክተሩን ከገደለ እንዴት እኔን አልገደለኝም ??... ወይስ እኔ የእርሱን ማንነት እንዳወኩበት አላወቀም? ግራ ነው የገባኝ...መቼም የውሸት ብር እያሰራጨ ከፍተኛ ወንጀል መስራቱን እያወኩ... መቼም ልጅ ባይኖረኝም የሚስኪን ህፃናትን ኩላሊት እየሸጠ እንደሚኖር እያወኩ... መቼም በወገኑ ኢትዮጵያዊያን ላይ የጭካኔ ተግባር እያከናወነ እያየሁ ዝም ለማለት፣ አላየሁም ለማለት፣ እጄን አጣጥፌ ለመቀመጥ አያስችለኝም... ህሊናዬም አይፈቅድልኝም! ውስጤ የተደበቀው የኢትዮጵያዊነት ስሜት አይፈቅድልኝም!! በመሆኑም በዝምታ እማ መቀመጥ የለብኝም...!! ይህን ጉዳይ ማጋለጥ ይኖርብኛል!!... ግን እንዴት??... ነገ በሚገባ አስቤ እወስናለሁ... በዚያ ላይ ነገ ይህ መሳይ አስመሳይ የሆነ ሰው ዱካውን እንዳያጠፋብኝ ከስራ ቀርቼም ቢሆን አዲስ የሚገባበትን ቤት በስውር ተከትዬው ማየት አለብኝ... ይህ የመጀመሪያው ተቀዳሚው ስራዬ ነው... እንዲህ በቀላሉ እማ አልፋታውም!!

ከነበርኩበት በመነሳት ለመተኛት ወደ መኝታ ቤት አመራሁ፤ ግን እንቅልፍ ከየት አባቱ ይምጣ?... ድንገት ከፖሊሱ የተቀበልኩት የደሊላ የቀን ውሎ መፃፍያ ትዝ አለኝና ከአልጋዬ ላይ በፍጥነት በመውረድ እና በመሄድ ሳሎን ካስቀመጥኩበትና ጠረጴዛ ላይ በማንሳት ማንበብ ገባሁ፡፡ ዋው የወረቀቱ ውበት ያምራል፤ የእጅ ፅሁፏም ይነበባል፡፡ በአማርኛ ፣ በኢንግሊዝኛ አልፎ አልፎ በእስራኤል ቋንቋ በእብራይስጥ የፃፈቻቸው እጅ

ታዲያ ይህ ፖሊስ እሺ አማርኛ እና እንግሊዝኛውን አነበበው! በእስራኤል ቋንቋ እብራይስጥ የተፃፈውን እንዝብቦት ይሆን? ምናልባት ሚስጢር ይሆናል... ለምን በእብራይስጥ ቋንቋ መጠቀም ፈለገች? እለፍ እለፍ እያልኩ ማንበብ ጀመርኩ:: በእርግጥ ፖሊሱ እንዳለው ደሊላ በብዛት የፃፈቻቸው ስለቀን ስሜቷ፣ የተለያዩ መፅሐፍትን አንብባ ስትጨርስ ስለተሰማት ስሜት... ስለ ህይወት አጠቃላይ ትንታኔ ነው:: እለፍ እለፍ እያልኩ ሳነብ ስለ እኔ የፃፈችውን አገኘሁ::

ቀን ላይ
ሠራ ሮታ
ህዳር 10

ለውዱ ኤ
ከ ዐዐ.ዘ

አይ አንተ ካለ እኔ ምንም አታውቅም:: እኔንና አንተ ቤት ተከራይቼ የገባው የመጀመሪያ ሳምንት ነበር የወደድኩህ... ከዚያ ካቀረብህ ይበልጥ ተመቻህኝ! የሆነ ደግ የሚል ነገር አለህ... ከሰው ልጅ ታዝናለህ፣ ሰብዐዊነት አለህ... ለገንዝ ክብር ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ቤት እንኳ የራስህ ሆኖ ቅንጦት አትሻም:: እንደ ዘመኑ ወንዶች መኪና ገዝተህ ሴቶችን የሚያምርው ሴትህ ወከፍ እያመጣህ አትፈጃቸውም:: ለተከራዮችህ ሙሉ ነፃነት ትሰጣለህ!

ውዱ ኤ

ሳወራህ ከልብ ታዳምጠኛለህ... ብቻ ወድ ጄሃለሁ ግን የእኔ ለማድረግ አልሞከርም

ምክንያቱም እኔ ከመቶኛ ነኝ ፲ በኪዜሳዩ ልጅ መውለድ አልፈልግም ብቻ ካንተ ጋር ከወልድ ደግሞ ይከፋል... በተለይ ዛሬ ካንተ ጋር በመቀፍ እንዳልኩት ደግሞ እኔ መሰከህ!!

————————— !! —————————

ማታ ላይ
ቤት
ህዳር 13

ለውድ K
ከD.D.H

ውድ K... ኖ... ምንድንነው ያከነገህኝ? ካንተ ጋር ከሆን ሙሉ ሰው እሆናለሁ.... ደስተኛ እሆናለሁ... እያፈቀርኩህ ነው..የእኔ እንደማትሆን እኮ አውቃለሁ...ልጅ መውለድ አልፈልግ! እነዚያ የተረገሙ የናዚ ጉራሬ ቀኖች የሆኑ እክራሲሎች አመከኑኝ...ግን እፍቅሎ ያለሁ... የሚገርምህ ዛሬ ከእሩ ከመጣ ሴትዮ ርሲቲያን በመሄድ ማልኩኝ! ለራሴ ቃል ኪዳን ገባሁ። አሀ...ለካ አንተ ካለ እኔ ያልነገርኩህ ነገር አለ፡፡ የእኔ ውድ K እኔ እኮ እንተን ከእምቤሩ ነው እንጂ ከሩ ቦታ እየ-ሜት እሳማለሁ... ሲገርም እኮ እሰማለሁ..ላንተ ካለ ማንዛሬ ለመተው ቃል ኪዳን ገባሁ...

አየህ ምን ያህል እንደምወድህ... ??

---

ቀን ላይ
ከሁሮታ
ታህሳስ 3

ለውድ D.D.H
ከ D.D.H

ዛሬ ከሁሮታ የገጠመኝ ሰውዬ በጣም የሚደንቅ የሰውነት ቅርፅ አለው ፤ ከጀርባው ጣይቱ የሚል ንቅሳት አለው። ነገሩ ካገረመኝ

“ ንቅሳትህ ያምራል የንግስት ጣይቱ አድናቂ ነህ?” አልኩት።

“ ውይ አይደለሁም! ይህን ንቅሳት የአበዴት 2ዜ የተነቀስኩት ነው”

“ ማለት?”

“ እጅግ በጣም የምወዳት ልጅ ነበረች !! ያኔ ትኩስ ፍቅር ውስጥ ሆነን በፍቅር አብዶ ገዳሚ ስንል ስሟን ተነቀስኩት... ሁለታችንም በኋላ ለመቆየት አልቻልንም... እሷ ተለየችኝ። ስሟ ግን ከጀርባዬ ቀረ... ለማስጠፋት ሞክሬ ነበር አልቻልኩም። የሚገርምሽ ሚስቴ

ይህን ታሪክ አታውቅም። ለእቴጌ ጣይቱ የተነ ቀከጡነው የመሰካት እንጂ እውነታውን ብነግርህ ቅናተኛ ከሆንኩ እንግካ ነበር ይልቅ ታነቢያለሽ

« በመጠኑ »

« ታሪክ? »

« እነግለሁ »

« ነክ እቴጌ ጣይቱ ንገሪኝ... »

« ይሄው ታሪክ እንደሚያወሳው እቴጌ ጣይቱ በ 1853 ዓ.ም ጎንደር ላይ ተወለዱት። የጣይቱ ገካገት ሴት የየጁ መሳፍንት ተወላጅ ከትሆን አባቷ ደጃዝማች ብጡል በንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዱል የሆ ነው የዝነኛው ደጃዝማች ውቤ ወንድም ነበር። የምኒልክና የጣይቱ ጋብቻ በእጡ ነ ማቴዎስ ሩሁ ቤ ወንበት 2/1883 ከ መፈፀሙ በፊት ጣይቱ መጀመሪያ የደጃዝማች ወልደ ገብርኤል ሚስት ነበሩ። ከዚያ ደጃዝማች ተክለ ጊዮርጊስን አገቡ... ከዚያ ከ አንድ ሹም ጋር ተጋቡ... እሱ ሲሞት በድጋሚ አንድ ተራ ወታደር አገቡ... ከዚያ ፊታውራሪ ዝቅ አሉንታውን አገቡ... ይህም ሳይሆን በመጨረሻ የሸዋውን ሚኒሊክን አገቡ። ብዙ ወንድ ነው ያተራመሱት። ለነገሩ ብዙ የማያውላት ለንግሥት ብቻ ነጣስ በ1414 ዓ.ም የሞተው

ቀዳማዊ ቴዎድሮስ ኣይሆን ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮ ስም ከቋሚ ሚኒስትሩ ውጪ ሀያ ሶስ ት የሚጠጉ እቁባቶች ነበሩትው... ሚገርም እኮ እን ግደይ በሳል የአመለካከ ቷ ችሎታ በነበራት በማቆቱ ውበት ፈዘው እዲስ አበባ ከተማን ለማቆቱ እስከመቆርቆር ደርሶዋል... »

« የምትገርሚ እስታዋሽ ነሽ እ ያሹ ትየዋለን ሴቶች ከሚስቴ ጋር አላዳንቃችውም ! እንገባ አይደሉም ! እንዳንቺ እንገባ ሚስ ት ብትኖርኝ ዳስ ዩኬኝ ነበር... ከሚስቴ ጋ ሁሌ ከንግብ ጋር ከተናገዝ እንዲተማላን ነው እርዛጣ እንጂ ማንበብ እንጀድም ! ለ እውነት አንባ ሴት ብልህ ናት ማንበብሽን እንዲታቆሚ »

ብዙ ነገር ነው ያወሩነው እ በመጨረሻ ማጎጅ ተጣቅም ሲጨርስ አምስት መቶ ብር ቲፕ ሰጠኝ። እስከዛሬ ትልቅ የተሰጠኝ ቲፕ 250 ብር ነበር። የሰውየው የአውነት ቅርፅ ማን ገዳይነው... ውሉብ ብናደርግ እንዴት ዳ ስ ይለኝ ነበር እርሱማን ለሚስቱ ታማኝ ነው የመጣው እውነተኛ ማጎጅ ለመጠቀ ም እንዲሆን ብቻ አሜወትኝ...።

ማታ ላይ
ሮብ
ታህሳስ 8

ለውድ K
ከD.D.H

ኸ.. ዛሬ ላንተ ካለ ሜት ፯ና ሲጋራ ገቆሞጡ ሁለት ሳምንት አለፈኝ:: አንተን የኔ ማድረግ ባልችልም የኔ K እወድሃለሁ ካንተ ጋር ሳወራ እንዴት ሀሴት ይሰማኛል መሰለህ! ውስጤ ያለውን የእውነት ባልነግርህም ውድድድ... አደርገዋለሁ... እንደውም ፍቅር የሚለው ለፈቀድነው ሰው እንደፈቀድነው ሳይናገሩ መፍቀር ነው... አይደለም K ??

———— :: ————

ቀን ላይ
ሥራ ላይ
ታህሳስ 20

ለውድ K
ከD.D.H

ሴትነት ይሰማኛል:: ካንተ ጋር ስሆን ሙሉነት ይሰማኛል... ብቸኝነት ይሰማኛል ካንተ ጋር ከሌለሁ ዓለም ሁሉ የኔ የሆነች ይመስለኛል... ግን አንተ ሳስብ ነው የምውከው

ህይወትህ ይገርመኛል ክሬ ፣ ከክሬ መልክ ንገብ ..በቃ እንዴት እንደተመቻቹኝ... አንተ ጃንዳ ዘመት ወንዶች ክርብቶን የሆነ ህይወት አትወድም ! ህይወት ማለት እኮ ክርብቶን ነች ፤ ካንተ ጋን ህይወት መንበብናት... ካንተ ህሃወት ሠራናት! ብቻ ከአንተጋር ከሆን የሚሰማኝ በቃኝ የማይገኘን ክፍት ወይፎችን... ምኑ ው የውስጡን ብትረዳልኝ... አሁ.. ለኘ.. ለጅ መውኪፎ አለችለም ይህን ጎበብ ውክሙ ይቀዘቅዛል..

1.

ቀንካይ
ክሬ ሰቷ
ኗር 3

ለOD.H
ከ D.D.H

ጉሬኝ! ጉሬኛነው! እንዴት እንደሚያሳጠከኝ! እንዴት አኅቷነው የሚበጣጠሰው እሱን ብኩ ዴሬሌ! ም ቀኝ ሰው እንዴት ዴሬሌ ይሆናል ቀኑል ጉሬውን ፓሬፓሬን

« ታነሪያለሽ? »

« ለመጠት »

« ኛኝነው የአጓዮችን ሴቶች ማማታም ናቻው

እኔ ብዙ ፕናቶ አፎርጌያለሁ የኢትዮጵያ ሴቶች ንስቲንግ ማንበብን የፈለኩ! ከሞኅኬ ሲቀ የሚሸጡ ፐፑፒ ክ ወዳኝ የሚሸጡ፤ ፀጉር ቤት የሚሠሩ ሴቶች በርካ ለማንበብ የሚሆን ጊዜ አላቸው ግን ንፉኝ ሚንቶካቶ ከካካቸው እና ከሌ ንጉብ ኝቆም ከከማይው ቂ እያነሱም እስቲ እንቼ በቅርቡ ካነበብከው መፅሐፍ ወደኝ ንገሬኝ

« እኛና አብዮቶ »

« ብዙ ተወራለት እንጂ ቀሽም መፅሐፍ ነው ለካ »

« ዶርዩጋዳ »

« ቀሽም ተረትተረት የሆነ መፅሐፍ ነው ለካ፡፡ »

« መጽሔፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ »

« ራሱ የጽሕፈ የማይረባ መፅሐፍ ነው »

« መሬቅ »

« ያውነው እሱም የማይረባ ነው »

« ቆዩ እንተ እንብበህ የተመቸህ የገኘው መፅሐፍነው

« እኔ የወግ ደራሲነኝ ከራሴ መፅሐፍ ሌላ አላደንቅም ምክንያቱም የኢትዮጵያ ደራሲዎች ለእኔ ሚንቅካት አይመጥኑኝም!! ሁለት ምርጥ የወግ መፅሐፍት አሉኝ... »

ብዙ ቀባጠረብኝ፤ በጣም የገረመኝ ደግሞ የእንደኛውን የራሱን የመፅሐፍን ርዕስ ከዶርገው ቂጡ አክባሪ መንቀሉ ነው፡፡ አቆርጥምም ? እንዴት

እንዳናደዱኝ ማን.. የሆነ ብሽቅ ነገር ነው። አሁን ብኮ ዉሬሉ! የብሩኝ ደህን ቀሮ አከተላለብ ፅሁውን ም ቀኛ ሰው ለምታገባ ኢጉዎቶቹዎች... በወሉም ካቀ የሴት ሙብት 100% የሚከበርባት እከሁሉ ቀህ ወንድ ቤሄድ ገዳ ቁሪና ነበር... ለነገ አብዛኛው የኢትዮጵያ ወንዶች ሴት ለጀን እንቁጥ መንጠባጠብ እንዳለባቸው በሚሬሉ አንድወቅም ፤ ትንሹም ትልቁም ወንድ ቂሴቶች የበላይ መሆን ቁሬልጋል ፤ ስለም የሚገርመኝ የሴቶቹም በዚህ በኢትዮጵያ ወንዶች አጉል ፀባቂ ዲስተኛ መሆናቸው ነው ጉድ እኮነው...።

በወሬት የተከፋፈለውን በእምርጃ፤ በኢንግሊዝኛ
በሥሁ ቦታ እና መኖሪያ ቤት ውጭ የዓይነቶውን
የዴሌካን የቀን ውሎ መመዝገቢያ በሚገባ
እንብብኩት... በጣም ብዙ ነው። እካፉ እካፉ
ጂያልኩ ነው ያነበብኩት ዴሊካ ክእኔ የተሻለ
የዴሊሌነት መክሊት እንዳለት ጥምር የተሬ
ዳሁበት እንጣሚነበር ፤ በተከፉ የኢንግሊዝኛ
ቋንቋ አጠቃቀሟ የሚገርም ነው። አለቹ
እለቹ በኢንብሬሽን ቋንቋ የም ትፅፋቸው
ነገሮች የተከየ ትርጉም ይኖራቸው ሳሆን
ክል ሬሴን ጠየኩኝ? ቁህን ለሚከተርጓም
ምን ማድረግ እንዳለብኝ ጎክብ ውዴያው
ክታዲያውም ፀሐት ተርጋሚዎች ትዝ አሉኝ
እናም በፍጥነት ለሚከተርጓም ውሰንኩ...
ምን ደተወቃል ፀፎ ሚከክን የሆነ ፍንጭ
ፀቀብት ቁሆዳል... በእምርጃ በመጨረሻ የዓይነቶው
የሚከተለውን ነበር...

ቀንሳዬ
ሥራ ቦታ
መንበገ28

ለወዳጄ
ከዐ.ዐ.ዘ

ጃጎንጃ ሰሞኑን ምንድን ነው የነካኝ? አሩ መከሩት እስጠለዩኛል... ሁሉ ነገር እስጠልዩ ኛል... ፍርሃት ፍርሃት ፋክኛል... በተከፋ ሁክ ቶን ቀናት መታመታ የማየው ህልም የሆነ አስፈሪ ነገሮች ነው... ሰውነቴ ከመለዐች ተንከፉ ፋን ቀጠቀጣል! ፍሙገቀኛል.. ፍርሃት ፍርሃት ፋሰመኛል አለታመምክም መን የመታመም ከሜት ፋሰመኛል የሆነ ከው ምእትካፋ እየመጣ መታነቂ ደ ገመዶ ያሠየኛል! ወፋትዶ! እንዴ ሰሞኑ የተቋኋታበኝ ጊዜ የከም ብቻ ለሠካው ያዶርመለኝ..

የእኔ ወዳጄ!

እንዴሰሞኑ ከ እንተ ጋር መተኛት ፣ ከንተ ጋር ብዙ ሰዓት መሳከፍ የፈከኩበት ጊዜ የከም.... እቅፍ አድርገህ እብረህኝ ብትተኝ ምናልባት ፍርሃቴ ፋጠፉ ፋሆናል... እንሴት በለዬ ቴ መዋረንቀናት በፍርሃት እሞካኩሁ... መደስት እኮ ነበረብኝ.. ህሌት ለሰመኝ ፀገባ እኮ ነበር

የእኔ ወዳጄ
ወፋ... ምንገበዬ ለገገርህ... አፈቅርሃኩሁ!

የሚል ነበር፡፡ ስለ ደሊላ እያሰብኩ እዛው እንቅልፍ አሸለበኝ፡፡ በዚያው ተኛው፡፡

ወይኔ!! የማልረባ ቀሽም! ደደብ! ከንቱ ሰው ነኝ!! ያ መሳይ አስመሳይ እንደ ህፃን ልጅ ነው የተጫወተብኝ… 1፡20 ደቂቃ ላይ ከመኝታዬ ተነስቼ ለዘበኛው መሳይ ዕቃ ሲያወጣ በፍጥነት እንዲነግሩኝ ገና ስጠጋቸው የእግዜር ሰላምታ ሰጡኝና ቁልፍ እና ብር አስረከቡኝ፡፡

"መቼ ወጣ?"

"ጠዋት 12፡00 ላይ ዕቃውን በመኪና አስጭኖ ሄደ፡፡ እንዳልቀሰቅስህ ብዬ ነው፤ ያው ማታ አውርታቹኋል ብዬ ነው" አሉኝ፡፡… በቃ እንደተጫወተብኝ ወዲያው ገባኝ፡፡ በእርግጠኝነት ከኢንስፔክተሩ ሞት ጀርባ የመሳይ እጅ እንዳለበት አሁን ይበልጥ ገባኝ… እኔንም በቅርቡ ሊገለኝ ይችላል…!!

መስሪያ ቤት ሄድኩ፡፡ የስራ ፍላጎት ባይኖረኝም እንደ ነገሩ ስሰራ ዋልኩና እስራ እንድ ሰዓት ላይ በፍጥነት ከመስሪያ ቤት በመውጣት በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ስታዲየውም አመራሁ፡፡ እንደ አሸን ካሉት የዕህፈት እና የትርጉም ቤቶች በተለምዶ አበበ ቢቂላ በር "ዞ" ቁጥር መግቢያ አጠገብ ካለው ቤት ገባሁ፡፡ ወዲያው አንድ ፀጉሩን ያንጨፈረረ፣ የቦብ ማርሊይን ቲሸርት ያደረገ፣ ቀዳዳዎች የበዙበት እፈርማ ሱሪ ያደረገ፣ ረዘም ያለ፣ ቲምበር ላንድ ጫማ ያደረገ … ብቻ ፍሪክ የመሰለ ወጣት

"እህ ቀዮ ምን ልርዳሽ?" አለኝ፡፡ ያው አዲስ አበባ ላይ አራዳ ነን ባዮች "ወንድን በሴት" ማናገር የተለመደ ሙድ ስለሆነ በፍጥነት ወደ ጉዳዩ ዘው አልኩኝ፡፡

"የእብራይስጥ ቋንቋ የሚችል ሰው አለ?"

"ላንቺ ነው?"

"አዎ"

"ምን ይደረግልሽ?"

"ውጪ ሆነን ማውራት እንችላለን" አልኩት:: ቤቱ ውስጥ ብዙ ሰው ስላለ ጨንቆኝ፤ በዚያ ላይ ቤቱ ውስጥ ንጹህ አየር በበቂ ሁኔታ የለም...

"ጣጣ የለውም" አለኝና ተያይዘን ወጣን:: የምፈልገውን ነገር ነገርኩት:: ዋጋውን ነገረኝ:: ወዲያው ጥሩ ቦታ ግዮን ሆቴል መዋኛው ጋር ንጹህ አየር ስላለ እዚያ ለመሄድ ተስማማን:: ወጣቱ ሲጋራ ሲጋራ ይሸታል:: ቃሚ፣ አጫሽ... እንደሆነ ያስታውቃል::

"እንዴት ቋንቋውን ቻልከው?" አልኩት ::

"ምን ባክሽ እዚህ አገር የኢህአዴግ ደጋፊ ካልሆንሽ በስተቀር ስራ አታገኚም እንጂ እውቀትማ በሽ ነው:: እብራይስጥ፣ ደች፣ አረብኛ ፣ ስዋህሊ፣ ፈረንሳይኛ እና ኢንግሊዝኛን በብቃት አውቃለሁ!! ምን ዋጋ አለው ችሎታው ቢኖረኝም አልተጠቀምኩበትም! እውቀት እያለሽ እውቀትሽን በተግባር ላይ አውለሽ ካልተጠቀምሽበት ዋጋ የለውም! አሁን ግን ደስ የሚለው በቅርቡ የሆነች የደች አሮጊት አስምጬ ከዚች ጣጣ የማያጣት ኮተታም ኢትዮጵያ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እሸበለላለሁ!! ፕሮሰሱ እያለቀልኝ ነው!!"

ከወጣቱ ጋር እያወራን ግዮን መግቢያ ገባን:: ምቹ ቦታ ፈልገን ተቀመጥን:: የሚጠጣ ነገር አዘዝን:: የደሊላን ዳያሪ ጠረጴዛው ላይ በማስቀመጥ ወደ ወጣቱ ገፋ አደረኩት::

"እንዴ ከመጀመራችን በፊት ሲጋራ ሳብሳብ ላድርግ?" አለኝ:: አማራጭ ስለሌለኝ

"እሺ" አልኩት::

"አንቺም ትሞክሪያለሽ? እንዴ?" አለኝ::

"በጭራሽ"

"የሚገርምሽ ሊሲ ገብረማርያም ነበር የምማረው እስራ አንደኛ ክፍል ነው ሴሽ ማጨስ የጀመርኩት ፣ አሁን ሰባት ዓመት ሆነኝ በጣም ጎጂ እንደሆነ አውቃለሁ፣ የሚገርምሽ ይህን ሲጋራ ባላጨስ ኖሮ ደች አልሄድም ነበር" አለኝ ሲጋራዋን ቡን እያደረገ::

"እንዴት?" አልኩት::

"ያቺ ደች የምትወስደኝ አሮጊት ፈረንጅ ፎንቃ ከኔ የጠለፋት በሲጋራ በማሳየው ትርኢት ነው" አለና ሲጋራውን በሀይለኛው ሳበ::

"ማለት?"

"በሲጋራ የፈለከውን ፅሁፍ እፅፋለሁ:: አንዳንዴ እረፍ ቤት ውስጥ ለተወሰኑ ሰዓት

ለዓት ትርኢት አሳያለሁ:: ያቺን የደች አሮጊት በሌ ቢግ ጋርደንን ታውቂዋለሽ? እዚያ ቤት ውስጥ ትርኢት ለጓደኞቼ በሲጋራ ሳሳይ ፎንቃ ገባላት፤ ከዚያ ተመቻቸን:: ቆይ ላንቺም ላስከፈምሽ ስምሽ ማን ነው?"

"ኪኖ"

"አባትህስ?"

"ዮሐንስ"

"ኪኖ አሮምኛ ነው"

"አዎ"

"Ok... ተመልከት..." አለኝና ወዲያው በሚገርም ሁኔታ የሲጋራውን ጭስ አፉ ውስጥ በብዛት ማገና አንገቱን ቀና አድርጎ በአፉ ጭሱን ለቀቅ... ለቀቅ... ለቀቅ... ሲያደርጋቸው ዋው!! ለማመን ነበር ያቃተኝ... በአየሩ ላይ ኪ...ኖ...ዮ...ሐ...ን ... ሲ... የሚል ስም ይነበብ ነበር:: የሚገርም ነው! የማይታመን ብቃት!!

"ዋው ይገርማል!"

"ልክ ነህ! ለማንኛውም በቀጥታ ወደ ስራው እንሂድ" አለና ሲያጨሳት የነበራትን ሲጋራ እግሩ ስር በማድረግ ረገጣት:: ከዚያ የደሊላን የቀን ውሎ በማንሳት መልከት መልከት አደረገው:: እኔ ደሊላ በአብራይስጥ ቋንቋ የፃፈቻቸው ቦታዎች ላይ እጠፍ እጠፍ አድርጌለታለሁ::

"ልጀምር ነው" አለኝ::

"እሺ" አልኩት ::

"የተፃፈውን ዋና መልዕክት ልንገርህ ወይስ እንዳለ መስመር በመስመር የተፃፈውን ላንብብልህ? ላንተ የምትፈልገውን ንገረኝ ለእኔ ሁለቱም ቀላል ናቸው"

"አንብብልኝ"

ቀን 14
ከሌ ሰዓት

ለD.D.H
ከD.D.H

ዛሬ የምሰራበት ማሳጅ ቤት አንድ ወጣት መጣ:: 1000 ሺ ብር ቲፕ ሰጠኝ! የሚገርመው ሰው ሴክስም ሆነ Extra አልተጠቀመም ሌላ ጊዜ እመለሳለሁ ብሎኝ ብቻ ሄደ::

---

ቀን 15
ሠሬ ሰዓት

ለDDH
ከDDH

ከሳምንት በኋላ ያ ሰው ተመልሶ መጣ ዛሬም 1000 ሺ ብር ቲፕ ሰጠኝ:: ዛሬም ሴክስ ይሁን Extra አልተጠቀመም:: ሌላ ጊዜ እመለሳለሁ ብሎኝ ብቻ ሄደ::

---

ቀን 15
ሠሬ ሰዓት

ለD.D.H
ከ.D.DH

ከሳምንት በኋላ ያ ሰው ተመልሶ መጣ::
“ማንነው ስምህ?”
“ዲኪና”

« መሳዩ ቁምነገቻው እንገላለሁ እንዴ ቀላል ይኬ ነበር
ለሰኝ ነገር»

« የምን ነበር?»

« በጣም ብዙ-ብር ታገኝበታለህ ነበረው ቀላለው»

«ምንድነው?»

« የታሸገ ጋዜጣ እሰጥሃለሁ ያንን ጋዜጣ እንደ
ጋር መስጠ ለሚጠይቁሽ መስጠት ብቻ ነው። ለእንዴ
ጋዜጣ 1000 ሺ ብር ቀሰጥሃል ፍቃደኛ ከሆንክ
ዝርዝሩን እናወራለን በዚህ ክልክ ያውቃልኝ»
ብሎኝ ከልክን እና 1000 ሺ-ብሩ እየተቀመለኝ ሄደ።

፡፡

በሁለተኛው ቀን ዕለታዊ ነፃ ከኪነበርጉኝ ከመሳዩ
ጋር የኪሪፕቶ ተገናኘን። ከኪ ነበረው አወራን። እኔን
ፋት እንደሆነ ገለው ቀም አሳመነኝ። የታሸገ ጋዜጣ
የሰጠኝል እኔ ወይዘሮ ቤት መኝተው 5640 የሚደል
ነጭ ሊንወስኝ ጋዜጣውን እሰጣለሁ ፤ እናም ቀደን
ቀላል የመቀበልና የመስጠት ነበር ለመነበራት ዛሬ ቤት
ወጣሁ

፣

የሚገርም ነው ከመሳዩ ጋር ከነበረውን እያሰብሁ
እንዴ ህወት አክሎኝ! እንዴም ቀን ከመሳዩ ጋር ሴትክ
እድርገን እናውቅም!! ከነበሩ ሰዎች ውጪ ለመጨረሻ
ጊዜ ፒፕቶ ከመገናኘት ውጪ ተገናኝተንም እናውቅም
ዛሬ ዶዕም እሲክ ቤት ፍንጫፍ ተበረየን!! ቁው
በቶን የበረየኝን ለዴ ወዲያው ወደዴክት... ከመሳዩ
ጋር እንደ ህወት ቀጥ ነው የምንሆነው መቼም በጉራጌና
ሳበዝነን ለነገሩ በሴት ለእረት ወረት ቤታቸውን ያበረትን
ሰውዬ መቼ ነቀበን...

የሌግሬ ፃክህ! እንደሃገሬ ልንግጨው አንወቅም። እሱ እኔ ወቀንም ደሀን ሆነብኩ ዘማደኛ ቆሀን እንወቅም ወገኑም ያክው ማሳሯ ጀፍለ ውስጥ የሃገሬውን የታሪክ ጋሻ ታ ማሳሪን ተጠቅሞ ሲመሪኩ 5640 የመራል ከሷ ተናገር የወለዱው ቤት ያጠራየን የኪሮ ጋሯኞ ሁሞኝ ነበር። እንዴ! ደጄ የታሪክ ጋሻ ምን ቆሆን?

---

ነገሩ ሲበላሽብኝ ከኩ ነበር ሆነብኝ ውሃ በማከነገጥ ውሃ ውስጥ ወደቀብኝ ለማከት ወስን ኪና ገብታውን ከመጫ በውሃ እከነዘኝ ከሬትኩት በግም በርግታ መቶብሮኛ ነቸው!! የምን ብር ቆሆን?? በማምት አከፒ እ ነቆሆን አቆቀርም ... አምከት ሰማት ካቆ የሆነ ፕቀርከው መጣና ማሳሯ ተጠቅሞ ሲመሪኩ "ዴኪካ" ኪከኝ

"አሉት" እሌኩት።

"5640" አከኝ።

« በግም ቆጆርታ ጠቃት ሷንገት ወደቁ ሮርኝ ውሃ ውስጥ ገብቶ መጫ እገገሩ ውሃ ነገብኝ ማን ለጀፋ እቆከፕም» አለኩት፡

በትኩረት ወረቀቱን ተመከተው።

«ከሃሪ ፕማፒ የከውም ኩካ ጊዜ ማን እንደቆከ መሯክ»

« እእ »

ተገብኩን ተከያየን ። ሰው የው ሲመግ ማን ከከፋ አሷን እየተመለጠተኝ ነበር። እሷማ በማያከሬሁ አሷን እየተመለጠተኝ ነበር።

---

ከአሁድ ቀናት በኋላ ፱ አስጢሪ ኖቂር
ሰው በጅጋወራ መጣ፡፡ በእንካዜን አስጢሪ በቀምቻ
ተመከከተኝ፡፡ ሠሁጃ ተሰርቶ እንጂ ጠራሰ

"ጅሌካ" እኮኝ

" አቢቷ"

" 5640"


" ሰጠሁት"

በቶትሬት እየተመከተኝ

"በቀጅም ሆን ብለሽ ነው እንጂ የምር
ወጅቀሽ ወሂ ወስኝ ፖስታው ገብቶ አቆሜሽ
ም?"

" አረ ወጅቆ ነው"

" ቆሆናል" አኮኝና የሆነ ወረቀት
ሰጠኝ፡፡ ወረቀቱ ላይ ፀሁፍ የለም ከ6ዐ ቢጠጣ
አለ... ግን አልገባኝም... ምን ለማለት ፈልጎ
ቆሆን ?



ቢታ ከዚህ በላይ ያለውን ነገር ለማወቅ አልፈለኩም፤ ለአስተርጓሚው ወጣት ያለኝን ብር ሰጥቼው ተለያየን፡፡ ያ ቀሽም ፖሊስ ምንም መረጃ የለውም ብሎ ዲያሪውን ሰለሰጠኝ አናደደኝ፤ ብዙ መረጃ ነበረው፤ ቢያንስ ለምን በተለየ ቋንቋ ተፃፈ ብሎ እንኳ ራሱን አይጠይቅም?? ለምን ይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣን ላይ መቀመጥ የሌለባቸው ተራ ሰዎች በየመስሪያ ቤቱ ውስጥ የተሰገሰጉት?? እንዴ በዚህ ውሃ ቅዳውሃ መልስ የሆነ ፖለቲካ እኮ አገር ትጎዳለች! ህዝብ ይጎዳል! ኧረ የት ሄደን ነው እሪ የምንለው? ኧረ ኢትዮጵያ ዝምታሽ በዛ!?

አሁን ለማመን ከቶ ቢያስቸግረኝም ከራሴ በላይ አውቀዋለሁ የምለው አብሮ አደግ ጓደኛዬም ራሱ የእነመሳይ ህገወጥ ገንዘብ ስርጭት እና የህፃናት ኩላሊት ንግድ ላይ እጁ እንዳለበት አወኩኝ!!

ይህ ለእኔ መራር እውነት ነው፡፡ በጭራሽ ለማመን የሚያስቸግር እውነታ ነው እውነት? ኢንስፔክተር አወቀ ስለ ራምስ የመኪና ግጭት ታሪክ የነገረኝ የተቀናበረ ነበር ማለት ነው? ራሱስ የእነ መሳይ ባልደረባ ይሆን?... ይህን ጉዳይ በመያዝ የት ነው የማመራው? ለማን ነው አቤት የምለው? እኔንስ እስካሁን እንዴት አልገደሉኝም? ኧረ ጭንቅላቴ በጥያቄ ተወጥሮ ሊፈነዳ ነው... ምንድንነው ማድረግ ያለብኝ?

ወይ ጉድ! ደራሲ እሆናለሁ፤ ገጸባህሪ እፈልጋለሁ... አንድ መጽሐፍ እፅፋለሁ ብዬ እዚህ ሁሉ ጣጣ ውስጥ ልግባ... ?? ኧረ ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ነው...!!

# 14

# እጀ ሙቅ

በቃ የመጣው ይምጣ:: ስለ እውነት ቆሜ እና እውነትን ተናግሬ ብሞት ይሻለኛል:: እኔንም በቅርቡ መግደላቸው አይቀርም:: መሞቴ ካልቀረ ተራ ሞት መሞት አልፈልግም ፤ ቢያንስ እነዚያን ወንጀለኞችን ማጋለጥ አለብኝ:: እነርሱ ድራማ እንደሰሩብኝ እኔም ከእነርሱ የበለጠ ድራማ መስራት አለብኝ፤ በጣም ያልተመለሰልኝ ጥያቄ ያ በጣም የምወደው ጓደኛዬ ራሞስ ስለምን ይሆን በድርሰት ሙድ አሳቦ መሳይ ቁምላቸውን ተከታተለው ያለኝ?? አሁን ገና ከስንት ዓመት ውድ ጓደኛዬ ጋር ያወራነው ትዝ አለኝ::

"... ለመፅሐፍ ገፀባህሪነት አትፈልገውም? አንተ እኮ ደራሲ ለመሆን እየሞከርከ ነው ፤ ይህን ሰው በትኩረት መከታተል አለብህ! እስቲ የት እንደሚያስተምር በዘዴ ጠይቀህ ት/ቤቱ ሄደህ ምን አይነት ሰው እንደሆነ ለማጣራት ጣር! ደራሲ ለመሆን የምትፈልግ ከሆነ መረጃ ለማግኘት ሰላይም መሆን ይኖርብሃል! ደራሲ ተጠራጣሪ መሆን አለበት! ዝም ብለህ ማመን የለብህም፤ ውሸቱን ቢሆንስ አስተማሪ ነኝ የሚለው? እስቲ እዚህ ቤት ውስጥ ያከራየሃቸውን ተከራዮች ሰልላቸው... ምናልባት እኮ በስለላህ ሂደት ለድርሰትህ መነሻ ሀሳብ ልታገኝ ትችል ይሆናል (ገፅ54 ላይ ይመልከቱ)"

ለምን ይሆን ይህን ያለኝ? እርሱ እንደሚያምት አስቀድሞ ስላወቀ እኔ ሲሰሩት የነበረውን ወንጀል እንዳጋልጥ ነው???

ይህን ጉዳይ ሳውጠነጥን አደርኩ:: ከዚያ በጠዋት ለባንክ ቤታችን የህግ አማካሪ በጠዋቱ ደወልኩኝ:: አቶ የማነ ብርሃኔ ይባላል:: እስከማውቀው ድረስ መልካም ሰው ነው:: በጣም በርካታ ሰዎች ሲያመሰግኑት አይቻለሁ፤ ሰምቻለሁም!! በዚያ ላይ ሌላ አማራጭ ስለሌለኝ ለእርሱ ለመንገር ወሰንኩኝ:: በፍጥነት ነው ስልኩን ያነሳው:: በጠዋት ስለደወልኩለት ደንግጦ ሳይሆን አይቀርም:: ከጠዋቱ 1:05 ደቂቃ ነበር::

"ምነው ኬኛ በሰላም ነው?"

"ለአስቸኳይ ጉዳይ ፈልጌህ ነበር፤ ዛሬ መስሪያ ቤት ትመጣለህ?" አልኩት፡፡ (ለባንክ ቤታችን የሚመጣው ሲደወልለት ብቻ እንደሆነ ስለማውቅ፡፡)

"የግል ጉዳይ ነው?"

"ትክክል"

"የት ልምጣልህ? መስሪያ ቤት ወይስ" ሲለኝ እነዚያ የማላውቃቸው ሰዎች የእኔን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ የሚከታተሉ ከሆነ ይህን ምንም የማያውቅ ሰው በእኔ ጦስ የተነሳ እንዳይገደል ስለፈራሁ "መስሪያ ቤት" አልኩት፡፡

"እመጣለሁ"

መሞቴ አይቀርም፤ ግን በክብር መሞት አለብኝ፡፡ ሠርግ ሲኖርብኝ ብቻ የማደርገውን እጅግ ውድ ሱፍ አደረኩ፡፡ ታላቅ ወንድሜ ከአሜሪካ ያመጣልኝን እጅግ ዘመናዊ መነፅር አደረኩ፡፡ ይሽ መነፅር "መነፅር" ብቻ አይደለችም፡፡ ወንድሜ እንደነገረኝ ከአሜሪካ በውድ ይግዛት እንጂ የተሰራችው እስራኤል ነው፡፡ ለስምንት ሰዓት ለዚያውም ኩልል አድርጎ የሚያሰማ እጅግ ዘመናዊ እና ረቂቅ የድምፅ መቅጃ መሳሪያም አላት፤ እናም ይቺን የዘመኑን የቴክኖሎጂ ውጤት ዛሬ ልጠቀምባት ወሰንኩኝ፡፡

መስሪያ ቤት ከወትሮው በተለየ ዝንጥ ስላልኩኝ ሁሉም ሰላምታ አበዛብኝ፡፡ በተለይ አዲስ ለልምምድ የመጣችው ተመራቂ አካውንታንት ሰላማዊት ቢታሉ በፍቅር አይን ተመለከተችኝ… የዓይን ፍቅር ቢጤ ሳይዛት አይቀርም፡፡ ግና ሲታየኝ የምትገባበት ነው የሚጠፋት… አሁን ስለፍቅር የማስብበት ሴኮንድ እንኳ የለኝም… አሁን እኔ ከሞት ጋር ግብግብ ላይ ነኝ… አሁን እኔ ሳልሞት ታሪክ ለመስራት እየጣርኩ ነኝ…

እንደ ነገሩ ስራዬን እየሰራሁ ልክ አራት ሰዓት የሻይ ሰዓት ላይ አቶ የማነ ብርሃኔ መጣ፡፡ ሻይ ቡና የምንጠጣበት ቤት በማንምራት እስፈላጊ ነው የምለውን ሁሉ ነገርኩት፡፡ ከልቡ ሲያዳምጠኝ ቆየ፡፡ ስጨርስ

"በጣም የተወሳሰበና አደገኛ ይመስላል፤ ከወንጀሉ ጀርባ ማንነቱ ያልታወቀ ከፍተኛ

ባለስልጣን እጁ ካለበት በጣም የተጠላለፈ ነው፤ ስለዚህ የተሻለው አማራጭ ይህን ጉዳይ በመያዝ ኢ . ብ . ደ ጋር ማምራት ይሆናል ፤ በእርግጠኝነት እነርሱ እንደዚህ አይነት ወንጀል ውስጥ እጃቸው ስለማይነካካ ለችግሩ መፍትሔ ይሰጡሃል የሚል ግምት አለኝ"

"ኢ.ብ.ደ ማለት?"

"የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት:: ሶስት ዓይነት ናቸው፤ ለመንግስት ብቻ ካድሬ ሆነው የሚሠሩ አሉ፤ ለኢትዮጵያ አገራቸው እና ስለ እውነት ብቻ የሚሠሩ አሉ፤ ለሀገርም ለመንግስትም የሚሠሩ አሉ፤ ቢሆንም ይህ ወንጀል ከፖለቲካ ጋር ንኪኪ ስለሌለው ማናቸውም ይረዱሃል፤ ለዚህ ደግሞ እኔ አንድ ለሀቅ ዘብ የሚቆም ደህንነት አውቃለሁ፤ የታላቅ እህቴ ባለቤት ነው" ገና ከማለቱ

"ታዲያ ለምን ደውለህ አታገናኘኝም" አልኩት::

"ይቻላል" አለና ወዲያው ሞባይሉን በማውጣት ደወለ:: ተነሳ::

"አጉፊን 0911060..." አለና የእኔን ስልክ በመንገር ተዘጋ:: ቀና ብሎ ተመለከተኝ::

"ከእንደዚህ አይነት ሰዎች ጋር በኮድ ነው ማውራት ያለብህ:: " አጉፊን" ማለት ለአስቸኳይ ጉዳይ ፈልጌህ ነበር ማለት ነው:: ትንሽ እንጠብቀው በእርግጠኝነት ምላሽ ይሰጥሃል"

"በጣም ነው የማመሠግነው"

"የሀገር ጉዳይ እኮ ነው! የሀሰት ብር ማሰራጨት እኮ ትልቅ ወንጀል ነው:: የህፃናትን ኩላሊት መሸጥ እኮ ትልቅ ወንጀል ነው:: እኔ የ14 ዓመት ሴት ልጅ አለችኝ፤ ይህ ወንጀል በእኔ ላይ አልደረሰም ማለት እኮ አይደለም ፤ ሌሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ልጆች እኮ የእኔም ልጆች ናቸው:: ቀጣይቷ ኢትዮጵያን እኮ የሚረከቧት እነርሱ ናቸው፤ እኔም በምችለው ሁሉ አንተን ለመርዳት በእርግጠኝነት ከአንተ አጠገብ ነኝ! አንተ በፊት እንደነገርከኝ አሜሪካ እኮ ወደ አምስት ጊዜ ወንድምህ ጋር ሄደሃል:: አሁንም ከፈለክ እኮ በሀያ አራት ሰዓት ውስጥ እኔ ምን አገባኝ ብለህ ይቺን ሀገር እኮ ጥለህ መውጣት ትችላለህ፤ ግን ሀላፊነት ስለተሰማህ እኮ ነው እዚህ ጣጣ ውስጥ በመግባት እስከ መጨረሻ ከሞት ጋር ግብግብ ገጥመህ ለመዋጋት የፈለከው!! በእውነት እኮራብሃለሁ! እኔም ከአንተ አጠገብ ነኝ" ብሎልከ ሲጨርስ እኔ ስልክ ላይ አጭር የፅሁፍ መልዕክት ገባ:: ወዲያው አውጥቼ አየሁት::

"ራገቡ3ሆዐ" የሚል ነበር:: አቶ የማነ ብርሃኔ ተቀበሉኝና "ጥሩ ዛሬ ልክ 7:30 ደቂቃ ላይ ካሳንቺስ ራዲሰን ብሉ ሆቴል ውስጥ ይጠብቅሃል" አሉኝና ከኋላ ኪሱ ውስጥ ዋሌት አውጥቶ ፎቶ ግራፍ አሳየኝ:: እጅግ በጣም ተጫዋች የሆነ ጢማም ሰው ነው...

"ታዲያ ይህ ሰው እንዲረዳህ መረጃ እጅግ በጣም ወሳኝ ነገር ስለሆነ አለኝ የምትለውን መረጃ ሁሉ ስጠው፤ ትንሽ መረጃ ከሰጠኸው እርሱ እና ባልደረቦቹ አነፍንፈው ይደርሱበታል"

ተጨማሪ ምክሮች ለገሰኝና ተለያየን:: አቶ የማነ እንደወጣ ያው ከመስሪያ ቤት ለወጉ ያህል አሊታዬን አስፈቅጄ ወጣሁኝ:: ምንም እንኳ ታታሪ ሰራተኛ ብሆንም ሰሞኑን ብዙ ቀናት ሥራ ላይ እየተገኘሁ ስላልሆነ መቼም በቅርቡ ያባሩኛል:: ችግር የለውም በህይወት ከቆየው ሌላ ባንክ ቤት ተቀጥሬ እሰራለሁ:: በቂ እውቀት ሆነ ችሎታ አለኝና... ካልገደሉኝ ማለቴ ነው!! ወዲያው በፍጥነት ኮንትራት ታክሲ በመያዝ ቤት እምርቼ የደሊላን ዲያሪ መፃፊያ ያዝኩ... በቃ ታሪክ መስራት ስላለብኝ ለመረጃ የሚሆን ነገር ለመሰብሰብ በኮንትራት ታክሲ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አመራሁ::

በኢንስፔክተር አወቀ ቦታ የተተካውን ሰው ጠይቄ አገኘሁት:: እንድቀመጥ ነገረኝ:: ተቀመጥኩ:: መነፅሬን አውልቄ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩት::

"ነፍሱን ይማረውና ኢንስፔክተር አወቀ ከመሞቱ በፊት አንድ መረጃ ሰጥቼው ነበር "በማለት ጀመርኩ::

"የምን መረጃ?"

"ስለ አንድ ተጠርጣሪ"

"ማን የሚባል?"

"መሳይ ቁምላቸው"

ገና ከማለቴ መርማሪው በፈገግታ ተሞልቶ ቀና ብሎ ተመለከተኝ...

"ስም በማጥፋት ወንጀል ልትከሰስ እንደምትችል ታውቃለህ?"

"አልገባኝም?"

"መረጃውን አይቼዋለሁ ስለተጠርጣሪው የቀረበው ነገር ውሸት ነው፤ በዚያ ላይ አንተ ጋር ተከራይቶ የነበረው መሳይ ቁምላቸው አገር ውስጥ አሁን የለም ዛሬ አራት ሰዓት ላይ በህጋዊ መንገድ ካርቱም ሄዷል:: እና አንድ የወዳጅነት ምክር ልምከርህ!?"

በገዘምታ እየሁት::

"እርፈህ ስራህን ብትሰራ ይሻልሃል! ገዘም ብለህ ጭራህን አትቁላ! ምንም ሳታመነ ዘራፍ! ዘራፍ! አትበል! የራስህን ህይወት ገዘም ብለህ ኑር!!"

"ቢቃ?"

"አይበቃኝም የምትል ከሆነ..." አለና የሰላት ግት ግቀብኝ:: ከንቷ እንደተመታች እርግብ መስዬ መነፅሬን በመያዝ በፀጥታ ከቢሮው ወጣሁ:: ቆሞ ሲጠብቀኝ የነበረው ኮንትራት ታክሲ ውስጥ በፍጥነት በመግባት የደሊላን ጉዳይ የያዘው ፖሊስ ጋር በቀጥታ አመራሁ:: ምናልባት ይቺ ቀን የመጨረሻዬ ልትሆን ትችላለች! እናም ማድረግ የምችለውን በፍጥነት ማድረግ አለብኝ፤ ስለ ዲያሪው ልነግረው ይገባኛል፤ ፖሊስ ጣቢያው ጋር ደርሼ ተፈትሼ ገባሁ:: የመርማሪውን ቢሮ አንኳኩቼ ግቡ ሲባል ገባሁ፤ ሌላ ሰው ነው የተቀመጠው:: የሆነች ወፍራም ሴትዮ... ወዲያው

"አቤት ምን ልርዳህ" አለችኝ

"መርማሪውን ፈልጌ ነበር"

"እ ዛሬ ጠዋት ወደ ቤንሻንጉል ተቀይሮ ሄደ እኮ"

"ተቀይሮ?"

"አዎ"

"አይመለስም ማለት ነው?"

"መሆኑ ነው"

"ከእርሱ ጋር ጉዳይ ነበረኝ"

"ምንን በተመለከተ"

"ማሳጅ ቤት ውስጥ ስለሞተች ደሊላ የምትባል ልጅ"

ከእግር እስከ ራሴ ቃኘችኝ:: ከዚያ በአይኗ ወንበር የተቀመጠበትን እያሳየችኝ እንድቀመጥ አዘዘችኝ:: ተቀመጥኩኝ::

"ማን ነህ አንተ?"

"ኬኖ ዮሐንስ"

"ማለቴ ምኗ ነህ?"

"ቤት አከራይ"

"እና አንተ ምን ቤት ነህ ጭራህን የምትቆላው? ያልበላህን ለምን ታካለህ? ለማንኛውም የእርሷ ጉዳይ እኮ ፋይሉ ተዘግቶ መዝገብ ቤት ገብቷል! በተደረሰበት የምርመራ ውጤት ከፍተኛ የደም ግፊት ነበረባት በዚያ የተነሳ ሞታለች:: አለቀ::"

በጣም ስለተናደድኩ የመጣው ይምጣ አልኩና መነፅሩን ይበልጥ ወደ ጠረጴዛው መሀከል በማስጠጋት "አይደለም! ውሸት ነው! አንቺ ቢያንስ ሴት ነሽ! ስለ ሴት ልጅ ሞት ልትራሪ ይገባል! የሚስኪን ህጻናት ኩላሊት ሲሸጥ እንደ ሴትም እንደ እናትም ልትራሪ ይገባል! ሀገ ወጥ ገንዘብ ምንዛሪ እየተከናወነ ህዝቡ ሲታመስ ልትቆረቆሪ ይገባል! ደሊላ የሞተችው በተቀነባበረ ወንጀል ነው..." ንግግሬን ሳልጨርስ

"በቃ" አለችኝ::

"በቃ?" አልኳት ተገርሜ::

"የግል ኑሮህን ለምን አትኖርም! ለምን ያልበላህን ታካለህ? አንድ የሀገራችንን ምሳሊያዊ አነጋገር ልንገርህ" አለችኝ:: በዝምታ እና በትዝብት እየዋት::

"አይጥ ሞት ሲያምራት የድመትን አፍንጫ ታሸታለች!! ሲባል አልሰማህም?"

"አለቀ" አልኳት::

ምንም ሳትናገር ድፍርስ ባለውና ሰማይ በሚያከለው አይኗ ጠቀሰችኝ:: እኔም ምንም ሳልናገር መነፅሬን በመያዝ ኩምሽሽ ብዬ ወጣሁ::

▪
▪
▪
▪
▼

ሰዓቱ ገና ነው:: ኮንትራት የያዝኩትን ታክሲ ሂሳብ ከጠየቀኝ በላይ ሰጥቼው ተለየሁት:: አ! በጣም የሚያምረው ራዲሰን ብሉ ሆቴል በመግባት የተቀጠርኩበት ሰዓት እስከሚደርስ Wifi በመጎርጎር ራሴን ነፃ ለማድረግ ጥረት ማድረግ ያዝኩኝ:: አይታወቅም ከደቂቃዎች በኋላ ልሞት እችላለሁ:: ከሞት ጋር ቁማር እየተጫወትኩ ነው፤ ግን አልፈራሁም:: ምናልባት ዛሬ ማታ ከሞትኩኝ በድጋሚ ምሳ ላልበላ ስለምችል እጅግ ውድ የሆነውን ምግብ በማዘዝ ግጥም አድርጌ ተመገብኩ:: Wifi ስጎረጉር ሳይታሰበኝ ከሶት 7:30 ደቂቃ ሆነ:: ልክ ባለው ሰዓት በፎቶ ላይ ያየሁት ቀጭን ረጅም ሰው ግርማ ሞገስ ባለው አረማመድ መጣ:: ገብቶ ጥግ ወንበር ላይ ተቀመጠ:: በፍጥነት በመሄድ እጄን ዘረጋሁለት::

"ኬኛ ዮሐንስ"

"በርቶሚዮስ"

ምንም ጣጣ ሳላበዝ እና ዙሪያ ጥምጥም ሳልዞር ያለውን ነገር ሁሉ ዘረገፍኩለት:: የቃን ውሎ መዛፊያውን እና መነፅሩን ሰጠሁት:: በርቶሚዮስ ምንም ሳይናገር እንድከተለው ነገረኝ:: የተመገብኩበትን አስቀድሜ ከፍዬ ስለ ነበር በፀጥታ ተከተልኩት:: ከሆቴሉ በስተጀርባ ቆማ የነበረች ቪ8 መኪና ውስጥ ገባሁኝ:: ከኋላ ወንበር ለብቻዬ አስቀመጡኝ:: ከዚያ መሀከል ላይ ያለው መስታወት ተነሳና ተዘጋ:: ወደ ውጪ ለማየት ጥረት አደረኩ፤ ምንም የሚታይ ነገር የለም፤ ሹፌሩን እና በርቶሚዮስን ለማየት ጥረት አደረኩ እነሱም በተሸፈነው ጥቁር መስታወት የተነሳ አይታዩኝም:: የት እየወሰዱኝ ይሆን??

ከአንድ ሰዓት ጉዞ በኋላ መኪናዋ ቆመች:: በሩ ግን አልተከፈተልኝም በዝምታ ተቀመጥኩኝ:: አንድ ሰዓት ሞላኝ:: በድጋሚ መኪናዋ ጉዞ ጀመረች:: ከተመሳሳይ አንድ ሰዓት ተጨማሪ ጉዞ በኋላ መኪናዋ ቆመች:: ከዚያ ድንገት በመሀከል የነበረው ጥቁር መስታወት ዝቅ አለ:: በርቶሚዮስ በትኩረት እየተመለከተኝ

"እዚሀ ጋር መውረድ ትችላለህ፤ ከዚህች ደቂቃ ጀምሮ ስለ ደህንነትህ እንዳትጨነቅ አንተን በስውር የሚከታተሉ ከበቂ በላይ የደህንነት አባላት ተመድበዋል:: ለተጨማሪ መረጃ ስትፈልግ እጠራሃለሁ! ስለመረጃው እና ለሀገር ተቆርቋሪነትህ እናመሠግናለን::" አለኝ::

በፍጥነት ወረድኩኝ:: በመጠኑ ውስጤ እርጋታ ተሰማኝ::

እንዴት እንደሆን አላውቅም ከሰንት ቀናት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥሩ እንቅልፍ ወሰደኝ:: ጠዋት ተነስቼ ወደ መስሪያ ቤት አመራሁ:: በተረጋጋ መንፈስ ስራዬን ሰሰራ ዋልኩኝ::

ትንሽ አዕምሮዬን ዘና ለማድረግ እና ውስጤ ያለውን ውጥረት ለመቀነስ ቢሔራዊ ትያትር በማምራት ተውኔት ቢጤ አይቼ ቤት ተመለስኩኝ:: ለማንበብ ጥረት አደረኩ ግን ሀሳቤን ለመሰብሰብ በጭራሽ አልቻልኩምና ተውኩት:: ቀጥሎ ማንበብ ባይሆንልኝ ለመፃፍ

ሸርብትን በማለት የመጀርኩትን የመጀመሪያ ድርሰቴን ትንሽ ገልፅ እንኳ ለመፃፍ አነሳሁት:: ለመፅሐፌ "ሸርብትን" የሚለውን ርዕስ የሰጠሁት "ሸርብትን" የሚለውን ሀሳብ ሰፋ አድርጌ ለማየት ነው:: በብዛት "ሸርብትን" የሚለው ቃል የሚያገለግለው ለመዝናናት ነው:: "እስቲ ዛሬ ሸርብትን እንበል" ይላሉ ወጣቶች:: እኔ ደግሞ ለወጣቶች እላቹኋላሁ... ኢትዮጵያ በእውቀት ሸርብትን ያሉ ወጣቶችን ትሻለች! ኢትዮጵያ በእውነተኛ ዲሞክራሲ ሸርብትን ማለት ትሻለች! ኢትዮጵያ ከአጉል ጠባብነት፣ ዘረኝነት፣ ኋላቀር አስተሳሰብ ወጥታ በአንድነት ሸርብትን ማለት ትሻለች! ኢትዮጵያ በስልጣኔ ሸርብትን ማለት ትሻለች! እስቲ የኢትዮጵያ ልጆች በአንድነት፣ በፍቅር ፣ በሠላም ፣ በፍትህ፣ ሸርብትን እንበል! እስቲ ከዘመን ጋር አብረን ዘምነን ሸርብትን እንበል! እስቲ ሁላችንም በኢትዮጵዊነት ስሜት ሸርብትን እንበል! እስቲ ያ ገጣሚ እንዳለው የመንፈስ ድውዮች ባለመሆን ሸርብትን እንበል! እስቲ የንዋይ ምርኮኛች ባለመሆን ሸርብትን እንበል! እስቲ የሆድ አምላኪዎች ባለመሆን ሸርብትን እንበል! እስቲ ከዘረኝነት ወጥተን በኢትዮጵያዊነት ስሜት ሸርብትን እንበል! እስቲ በፍቅር እየተሳሰብን በአብሮነት መራመድ ሸርብትን እንበል! እስቲ ከአማራ ነህ፣ ትግሬ ነህ! ኦሮሞ ነህ፣ ሀድያ ነህ... አስተሳሰብ ወጥተን በኢትዮጵያዊነት ስሜት! በሰው ልጅነት ስሜት! ሁላችንም የእግዚአብሔር ድንቅ ፍጡርነን ስሜት ሸርብትን እንበል! እስቲ ካለማወቅ በማውቅ ሸርብትን እንበል! እስቲ ባለፈ ታሪካችን ከመንታረክ፣ ካለፈ ታሪካችን በመማር ሸርብትን እንበል!

ጥላቻን ከመስበክ ፍቅርን በመስበክ ሸርብትን እንበል! በቋንቋ ልዩነት ከመባላት ቋንቋ መግባቢያ ብቻ መሆኑን አውቀን ሸርብትን እንበል! የማንነታችን መሠረት ሰብዓዊነት ላይ ብቻ መሠረት አድርገን ህይወትን ሸርብትን እንበል! በተለይ ስለ ራሳችን ሆነ ስለዓለም ፣ ስለ ህይወት፣ ስለ አመለካከታችን ጤነኛነት በመጠንቀቅ ሸርብትን እንበል! አስተሳሰባችንን በአምንታዊና በቀናነት ላይ የተመሠረተ በማድረግ ሸርብትን እንበል! የራሳችንን ግላዊ ስሜት እና ፍላጎት ብቻ ለማሳካት በራስ ወዳድነት ስሜት ከመታጠር ወጥተን ሸርብትን እንበል! ከምንም በላይ የተሳሳተ ዓመለካከት ካለን ያን እይታችንን በመቀየር ሸርብትን እንበል!

ይህ ለመጨረሻ ጊዜ የፃፍኩት አንቀፅ ነው:: ተጨማሪ ለመፃፍ ባውጠነጥን ሀሳብ ሊመጣልኝ ስላልቻለ ለተወሰነ ደቂቃዎች የBBC ዜና ስከታተል ቆየሁና ተኛሁ፤ ጠዋት ተነስቼ፣ ቁርሴን በልቼ ከቤት ልወጣ ስል ዘበኛዬ መጥተው ጠሩኝ::

"አቤት ጋሼ" አልኳቸው፡፡

"በር ላይ ሰዎች ቆመዋል"

"ማን ናቸው?"

"አላውቃቸውም"

በፍጥነት ወጣሁኝ፡፡ ሲቪል ልብስ የለበሱ ቢሆንም የፖሊስ ሠላምታ አቀረቡልኝ፡፡ ሁለት ናቸው፡፡ ከበራችን ፊት ለፊት የፖሊስ መኪና ቆማለች፡፡ በቀኝ ያለው መታወቂያ አሳየኝ፡፡ የመጥሪያ ወረቀት እና ባለበት ቦታ በፍጥነት ተይዞ ይምጣ የሚል ወረቀት አሳየኝ፡፡

"አንድ ጊዜ መልዕክት ተናግሬ መምጣት እችላለሁ"

"ይቻላል! ለማምለጥ ሙከራ ለማድረግ ግን በጭራሽ እንዳታስብ!!"

"በጭራሽ!! አብረኸኝ መግባት ትችላለህ" አልኩት፡፡ ለምን እንደሆነ አላውቅም አልተከተለኝም፡፡ የሆነ ፎቅ ላይ ተቀምጠው በስናይፐር እየተከታተሉኝ ይሆናል፤ ለማንኛውም በፍጥነት ዘበኛዬ ጋር አመራሁ፡፡

"ጋሼ ዛሬ ማታ እና ነገ ማታ ቤት የማልመለስ ከሆነ ለወንድሜ ደውለው ይንገሩት! ስልኩ አለዎት አይደለም?" ዘበኛዬ በድንጋጤ አንገታቸውን ነቅ አደረጉ፡፡ ምናልባት ላልመለስ ስለምችል እቅፍ አድርጌ ግንባራቸውን ሳምኳቸው፡፡ ለእኔ የአባቴ ያህል ናቸው፡፡ ከዚያ በታዘዝኩት መሠረት በፍጥነት ወጥቼ የፖሊስ መኪናዋ ውስጥ ገባሁ፡፡

ከፖሊሶቹ ጋር ምንም ቃል ሳንነጋገር መኪናዋ በፍጥነት እየበረረች ማዕከላዊ ተብሎ የሚጠራው እስር ቤት ስትደርስ ቆመች፡፡ ሁለቱ የሲቪል ልብስ የለበሱ ፖሊሶች ከመኪናዋ አስወርደውኝ እያጣደፉ መሩኝ፡፡ አንድ ብቸኛ ክፍል ውስጥ ወረወሩኝ፡፡

ከአንድ ሰዓት ተኩል ገደማ ቆይታ በኋላ ሁለት ሲኖትራክ ሲኖትራክ መኪና የሚያክሉ መርማሪዎች መጡ፡፡ ሌላ ወንበር ያለበት ክፍል ውስጥ ወስደው አስቀመጡኝ፡፡ ሁለቱም ከእኔ ፊት ለፊት ወንበር ላይ ተቀመጡ፡፡ በስተቀኝ ያለው መርማሪ

"ለምጠይቅህ ጥያቄዎች እውነት የምትለውን ብቻ ትናገራለህ"

"እሺ"

"ከሟች ደሊላ ዶ/ር ሐይለመስቀል ጋር የነበራችሁ ግንኙነት ምን ነበር?"

ያለውን ነገር ሁሉ ምንም ሳልደብቅ ነገርኳቸው:: እኔ የምናገረውን በግራ በኩል ያለው በሚገርም ፍጥነት ይቸከችካል...

"ይህን ወጣት ታውቀዋለህ?" አለኝና ፎቶ አሳየኝ:: አዲስ አልሆነብኝም የሆነ ቦታ የማውቀው መሰለኝ

"የሆነ ቦታ የማውቀው ይመስለኛል"

"የት?"

"እርግጠኛ አይደለሁም ባንክ ቤት ስለምሰራ ምናልባት ደንበኛችን ይሆናል"

"እሺ ይህን ፎቶስ?" አለና ያንኑ ወጣት ከሆነ ታክሲ ጋር ቆሞ የተነሳውን አሳየኝ:: ወዲያው አስታወስኩት

"እ! አስታወስኩት"

"የት?"

"የታክሲ አገልግሎት ሰጥቶኛል"

"ሌላስ?"

"እህ..." አልኩና መዋሸት ስለሌለብኝ እውነቱን ተናገርኩ::

"ቢቃ??"

"በቃ!!"

"ለዚህ ወጣት ደሊላ ፍቅረኛዬ ነች አላልከውም?"

"ብያለሁ"

"ከዚያ ይህ ወጣት ፍቅረኛህን በረቀቀ መንገድ እንዲገላት 80,000 ሺ ብር ከፈልከው ፣ ይህ ወጣት ደግሞ ደሊላን ገደላት፤ አንተ ብልጥ ሆነህ ወንጀሉን ለማስቀየስ ዙሪያ ገጠምም ትዞራለህ?"

"በጭራሽ!!"

መርማሪው ሣቀና በአይኑ ቂጥ እየመነጠረኝ አጠገቡ የነበረውን ቦርሣ ከፈተና በስስ ኮዳ ፌስታል ውስጥ የተቀመጠ መሣሪያ አወጣና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ::

"ሽጉጥ አለህ" አለኝ::

"ኧረ የለኝም"

"ሽጉጥ በእጅህ ይዘህ አታውቅም ?"

"አላውቅም" ስለው በድጋሚ ሣቀና ይህ የምታየው መሳሪያ ላይ የአንተ እጅ አሻራ እንዳለበት ተረጋግጧል"

"የዚያን ቀን በአጋጣሚ የልጁ. ታክሲ ውስጥ ስጎረጉር ነኩቼው ነበር"

"ኧረ ባክህ?" አለ መርማሪው በስላቅ አነጋገር፡፡

"ደሊላን በመርዝማ ጨርቅ አፍኖ የገደላት ይህ ወጣት ነው! ወንጀሉን ከፈፀመ ከሶስት ቀናት በኋላ ግንባሩ ላይ ሁለት ጊዜ ተመቶ የሞተው በዚህ ሽጉጥ ነው! ሽጉጡ ላይ ያለው አሻራ ደግሞ የአንተ እጅ ነው"

"በእጅ መንካቴን አልክድም፤ ከዚህ ውጪ የማውቀው ነገር የለም"

ተጨማሪ ጥያቄዎችን ሳልጠየቅ ቅድም የነበርኩበት ብቸኛ ከፍል መልሰው ወረወሩኝ፤ ገና መኪና ውስጥ ከቤት ወጥቼ ስገባ ነበር የእጅ ሰልኬን የተቀበሉኝ፤ እናም ለማንም መደወል አልችልም፡፡ የነገሮች መገጣጠም በጣም ገረመኝ፡፡ ያ ሚስኪን የምለው እና እውነተኛ ጓደኛዬ የምለው ራምስ እንደ ህፃን ልጅ "ደራሲ ሰላይ ነው ብሎ" እንደተጫወተብኝ አሁን ገና ገባኝ፤ ቢሆንም ከራሴ ጋር ተወያይቼ የገባሁበት ጉዳይ ስለሆነ የሚመጣውን በፀጋ ከመቀበል ውጪ ምን አማራጭ አለኝ... ምንም!! ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ ይባልስ የለ? ... እውነት ነው፡፡

pdf by @shuktus_books

# 15

## 777,600 ሴኮንዶች!!

በጠባቧ ክፍል ውስጥ ብቻዬን ተቀምጬ ብዙ ነገር አስታወስኩኝ:: ስለ ቃሊት እስር ቤት ፣ ስለ ቂሊንጦ እስር ቤት፣ ስለ ደዴሣ እስር ቤት፣ ስለ ሸዋሮቢት እስር ቤት... ስለ ቀደምቱ ግሸን አምባ እስር ቤት... ብቻ እጅግ በርካታ ያነበብኳቸው የእስር ቤት መፅሐፍት አንቃጨሉብኝ... የህንዳዊው ኦሾ "አለም ሰፊ ስለምትመስለን ነው እንጂ እያንዳንዳችን እስር ቤት ውስጥ ነን! አለም ሰፊ እስር ቤት ናት" የሚለው ንግግሩ አንቃጨለብኝ... የዶ/ር ኤሪካ ዋርነር ስለ እስር ቤት የሚያወራ ጣፋጭ ታሪክ ትዝ አለኝ... ስለ እስር ቤት የተሰሩ ፊልሞች ትዝ አሉኝ...

"ማንኛውም በዓለም ያለ ሰው ባልታሰበ አጋጣሚ በህይወት ዘመኑ እስር ቤት መግባቱ ስለማይቀር ውስጡን ማጀገን አለበት" የሚለው የዝነኛው ዳንቴ ንግግር አንቃጨለብኝ... እናም የመጣውን ለመቻል ጥረት ማድረግ እንዳለብኝ ለውሰጤ ሹክቴስ አልኩት:: አሳመንኩት::

ሶስት በቃላት ሊገለፁ የማይችሉ አስቀያሚ ቀናት አለፉ:: በትንሿ ክፍል ውስጥ ብቻዬን ተቀምጫለሁ:: ምግብ ለማለት የሚያስደፍር "ምግብ" ቁርስ፣ ምሳ እና እራት ላይ ሳይቋረጥ ይመጣልኛል:: ዛፍ የሚያክል ጥቁር የሚያስፈራ ፖሊስ አንገቴን እንደ ዶሮ በመያዝ ሽንት ቤት ይወስደኝና ይመልሰኛል... ሽንት ቤት ፣ ምግብ መብላት ፣ በቁዘማ ትንሿ ክፍል ውስጥ መቀመጥ... በቃ እነዚህ ናቸው:: አንዳችም ሰው አላናገረኝም... ቢያንስ በቁጥጥር ስር በዋልኩ 24 ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት ወይም ዳኛ ጋር መቅረብ እንዳለብኝ ስለ ወንጀል

የሚያወራ መፅሐፍ ሳነብ ተረድቻለሁ... ግን ማንም መጥቶ ያናገረኝ የለም..!!

የዋቃ ያለህ!! በትንሽ ከፍል ውስጥ የሚያዋራ፣ የሚነበብ፣ የሚታይ... አንዳችም ነገር በሌለበት ሁኔታ መቀመጥ እንዴት ይሰለቻል!? እንዴት ይከብዳል!? እንዴት የሚያስፈራ ነገር ነው!? ... ምናለ እንዳወራ እንኳ ከሌሎች እስረኞች ጋር ቢቀላቅሉኝ.. ቢያንስ እንዴት እንደ ታሠሩ እየነገሩኝ... ስለ ህይወት እየተበረጨቱኝ... ጊዜው ያልፍ ነበር፡፡

"ጀግና" የሚለውን ቃል ለራሴ መጠቀም ባልፈልግም እስር ቤት እነሆ ከገባሁ! እዚያች ትንሿ ከፍል ውስጥ ብቻዬን እየቆዘምኩ መዋል ከጀመርኩ 777.600 ሴኮንዶች ሆነኝ፡፡ ዘጠኝ ቀናት ማለት ነው፡፡ እናም ሳይደብረኝ! በጭንቀት ራሴን ሳልወጥረው ... ስለ ህይወት ... ስለ አለም ሁኔታ... ስለምፅፈው ሽርብትን የተሰኘ ድርሰቴ እያውጠነጠንኩ አሳለፍኩኝ.. ራሴን እየፈተሽኩ አሳለፍኩኝ... ምሳ ሰዓት ሊደርስ ገደማ ይመስለኛል፣ ምክንያቱም ትክክለኛውን ሰዓት አላውቅም፤ ሰዓት የለኝማ፡፡ ሁለት ጠባቂዎች እና ራዲሰን ብሉ ሆቴል ያገኘሁት በርቶሚዮስ የሚያምር ውድ ጥቁር ሱፍ ልብስ አድርጎ መጣ፡፡ ለምን እንደሆነ ባላውቅም ገና ሳየው ውስጤ ደስታ ቢጤ ተሰማኝ... ከሁለቱ ጠባቂዎች ጋር ያወሩትን ባላዳምጥም ተነጋገረና የታሰርኩበት ከፍል ውስጥ እነርሱ ወጥተው እርሱ ብቻውን ቀረ፡፡ በትኩረት ተመለከተኝ፡፡ ጨበጠኝ፡፡ እቀፈኝ፡፡

"ስለጠፋሁብህ ይቅርታ እንዴት ነህ?"

"ሠላም ነኝ!"

"የደረሰብህ ነገር አለ? ግርፋት? ምት? ምግብ አለመስጠት?..."

"የለም"

"ለነገሩ በጣም እንዲጠነቀቁልህ ነግሬያቸው ነበር ፡፡ አንተ እድለኛ ነህ! እዚህ ቦታ የገባኸው ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ወይም የመንግስት ተቋዋሚ ብትሆን ኖሮ ዛሬ ከዚች ከፍል ውስጥ ሬሳህ ነበር የሚወጣው፡፡ የግርፋት እና የስቃይ አይነት ትቀምሳት ነበር፡፤ ለማንኛውም እንኳን ደስ አለህ?"

"ተያዙ?" አልኩት፡፡ ምንም ሳይናገር በእጁ ይዞት የነበረውን ፖሊስና እርምጃው

የተባለ ጋዜጣ ሰጠኝ:: በፍጥነት ተቀብዬ የመጀመሪያውን ገፁን አየሁት:: ከዚያ ሣኩኝ:: ገና የመጀመሪያ ርዕስ ላይ "ሀሰተኛ የብር ኖት በማሰራጨት እና የህፃናት ኩላሊት በመሸጥ ወንጀል ላይ የተሰማሩ 28 ግለሰቦች እና ሁለት ከፍተኛ ባለስልጣናት በቁጥጥር ስር ዋሉ" ይላል:: በደስታ ተውጬ በፍጥነት አነበብኩት... 24ቱ የተያዙት ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን አራቱ የተያዙት ከኢትዮጵያ ውጪ በኢንተርፖል አማካኝነት ሱዳን ውስጥ እንደሆነ ያብራራል፤ የመሳይ ቁምላቸው ስም ግን አልተጠቀሰም! እናም በፍጥነት

"መሳይ ቁምላቸውስ?" አልኩት:: በርቶሚዮስን በትኩረት እያየሁት::

"እሱ የውሸት ስሙ ነው:: እውነተኛ ስሙ ማንደፍሮ ወይም መሳይ ሳይሆን መከት ዳናቸው ነው" አለኝና ጋዜጣውን ተቀብሎኝ ስሙን አሰነበበኝ

"ምክትል የወንጀሉ አንቀሳቃሽ እርሱ ነው ፤ በእርግጥ ከዚህ በፊት ለሶስት ዓመታት አስተማሪ እንደነበረም ደርሰንበታል:: ለማንኛውም በጣም ትልቅ ውለታ ነው ለአገርህ የሰራኸው:: እንዳንተ ዓይነት ለወገናቸው የሚቆረቆሩ ሰዎች ያስፈልጋሉ ፤ ምክንያቱም ይቺ አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም በርካታ ለሆዳቸው ብቻ የሚኖሩ! ህሊናቸውን በርካሽ ነገር የሸጡ! የኢትዮጵያ ትልቅነትን የማይፈልጉ ከግለሰቦች እስከ ባለስልጣናት ያሉባት አገር ነች፤ ሌላ ጊዜ በሰፋት እናወራለን!! ከአሁን ሰዓት ጀምሮ ነፃ ነህ! ወደ ቤትህ እደርስሃለሁ:: ታላቅ ወንድምህ አንተን ለማግኘት እጅግ በጣም ጓጉቷል::

በርቶሚዮስን በደስታ አቀፍኩት:: ለዘጠኝ ቀናት የናፈቀኝን ሰማይ ለማየት በፍጥነት ከትንሿ ክፍል ውስጥ ወጣሁ... ንፁህ አየር ተነፈስኩ:: እንደ ንፁህ አየር ምን ደስ የሚል ነገር አለና? ንፁህ አየርን ለፈጠረው ዋቃ ባለበት ክብር ይድረሰው!!

ከማዕከላዊ እስር ቤት ወጥቼ ንፁውን አየር በሚገባ አስገብቼ አስወጣሁ:: በእነ በርቶሚዮስ ዘመናዊ ቪ8 መኪና እየሄድኩኝ ድንገት አንድ ነገር አንቃጨለብኝ፤ አጠገቤ ወደተቀመጠው በርቶሚዮስ ፊቴን አዞርኩኝ::

"ጥያቄ ነበረኝ"

"ጠይቅ"

"ቅድም ስትነግረኝ ምክትል የወንጀሉ እንቅሳቃሽ መሳይ ቁምላቸው ከሆነ ዋናው ማን ነው? ተይዟልስ? ማሉቴ ከተያዙት መሀከል ነው?"

"ያው እንዳትሸበር በማለት ጥሩውን ዜና ነገርኩህ እንጂ መጥፎውን ዜና አልነገርኩህም!! እህ... ዋናው የወንጀሉ እንቀሳቃሽ ማንነት እስካሁን ሊታወቅ አልቻለም! የተያዙት ሁለቱ ባለስልጣናት ሆኑ ሀያ ሰምንቱ ሰዎች ራሱ ዋናውን በጭራሽ እያውቁትም ወይም መናገር በጭራሽ አልፈለጉም:: ከተያዙት ሀያ ሰምንቱ ሰዎች አንደኛው ግን ዋናዋን የወንጀሉን አቀናባሪ በመልክ ባያውቃትም ወጣት ሴት እንደሆነች ፍንጭ ሰጥቶናል፤ በዚህ ጉዳይ አትጨነቅ! ከፌዴራል ፖሊስ ጋር በመቀናጀት ይቺን ሴትም በቅርቡ በቁጥጥራችን ስር እናውላታለን!! ስለ ደህንነትህ ሰግተህ ከሆነ ይቺ አደገኛ ወንጀለኛ በቁጥጥር ስር እስከምትውል ድረስ አንተን ሀያ አራት ሰዓት በስውር የሚጠብቁ የደህንነት አባላት ተመድበዋል"

"ይገርማል!" አልኩት::

"ምኑ?" አለኝ::

"ሴት ልጅ ሆና የገንዘብ ፍቅር እና የንዋይ ፍቅር ሊኖራት ስለሚችል የውሸት ብር ብታባዛ ላይደንቅ ይችላል!! ሴት ሆና ልጅ ከማህፀኗ እንደሚወጣ እያወቀች የህፃናት ኩላሊት ንግድ ላይ መሠማራቷ በጣም ጨካኝ መሆን አለባት!!"

"ልክ ነህ! ማንኛውም ወንጀለኛ ወንጀል የሚሠራበት ምክንያት አለው፤ የዚያችን ልጅ ምክንያት የምናውቀው ስንይዛት ብቻ ነው:: በቅርቡ በወንጀለኞች ላይ በተደረገ ጥናት በርካታ ሴቶች ወንጀል አይሠሩም!! ከወንጀል ራሳቸውን ያሸሻሉ፤ የሚገርምህ ጥቂት ሴቶች ደግሞ ወንጀል ውስጥ ይዘፈቃሉ፤ ታዲያ ጥቂቶቹ የሚሠሩት ወንጀል እጅግ አሰቃቂ የምትለው ነው፤ ይህን ጉዳይ በተመለከተ..."

በርቶሚዮስ ስለሴቶች የወንጀል አሠራር መነሻ ምክንያቶች እያወጋኝ ሳናስበው ቤቴ ደረስኩ:: ከበርቶሚዮስ ጋር ተሰነባብተን ተለያየን.. ገና በሩን እንኳኩቼ ሰገባ ታላቅ ወንድሜ እና ዘበኛችን ጥምጥም አሉብኝ... ስለ እውነት ለመናገር ከዓመቶች በኋላ ከእስር ቤት የተፈታሁ ያህል ነበር የተሰማኝ ... ከእስር ቤት በሠላም አውጥቶ ለቤቴ ያበቃኝን ሰማይና ምድርን በጥበቡ የፈጠረውን ዋቃን ቀና በማለት ከልቤ አመሠገንኩት!!

እንደዛሬ ተደስቼ አላውቅም፤ ይቺ ሀይወት የምንላት ጉድ ደግሞ የደስታ እና የሀዘን ቅንብር አይደለችም...?... ነች::

# 16

## ድ
## ህ
## ረ
## ታሪክ

## ውቧ ሴት...!

ሰኔ 18—እርብ ፡፡ ቦሌ አየር መንገድ፡፡

ከታላቅ ወንድሜ ጋር አዕምሮዬን ዘና ለማድረግ አንድ ሳምንት ሀዋሳ አሳልፈን መጣን፡፡ በመዝናናት ሽርብትን አልን፡፡ ናፍቆታችንን በመወጣት ሽርብትን አልን፡፡ በመጨረሻ አዲስ አበባ ተመለስን... ከታላቅ ወንድሜ ጋር ስለሚቀጥለው የህይወት ጉዞዬ በሚገባ አወራን፤ ተስማማንም፡፡

የወንድሜ ባለቤት ሙሉ ለሙሉ ጤንነቷ ስላልተመለሰ በፍጥነት ወደ አሜሪካ መመለስ ስላለበት በአሁኑ ሰዓት ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት እገኛለሁ፡፡ አቤት የምሽቱ ብርድ!... እንዴት የሚያንዘፈዝፍ ነው??

ልክ ከምሽቱ 3፡55 ደቂቃ ሲል ወንድሜን ሸኝቼው ወደ ቤት ለመመለስ ታክሲ ለመያዝ ታክሲ ተራ ስጠጋ ... የዋቃ ያለህ!! እጅግ ውብ፤ እስደማሚ የተስተካከለ ቁመና ያላት! ሸንቃጣ ወጣት! የሚያምር ጃኬት ያደረገች፤ ፈዘዝ ያለ ሰማያዊ ጂንስ ሱሪ ያደረገች፤ ደማቅ ፀጉር ያላት፤ የውበት ምሳሌ የምትሆን... ብቻ ፈረንጆቹ ከውብም በላይ ውብ የሆነች እያሉ የሚገልጿት ወጣት... በፍፁም አፍዝ አደንግዝ ፈገግታ ተሞልታ

"ታክሲ" አለችኝ:: በውበቷ የተነሳ ከመደንገጤ መናገር ስላቃተኝ በአንገቴ ምልክት ሰጠዋት::

"ሀይ"

"ሀይ"

"የት"

"ጃንሜዳ"

"ስንት ትከፍላለህ?"

"200 ብር"

"300 ብር"

"እሺ"

የዋቃ ያለህ!! ይቺን የመሰለች ውብ ወጣት እንዴት ያ የአገራችን ሼክ ሁብታም አላያትም? ምጭለፍ ነበር የሚያደርጋት!! በልጅቷ ውብት ተገርሜ ታክሲዋ ውስጥ ገባሁ... ታክሲዋ ከምላ ጎደል በንጽህና የተያዘች እና ገና ብዙ ያልለፋች አዲስ ትመስላለች::

"የሰፈራችሁ መጠሪያ ጃንሜዳ ነው ጃልሜዳ ነው? የሚባለው?" አለችኝ::

"ጃንሜዳ"

"ጥሩ ነው! ሙዚቃ ትወዳለህ ልከፈትልህ? አስቴር አለች፣ ቴዲ አለ፣ ማዲንጎ አለ፣ የህንድም አለኝ"

"እመሠማናለሁ! በሙዚቃው ፋንታ አንቺን ማዋራት እችላለሁ?"

"መኪና የሚነዳን ሹፌር አያዋሩ ትኩረቱን ይሰርቀዋል የሚለውን የመንገድ ትራንስፖርት ምክር አልሰማህም? ስቀልድ ነው ይህ ለወንድ ነው!! እኛ ሴቶች በአንድ ጊዜ ሁለት ነገር ማከናወን እንችላለን አዋራኝ"

"አንቺን የመሰለች ቆንጆ እንዴት የታክሲ ሹፌር ሆነች? በተሳይ ማታ ማታ አትፈሪም?"

"ቆንጆ ነኝ እንዴ?"

"በቃላት አይገለፅም!!"

"እውነት?"

"እውነቱን ነው!"

ታክሲዋ በፍጥነት ከአየር መንገዱ በመውጣት የቀለበት መንገዱ ላይ ገባች፤ በጣም በፍጥነት ነው የምታሽከረከረው::

"የታሪክ መፅሐፍትን ታነባለህ?"

"አነባለሁ"

"ናፖሊዮን በናፖርት ለምን ወደቀ?"

"በቆንጆ ሴት"

"የመፅሐፍ ቅዱሱ ሳምሶን"

"በቆንጆ ሴት"

"የመፅሐፍ ቅዱሱ ሰለሞን?"

"በቆንጆ ሴት"

"ንጉስ ራዲሽ?"

"በቆንጆ ሴት"

"ሊዊ አራተኛ"

"በቆንጆ ሴት"

"ስለዚህ አንተም ቆንጆ ሴትን አትመነን! በውቧ ግብጻዊት ኪሎፓትራ ስንት መሪዎች እንደወደቁም አስታውስ! ቆንጆ ሴት ትገልሃለች ወይም የሞትህ ምክንያት ትሆናለች"

"አንቺ ስንት ሰው ገደልሽ?"

" አንተን አሁን ስገድል ሰባተኛ ሰው ነህ!"

"ቀልደኛ ነሽ!!"

"ቀልጄ አላውቅም ኬኛ ዮሐንስ"

በድንጋጤ አየዋት:: እንዴት ስሜን አወቀችው...??

"ማ...ነ...ሽ"

"ሀያ ስምንቱን አባሎቼን እስር ቤት ከተህ አንተ በሰላም ልትኖር አምሮህ ነበር የኛ ጀግና?"

ከዚህ በኋላ ትዝ የሚለኝ በግራ እጇ የመኪናውን መሪ እንደያዘች በቀኝ እጇ በሚገርም ፍጥነት ከየት እንደመዘዘችው በግልፅ ባይገባኝም ኮልት ሽጉጥ በመምዘዝ መሀል ግንባሬን ስትበረቅሰኝ ነው... ከዚያ በኋላ... ሞ... ት... !!

አፈር ነህና

ወደ አፈር

ትመለሣለህ፡፡

የሚል ቃል ሲያንቃጭልብኝ ይሰማኛል ፤ ከዚህ በላይ የምተርከላችሁ ነገር የለም... ምንም ይፈጠር ምን ሀቅ እና እውነትን ይዞ መሞት የከብር ሞት ነው፣ ተራ ሞት እንዳልሞትኩ ውስጤ ሹክቱስ ይለኛል... በእርግጥ በታሪኬ አጨራረስ ትበሳጩ ይሆናል! መሞት አልነበረብህም ትሉ ይሆናል! ወይም እንዲህ የሚል ታሪክ ትጠብቁ ይሆናል "... በመጨረሻ ወንጀለኞቹ ተያዙ፤ እኔም ከእስር ነፃ ወጣሁ፣ እሪፍ ቺክ አግብቼ፣ እሪፍ ኑሮ መኖር ጀመርኩ..." እይነት ታሪክ ግና ህይወት ቁማር ናት! ሀቅን መያዝ መስዋዕት ያስከፍላል!! አንዳንዴ የጠበቃችሁት ሳይሆን ያልጠበቃችሁትም በህይወት ጉዞ ላይ ድቅን ይላል! ለማንኛውም ሞት ራሱ አንፃራዊ ነው... በተረፈ የመጨረሻ መልዕክቴ ይቺ ነች እናንተንም ከተራ ሞት ዋቃ ይጠብቃችሁ! ለእውነት እና ስለ እውነት ዘብ ቁሙ... እኔ ግን ለጊዜው በሞት ሽርብትን ብያለሁ ... ስለ እውነት መሞት ሞት ይባል ይሆን? ወንጀለኛን አጋልጦ መሞት ሞት ይባል ይሆን...? አይ ህይወት .... እንቆቅልሽ ነች...!!


አበቃሁ፡፡

ኬኛ ዮሐንስ ነበርኩ፡፡

አሮማይ፡፡

pdf by @shuktus_books

# ማስታወቂያ



እስከ ዛሬ ከታተሙት አስራ አንድ መፅሐፍት በአፃፃፍ ሆነ በይዘት የተለየ የአዘርጋ

12ተኛ መፅሐፍ! ... ቋ!

ከሚያዚያ 2008 ጀምሮ

ለንባብ ይበቃል!!

ኢያንዳንዱ ቤት የሚቀመጥ! እንደ ሌሎቹ መፅሐፍት የኢድሜ ገደብ የሌለው ማራኪ የአዘርጋ ልዩ ስጦታ ...!!

ቋ...!!

ቋ...!!




ጉ·መቶ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማኅበር
011 156 53 52

ዋጋ 50.60